# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

### ዘጠነኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

ኅዳር
፳፻፮ ዓ.ም.

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፮ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

አድራሽ:-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website;-www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው

www.zeorthodox.org

## ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል።



# መታሰቢያነቱ

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሳሉ የዚህን መርሐ ግብር አስፈላጊነት በመረዳትና መመሪያ በመስጠት የሚጀመርበትን ሁኔታ ላመቻቹ ለብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድዖ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ ይሁንልኝ፡፡

# ምስጋና

www.zoorthodox.org

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መጋቤ አዲስ እሸቱ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ፡፡ በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም፡፡

# ማውጫ


| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት | 1 | መስከረም | 1 | |
| 2. | ምልክት | 5 | | 2 | |
| 3. | የሉቃስ ወንጌል (አንድ) | 10 | | 3 | |
| 4. | የሉቃስ ወንጌል (ሁለት) | 14 | | 4 | |
| 5. | የሉቃስ ወንጌል (ሦስት) | 17 | ጥቅምት | 5 | |
| 6. | ፩ኛ ጢሞቴዎስ | 20 | | 6 | |
| 7. | ፩ኛ ጢሞቴዎስ | 23 | | 7 | |
| 8. | ቲቶ | 26 | | 8 | |
| 9. | ፊልሞና | 29 | ኅዳር | 9 | |
| 10. | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (አንድ) ከ5-6ኛ መ/ክ/ዘ | 32 | | 10 | |
| 11. | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ሁለት) ከ7-13ኛ መ/ክ/ዘ | 36 | | 11 | |
| 12. | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ(ሦስት) ከ7-13ኛ መ/ክ/ዘ | 40 | | 12 | |
| 13. | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (አራት) ከ14ኛው መ/ክ/ዘ | 44 | ታህሳስ | 13 | |
| 14. | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ(አምስት) ከ14ኛው መ/ክ/ዘ | 48 | | 14 | |
| 15. | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ስድስት) 15ኛው | 52 | | 15 | |
| 16. | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ሰባት) | 56 | | 16 | |
| 17. | ጠፍተው የተገኙ | 60 | ጥር | 17 | |
| 18. | ዘመነ አስተርእዮ | 63 | | 18 | |
| 19. | ትንቢተ ዮናስ | 68 | | 19 | |
| 20. | ጾም እና አስፈለጊነቱ | 73 | | 20 | |
| 21. | ቅዱስ ቄርሎስ | 76 | የካቲት | 21 | |
| 22. | ሰዓታት | 84 | | 22 | |
| 23. | ምስጢረ ሥላሴ | 87 | | 23 | |
| 24. | ልባሞቹና ሰነፎቹ ደናግላን | 91 | | 24 | |
| 25. | ገብር ኄር | 94 | | 25 | |


www.zeorthodox.org

| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 26. | ሆሳዕና በአርያም | 97 | | 26 | |
| 27. | ትንሣኤ | 101 | መጋቢት | 27 | |
| 28. | ሰባቱ ምስጢራተ ቤ.ክ - መግቢያ | 106 | | 28 | |
| 29. | ሰባቱ ምስጢራተ ቤ.ክ - ጥምቀት | 110 | | 29 | |
| 30. | ሰባቱ ምስጢራተ ቤ.ክ - ሜሮን | 113 | | 30 | |
| 31. | ሰባቱ ምስጢራተ ቤ.ክ - ቁርባን | 116 | ሚያዝያ | 31 | |
| 32. | ሰባቱ ምስጢራተ ቤ.ክ - ንስሓ | 121 | | 32 | |
| 33. | ሰባቱ ምስጢራተ ቤ.ክ - ክህነት | 125 | | 33 | |
| 34. | ሰባቱ ምስጢራተ ቤ.ክ - ተክሊል | 130 | | 34 | |
| 35. | ሰባቱ ምስጢራተ ቤ.ክ - ቀንዲል | 134 | ግንቦት | 35 | |
| 36. | ቅዱስ ጊዮርጊስ | 137 | | 36 | |
| 37. | ዕርገት - የሰማዩ መንገድ | 142 | | 37 | |
| 38. | ጾንጤ ቆስጤና የመንፈስ ፍሬዎች | 146 | | 38 | |
| 39. | ዐዔ ካሌብ እና ሀገረ ናግራን | 150 | ሰኔ | 39 | |
| 40. | እኔነት | 154 | | 40 | |
| 41. | ዜማ | 158 | | 41 | |
| 42. | አደገኛ ዜማዎች | 161 | | 42 | |
| 43. | ተቀባይነት ያለው ዜማ | 164 | ሐምሌ | 43 | |
| 44. | ኢየሱስ ብቻ - የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን | 169 | | 44 | |
| 45. | አቡነ ዜና ማርቆስ | 172 | | 45 | |
| 46. | ቂርቆስና ኢየሉጣ | 177 | | 46 | |
| 47. | ዘላለማዊ መንገድን መመርመር | 180 | ነሐሴ/ | 47 | |
| 48. | ፍልሰታ ለማርያም | 183 | ጳጉሜን | 48 | |
| 49. | መታመንና መታረም | 185 | | 49 | |
| 50. | አቡነ ተክለ ሃይማኖት | 189 | | 50 | |


www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሥራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

www.zeorthodox.org

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል። በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ።

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኅትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ።

***“እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል።” ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው። በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል። በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል። ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ።

www.zeorthodox.org

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም። በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት

# አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ከእያዳንዳችን የሚጠበቅብንና ማድረግ ያለብንን ነጥቦች ያውቃሉ፤ የሚሰጣቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም፡፡"* ፩ኛ ቆሮ.፪÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባብ** ‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት›› ክፍል፩ እና ፪፣ ዲያቆን ዓባይነህ ካሴ

**መግቢያ፡-** በዛሬው ትምህርታችን መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመረዳት ምን ማድረግ እንዳለብን እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የሚከተሉትን ነጥቦች መገንዘብ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ይጠቅሙናል፡፡

1. **በፊደል ሳይሆን በመንፈስ መረዳትና መተርጐም፡-** ***"ፊደል ይገላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል፡፡"*** ፪ኛቆሮ.፫÷፮ ቃሉን በመንፈሳዊ ትርጕሙ ለመረዳት፤ ከፊደል ባለፈ ያስጻፈውን የመንፈስ ቅዱስን ትምህርት ፈቃድ እና ሓሳብ መረዳት ነው፡፡
2. **በገዛ ራስ መረዳት አለመተርጐም** ፡- በደምና *ሥጋ* ፍላጐት (በራስ ስሜት) እና አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅድስን መረዳት አይቻልም፡፡ ጌታችን ለቅዱስ ጴጥሮስ ***"ሥጋና ደም አልገለጠልህም በሰማያት ያለው የአባቴ መንፈስ እንጂ"*** ማቴ.፲፮÷፲፰ እንዳለው በራሳችን መረዳት እና በሥጋዊና ደማዊ እውቀት ብንተረጕመው እንሳሳታለን፡፡ **"ማንም ለገዛ እራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደለትምና፡፡"** ፪ጴጥ ፩÷፲፱-፳፩
3. **ጸጋና ዕውቀት ያስፈልጋል፡-** ***"የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው…ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል፤ ለአንዱም በዚያው መንፈስ ዕውቀትን መናገር ይሰጠዋል፡፡"*** ፩ኛ ቆሮ ፲፪÷፰ ***"እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶችን አስቀድሞ ሐዋርያትን ሁለተኛም ነቢያትን ሦስተኛም አስተማሪዎችን … አድርጓል፡፡"*** ፲፪÷፳፰ ተብሎ እንደተጻፈ የመጽሐፍ ቅዱስን ዕውቀትና ትርጓሜ የመግለጥ

www.zeorthodox.org

ጸጋን መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን አበው ሰጥቷል፡፡ በሌላ ቦታ ***“ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን፡፡”*** ኤፌ ፬÷፯ ያለውንም በሮሜ ፲፪÷፫-፰ አጽንቶታል፡፡ በዚህ መሠረትም የመተርጐም ጸጋ የተሠጣቸውን ***“መምህራን” “ሊቃውንት”*** ወ.ዘ.ተ….. እንላቸዋለን፡፡ ከእነርሱም የመጻሕፍትን ምስጢር እንሰማለን፡፡

4. **የአባቶችን (ቅዱሳን ሊቃውንት) የትርጉም ዘዴ መከተልና በመሠረታዊ ሐሳቦች አለመለየት**፡ ሚልክ ፬÷፯፡፡ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ አትናቴዎስ የመሳሰሉ…እውነተኛይቱን ሃይማኖት ያጸኑ፣ የመጻሕፍት ምስጢር የተገለጠላቸው እና ተመስክሮላቸው ያለፉ አባቶቻችን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጽሐፍ ቅዱስን ተርጒመዋል፡፡ ፍለጋቸውን ተከትሎ መተርጎም በተሻለ ለመረዳት ያግዛል፡፡ ከዚህ ወጥቶ አዲስ መረዳት አግኝቻለሁ ብሎ አዲስ ትምህርተ ሃይማኖት ሊዘጋጅ አይችልም፡፡
5. **መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን ቋንቋ እና ባህል መረዳት**፡- ከለመድናቸው የተለዩ አገላለጾችና ባህሎች መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ባህልና ቋንቋ ውስጥ አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ቃላት መድገም እውነት እውነት፣ አብርሃም አብርሃም … ፤ ወንድም ብሎ የሀገር ልጅ መጥራት፣ ጫማ በማውለቅ ሓላፊነትን ማስተላለፍ፣ እኔነት…የመሳሰሉትን መረዳት መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ለመረዳት ያስችላል፡፡

እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምክንያተ ጽሑፍ፣ የተጻፈበት ዘመንና የተገለጸበት ባህል አለው፡፡ ለምን? ለማን? እንዴት? ተጻፈ እና ተነገረ የሚሉትን ነጥቦች ማጥናት እና መልሶቻቸውን ማግኘት እንደተጻፈበት ዘመንና ሁኔታ ሆነን መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ያግዛል፡፡ ትንቢተ ኤርሚያስን ለመረዳት የባቢሎን መንግሥት፣ የአይሁድን ነባራዊ ሁኔታና ታሪኮች ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

## ታዲያ ከእኛ ምን ይጠበቃል?

ሀ. **ጸሎት**፡- ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት ፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የምንቀበልበት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ያስጻፈውን የእግዚአብሔር ፍቃድ እና ሐሳብ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን መረዳት ለማግኘትም በጸሎት መጠየቅ ይገባል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ዕውቀቱና ጸጋው እያለው ***‹‹እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለኛ ጸልዩ››*** ቆላ ፬፥፪ ብሏል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የምንረዳበትን የመንፈስ ኃይል እና ጥበብ ለማግኘት የቃሉን ባለቤት በጸሎት መጠየቅ አለብን፡፡ ***‹‹ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን ለእርሱም ይሰጠዋል፡፡”*** ያዕ ፩፥፭ ዳዊትም ***‹‹ከሕግህ ተአምራትን አያለሁና ዓይኖቼን አብራ፡፡››*** መዝ ፻፲፰÷፻፲ እያለ መለመኑ እግዚአብሔር ሳይገልጽለት መረዳት ስለማይቻል ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታ ለሐዋርያት *‹‹የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል››* ዮሐ. ፲፮፥፲፫ እንዳላቸው መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ የተሰወረው ተገልጦላቸው መጻሕፍትን ተረጎሙ፡፡ ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ተስፋ ከመቁረጥ ተመልሶ *‹‹አቤቱ ዓይነ ልቦናዬን አብራልኝ››* ብሎ ከጸለየ በኋላ ነው ፤ ብሉያት ከሐዲሳት ተገልጸውለት ተአምራዊ ድርሰቶቹን ያዘጋጀው፡፡ እኛም መጽሐፍ ቅዱስን የምንረዳበት ጥበብ ለማግኘት የጥበባት ጌታ ልዑል እግዚአብሔርን እንለምነው፡፡ የእግዚአብሔርን ሐሳብ በሰውኛ ጥበብ መረዳት አይቻልምና፡፡

**ለ. ማንበብ፡-** መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወት እንዲሆንልን ተጽፎልናል፡፡ ሕይወትን የሚፈቅድ ሁሉ ሊያነበው ይገባል፡፡ በማንበብ በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር እናገኛለን፡፡ ከእግዚአብሔር እንማራለን፡፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባው በመንገዱ ሁሉ በሰረገላው ላይ ተቀምጦ የኢሳይያስን የትንቢት መጽሐፍ ያነብ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ፊልጶስን ልኮ ተረጎመለት፡፡ የሐዋ.ሥራ ፰፥፳፮-፴

መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ያልለመደ ሰው ፡- ከዳር እስከ ዳር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በማንበብ ፤ የሚቀለውን መርጦ በማንበብ /ለምሳሌ ታሪክ የሚስበው ታሪካዊ ክፍሎችን፣ ቀጥተኛ ትምህርት የሚፈልግ መልእክታቱን በማንበብ/ ቢጀምር መልካም ነው፡፡ አንድ ርእሰ ጉዳይ መርጦ በርእሱ ዙርያ የሚናገሩትን ከህዳግ (foot note) እየመረጡ ማንበብም ጠቃሚ የንባብ መንገድ ነው፡፡ የተወሰነ ጥቅስ በየቀኑ ማንበብም ጊዜ መስጠትን ያለማምዳል፡፡

በእነዚህና በሌሎች እኛ በመረጥናቸው መንገዶች ስናነብ ማስታወሻ መያዝ እና በተቻለ መጠን ሐሳብ በማይበተንበት ሁኔታ መሆንም ይመረጣል፡፡ ይህም ለማስተዋል ያግዘናል ፤ በማስታወሻ መያዛችንም ያልተረዳነውን ከመጻሕፍት ለማየት እና ለመጠየቅ ይጠቅመናል፡፡

**ሐ. መጠየቅ፡-** ያልተረዳነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከእውነተኛ መምህራን በመጠየቅ መረዳት ይቻላል፡፡ መጠየቅ የዕውቀት መንገድ ነው፡፡ ሐዋርያት ጌታችንን ‹‹*ፍክር ለነ-ተርጉምልን*›› ይሉት ነበር፡፡ ማቴ.፲፫፥፲፣፲፯፥፴፯ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም ሀብቱና ሥልጣኑ ኩራት ሳይሆኑበት ***‹‹የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል፡፡….እባክህ ነቢዩ ይህን ስለማን ይናገራል?››*** የሐዋ.፰፥፴፩-፴፬ እንዳለ እኛም ከእውነተኛዎቹ አባቶች መምህራን ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን መጠየቅ ይገባናል፡፡

1. **ከእውነተኛ መምህራን እንጠይቅ፡-** በእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ትምህርታቸው እና ሕይወታቸው ከተመሰከረላቸው መምህራን በመጠየቅ የቅዱሳት መጻሕፍትን ምስጢር መረዳት ይቻላል፡፡ ‹‹***አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል፤ ሊቃውንት ጠይቅ ይነግሩህማል***›› ዘዳ.፴፪፥፯ እንደተባለም ቅዱሳት መጻሕፍትን በዕውቀት እና በሕይወት ልምድ ከበሰሉት መጠየቅ ጠቃሚ ነው፡፡

2. **የትርጓሜ መጻሕፍት እናንብብ፡-** በቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተጻፉ ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች (interpretation)፣ ሐተታዎች (Homilies)፣ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች የተሰጡ

www.zoorthodox.org

ትምህርቶች እና ማብራሪያዎችን የያዙ መጻሕፍት አሉ፡፡ እነዚህን መጠቀም ያልተረዳንን ለመገንዘብ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እና የትርጉም መንገዶች ለመረዳት ያስችለናል፡፡ **ለምሳሌም፡-** የቅዱስ አትናቴዎስ፣ የቅዱስ ባስልዮስ፣ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እና ማብራሪያዎችን ማንበብ፤ የቤተ ክርስቲያናችንን የትርጓሜ መጻሕፍት መመልከት ወደ እውነተኛው መረዳት ያደርሳሉ፡፡

**መ. መተግበር፡-**

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያለን ግንኙነት መጽሐፉን ለማወቅ ብቻ አይደለም፡፡ የተጻፈውን ለመተግበር፣ ትእዛዛቱን ለመከተል፣ ራሳችንን ለማስለመድም ነው፡፡ የምናነበውን በዕለታዊ ውሎአችን በተገበርነው ቁጥር በልባችን ይታተማል ይረዳናልም፡፡ ቅዱሳን ዓለምን የቀየሩት የእግዚአብሔርን ቃል በሕይወታቸው በማሳየት ነው፡፡ ለቅዱስ ቃሉ ያለንን ታማኝነት ከሕይወታችን ጋር አዛምደን በመተግበራችን ይታወቃል፡፡ ***"ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ"*** *ያዕ.፩፥፳፪፡፡*

አይሁድን ያህል መጽሐፍ ቅዱስን የመረመረ አልነበረም፤ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አቃታቸው እንጂ፡፡ ለዚህም ነው ጌታችን፡-***" ለእናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነሱን ትመረምራላችሁ እነርሱም ስለኔ የሚመሰክሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደኔ ልትመጡ አትወዱም "*** ዮሐ ፭፥፴፱ ያላቸው፡፡ ሐዋርያው ***‹‹በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏልና››*** ሮሜ ፲፭፥፬ እንዳለን የተጻፈው ሁሉ እኛን ሊያጸናንና ሊያጽናናን ተጽፎአል፡፡ እናም ***‹‹ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ቤቱን በመልካም አለት ላይ ያነፀ ልባም ሰውን ይመስላል፡፡››*** ማቴ.፯፥፳፬ እንደተባለው ለመሆን መጣር አለብን፡፡ ይህን በማድረግ ስናነብ ቃሉ ምን እንደሆነ ከቃላት በላይ ትርጉም ይሰጠናል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት፡- በራስ ሐሳብ አለመደገፍ እና በጸሎት እግዚአብሔርን፣ በትሕትናም ከእኛ የተሻሉትን መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ የተረዳነውንም መተግበርም ቅዱስ ቃሉ የሕይወታችን አካል እንዲሆን ያስችለናል፡፡

www.zoorthodox.org

**ተግባር፡-** የተማራችሁትንና ያነበባችሁትን ቃል በጥቂት በመተግበር በብዙ በሚሾመው በእግዚአብሔር ፊት ታመኑ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የሚጠቅሙ አምስት ዐበይት ነጥቦችን ግለጽ
2. መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ተገንዝቦ ለመረዳት እና ቅዱስ ቃሉ የሕይወታችን አካል እንዲሆን ከእኛ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል ዋና ዋና ነጥቦችን በመጥቀስ አብራሩ፡፡

# ምልክት

# ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የኃጢአትን ውጤት እና የመዳንን ምልክት አውቀው፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ፥ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው፡፡››*** መዝ.፴፥፬

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘኑ.፳፩፥፬-፱

## መግቢያ፡-

መጽሐፍ ***‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ››*** ሮሜ.፮፥፳፫ ሰዎች የእግዚአብሔርን ምክር ትተው የዲያብሎስን ሽንገላ በመከተላቸው ሞት ወደ ዓለም ገባ፡፡ ለዘመናትም በዲያብሎስ አገዛዝ በነፍስ ባርነት መኖር ቅጣታቸው ሆነ፤በዚያን ዘመን ተስፋውን ለሰው ልጆች ያለውን የማዳን ዓላማ የገለጠባቸው ምርጦቹም ነበሩ፤ እስራኤል ዘሥጋ፡፡

በመከራችን ሁሉ የማይለየን ታዳጊያችን እግዚአብሔር የሕዝበ እስራኤልን በባርነት መኖር ተመልክቶ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ ለማውጣት ዐሥር ምልክቶችን አድርጎ ፈርኦንንም በተአምራት ድል በማድረግ ነጻ አወጣቸው፡፡

ከግብጽ ሲወጡም በሲና በረሓ ከቀኑ የፀሐይ ሐሩር በደመና እየጋረደ፣ሌሊቱንም በብርሃን ዓምድ እየመራ አብሮአቸው ይጓዝ ነበር፡፡ ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ኃይል ዘንግተው እያጉረመረሙ እግዚአብሔርን ያሳዝኑ ሙሴንም ያበሳጩ ነበር፡፡ ከጥፋታቸው ሲመለሱም የሙሴን ምልጃ ተቀብሎ የሚድኑበትን እየሰጠ ታደጋቸው፡፡

በዛሬው ትምህርታችንም በእግዚአብሔር አለመታመን እና በእርሱ ላይ ማመፅ ምን እንደሚያስከትል፣ ንስሐ ሲገቡም የእግዚአብሔር እንዴት እንደሆነ እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

አባታችን ልዑል እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ አውጥቶ፤በበረሐው መና እየመገበ መራቸው፡፡ ሆኖም ሕዝበ እስራኤል እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ድንቅ ነገር ከማመስገን ይልቅ ሲፈተኑ ትዕግሥት አጥተው ያጉረመርሙ ነበር፤

ቀድሞ ያደረገላቸውን አስበው እርሱን ከመለመን ይልቅ አሳዘኑት፤ በበረሐው ጥም እንዳይዝሉ ውኃ ከዐለት አፍልቆ ያጠጣቸውን እግዚአብሔርን ረስተው አሁንም ዐመፁ፡፡ በዚህም የእግዚአብሔርን ቁጣ አስነሡ፡፡

ይህን ታሪክ የዘገበልን አራተኛው የሙሴ መጽሐፍ ዘጸአት እንዲህ ይለናል፦‹‹ *ከሖርም ተራራ ከኤዶምያስ ምድር ርቀው ሊዞሩ በኤርትራ ባሕር መንገድ ተጓዙ፤ የሕዝቡም ሰውነት ከመንገዱ የተነሣ ደከመ። ሕዝቡም በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ፤ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብጽ ለምን አወጣችሁን? እንጀራ የለም፥ ውኃ የለም ሰውነታችንም ይህን ቀላል እንጀራ ተጸየፈ ብለው ተናገሩ። እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ፥ ሕዝቡንም ነደፉ ከእስራኤልም ብዙ ሰዎች ሞቱ። ሕዝቡም ወደ ሙሴ መጥተው። በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ ስለ ተናገርን በድለናል እባቦችን ከእኛ ያርቅልን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን አሉት። ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ። እግዚአብሔርም ሙሴን፦ እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያየው በሕይወት ይኖራል አለው። ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ።››* ዘኍ.፳፩፥፩-፱

ማየት ያልቻሉትም የናሱን ድምፅ ሰምተው ዳኑ። ያ የናስ እባብ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነበር።‹‹ *ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ›› ዮሐ. ፫፥፲፬-፲፮።*

የናሱ እባብ ተሰቅሎ እስራኤል ዘሥጋን ከምድሩ እባብ እንዳዳናቸው፤ ጌታችንም ተሰቅሎ ፤ዓለሙን በቀደመው እባብ እርሱም ዲያብሎስ ተንኮል ካመጣብን የዘላለም ሞት አድኖናል። የነሐሱን እባብ ያዩት እና ድምፁን የሰሙት እንደዳኑም ጌታችን ስለኃጢአታችን ተሰቅሎ የእጁን ተአምራት፣ የቃሉን ትምህርት፣ የማዳን ሥራውን ያዩት ሐዋርያት እንዲሁም በዘመናት ሒደት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰምተን ያመንነውም ድነናል።

ለዚህም ነው አባ ሕርያቆስ ‹‹*ከእርሱ ጋር አብረን በላን አብረን ጠጣን*›› ሲል የሐዋርያትን ከጌታችን ማእድ መካፈል(ማቴ.፳፮፥፳፮) የእኛን መቁረብ አድርጎ ያስተማረን።

www.zeorthodox.org

ዛሬም በመስቀሉ ምልክትነት ክፉውን ድል የምናደርግበት ኃይላችን ነው። *“የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነው። ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው።”* 1ኛ.ቆሮ.1፡18 ጌታችን የተሰቀለበት መስቀል ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ የተፈለገው እና የተገኘበትን ዕለት እንደ ድል በዓል በየዓመቱ በዓለ መስቀል ብለን የምናከብረውም ለዚህ ነው።

## ማጠቃለያ

የነሐሱ እባብ በዘመነ ብሉይ የተሰጠ የሐዲስ ኪዳን ምሳሌያችን ነበር። ፍጻሜውን በጌታችን መሰቀል አግኝቶአል።

መስከረም ፲፯ ቀን የምናከብረው በዓል የጌታችን መስቀል ከተቀበረበት ቦታ ሦስት መቶ ዓመታት ቆይቶ የወጣበት ቀን ነው፡፡

በነዚህ ታሪኮች የእውነትን ድል፣ የመስቀልን ኃይል፣ ለእግዚአብሔር መታመንን፤ ትዕግሥት ፣ ንስሐንና የጸሎትን ጥቅም ተምረናል፡፡ የተማርነውን ለፍሬ ያብቃልን፡፡

## ተግባር

**በሕይወታችን ሁሉ በእግዚአብሔር እንታመን:-**

መዝሙረኛው ዳዊት በእግዚአብሔር ታመን ሲል ይመክረናል፡፡ እስራኤል ከግብጽ ወደ ከነዓን ያደረጉት ጉዞ እኛ ከዚሕች ዓለም ወደ መንግሥተ ሰማያት የምናደርገው ጉዞ ምሳሌ ነው፡፡ መልካም እና ክፉ፤ ድል እና ሽንፈት እንዳጋጠማቸው እኛም በብዙ እንፈተናለን፡፡

በዚህ ጉዞአችንም እግዚአብሔር ስላደረገልን ሁሉ ማመስገን ፣ በፈተናችን በእርሱ ብቻ መታመን እና አምላካችንን በፍጹም ልባችን መውደድ አለብን፡፡ ይህን ስናደርግም ጠላታችን ከሚያመጣብን ክፉ ነገር ያወጣናል፡፡‹‹***ኃይላችን ነውና፡፡***›› ፩ኛ ቆሮ.፩:፲፰

*በፍጹም ልቡ በእግዚአብሔር የሚታመን ክርስቲያንም ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ‹* ***ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ፡፡*››** ገላ.፮:፲፬ ይላል፡፡

**ትዕግሥተኞች እንሁን:-**

- አንዳንዴ በረከት የምንቀበልበት መንገድ እና በምናስበው ጊዜ ላይሆን ይችላል፡፡ ወይም ሊረዝም ይችላል፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን ፍቃድ ስላልተረዳን ወይም በድካማችን መከራችንን አርዝመነው ይሆናል፡፡ የዚህ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ጋር በትዕግሥት መጓዝ ሲያቅተን እና እምነታችንን ስናጣ ይሆናል፡፡ መጽሐፍ ‹‹***ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት እርሱም ዘንበል አለልኝ ጩኸቴንም ሰማኝ፤***›› እንዳለ በትዕግሥት ከጠበቅነው መልካም ስጦታዎችን ይሰጠናል፡፡
- የአርባ ቀኑ ጉዞ በአርባ ዓመት የተፈጸመው የእግዚአብሔርን ሥራ በሙሉ ልባቸው እና በትዕግሥት ስላልጠበቁት ነው፡፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ያልገቡትም ብዙዎቹ ሲሆኑ፤ ***የታገሰ ፍሬዋን ይበላል*** እንደተባለ ምድሪቱን ከመጀመሪያው ትውልድ የወረሱት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡
- ትዕግሥት ማጣት የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያሳጣ ይችላል፡፡ ጠላታችን ሰይጣን ትዕግሥት በማሳጣት በተለያዩ መንገዶች ሲፈትነን፤ ***፩ኛ. ጴ ጥ. ፭:፮-፲፩*** የእግዚአብሔር ቃል ማስታወስ መቻል መልካም ነው:‹‹***የቅዱሳን ትዕግሥት እና እምነት በዚህ ነውና፡፡***›› ራእ. ፲፫፥፲

www.zoorthodox.org

- ሰዎች በከንቱ ሲቆጡንም ***‹‹በትዕግሥት አለቃ ይለዝባል ››*** ምሳ.፳፭፥፲፭ እንደተባለ ከትዕግሥታችን መልካምነትን እናስተምር፡፡ ከዚሁም ጋር፦ ***‹‹መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ፤ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል፡፡›*** ፩ኛ ጴጥ.፪፥፳ እንደተባልንም በነገር ሁሉ ታጋሾች እንሁን፡፡

**ንስሐ፦**

- ሕዝበ እስራኤል ኃጢአታቸውን አምነው ተጸጸቱ፤ ወደ ሙሴ መጥተውም እግዚአብሔርን ለምንልን ሲሉት በትሕትና እና ኃጢኣታቸውን በማመንም ነበር፡፡ ለዚህም ነው፡፡‹‹ ***በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ ስለ ተናገርን በድለናል ……*** ›› ያሉት፡፡
- እኛም ‹‹ ***ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ***››…የሐዋ.ሥ.፪፥፴፫ እንደተባልን በበደላችን ልንጸጸት ንስሐም ልንገባ ይገባል፡፡
- ንስሐ የእግዚአብሔርን ቁጣ ታብርዳለች ምሕረትንም ታሰጣለች፡፡ ‹‹***ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል፡፡›*** ምሳ.፳፰፥፲፫

**ጸሎት እና ምልጃ**

- ሕዝበ እስራኤል በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ከመጠየቅ ሙሴን ‹‹.***.ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን….፡፡***›› ያሉት፤ በእግዚአብሔር ፊት መቆም አይገባንም፤ ከሚል ትሕትና እና ኃጢአትን ከማወቅ ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያስተምሩን በምልጃ ውስጥ ያለ ትሕትናም ይህ ነው፡፡ ጌታችንም በዚህ ሕይወት የሚኖሩትን ታላቅ እምነት ሲል አመስግኖአቸዋል፡፡ ሉቃ.፯:፩-፲፣፲፰:፱-፲፬
- ***በተጨማሪም*** እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ቢለያቸውም ሞገስ አግኝቶ ከፈጣሪው ጋር የነበረውን ሙሴን በመሰላልነት ተጠቅመው ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀዋል፡፡ እኛም ‹‹ ***የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች*** ›› ያዕ.፭:፲፯ እንደተባለ፤ ከእኛ ይልቅ በሃይማኖት፣ በቅድስና የበረቱትን ‹‹አስቡን›› ማለት ዓለሙን ያሸነፉትን ቅዱሳንንም ‹‹አማልዱን›› ብለን መማጸን ይገባናል፡፡

www.zeorthodox.org

**የመዳን ምልክት**

- የነሐስ እባብ በምድር እባብ ለተነደፉት የመዳን ምልክት እንደሆነ ለእኛም መስቀል የመዳኛችን ምልክት ነው፡፡ ጌታችን ከወንበዴዎች ጋር ተቆጥሮ የሞተልን ከኃጢአት ባርነት ነጻ ሊያወጣን ነው፡፡
- ጠላታችን ሲዋጋን በእምነት ሆነን ቀድሞ ድል በተነሳበት መስቀል ከተቃወምነው

ይሸነፋል። በክፉ ሐሳቦች፣ በኃጢአት እና በክህደት ሲፈታተናችሁ የሥላሴን ስም በመጥራት፣በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል አማትቡ።ታሸንፉታላችሁ።« ***የመስቀሉ ቃል ....... ለእኛ ለምንድን ... የእግዚአብሔር ኃይል ነው።»*** ፩ኛ ቆሮ. ፩፥፲፰

- ***‹‹ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ፥ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው።››*** መዝ.60፡4 ተብሎ እንደተጻፈ፤መስቀል ማፈሪያ ሳይሆን ድል ማድረጊያ ጦራችን መመከቻ ጋሻችን ነው። የዲያብሎስ ቀስት ድል ማድረጊያችንም ነው።
- ***‹‹እኔ ለዓለም ዓለምም ለእኔ ከተሰቀለበት መስቀል ውጪ ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ››*** ማለት እና በምድር ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ መመካትን ልንለምድ ይገባል።
- የመስቀል ምልክት እና በዓል ***በዓይናችን ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ እንዲሳል*** (ገላ.፫፥፩) ይረዳናል። ውለታውን እንድናስታውስም ያግዘናል፤እውነት በሐሰት ላይ ድል ያገኘችበት መንፈሳዊ በዓላችንም ነው። አሜን!!

**ጥያቄ፡-**

1. ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ እንዲወጡ የመራቸው በእግዚአብሔር የተሾመው ነቢይ ማነው?
2. ሕዝበ እስራኤል በሲና በረሓ ሲጓዙ እግዚአብሔር ምን ያደርግላቸው ነበር? እግዚአብሔርንስ እንዴት አሳዘኑት?
3. ሕዝበ እስራኤል በሲና በረሐ በእባብ ሲነደፉና ሲሞቱ ሕዝቡ ምን አደረጉ?
4. ሙሴ ስለ ሕዝቡ የጸለየው ለምን ነበር?
5. በእግዚአብሔር በታዘዘው መሠረት ሙሴ የነሐስ እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቅሎ በእባብ የተነደፈው ሁሉ ድኗል። የነሐሱ እባብ ምሳሌ የማን ነው?
6. መስከረም ፲፯ ቀን የመናከብረው በዓል ለምንድነው? አብራሩ።

www.zeorthodox.org

# የሉቃስ ወንጌል - (አንድ) - ታሪክና መግቢያ
# ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ታሪክና ሥራ ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ"*** /ሉቃ.፩፥፫-፬/

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ‹‹ወንጌል ትርጓሜ መግቢያ›› ‹‹ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ››፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ መጽሐፈ ስንክሳር ጥቅምት ፳፪፡፡

**መግቢያ፡-** ይህ በተከታታይ የምንማረው የሉቃስ ወንጌል ጥናት የመጀመሪያው ክፍል ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የወንጌላዊውን ታሪክና የወንጌሉን መግቢያ እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. ጸሐፊው

ሉቃስ በላቲን ሉካኖስ ይባላል፡፡ መብራት ማለት ነው፡፡ ከሰባ ሁለቱ አርድዕት(ሉቃ.፲፥፩) አንዱ ነው፡፡ (መጽሐፈ ስንክሳር ጥቅምት ፳፪፤ወንጌል ትርጓሜ መግቢያ) በትውልዱ ሶሪያዊ የአንጾኪያ ሰው ነበር፡፡ ሉቃስ ሠዓሊና ባለመድኃኒት (የሕክምና ባለሞያም  ነበር፡፡ቆላ ፬፡፲፬) በመጽሐፍ ቅዱስ በስሙ የሚጠራውን ወንጌልና የሐዋርያት ሥራን ጽፏል፡፡

በዮሐ.፲፪፥፳-፳፩ ለበዓል ሊሰግዱ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጡት አሕዛብ ወደ ፊልጶስ በጥተው ***መጥተው... ‹‹ጌታ ሆይ፥ ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን››*** ካሉት ጋር ሉቃስ እንደነበር ይታመናል፡፡ ከሁለቱ የኤማሑስ መንገደኞችም (ሉቃ.፳፬፥፲፫) አንዱ ሉቃስ ነው፡፡ ሐዋርያት ለማስተማር ሲወጡ ሉቃስ ዮሐንስን ተከትሎ በመቄዶንያ እያስተማረ ወደ አንጾኪያ እና ጠርሴስ ሄደ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ከአይሁድ በተነሳበት ስደት ወደ ትውልድ ሀገሩ ጠርሴስ ሄዶ ለረጅም ጊዜያት ኖረ፤ (የሐዋ.ሥ.፱፥፴)፡፡ ከሉቃስ ጋር የተገናኙትም ያኔ ነው፡፡ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያንም አብረው ነበሩ፡፡ የሐዋ.፲፫፥፩ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ቅዱስ ጳውሎስን ተከትሎ አገለገለ፡፡

www.zeorthodox.org

(የሐዋ.ሥ. ፲፮÷፲-፲፯፣፳÷፭-፲፭፣፳፩÷፩-፲፰፣፳፯÷፩-፳፰፣፲፮)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሰማዕትነት ካረፈ በኋላ፤በሮምና በዳርቻዋ ባሉት ደሴቶች ያስተምር ጀመር። ከእነዚህ አንዱዋ የድልማጥያ ደሴት ናት። ሉቃስ ከሮም ወደ ድልማጥያ ሸሽቶ የክርስቶስን ወንጌል ማስተማር ቀጠለ። ዕድሜው ገፍቶ ሰማንያ አራት ዓመት ሆኖታል። አይሁድና የአሕዛብ የጣዖት ካህናት ነገር ሠርተው በንጉሥ ኔሮን ፊት፤‹‹ሉቃስ ሕዝቡን እያሳተ በድልማጥያ አለ፤›› ብለው ከሰሱት። ንጉሡም ሁለት መቶ ወታደሮችን ወደ ሉቃስ ሰደደ።

ሉቃስ ይህንን አውቆ ሕዝቡን አሰናበተና፤ ወደ ባሕር ዳርቻ ተጠጋ። በዚያም አንድ ገበሬ ዓሣ ሲያጠምድ አገኘው። ሉቃስ ሰላም ብሎት ወንጌልን ይሰብክለት ጀመር። በዚህ ጊዜ ወታደሮቹ ወደ እርሱ እየቀረቡ ነው። ሉቃስ ስብከቱን ቀጥሏል። ያ ገበሬ በክርስቶስ አምኖ ‹‹ምን ላድርግ?›› አለው። ‹‹እነዚህ የሕይወትን መንገድ ይመሩሃል›› ብሎ ሉቃስ በእጁ ያሉትን መጻሕፍት ሰጠው። ከገበሬው ዞር ብሎም ወታደሮች በሚመጡበት አቅጣጫ ሄደ። ራሱንም ለወታደሮቹ ገለጠ። እነርሱም ተረባርበው ያዙት። ወደ ንጉሥ ኔሮንም ቀረበ።

ኔሮን በፍርድ አደባባይ ተቀምጦ ፍርድ ያጣምማል ፤ ቅዱስ ሉቃስን እስከመቼ በሥራ ይህ ታስታለህ? አለው። ቅዱሱም ***"እኔ መሰርይ አይደለሁም፤የሕያው እግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ነኝ።"*** ብሎ መለሰ። ኔሮን እጁን እንዲቆርጡት አዘዘ። ሆኖም የተቆረጠውን እጁን በተአምራት መለሳት። በዚያን ጊዜ 270 ወታደሮች ከአለቃቸው ጋር አመኑ። ኔሮንም ሉቃስን ጨምሮ ወታደሮቹ እንዲሰየፉ አዘዘ። ባለ ሰይፉ ወታደር አንድ ዐይና ነበር። ሌሎችን ሰይፎ ወደ ሉቃስ ዘንድ ሲደርስ ዓይኑን አበራለት። እርሱም ክርስቲያን ሆነ። በመጨረሻም ጥቅምት ፳፪ ቀን ፰ ፰ ዓ.ም ሉቃስን ሰይፈው አካሉንም በአሸዋ በተሞላ ጆንያ አስረው ወደ ባሕር ጣሉት።

## 2. የወንጌሉ መጻፍ

**ተደራሹ፡-** ሉቃስ ወንጌሉንና ግብረ ሓዋርያትን ቴዎፍሎስ ለተባለ ሰው ጽፎለታል። ሉቃ.፩÷፩፤ የሐዋ.ሥ.፩÷፩ ቴዎፍሎስ በእግዚአብሔር የተወደደ ማለት ሲሆን፤ ግሪካዊ ሀገረ ገዥ ነበር። በሉቃስ ስብከት አምኖ ክርስቲያን ሆነ።(ወንጌል ትርጓሜ መግቢያ) ሉቃስም በቃል ያስተማረውን በጽሑፍ ሊያስረዳው ጻፈለት።***"ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ"*** /ሉቃ.፩÷፫-፬/

**አጻጻፉ፡-** ሉቃስ ወንጌሉን የጻፈው ***"ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት"*** ካስተላለፉለት ***"በጥንቃቄ"*** ወስዶ ነው፡፡ ሉቃ.፩÷፪-፫ ለዚህ ነው፤ በሌሎች ወንጌላት የማናገኛቸውን (ለምሳሌ፡- የጌታ ጽንሰትና ልደት ፣ የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ታሪክ ፣ ጠፍተው የተገኙት ልጅ ድሪምና በግ ምሳሌ …) በሉቃስ ወንጌል እናገኛለን፡፡ ይህም ወንጌሉን ሲጽፍ

www.zeorthodox.org

ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም፣ ከሐዋርያትና ከመጀመሪያዎቹ የጌታችን ተማሪዎች ሰምቶ መጻፉን ያስረዳናል፡፡ በተጨማሪም ሉቃስ ሠዓሊ ስለነበር ገላጭ በሆነ በሥዕላዊ የአጻጻፍ ስልት ጽፎልናል፡፡

**ቦታና ዘመን፡-** ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር በነበረው አገልግሎት የመጻፊያ ጊዜ ያልነበረው ሉቃስ በጳውሎስ የመጀመሪያ እስር (ከ፶፰-፷ ዓ.ም) ጊዜ አገኘ፤ (የሐዋ.ሥ.፳፩፥፲፯-፳፰፥፴፩) በዚህ ጊዜ ሉቃስ በግሪክ-መቄዶንያ ነበርና በግሪክ ቋንቋ ለግሪካዊው ቴዎፍሎስ ጻፈለት፡፡

**ከወንጌሉ ይዘት በመነሣት በሊቃውንቱ ዘንድ ሉቃስና ወንጌሉ በተለያዩ መጠሪያዎች ይታወቃሉ፡፡**

- ሰባኬ መንፈስ ቅዱስ - ስለ መንፈስ ቅዱስ ጸጋ ደጋግሞ ስላነሣ፡፡
- የአንስት ወንጌል - የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምንና የሌሎች ሴቶችን ቅድስና፣ አገልግሎትና ተማኝነት በማንሣቱ፡፡(፩፥፳፮-፶፮፤፩፥፴፱-፵፪፤፲፥፴፰-፵፪፤፳፫፥፳፯-፴)
- የአሕዛብ ወንጌል - ለእነርሱ በመጻፉ፡፡ የተጻፈለት ቴዎፍሎስ ስሙም ሆነ ትውፊታዊ ታሪኩ ከአሕዛብ ወገን እንደነበር ያስረዳናል፡፡
- የድሆችና የተናቁ ወንጌል- ስለእነዚህ በትምህርትና በታሪክ በብዛት ያነሣል፡፡(፪፥፰-፲፰፤፲፯፥፱-፴፩፤፲፬፥፲፫-፳፩፤፫፥፲፤፲፪፥፳፩)
- የጸሎት ወንጌል - ስለ ጸሎት ተደጋጋሚ ትምህርቶችን በመያዙ፡፡ (ሉቃ.፲፩፥፩-፰፣ ፶፰፣ ፲፰፥፩-፯;፲፰፥፱-፲፬;) በሌሎች ወንጌላት የሌሉ አራት ጸሎታትም አሉት፡፡(፩፥፵፮-፶፭፤፩፥፷፰-፸፱፤፪፥፲፬፤፪፥፳፱-፴፪)

## የተጻፈበት ዓላማ፡-

1. ስለክርስቶስ እርግጡን ለማሳወቅ፡፡ ሉቃ.፩፥፩-፬፡፡ ይህ ለጻፈለት ለቴዎፍሎስ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለምና ለመጭው ትውልድ የተሠራ የመንፈስ ቅዱስ ምስጢርና ፍቃድ ነው፡፡
2. አሕዛብን በዝንባሌያቸው ወደ ክርስትና መጥራት የወንጌሉ ዓላማ ነው፡፡ በመሆኑም ለዓለም የሆነውን መዳን ያውጃል፤አሕዛብ የማያውቁትን የነቢያትን ትንቢት በብዛት አልጠቀሰም፤ የእብራይስጥን ቃላት ተርጉሟል፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

- ሶርያዊው ሉቃስ ሁለት መጻሕፍትን ጽፎልናል፡፡ ከሰባ ሁለት አርድእት አንዱ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ዮሐንስን ተከትሎ ወጣ፡፡ በኋላም ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር በማስተማር ኖረ፡፡ በመጨረሻም ተሰይፎ በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡

## ተግባር፡-

- የሉቃስ ወንጌልን አንብቡ፡፡ በትኅትናና በፍቅር የምታገለግሉ ሁኑ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ሉቃስ ማለት ምን ማለት ነው? የተወለደበት ሀገር የት ነው? ምን ምን ዓይነት ሞያ ነበረው?
2. ሉቃስ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር የተገናኙት የት ነው? የተገናኙበት ምክንያት ምንድነው?
3. ሉቃስ የጻፈው ስንት መጻሕፍትን ነው? ምን ይባላሉ? መጻሕፍቱን ለማን ነበር የጻፈው? በምን ምክንያት ጻፈለት?
4. ከወንጌሉ ይዘት በመነሣት በሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ዘንድ ሉቃስ እና ወንጌሉ በተለያዩ መጠሪያዎች ይጠቀሳሉ፡፡ ዋና ዋናዎቹን ከነ ምክንያታቸው እየጠቀሳችሁ አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የሉቃስ ወንጌል - (ሁለት) - መሠረታዊ ሐሳቡ ይዘቱና አከፋፈሉ

## አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለሉቃስ ወንጌል ያላቸውን ዕውቀት ያዳብራሉ፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ይህም (ክርስቶስ) ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው።"*** ሉቃ.፪፥፴፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** በክፍል አንድ ትምህርት የተጠቀሱትን መጻሕፍት እና የተሰጡትን ጥቅሶች በሚገባ አንብቡ፡፡

**መግቢያ፡-** ይህ በተከታታይ የምንማረው የሉቃስ ወንጌል ጥናታችን ሁለተኛው ክፍል ነው፡፡ ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን፤ የወንጌላዊውን የቅዱስ ሉቃስን ታሪክ እና የወንጌሉን መጻፍ አይተናል፡፡

የክለሳ ጥያቄዎች፡-

ሉቃስ ማለት ምን ማለት ነው ?

ሉቃስ እንዴት እና በማን ተጠራ ?

ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር የት ተገናኙ ?

ወንጌሉን የት ለማንና መቼ ጻፈው ? የወንጌሉ ዓላማ ምንድነው ?

ሉቃስ መንፈሳዊ ተጋድሎውን እንዴት ፈጸመ?

በዛሬው ትምህርታችንም የወንጌሉን ዋና ጭብጥ እና ይዘት እናያለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

**የወንጌሉ ዋና ጭብጥ (መሠረታዊ ሐሳብ)፡-**

ሉቃስ ስለ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በርካታ ጭብጦችን አንሥቷል፡፡ ከሁሉም በላይ የሆነውና ዋነኛው ጭብጥም የዓለም መዳን ነው፡፡ የሉቃስ ወንጌል ዋነኛ ጭብጥ ክርስቶስ ሕዝብና አሕዛብን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ሊያደርግ እንደመጣ ማሳየት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም፡-

1. **የእስራኤል መዳን፡-**

የሉቃስ ወንጌል መልሕቅ መጀመሪያ ያረፈው በብሉይ ኪዳን ትንቢት በተነገረላቸው ሕዝቦች ላይ ነው፡፡ ክርስቶስ እስራኤልን እንደሚታደግ ቀድሞ ተተንብዮአል፡፡ (ኢሳ.፲፩፥፲-፲፪፣፵፱፥፮፣ ሕዝ.፴፱፥፳፫-፳፱) የወንጌሉ ዓላማ የትንቢቱ ፍጻሜ ክርስቶስ መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ ይህንንም ክርስቶስ ከዳዊት ዘር የተገኘ ንጉሥ መሆኑን በማሳየት አስረግጧል፡፡ (ሉቃ. ፩፥፴፫-፷፰፣ሉቃ ፳፪፥፳፰-፴) ይህ የወንጌሉ ዋና ጭብጥ ***እስራኤል*** የሚለውን ቃል በተደጋጋሚ በመግለጡ ይታወቃል፡፡(ሉቃ. ፩፥፶፬፣፷፰፣፹፣፪፥፴፪፣፳፬፥፳፩) ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን የተነገረላቸውን ሕዝቦች ሊሰበስብና በትንቢቱ መሠረት ሊያድን እንደመጣ ይገልጻል፡፡ የሳምራውያንን በክርስቶስ መወደድም ትኩረት ሰጥቶታል፡፡(ሉቃ. ፲፥፴፫፣፲፯፥፲፮)

2. የአሕዛብ መዳን፡-

ክርስቶስ ለእስራኤል ያደረገው ምሕረት ለሁሉም ነው፡፡ አሕዛብ የቃል ኪዳኑ ሕዝቦች እንዲሆኑ ተጠርተዋል፡፡ ይህም የድኅነትን ዓለም አቀፋዊነት ያሳያል፡፡ ስምዖንም ***"ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን..."*** ሉቃ.፪፥፴፪ መጥምቁ ዮሐንስም ***"ሥጋም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ"*** ሉቃ.፫፥፮ በማለት የክርስቶስ ማዳን ለሁሉም እንደሆነ ሉቃስ ይጠቅሳል፡፡ ይህን ጭብጥ ጉልህ የሚያደርገው ደወል ያለው ጌታችን ንስሐና ምሕረት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ***"በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል"*** ባለው አማናዊው ቃል ነው፡፡ ሉቃ. ፳፬፥፵፯

3. የተዋረዱት መዳን፡-

ለሕዝብና ለአሕዛብ የተላለፈው የክርስቶስ ማዳን መልእክት፤ ለድሆች ለተገለሉና ለተዋረዱትም ሁሉ ነው፡፡ ይህ ወንጌል እግዚአብሔር የተዋረዱትን እንደሚጎበኝ በትኩረት ጠቅሷል፡፡ (ሉቃ.፩፥፶፪-፶፫፣፬፥፲፰፣፮፥፳-፳፮፥፲፬፥፯-፲፩) በማኅበረሰቡ ዘንድ ሴቶች ለዘመናት ይናቁና ዝቅተኛ ቦታ ይሰጣቸው ነበር፡፡ የሉቃስ ወንጌል ክርስቶስ የተገፉትን ማክበሩን ይገልጣል፡፡ ይህም ሴቶችን በተለየ ሁኔታ በማሳያነት በማቅረቡ ይታወቃል፡፡

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ሉቃስ የገለጠበት ሁኔታ እንደ አንድ ብስራት አልነበረም፤ በተለየ የአገላለጽ ውበትና ክብር አሳይቶናል፡፡ (፩፥፳፮-፶፮፣፪፥፲፱፣፶፩) በተጨማሪም ድንግል፣ ቀዳማዊት ሔዋንን ወክላ፡- ***"የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና።"*** ሉቃ.፩፥፵፰ ብላለች፤ በአጋንንትና በሰዎች የተዋረዱትን ጌታ እንደሚታደግ ***"ኃያላንን ከዙፋናቸው አዋርዶአል፣ ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል፣የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል፣ ባለ ጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል።"*** ፩፥፶፪-፶፫ ማለቷን ሉቃስ ጽፏል፡፡ ይህም የሰው ልጅ በቀዳሚት ሔዋን ተዋረድን ብሎ ለሴቶች የነበረው ንቀት በዳግማዊት ሔዋን በድንግል ማርያም ክብር መለወጡን ያሳያል፡፡

www.zeorthodox.org

* ሌሎች ሴቶችም የመሪነት ሚና ተሰጥቶአቸው ተጠቅሰዋል፡፡ ኤልሳቤጥ (ሉቃ.፩፥፴፱-፵፮)፣ ነቢይት ሀና (ሉቃ.፪፥፴፮-፴፰), የናይና መበለት (ሉቃ.፯፥፲፩-፲፯)፣ ኃጢአተኛዋ ሴት (፯፥፴፮-፶)፣ መግደላዊት ማርያም፣ ዮሐና፣ሦስና (ሉቃ.፰፥፪-፫)፣ ማርያምና ማርታ (ሉቃ.፲፥፴፰-፵፪)፣ ድካም ያደረባት ሴት መዳን (ሉቃ.፲፫፥፲-፲፯)
* ሴቶች በክርስቶስ ምሳሌዎችም ዋና ተጠቃሽ ነበሩ፡- የጠፋውን ሳንቲም የፈለገችው(15፡8-10) እና አመጸኛውን ዳኛ የለመነችው ሴት (፲፰፥፩-፰)………

## ማጠቃለያ

የሉቃስ ወንጌል ዋና ጭብጥ (Theme) የዓለምን መዳን ማወጅ ነው፡፡ ቀድሞ ለተተነበየው ድኅነት፡- እስራኤል በመጠራት ይቀድማሉ፡፡ አሕዛብም ተጠርተዋል፡፡ ወንጌሉ ***"ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው።"*** ሉቃ.፪፥፴፪ ሲል አረጋግጦልናል፡፡

ክርስቶስ ለድሆች ፣ ለተናቁና ለተጠቁ ያዝን ፣ ይጎበኛቸውም ነበር፡፡ ***"የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ"*** ሉቃ.፬፥፲፰ በተደጋጋሚም ስለ እነርሱ አስተምሯል፡፡ የሉቃስ ወንጌል ልዩ ትኩረትም ይህ ነው፡፡ ***"ገዥዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል፤ ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል፤የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል፤ ባለ ጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል።"*** /ሉቃ.፩፥፶፪-፶፫ እኛም በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለናልና በፍቅር እና በእውነት ለድሆችና ለተናቁ ትኩረት ሰጥተን ልንታደጋቸው ይገባል፡፡

## ተግባር

የተማርነውን ለሌሎች ስለምናዳርስበት መንገድ ተወያዩ፡፡

www.zeorthodox.org

ይህንን በራሳችሁ በመተግበር ለሌሎች መትረፈንም ቀስ በቀስ ተለማመዱ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. የጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማዳን ለሁሉም እንደሆነ በሉቃስ ወንጌል ተጠቅሷል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ በሉቃስ ወንጌል የሚገኙ ጥቅሶችን እየጠቀሳችሁ አብራሩ፡፡
2. ስለ ሴቶች የመሪነት ሚና በሉቃስ ወንጌል የተጠቀሱ ጥቅሶችን በምሳሌነት እያቀረባችሁ ግለጹ፡፡

# የሉቃስ ወንጌል - (ሦስት) - ዝርዝር ይዘቱና አከፋፈሉ

# አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የሉቃስ ወንጌልን ይዘት በዝርዝር ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እርሱም፦ ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤"*** /ሉቃ.፳፬፥፵፬-፵፭/

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** በክፍል አንድ እና ሁለት የተገለጹትን መጻሕፍትና የሉቃስ ወንጌልን አንብቡ፡፡

## መግቢያ፡-

ይህ በተከታታይ የምንማረው የሉቃስ ወንጌል ጥናታችን ሦስተኛው ክፍል ነው፡፡ ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን፡- የወንጌሉን ዋና ሐሳብ (ጭብጥ) ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ከወንጌሉ ዋና ጭብጥ ጋር ይዘቱን እናያለን፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች፡-**

1. የሉቃስ ወንጌል ዋና ሐሳብ ምንድነው?
2. የሉቃስ ወንጌል ስለ ሴቶች ምን ይነግረናል?

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

1. **በሉቃስ ወንጌል ብቻ የተጠቀሱ ታሪኮችና ትምህርቶች፡፡**

የሳምራዊው ምሳሌ (ሉቃ.፲፥፳፭-፴፯) የጠፋው ልጅ ምሳሌ (ሉቃ. ፲፭፥፲፩-፴፪)፡፡ የመልአኩ ብስራት (ሉቃ. ፩፥፳፮-፴፰) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በልጅነቱ በቤተ መቅደስ ማሳለፉ(ሉቃ.፪፥፵፩-፶፩) የዕርገቱ ማብራሪያዎች (ሉቃ. ፳፬፥፶-፶፫) ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸው ጸሎትና ምሥጋናዎች፤ ለምሳሌ የእመቤታችን ጸሎት(ሉቃ.፩፥፵፮-፶፭) ፣ የዘካርያስ ምሥጋና (፩፥፷፰-፸፱) የስምዖን የስንብት ጸሎት (ሉቃ.፪፥፳፱-፴፭) መላእክት በልደት ሌሊት ያደረሱት ምሥጋና (ሉቃ.፪፥፲፬) ይጠቀሳሉ፡፡

## 2. ታሪካዊ ቅደም ተከተሉን የጠበቀው አቀራረብ

የሉቃስ ወንጌል ሥነ ጽሑፋዊ ውበት ተላብሶ የተጻፈ እና በምክንያታዊ አደራደር የቀረበ መጽሐፍ ነው፡፡ በመግቢያው ***"ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ*** (ሉቃ.፩÷፫) እንዳለው፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ የመገለጥ ታሪክ ከፅንሰቱ እስከ ዕርገት አስተምሮናል፡፡ ይህንንም፡-

በጥንታዊ ጽሑፎች በተለመደው መግቢያ ይጀምራል፡፡ (ሉቃ.፩÷፲፬) የክርስቶስን የሕፃንነት ዘመን መተረክን ያስቀድማል፡፡ (ሉቃ.፩÷፭፡፪÷፶፪) የወንጌላት ሁሉ ዋና ማዕከል የሆነው የክርስቶስ ለዓለም መገለጥ ይከተላል፡፡ (ሉቃ.፫÷፩-፬፡፲፫) ክርስቶስ ባደገበት በገሊላ በመጀመሪያ ማስተማሩ፡፡ (ሉቃ.፬÷፲፬፡፱÷፶) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ረጅም ጉዞ፡፡ (ሉቃ.፱÷፶፩፡፲፱÷፳፯) መድኅኑ በክብር ኢየሩሳሌም ገባ ፣ መከራ ተቀበለ ፣ በሞቱም ዓለምን አዳነ፡፡ (ሉቃ.፲፱÷፳፰፡፳፫÷፶፮) የወንጌሉ መጨረሻና ዋና ክፍል የክርስቶስ ድል - እርሱም ትንሣኤና ዕርገት ነው፡፡ (ሉቃ.፳፬÷፩-፶፫)

በዚህ አጠቃላይ ይዘቱ ከማቴዎስና ከማርቆስ ወንጌል ጋር ይመሳሰላል፡፡ በመሆኑም ሦስቱም ወንጌላት ተመሳሳይ ወንጌላት (synoptic Gosples) ይባላሉ፡፡

## 3. ዝርዝር ይዘትና አከፋፈሉ

1. **መግቢያ**(ሉቃ.፩÷፩-፬) በዘመኑ በነበሩ ግሪካዊ ጽሑፎች መግቢያ መስጠት የተለመደ ነው፡፡ ሉቃስም ከእርሱ ቀደም የተጻፉትን አንሥቶ፣ የጽሑፉን ዓለማና ምንጭ ገልጾ፣የተደራሹን ማንነት በመጥቀስ ይጀምራል፡፡
2. **ከፅንሰት እስከ ሕፃንነት ዘመን** (ሉቃ.፩÷፭፡፪÷፶፪) በዚህ ክፍል አራት ዐበይት ነገሮችን እናገኛለን፡፡ እነርሱም፡- መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ካህኑን ዘካርያስን እና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ማብሰሩ (ሉቃ.፩÷፳፮-፴፰) የድንግል የፅንስ ወራት (ሉቃ.፩÷፴፱-፹) ልደተ ክርስቶስ (ሉቃ.፪÷፩-፳) እና የክርስቶስ የሕፃንነት ዘመን (ሉቃ.፪÷፳፩-፶፪) ናቸው፡፡
3. **የክርስቶስ ለዓለም መገለጥ** (ሉቃ.፫÷፩-፬፡፲፫) የዮሐንስ ትምህርት እና አገልግሎት(ሉቃ.፫÷፩-፳) የጌታ ጥምቀት (ሉቃ.፫÷፳፩÷፳፪) የጌታችን ትውልደ ሐረግ እስከ አዳም (ሉቃ.፫÷፳፫-፴፰) የጌታ ጾምና መፈተን(ሉቃ.፬÷፩-፲፫)
4. **ክርስቶስ የገሊላ ትምህርቱና ሥራዎቹ** (4፡14-9፡50) በዚህ ሥፍራ በገሊላ አውራጃዎች እየተዘዋወረ ማስተማሩና ተአምራት መሥራቱ ተገልጦአል፡፡
5. **የኢየሩሳሌም ጉዞው** (ሉቃ.፱÷፶፩፡፲፱÷፳፯) በሉቃስ ወንጌል የምናገኘው ይህ ረጅም ጉዞ ፤ ጌታችን በጉዞው ያስተማረው ትምህርትና የሠራቸውን ድንቅ ሥራዎች ይዟል፡፡

www.zeorthodox.org

6. **የመጨረሻዋ ሳምንት** (ሉቃ.፲፱÷፳፰፡፳፫÷፶፮) ጌታችን በዚህ ምድር በሥጋ በተገለጠበት ዘመን ፤ በነበሩት የመጨረሻዎቹ ስድስት ቀናት (ከእሑድ እስከ ዓርብ) የፈጸመውን ዓለምን የማዳን ሥራ ይህ ክፍል ይተርክልናል፡፡
7. **ትንሣኤና ዕርገት** (ሉቃ.፳፬÷፩-፶፫) በዚህ ክፍል በሌሎች ወንጌላት ያልተገለጡ የትንሣኤው ሰሞን ታሪኮች አሉ፡፡ የኤማሁስ መንገደኞችና የክርስቶስ ዕርገትም በስፋት የተነሣበት ክፍል ነው፡፡

## ማጠቃለያ

- ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉ በሌሎች ወንጌላት ያልተጠቀሱና ክርስቶስ ለተዋረደው የሰው ልጅ ያለውን ፍቅርና ውለታውን የሚያስረዱ በርካታ ታሪኮችን በመተረክ ብዙዎችን ፤ የነፍስ ዕረፍት ወደ ሆነችው ንስሐ አድርሷል፡፡ ይህም ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ ***“ስለዚህ የላሉትን እጆች የሰለሉትንም ጉልበቶች አቅኑ፤ ያነከሰውም እንዲፈወስ እንጂ እንዳይናጋ፥ ለእግራችሁ ቅን መንገድ አድርጉ።”*** /ዕብ.፲፩÷፲፪-፲፫/ ያለውን ያስታውሰናል፡፡ እኛም ***“እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።”*** /ማቴ.፲፩÷፳፰/ እንደተባለ ድሆች፣ሕሙማን፣ ምስኪኖችንና ኃጢአት የከበደባቸውን በክርስቶስ ትምህርት ማጽናናትና መመለስ ይገባናል፡፡
- በማራኪ ሥነ ጽሑፋዊ ውበትና አደራደር የተጻፈው የሉቃስ ወንጌል ፤ ክርስትናን ለማስተላለፍ ያለንን ጥበብና ጸጋ መጠቀምን ያስተምረናል፡፡
- ሦስተኛው ወንጌል የሉቃስ ወንጌል ሃያ አራት ምዕራፎች፣ 1149 ቁጥሮች አሉት፡፡

## ተግባር

- ለሰዎች ሁሉ ለመዳን የምትተጉ ሁኑ፡፡ ባላችሁ ጸጋና እውቀት ለሌሎች ትረፉ፡፡ የተናቁትንና የተገፉትን ጎብኙ እርዱም፡፡
- ወንጌሉን ከፋፍላችሁ በአንድ ሳምንት አንብቡ፡፡

www.zeorthodox.org

**ጥያቄዎች፡-**

1. በሉቃስ ወንጌል ብቻ የተጠቀሱ ትምህርቶችን ጥቅሶችን እያቀረባችሁ አብራሩ፡፡
2. ተመሳሳይ ወንጌላት (Synoptic Gospels) የሚባሉትን ወንጌሎች በዝርዝር ግለጹ፡፡
3. የሉቃስ ወንጌል ምን ያህል ምዕራፎች እና ቁጥሮች አሉት?

# ፩ኛ ጢሞቴዎስ

# ስድስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** *ተማሪዎች ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ጢሞቴዎስ ከላከው የመጀመሪያው መልእክት በእግዚአብሔር ቤት ስለመኖር ይረዳሉ፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡*

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፣ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት፥ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው"*** ፩ኛ ጢሞ.፫፥፲፭

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** *ሙሉ መልእክቱን አንብቡ፤ የቅዱስ ጳውሎስ ትርጓሜ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡*

## መግቢያ፡-

*ቅዱስ ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዐሥራ አራት መልእክታትን ጽፎልናል፡፡ ከእነዚህ አራቱ በግል ለሰዎች የተላኩ ናቸው፡፡ ሁለቱ ለጢሞቴዎስ፣ አንድ ለቲቶና አንድ ለፊልሞና ተላኩ፡፡ ከእነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሦስት መልእክታት መልእክታት የቤተ ክርስቲያን ጠባቂነት /የኖላዊነት/ መልእክታት ይባላሉ፡፡ በእነዚህ የኖላዊነት መልእክታት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት መምራት እንዳለባቸው፤ የክህነትን አሰጣጥና መዓርግ አሳይቷል፡፡ ምእመናን እንዴት ማገልገል እንዳለባቸውም አስተምሯል፡፡ /፩ኛ.ጢሞ.፫፥፩-፲፫፣ ቲቶ.፩፥፭-፱/፡፡ በፊልሞና መልእክትም ቅዱስ ጳውሎስ ያስታረቀበት መልእክት ነው፡፡*

*በዛሬው ትምህርታችን ቀዳማዊ ጢሞቴዎስን እንማራለን፡፡*

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

### 1. ጢሞቴዎስ

*ጢሞቴዎስ በሊቃዖንያ አውራጃ በልስጥራን ተወለደ፡፡ አባቱ ግሪካዊ እናቱ አይሁዳዊት ነበሩ፡፡ (የሐዋ.፲፮፥፩-፫) ጢሞቴዎስን ለመጀመሪያው ጊዜ እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ያደረጉት አያቱ ሎይድና እናቱ ኤውንቄ ናቸው፡፡(፩ኛ ጢሞ.፩፥፭፤፫፥፲፭) የቅዱስ ጳውሎስ በኩር የመንፈስ ልጅ ነው፡፡ ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስም በምግባሩና በሃይማኖቱ ይወደው ነበር፡፡ (፩ኛ.ቆሮ. ፬፥፲፯፣ ፩ኛ. ጢሞ.፩፥፪፣ ፪ኛ.ጢሞ.፩፥፪)*

*ክርስቲያናዊ ትምህርትን በሚገባ ያገኘው ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው ፣ ቅዱስ ጳውሎስ*

በሁለተኛ ሐዋርያዊ ጉዞው ወደ ልስጥራ ሲሄድና በመንፈሳዊ ቅንዓት ሲያስተምር አገኘው። ጢሞቴዎስ አዲስ አማኒ እና በዕድሜውም ወጣት ነበር። በክርስቶስ ያለው እምነቱ እና አገልግሎቱ ፍጹም ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን አይቶ ዲቁና ሾመው። ፩ኛ ጢሞ.፬÷፲፬

በ፶፩(51) ዓ.ም ጀምሮ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር አገልግሏል። በልዩ ልዩ ሃገሮች መልእክትን በማድረስ ተልኳል። በቃልም እየተላከ ብዙ መንፈሳዊ ግዳጅን ፈጽሟል። በመጨረሻ ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾመው። ከቅዱስ ጳውሎስ ሰማዕትነት በኋላ በሐዋርያነት ሥራ ለረጅም ዓመታት ደክሞ፤ ድምጥያኖስ የተባለው ከሐዲ ንጉሥ አስገድሎት በሰማዕትነት በ፺፮(96) ዓ.ም ገደማ ዐረፈ።

## 2. የመልእክቲቱ መጻፍ።

### ምክንያተ ጽሒፍ

1. **የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ለማሳወቅ**። ጢሞቴዎስ ሲሾም ብዙ እንቅፋት አጋጠመው።ይህንንም ለቅዱስ ጳውሎስ ገልጦለታል። ቅዱስ ጳውሎስም ለአገልግሎቱ መመሪያ እንዲሆነው እነዚህን መልእክቶች ጻፈለት።(፩ኛ ጢሞ.፫÷፫ እና ፲፫) ይኸንንም ከጻፈለት በኋላ እራሱ መጥቶ እንደሚጎበኘው ተስፋ ሰጠው። (፩ኛ ጢሞ.፫÷፲፬) በትጋትና በንቃት እንዲሠራ (፬÷፲፬) ጤናውን እንዲጠብቅ (፭÷፳፫) በሕፃንነቱ የሚንቀው እንዳይኖር አሳሰበው (፬÷፲፪) ሊሰራው የሚገባውን ዘርዝሮ ጻፈለት።
2. **ከሐሰተኞች ትምህርት እንዲጠነቀቅና ምእመናንን እንዲጠብቅ** ሊያሳስበው። (፩ኛ ጢሞ.፩÷፲፰-፳፤፬÷፩-፯)

**መቼና የት ተጻፈ**? ይህች መልእክት በ66 ዓ.ም አካባቢ ኤፌሶን ተጻፈች።

## 3. አከፋፈሉ

1. መግቢያ ፩÷፩-፪
2. ከሐሰተኛ ትምህርት እንዲጠበቁ። ፩÷፫-፳
3. ሥርዓተ ጸሎት። ፪÷፩-፲፭
4. ስለ ኤጲስ ቆጶሳት እና ዲያቆናት ምርጫ።፫÷፩-፲፮
5. የሐሰት ትምህርት እና መፍትሔው። ፬÷፩-፲፯
6. ሁሉንም በዕድሜ በሚገባቸው ቀረቤታ ስለመርዳት።፭÷፩-፲፯
7. ልዩ ልዩ ምክሮች። ፯÷፫-፳፩

www.zeorthodox.org

**ማጠቃለያ፡-** ጢሞቴዎስ የቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጅ ነው። የአባቱን ምክር እና ትምህርት ሰምቶ ለታላቅ ክብር በቃ። እኛም የመንፈስ አባቶቻችንን በምግባር እንምሰላቸው።

የጢሞቴዎስ መልእክት ብዙ ምክሮችን የያዘች ናት። ለሁላችንም በእግዚአብሔር ቤት

በንጽሕናና በእውነት ማገልገልን ያስተምረናል፡፡

## ተግባር

♣ መልእቲቱን አንብቡ፡፡ ተወያዩበት፡፡ ያልገባችሁን ከመምህራን ጠይቁ፡፡

***ጥያቄዎች:-***

1. ቅዱስ ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጻፋቸው መልእክታት ስንት ናቸው? ዝርዝራቸውን ግለጹ፡፡
2. ጢሞቴዎስ የተወለደበት ቦታ የት ነው? እናትና አባቱ የምን ሀገር ሰዎች ናቸው? እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ያደረጉት እነማን ናቸው?
3. ስለጢሞቴዎስ አገልግሎት እና መዓርጋት በዝርዝር አብራሩ፡፡
4. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የመጀመሪያውን መልእክት የጻፈለት ምክንያት ለምንድነው?አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ፪ኛ ጢሞቴዎስ

# ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ከሁለተኛው የቅዱስ ጳውሎስ ወደ ጢሞቴዎስ መልእክት በፈተና ወቅት ስለሚኖረን ቅድስናና የክርስትና ኑሮ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"በቶሎ ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ"*** /፪ጢሞ.፬፥፱/

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሙሉ መልእክቱን አንብቡ፤ ጳውሎስ ትርጓሜ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በግል ለአገልጋዮች (ሰዎች) የተላኩትን ማየት ጀምረናል፡፡ በዚህ መሠረትም ፩ኛ ጢሞቴዎስን ተምረናል፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. በግል የተላኩ መልእክታት የምንላቸው የትኞችን ነው? ዘርዝሩ፡፡
2. የኖላዊነት መልእክታት ማለት ምን ማለት ነው? ለምን በዚህ ስም ተጠሩ፡፡
3. ፩ኛ ጢሞቴዎስ ለምን ተጻፈ?

በዛሬው ትምህርታችንም ተከታዩን መጽሐፍ ፪ኛ ጢሞቴዎስን እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. መቼና የት ተጻፈ

ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን መልእክት ለጢሞቴዎስ የጻፈው በመጨረሻውና በሁለተኛው እስራቱ ነው፡፡ ይህንንም ከመልእክቱ እንረዳለን፡፡ ለዚህ ነው የሕይወት ጉዞውን እንደፈጸመ፣ ሩጫውን እንደጨረሰ፣ ሁሉን እንዳደረገ፣ የሚቀረው ነገር ቢኖር ከእውነተኛው ዋጋ ከፋይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሕይወት አክሊልን ማግኘት እንደሆነ የገለጠው፡፡ (፪ኛ.ጢሞ.፬፥፰) ይኸም ከመሞቱ ትንሽ ቀደም ብሎ በመጨረሻ ሕይወቱ በ፷፰(68) ዓ.ም ገደማ የጻፈው እንደሆነ ያመለክተናል፡፡

www.zoorthodox.org

እርሱ በችግርና በእስራት ሳለ ወዳጆች ሁሉ ጥለውት በመሄዳቸው አዘነ፡፡ በዚህም ሃይማኖታዊ ልጁ ጢሞቴዎስ በፍጥነት ክረምት ሳይገባ ወይም ሳይሞት እንዲደርስ እንዲያየው ቸኩሎ የጻፈው መልእክት ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በሮም ሳለ እንደጻፈው ያስረዳል፡፡

### 2. ምክንያተ ጽሒፍ

2.1. **ለማጽናት፡-** ብዙ መናፍቃን ጢሞቴዎስን እንደሚቃወሙት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

በሰማ ጊዜ ምንም በእስር ቤት ቢሆን ሊታገስ አልቻለም፡፡ ስለዚህ በማንኛውም ጊዜና ቦታ ጢሞቴዎስ ዝም ማለት እንዳይገባው፤ ተግቶ ነቅቶ እንዲያስተምር፤ የክርስቶስ ወታደር እንደመሆኑ መጠን ጠንክሮ እንዲዋጋ /፪፥፫/ የተሰጠውን ቃል ኪዳን በትክክል እንዲፈጽም ለመምከር ነው፡፡ /፫፥፲-፲፬/

2.2. **ጢሞቴዎስ እንዲመጣለት ፈልጎ፡-** ቅዱስ ጳውሎስ ዕረፍቱ እንደደረሰ አውቋል፡፡ /፬፥፬-፯/ በመሆኑም ሳይሞት የሚወደውን ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን ለማየት ናፍቋል፡፡/፩፥፬/ ዕቃዎችንም በተለይም መጻሕፍትን እንዲያመጣለት ስለፈለገ፡፡/፬፥፲፫/ ***"በቶሎ ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ"*** /፬፥፱/ይላል፡፡

## 3. ዝርዝር ሐሳቡና ይዘቱ

ትምህርተ ኖሎት ነው፡፡ ጢሞቴዎስ አገልጋይ ነው፡፡ ያውም በከፍተኛው የጵጵስና መዓርግ ያለ አገልጋይ ነው፡፡ ሆኖም በቤተ ክርስቲያን ሁሉ የደረሰው የውጭና የውስጥ ፈተና በእርሱም ላይ ደርሶበታል፡፡ በመሆኑም ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ፍቅሩን ይገልጥለታል፡፡ (፩፥፩-፲፰) በውስጡ ያለውን ጸጋ እንዲያነሣሣ ይመክረዋል፡፡(፪ኛ ጢሞ.፩፥፯-፲፬) ለሚያስተምሩ አደራ ስጥ ይለዋል፡፡ (፪፥፩-፪) እንደወታደር ለመከራና ለመንፈሳዊ ጦርነት እንዲዘጋጅ ይመክረዋል፡፡ (፪፥፫-፲፫)

ለአገልጋይ ከማይገቡ ከከንቱ መለፍለፍ ከዝሙትና ከጥል እንዲርቅ ይመክረዋል፡፡ ይልቁንም አደራውን እንዲወጣ ያሳስበዋል፡፡ (፪፥፱-፳፬) በመጨረሻው ዘመን ስለሚነሡ ገልጦ ከእነርሱ እንዲርቅ፤በተማረው እንዲጸና ያዘዋል፡፡/፫፥፩-፲፯/ መጽናት በጊዜውም አለጊዜውም ነው፡፡ /፬፥፩-፰/

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መሄጃው ደርሷል፡፡ መከራውም ጸንቷል፡፡ /፬፥፮-፱/ በዚህ መከራ ሉቃስ ብቻ ሲቀር ሌሎቹ የሉም፡፡ እናም እውነተኛ ወዳጁንና ልጁን ጢሞቴዎስን ከማርቆስ ጋር እንዲመጣ ፈልጎታል፡፡ /፬፥፲-፳፪/

## 4. አከፋፈሉ

4.1. መግቢያ ፩፥፩-፰
4.2. በፈተና እንዲጸና ፩፥፯-፲፰
4.3. ለአገልግሎቱ እንዲጠነቀቅ ፪፥፩-፳፯
4.4. ስለ መጨረሻው ዘመን የተነገረ ትንቢታዊ ማስጠንቀቂያ (፫፥፩-፲፯)
4.5. ማጠቃለያ (፬፥፩-፳፪)

www.zeorthodox.org

**ማጠቃለያ**፡- ሁልጊዜም ፈተና አለ፡፡ የአንድ ክርስቲያን ጽናት የሚታየው በፈተና ጊዜ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ማንም አጠገቡ ባልነበረበት ጊዜ እውነተኛ ወዳጆቹንና የሚያገኘውን አክሊል አየ፡፡

ክርስትና እንደ ወታደር ዘወትር በተጠንቀቅ ሆኖ መጋደል ነው። ከእኛም ይህ ይጠበቃል። ግራ በሚያጋቡን ሰዎች መሐል ሆነን ከማይገባ ንግግርና ድርጊት በመቆጠብ በመንፈሳዊነት እንጽና።

በዘመኑ መጨረሻ የሚነሡ ***"ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤"*** ናቸው። ፪ኛ ጢሞ. ፫፥፩-፬

የታዘዝነው ከእነዚህ መራቅን ነው። /፪ኛ ጢሞ.፫፥፭/ አብረናቸው ብንሆን ልንመስላቸው እንችላለን። ከዚሁም ጋር እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ***"አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግሥቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ፤"*** እንደተባለ የበረቱተን እንከተላቸው። /፪ኛ ጢሞ.፫፥፲/

## ተግባር

- የተማራችሁትን በንባብ አዳብሩ። መልካም አርአያቸውን በመከተል እውነተኞችን ለመምሰል ተለማመዱ። ከክፉ ሰዎችና ድርጊታቸው ተጠበቁ።

**ጥያቄ፡-**

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ጢሞቴዎስ የላከውን ሁለተኛውን መልእክት የጻፈው የት ሆኖ መቼ ነው? ይህን መልእክት የጻፈለት ቅዱስ ጳውሎስ በምን ሁኔታ ላይ እያለ ነበር? አብራሩ።
2. ቅዱስ ጳውሎስ ሁለተኛውን መልእክት ለጢሞቴዎስ የጻፈበት ምክንያት ለምንድነው?
3. ሁለተኛውን የጢሞቴዎስ መልእክት ዝርዝር ሐሳብና ይዘት አብራሩ።

www.zeorthodox.org

# ወደ ቲቶ

# ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀመዝሙሩ ለቲቶ ከጻፈው መልእክት፤ በእግዚአብሔር ቸርነት ስለማመንና በመልካም ሥራ ስለ መጽናት ይገነዘባሉ፤ በመምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤"*** / ቲቶ. ፪፥፲፩-፲፫/

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መልእክቱን በሙሉ አንብቡ፤ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ትርጓሜ

**መግቢያ፡-** ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በግል ለሰዎች ከላካቸው መልእክታት ውስጥ ባለፉት ተከታታይ የትምህርት ክፍሎች ለጢሞቴዎስ የላካቸውን መልእክቶች ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ሦስተኛውን እና በግል ወደ ቲቶ ስለላከው መልእክት እንማራለን፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

| | |
|---|---|
| 1. 2ኛ ጢሞቴዎስ ለምን ተጻፈ? | 2. በመጨረሻው ዘመን ምን ዓይነት ሰዎች ይነሣሉ? |
| 3. ጢሞቴዎስ ያጋጠመው ፈተና ምን ነበር? | 4. እኛስ ምን ማድረግ አለብን? |

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. ቲቶ

www.zeorthodox.org

ቲቶ ቅዱስ ጳውሎስ ከሚወዳቸው ደቀ መዝሙሮቹ መካከል አንዱ ነው፡፡ በሥራ ረዳቱ፣ በመከራውም ጊዜ አብሮት የቆመ ነው፡፡(ገላ.፪፥፫) ትውልዱ አረማዊ የአንጾኪያ ሰው ነው፡፡ በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ስለ አመነ እውነተኛ የመንፈስ ልጁ ይባላል፡፡(ቲቶ.፩፥፬) ቲቶ ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ከአንፆኪያ ወደ ኢየሩሳሌም በ፶(50) ዓ.ም ሄዶአል፡፡ /የሐዋ.፲፭፥፪/ የቅዱስ ጳውሎስ ተላላኪ ሆኖ በብዙ ቦታዎች ረድቷል፡፡ በተለይም ወደ ገላትያ ቤተ ክርስቲያን ይመላለስ ነበር፡፡(ገላ.፪፥፪) ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በመልእክት እንደተመላለሰ ሐዋርያዊ ተግባሩንም እንደፈጸመ ተጽፏል፡፡

(፪ኛ.ቆሮ.፰፥፲፰)

በዚህ በሐዋርያዊ ሥራ ሁሉ የተጋ የነቃ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ በብዙ በኩል ተረድቶ የቀርጤስን ቤተ ክርስቲያን እንዲያስተዳድርለት ኤጲስ ቆጶስነት ሾመው፡፡ ሕግም ሠርቶ አስቀመጠው (ቲቶ.፩፥፩)

ቲቶ በተሾመበት ቦታ በትጋት አገለግለ፡፡ ሐዋርያዊ ተግባሩንም በሚገባ ፈጸመ፡፡ ዕድሜ ጠግቦና አርጅቶ ዐረፈ ሲል የቤተ ክርስቲያን ትውፊት በሰፊው ያስረዳል፡፡

## 2. የቀርጤስ ቤተ ክርስቲያን

ቀርጤስ በታላቁ ባሕር (ሜድትራንያን ባሕር) በአፍሪካና በግሪክ መካከል ትገኛለች፡፡ ተራራማና ሰፊ ደሴት ናት፡፡ ***"የቀርጤስ ሰዎች ዘወትር ውሸተኞች፥ ክፉዎች አራዊት፥ በላተኞች፥ ሥራ ፈቶች ናቸው"*** (ቲቶ.፩፥፲፪) ተብሎ በራሳቸው ሰዎች ተነግሮባቸው ነበር፡፡ በቀርጤስ አይሁድ በብዛት ይኖሩባት ነበር፡፡ የቀርጤስ ሰዎች በበዐለ ኀምሳ ተገኝተው ነበር፡፡ (የሐዋ.፪፥፲፩) ቅዱስ ጳውሎስ ታስሮ በመርከብ ሲጓዝ በቀርጤስ አልፏል፡፡ (የሐዋ.፳፯፥፯) እንዳስተማረ የሚተርኩ ትውፊቶችም አሉ፡፡

## 3. የመልእክቲቱ መጻፍ

በይዘት ከመጀመሪያው የጢሞቴዎስ መልእክት ጋር ይመሳሰላል፡፡ በተመሳሳይ ቦታና ዘመን የተጻፈ መልእክት ነው፡፡ የተጻፈበትም ምክንያት በቀርጤስ አብያተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ ቦታዎች ተቋቁመው በቁጥር በዝተው ቢገኙም ገና አልደረጁም ነበር፡፡ ይህን ሁሉ መልክ ሰጥቶ እንዲያስተዳድር መመሪያ ለመስጠት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቲቶ ጻፈለት፡፡

ከላይ እንዳየነው የቁርጤስ ሰዎች ጠባያቸው የከፋ ስማቸው የጠፋ ነበር፡፡ መከራ እንዳይበዛበት በመጣበት ጊዜም እንዲታገሥ አስቀድሞ የሰዎቹን ጠባይ ይገልጥለታል፡፡ (ቲቶ.፩፥፲፪) ደግሞም ዓለማዊ ጠባያቸውን ይዘው ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡ ነበሩ፡፡ በመካከላቸውም መናፍቃን ነበሩና ቲቶ ከነርሱ እንዲርቅና ምእመናንንም እንዲጠብቅ ቅዱስ ጳውሎስ ጻፈለት፡፡ (ቲቶ. ፩፥፲-፲፪፤፪፥፲፭፤፫፥፱-፲፩) ከዚህ ሌላ የተገለጠው ዋና ዓላማ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ የሆኑትን እየመረጠ እንዲሾምና እርሱም በትጋት እንዲጠበቅ ነው፡፡ (ቲቶ. ፩፥፭-፱፥፲)

**4. አጠቃላይ ይዘት፡-** ሓላፊነቱን በአግባብ እንዲወጣ፡፡ ከስሕተት ትምህርት ጠብቆ ምእመናንን ***"በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ"*** እንዲወቅሳቸው፤ ስለ ቀሳውስትና የኤጲስ ቆጶሳት ሹመት መስፈርት፤ ስለ መልካም ሥራ ፤ ሃይማኖትና ሥርዓተ ኖሎት አብራርቷል፡፡

## 5. አከፋፈል

www.zoorthodox.org

**መግቢያ (፩፥፩-፬)**

✍ በዚህ ቦታ ጳውሎስ ራሱንና ኃላፊነቱን ገልጦ ፤ ሰላምታ ለቲቶ ያቀርባል፡፡

**ሥርዓተ ኖሎት (፩፥፭-፱)**

✍ የኤጲስ ቆጶሳትና የቀሳውስት ሹመት መመዘኛ፡፡

**ከስሕተት ትምህርት መጠበቅ (፩፥፲-፲፮)**

✍ ስሕተቱ ርኩስ አለ እያሉ ያመኑትን የሚገለብጡ ናቸው፡፡ ዓላማቸውም ክርስቲያኖችን ወደ ይሁዲነት መመለስ ነበር፡፡ እነዚህ መናፍቃን የማይታዘዙ ነውረኛ ረብ የለሽና ለበጎ ሥራ የማይበቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ራሱንና መንጋውን እንዲጠብቅ ይመክረዋል፡፡

**ክርስቲያናዊ አኗኗር (፪፥፩-፲)**

✍ በተለያየ ዕድሜና ኑሮ የሚገኙ ምእመንን ሊኖራቸው ስለሚገባው ሕይወትና ስለቲቶን ሓላፊነት፡፡

**የመዳንና የነገረ ሥጋዌ መሠረታዊ ትምህርት (፫፥፩-፲፩)**

✍ ሰዎችን የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአል፡፡ /፪፥፲፩-፲፭/ ይህ ድኅነት በእግዚአብሔር ቸርነት ነው፡፡ /፫፥፩-፯/ ሆኖም በመልካም ሥራ መጽናት ከአማንያን ይጠበቃል፡፡ /፫፥፰-፲፩/

**መዝጊያ (፫፥፲፪-፲፭)**

✍ በዚህ ቦታ ምክርና የማጠቃለያ ሰላምታ በማቅረብ ዘግቶታል፡፡

**ማጠቃለያ፡-** ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ አግባብ የምትመራ ናት፡፡ ከሃይማኖት ስሕተት መጠበቅ ይገባል፡፡ መዳን በእግዚአብሔር ቸርነት ተደርጎልናል፡፡ ለእግዚአብሔር ቸርነት የሚኖረን መልስ በመልካም ሥራ በመጽናት እርሱን በማሳየትም መሆን አለበት፡፡

www.zeorthodox.org

**ተግባር፡-** መልካም አኗኗርን በተግባር እና በቀጣይነት የምትሳዩ ሁኑ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሚወዳቸው ደቀመዛሙርት አንዱ የሆነው ቲቶ ትውልዱና ሀገሩ የትነው? በየት ሀገር(በማን) ቤተክርስቲያን ተሾመ?
2. የቲቶ መልእክት አጠቃላይ ይዘት ምንድነው? አብራሩ፡፡
3. በቲቶ መልእክት ስለ ሥርዓተ ኖሎት የተጠቀሰውን ገልጻችሁ አብራሩ፡፡

# ወደ ፊልሞና
# ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልሞና ከላከው መልእክት ተማሪዎች ስለ ይቅርታና ስለ ፍቅር ይገነዘባሉ፤ በመምህሩ የሚሰጧቸው ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ስለ ፍቅር እለምናለሁ"* ፊልሞ.፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መልእክቱን በሙሉ ፤ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ትርጓሜ ፤

**መግቢያ፡-** ባለፉት ተከታታይ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በግል የላካቸውን መልእክታት ተምረናል። ከእነዚህም ውስጥ ወደ ጢሞቴዎስ እና ወደ ቲቶ የላካቸው መልእክታት ይገኙባቸዋል። ዛሬም ትምህርታችንን በመቀጠል ወደ ፊልሞና ስለላከው መልእክት እንማራለን።

**የክለሳ ጥያቄዎች**

ወደ ቲቶ የተላከው መልእክት ዋና ሐሳብ ምን ነበር?

ቀርጤስ የት ትገኛለች? የቀርጤስ ሰዎች ችግር ምን ነበር?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

1. ፊልሞና ማነው ?

ፊልሞና በቆላስይስ የሚኖር ባዕለ ጸጋ ነው። ወደ ክርስቶስ ትምህርት የተመለሰው በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ነው። እርሱም ከሚስቱ አምጽፍያና ከልጁ አርክጳ ጋር የሚያገለግል ብርቱ ክርስቲያን ነበር። የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በፊልሞና ቤት ነው። ፊልሞና ደግ ባለጸጋ ስለነበር ማንኛውንም ክርስቲያን በቤቱ ያስተናግድ፣ ምስኪኖችን የሚረዳ፣ የተቸገሩ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆችንም ያሳድግ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ማስተናገጃ ቤት እንዲያዘጋጅ ጠይቆታል። ብዙ አገልጋዮችም ነበሩት ከአገልጋዮቹ መካከል አንዱ አናሲሞስ ነው።

2. አናሲሞስ

አናሲሞስ የፊልሞና አገልጋይ ነበር። ሆኖም የጌታውን ገንዘብ አጥፍቶና ከድቶት ሄደ። ቅዱስ ጳውሎስ በቁም እስር እያለ አግኝቶት። አናሲሞስ ቀርቦ ያገለግለው ጀመር። ከዚያም ራሱን ገለጠለት። አናሲሞስ በሥራው መጸጸቱንም ተናዘዘ። ሐዋርያው አማላጅ እንዲሆነውም ለመነው።

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጳውሎስም አናሲሞስ እውነተኛ ተነሳሂ ክርስቲያን መሆኑን መርምሮ ከተረዳ በኋላ አናሲሞስ ከወዳጁ ተጣልቶ፣ ከቤቱ ወጥቶ ሊቀር አልፈቀደም። ከዚሁም ጋር በሮም ሕግ የኮበለለ ባርያ በሞት ይቀጣል። በመሆኑም ሁለቱን በማስማማት ፍቅር ለማውረድ ይህችን ደብዳቤ ጻፈ።

## 3. መልእክቱ የት እና መቼ ተጻፈ?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮም በእስር በነበረበት ጊዜ። ስለ ቆላስያስ ቤተ ክርስቲያን ሰምቶ መልእክት ጻፈ። /ቆላስ.፬፥፯-፲/ አብሮም ይህችን መልእክት በግል ለፊልሞና እንድትደርስ አዘጋጀ። ከቲኪቆስም ጋር አናሲሞስን አብሮ ላከው። ጳውሎስ አናሲሞስን ለራሱ ሊያስቀረው ይፈልግ ነበር። ሆኖም የፊልሞናን ፍቃድ ሳያገኝ ማስቀረት አልፈለገም። በመሆኑም ይህች መልእክት በቁም እስራቱ በ፷፫(63) ዓ.ም ገደማ ተጻፈች።

## 4. የመልእክቱ ይዘት፡-

4.1. **እርቅና ፍቅር ማውረድ ነው፡-** ፊልሞና አናሲሞስን ይቅር ብሎ እንዲቀበለው ከቁ.9-22 ***ስለ ፍቅር እለምናለሁ.....ተቀበለው ...***በማለቱ በሁለቱ መካከል እርቅና ፍቅር መለሰ።

4.2. **የባሮችን ነጻነት ያስተማረበት ነው፡-** ክርስትና የባርያ አሳዳሪ ሥርዓትን አይፈቅድም። ምክንያቱም ሁሉም ፍጥረት እኩል ነው። ሆኖም በታላቁ የሮም መንግሥት ፤ ሥር የሰደደውን ይህን ሥርዓት በቀጥታ መቃወም ከፍተኛ ማኅበራዊ ቀውስ መፍጠር ነው። ለባሮችም በወቅቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያይልባቸው ይችላል። የፊልሞናን ዓይነት ታዛዥ ክርስቲያን ሲገኝ ይህን ማስተማር ስለሚገባ ሐዋርያው ***"ከእንግዲህ ወዲህ እንደ ባሪያ አይሆንም፥ ነገር ግን ለእኔ በተለየ የተወደደ ወንድም ከሆነ፥ ለአንተማ ይልቅ በሥጋውም በጌታም ዘንድ ከባሪያ የሚሻል የተወደደ ወንድም እንዴት አይሆንም"*** ቁ.፲፮ ብሎታል።

4.3. **ወደ ቆላስያስ ስለሚሄድ እንዲዘጋጁ ለማሳሰብ ነው፡-** የቆላስያስ ክርስቲያኖች የመንፈስ አባታቸው ጳውሎስ እንዲመጣላቸውና ቡራኬና ትምህርት እንዲቀበሉ ይጸልዩ ነበር። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ፊልሞና ማረፊያ ቤት እንዲያዘጋጅለት ለማዘዝ ጻፈ፡- ***"ደግም ከዚህም ጋር የማስተናገጃ ቤት አዘጋጅልኝ፤ በጸሎታችሁ ለእናንተ እንድሰጥ ተስፋ አደርጋለሁና"*** ቁ.፳፪

www.zeorthodox.org

## 5. አከፋፈል

የመግቢያ ሰላምታ (ከቁጥር ፩ እስከ ፯)

የዕርቅ ልመና (ከቁጥር ፰ እስከ ፳፪)

የመዝጊያ ሰላምታና ቡራኬ (ከቁጥር ፳፫ እስከ ፳፭)

## ማጠቃለያ

- ደግና እውነተኛ ክርስቲያን የነበረው ፊልሞና በአናሲሞስ ክህደትና ስርቆት አዝኗል፡፡ ይህ የአናሲሞስ ድርጊት ከክርስትና ትምህርት አንጻር ስሕተት ነው፡፡ በሮም ሕግም በሞት ወይም በሌላ ከባድ ቅጣት ያስቀጣዋል፡፡ ከስርቆትና ሰዎች ሲያምኑን ከማጉደል መጠበቅ አለብን፡፡
- የአናሲሞስ ጸጸትና መመለስ የእውነት ነበር፡፡ ***"እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን ጸጸት የሌለበትን፥ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና፤ የዓለም ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል።"*** ፪ኛ.ቆሮ.፯፥፲ እኛም በጥፋታችን የእውነት ተነሳሕያን መሆንን እንማርበታለን፡፡
- ይቅርታ የክርስትና መሠረታዊ ትምህርት ነው፡፡ ***"እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።"*** /ማቴ.፭፥፳፫-፳፬/ በዕለታዊ ጸሎታችን ***በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል*** የምንለውም ለዚህ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ የለመነውም ይህንኑ ነው፡፡
- አስታራቂነት ክርስቲያኖች በመስቀል ከተሰቀለው ጌታ የተማርነው የተቀደሰ ተግባር ነው፡፡ ማስታረቅ ብጽዕና ነው፡፡ ***"የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።"*** ማቴ.5፡9 ቅዱስ ጳውሎስም ***ስለፍቅር አለምናለሁ*** ቁ.፱ ብሎ አስታረቀ፡፡ በማስታረቅ ፍቅርን እናነግሣለን፡፡ እውነተኛ ፍቅር ባለበት እግዚአብሔር አለ፡፡

## ተግባር

- ክርስትና የንስሐ ሃይማኖት ነው፡፡ ከጥፋታችሁ ታረሙ፡፡ከተቀያየማችሁት ጋር ዛሬውኑ ይቅር ተባባሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ጥያቄዎች፡-

1. ፊልሞና የየት ሀገር ሰው ነበር? እንዴት ክርስቲያን ሆነ?
2. ስለፊልሞና ማንነትና አገልግሎት ግለጹ፡፡
3. የፊልሞና አገልጋይ የነበረው አናሲሞስ ከጌታው ከፊልሞና ጋር የተጣሉት /የተለያዩት/ በምን ምክንያት ነበር?
4. አናሲሞስ ከፊልሞና ጋር እንዴት ሊታረቅ ቻለ?

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ(ከ፭ እስከ ፮ኛ መ.ክ.ዘ) - (አንድ)

# ዐሥረኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች በአምስተኛው እና በስድስተኛው መቶ ክፍል ዘመን ስለነበረው የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ያውቃሉ፡፡ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** **"ለኢትዮጵያ ሰዎች ምግብቸውን ሰጠሃቸው"** /መዝ.፸፬፥፲፬/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› ፤ አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) ፣ ሉሌ መልአኩ

**መግቢያ፡-** ከዚህ በፊት ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተምረናል፡፡ በትምህርታችንም ክርስትና በጃንደረባው አማካኝነት በ፴፬(34) ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጣ፤ በአባ ሰላማ አማካኝነት ከሰሜን እስከ ደቡብ መስፋፋቱንም ተመረናል፡፡

ከዚህ የትምህርቱ ክፍል ጀምሮ በቀጣዮቹ ክፍላተ ዘመናት በታዩት ዋና ዋና ታሪካዊ ክሥተቶች ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡ ዛሬ የዘጠኙ ቅዱሳንን ወደ ሀገራችን መግባት እና የቅዱስ ያሬድን ታሪክ በማስቀደም ለሰባት ተከታታይ ክፍሎች የምንማረውን ትምህርት እንጀምራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### ዘጠኙ ቅዱሳን፡-

ዘጠኙ ቅዱሳን በ፬፻፶፩(451) ዓ.ም የተካሄደውን የኬልቄዶን ጉባዔ ተከትሎ የቢዛንታይን መንግሥት የሚያራምደውን የሁለት ባሕርይ ትምህርት አንቀበልም በማለታቸው የደረሰባቸውን መከራ ሸሽተው ወደ ሀገራችን የገቡ ቅዱሳን አባቶች ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

**ስማቸው፡-** አባ ሊቃኖስ ፣ አባ አረጋዊ ፣ አባ ጰንጤሌዎን ፣ አባ አፍጼ ፣ አባ አሌፍ ፣ አባ ጽሕማ ፣ አባ ገሪማ ፣ አባ ይምዓታ ፣ አባ ጉባ ይባላሉ፡፡

*ሥራዎቻቸው፡-* ገዳማትን እና ገዳማዊነትን መሥርተዋል አስፋፍተዋል ፣ የሀገራችንን ግእዝ ቋንቋ ተምረው በጽርዕ እና ሱርስት ቋንቋዎች የተጻፉ ወደ ግእዝ ቋንቋ ተርጉመዋል፡፡ ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዘጠኙንም ቅዱሳን አባቶች ታስባቸዋለች ፣ ታከብራቸዋለች፡፡

### ዐፄ ካሌብ፡-

ክርስትናን በማስፋፋ ረገድ ከአብርሃ እና አጽብሃ ቀጥሎ የሚጠራ ንጉሥ ነው፡፡ ንጉሥ ካሌብ

ኢትዮጵያን ይመራ በነበረበት ጊዜ የሀገራችን ግዛት እስከ ደቡብ ዐረቢያ ድረስ ነበር፡፡ በዚያ የሚኖሩ ክርስቲያኖች በአይሁዳውያን ተጽዕኖ ስር ነበሩ፡፡ አይሁዳውያኑ በተለያየ ጊዜ ክርስቲያኖቹን ያሰቃዩአቸው ይፈጇቸው ስለነበር ካሌብ እዚያው ድረስ ሄዶ ነጻ አውጥቷቸዋል፡፡

ዐፄ ካሌብ ወደ ዛሬዋ የመን (የጥንትዋ ዚፋር) ክርስቲያኖችን አይሁዳውያኑ ከሚያደርሱባቸው ስቃይና መከራ ነጻ ለማውጣት ወደ ጦርነት ከመሔዱ በፊት ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ ወደ ሆኑት አባ ጰንጠሌዎን ዘንድ ሄዶ ቡራኬ ተቀብሏል፡፡ ጦርነቱን ድል አድርጎ ክርስቲያኖችን ነጻ ካወጣም ቀሪ ዘመኑን በምንኩስና ሕይወትን እንደሚመራ ስዕለት ተስሎ ነበር፡፡ ዐፄ ካሌብ በየመን የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ የነበረውን አይሁዳዊ ፊንሐስን ድል ካደረገ በኋላም በቃል ኪዳኑ መሠረት በምናኔ ለመኖር ወደ ገዳም ገብቷል፡፡ ከዚያም በእርሱ ፈንታ ልጁ ዐፄ ገብረ መስቀል ዙፋኑን ተረክቧል፡፡

### ዐፄ ገብረ መስቀል፡-

ዐፄ ገብረ መስቀል ቅዱስ ያሬድ በነበረበት ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበሩ ናቸው፡፡ ንጉሡ ለቤተ ክርስቲያን እጅግ የተለየ ፍቅር ነበራቸው፡፡ ቅዱስ ያሬድ ሲያዜም መስማት ደግሞ በጣም ያስደስታቸው ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ቅዱስ ያሬድ በጸናጽል እና በመቋሚያ እያሸበሸበ ሲዘምር ንጉሡ በጣም ተደሰቱ፡፡ በዜማውም ተመስጠው ሳያውቁት በያዙት ጦር የቅዱስ ያሬድን እግሩን ወጉት፡፡ ነገር ግን ሁለቱም የሆነውን ነገር ያወቁት ዜማው ሲያልቅ ነበር፡፡ ቅዱስ ያሬድ ራሱ በዜማው ተመስጦ ስለነበር መወጋቱን አላወቀም ነበር፡፡

### ቅዱስ ያሬድ፡-

ሚያዚያ ፭ ቀን ፭፻፭ ዓ.ም በአክሱም ከተማ ተወለደ፡፡ አባቱ አብድዩ እናቱ ደግሞ ታውክልያ ይባላሉ፡፡ አባቱ በልጅነቱ ስለሞተበት ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ ወደ አጎቱ ጌዴዎን ዘንድ ሊማር ሄደ፡፡ ጌዴዎን በወቅቱ የታወቀ መምህር ነበር፡፡ ቅዱስ ያሬድ ግን ትምህርት አይገባውም ነበር፤ በዚህም የተነሣ ተበሳጭቶ ትምህርቱን ተወውና ጠፍቶ ሄደ፡፡ በመንገድ ላይም በትል ዛፍ ሥር ዐረፍ ብሎ እንዳለ አንዲት ትል በዛፉ ወደላይ ለመውጣት እየሞከረች በተደጋጋሚ ስትወድቅ አየ፡፡ ያቺ ትል ተስፋ አልቆረጠችም፡፡ ከወደቀችበት እየተነሣች ደጋግማ ሞክራ በመጨረሻው ተሳክቶላት በዛፉ ወደ ላይ ወጣች፡፡ ቅዱስ ያሬድም ከዚያች ትል ተደጋጋሚ ጥረት ተስፋ መቁረጥ እንደማይገባው ተማረ፡፡ ቅዱስ ያሬድ በአንድ ወቅት መላእክት በሦስት ወፎች ተመስለው ዜማን አስተማሩት፡፡ እርሱም ለዓለም ግእዝ፣ ዕዝል፣ አራራይ የተባሉ የዜማ ስልቶችን አስተዋወቀ፤ ታላቅ የዜማ ሰውም ሆነ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ያሬድ የሠራቸው ሥራዎች በርካታ ናቸው፡፡ ድጓ ፣ ጾመ ድጓ ፣ ዝማሬ ፣ መዋሥዕት ፣ ምዕራፍ የተባሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ሥነ ምግባርን የሚያስተምሩ፣ ታላላቅ ሥነ መለኮታዊ መልእክት ያዘሉ መጻሕፍትን አዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቅዱስ ያሬድ ብዙ ደቀ መዛሙርትን በማስተማር እስከ አሁን ድረስ ቤተ ክርስቲያናችን የምትገለገልበትን ዜማ አበርክቷል፡፡ ቅዱስ ያሬድ በሰሜን ራስ ዳሽን ተራራ ላይ በምናኔ ሳለ ግንቦት ፲፩ ቀን ተሰውሯል፡፡

## ማጠቃለያ

- ሀገራችን የኦሪትን እምነት ቀድማ የተቀበለች በመሆኗ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ በሐዲስ ኪዳን ክርስትና ሲሰበክላት በሰላም የተቀበለች ሀገር ናት፡፡ ስለዚህም በውጭ ከሚገኙ ልዩ ልዩ ሀገሮች ክርስቲያኖች በስደት ሲመጡ መጠጊያቸው ነበረች፡፡
- በተጨማሪም ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከሚያሳወቃት ነገሮች አንዱ የቀዳሚው ዜማ ሊቅ የቅዱስ ያሬድ ሀገር መሆኗ ነው፡፡

## ተግባር፡-

- ዐፄ ካሌብ ወደ ናግራን ከመሄዱ በፊት አባቶችን በጸሎት እንዲረዱት እንደ ጠየቀ ሁሉ፤ ማንኛውንም ሥራ ከመጀመራችን በፊት አባቶችን ማማከርንና እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅን አትርሱ፡፡
- ለእግዚአብሔር የገባችሁት ቃል ካለ ቃል ኪዳናችሁን ጠብቃችሁ ማድረግን አትርሱ፡፡

**መዝሙር 1**

መሠረተ ዜማ ወጠነ ያሬድ ካህን
ያሬድ ካህን ጥዑመ ልሳን

**መዝሙር 1**

www.zeorthodox.org

አልቦ እምቅድሜሁ ወአልቦ እምድኅሬሁ ማሕሌታይ ሰብእ ዘከማሁ
ያሬድ ካህን ይኬልል ትንሣኤሁ ኢየአዱ እንስሳ ወሰብእ እምነ ሰላስ ዜማሁ

**ጥያቄዎች፡-**

1. ክርስትና መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በማን አማካኝነት ነበር? መቼ ? ከሰሜን ወደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ክርስትናን ያስፋፋው አባት ማን ይባላል?
2. ዘጠኙ ቅዱሳን ተብለው በቤተ ክርስቲያናችን የሚከበሩትና የሚታሰቡት አባቶች እነማን ናቸው? ስማቸውን ዘርዝሩ፡፡

3. ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በምን ምክንያት ነው? አብራሩ፡፡
4. ዐፄ ካሌብ ወደ የመን የዘመተው ለምን ነበር ? ለጦርነት ከዘመተበት የመን ሲመለስ ምን አደረገ? ሥልጣኑን ያስረከበው ለማን ነበር?
5. ቅዱስ ያሬድ የት እና መቼ ተወለደ? እናትና አባቱ ማን ይባላሉ?
6. ቅዱስ ያሬድ መላእክት በሦስት ወፎች ተመስለው ባስተማሩት መሠረት ለዓለም ያስተዋወቃቸው የዜማ ሥልቶች ምን ምን ናቸው?
7. ቅዱስ ያሬድ ያዘጋጃቸው መጻሕፍት ስንት ናቸው? ዝርዝራቸውን ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ከ፯ኛው እስከ ፲፫ኛው መ/ክ/ዘ) — (ሁለት)

# ዐሥራ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለአክሱም መንግሥት መዳከም እንዲሁም ከዚያ በኋላ ስለተነሡት የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ነገሥታት እና በወቅቱ ስለነበረው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠኑ ጥቅሶች፡-** ***"ምክር ከሌለች ዘንድ የታሰበው ሳይሳካ ይቀራል መካሮች በበዙበት ዘንድ ግን ይጸናል"*** */ምሳ.፲፭፥፳፪/* ***"አንተ መብራቴን ታበራለህና እግዚአብሔር አምላኬ ጨለማዬን ያበራል፡፡"*** */መዝ.፲፰፥፳፰/*

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያ ታሪክ››፤ አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ሉሌ መልአኩ

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ትምህርታችን በአምስተኛው እና በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የቤተ ክርስቲያን እድገት እና በጎ ገጽታ አይተናል፡፡ በዚህም የዘጠኙ ቅዱሳን ከቢዛንታይን መንግሥት ሸሽተው ወደ ሀገራችን በመምጣት የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍትን ተርጉመው፣ ገዳማትን በመገደም፣ ክርስትናን እንዳስፋፉ ተምረናል፡፡ የዐፄ ካሌብ የናግራን(የመን) ክርስቲያኖችን ነጻ ማውጣቱን እና የቅዱስ ያሬድን ታሪክና የዜማ ድርሰት ሌሎች ታላላቅ መጻሕፍትን ማዘጋጀቱንም ተመልክተናል፡፡ በዛሬውም ትምህርታችንም ቀጣዩን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንማራለን፡፡ የሚቀጥለው ታሪክ በእስልምና መስፋፋት ፣ በአክሱም መንግሥት መዳከምና ከውስጥ በተነሡት የዮዲት እና መሰል ወረራዎች ክርስትና በኢትዮጵያ የተዳከመበት ዘመን ነው፡፡ ሆኖም በጨለማ ብርሃን ይሁን ያለ ጌታችን ልዑል እግዚአብሔር አሁንም ጨለማውን በሌላ ብርሃናዊ ታሪክ በቅዱሳኑ ነገሥታት ድንቅ ሥራዎች ሲቀይር እንመለከታለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**የጨለማው ዘመን፡-** ይህ ዘመን ከሰባተኛው እስከ ዐሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለውን

ያጠቃልላል፡፡ በታሪክ ምሁራን የጨለማው ዘመን የተባለበት ምክንያት ታሪካዊ መረጃዎች የሌሉበት ዘመን በመሆኑና ገናናው የአክሱም መንግሥት የወደቀበት ዘመን በመሆኑም ነው፡፡

## የአክሱም ዘመነ መንግሥት መዳከም ምክንያቶች፡-

የአክሱም መንግሥት የባሕር በሮቹን ለንግድ እንቅስቃሴ የሚጠቀም መንግሥት ነበር፡፡ ነገር ግን በእስልምና መነሣት የተጠናከሩት ዐረቦች መሉ በሙሉ የባሕር በሮቹን በመቆጣጠራቸው የተነሣ ከፍተኛ መዳከም ደረሰበት፡፡ መንፈሳዊ መሪ የሚሆን ጳጳስ ከእስክንድርያ አለመምጣቱ፡፡ መጽሐፍ“ ***መልካም ምክር ከሌለ ዘንድ ሕዝብ ይወድቃል በመካሮች ብዛት ግን ደኅንነት ይሆናል፡፡*** ” ምሳ. ፲፩÷፲፬ የክርስቲያኑ የአክሱም መንግሥትም መንፈሳዊ ምክር በማጣቱ የተፈጠረው ክፍተት የወድቀቱ ምክንያት እንደሆነ የሚተነትኑ የታሪክ ሊቃውንት አሉ፡፡

የእርስ በእርስ (የሀገር ውስጥ) ጦርነት ፤ የውጭ ጠላትን የሚመከቱት ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ጥቃት እንዲሁም የሀብትና ንብረታቸው ይድርስባቸው የነበረው በእርስ በእርስ ግጭቶች ነበር፡፡ በዚህ ዘመን ገናናውን የአክሱምን መንግሥት በጣም የጎዳውም ይኸው ነበር፡፡ ከእነዚህ ጦርነቶች፡- ከይሁዲ ቤተሰብ የተወለደችው ዮዲት ክርስትናን አዳክማ ይሁዲነትን ለማስፋፋት በዳረገችው ጦርነት የደረሰው ከፍተኛ ጥፋት ይጠቀሳል፡፡ እንዲሁም ቤጃና የመሳሰሉት ጎሳዎች ባነሡት የውስጥ ጦርነትና ቅራኔ የአክሱም መንግሥት እና ክርስትናም በኢትዮጵያ ክፉኛ ተዳከመ፡፡ በነገደ ዛጒዬ እና በሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት መካከል የተነሣው የሥልጣን ይገባኛል ትግል የፈጠረውና ያስከተለው ችግርም ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡

**ዮዲት ጉዲት፡-** ዮዲት የአገው ተወላጅ እና የአይሁድ እምነት ተከታይ ነበረች፡፡ ዮዲት ከግብረ አበሮቿ ጋር በመሆን ብዙ ክርስቲያኖችን ገድላለች ፤ አብያተ ክርስቲያናትን አፈራርሳለች ፣ ንዋያተ ቅድሳትን አጥፍታለች፡፡ ዮዲት በነበረችባቸው አርባ ዘመናት ሙሉ ክርስቲያኖች ነጻነታቸውን አጥተው ኖረዋል፡፡ ነገር ግን አባቶች የቃል ኪዳኑን ታቦትና ንዋያተ ቅድሳትን ቆፍረው በመቅበር ፣ ዋሻ ውስጥ በመደበቅ …ወዘተ ከዮዲት እጅ አድነዋቸዋል፡፡ ለምሳሌ ታቦተ ጽዮን ከአክሱም ተሰዳ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ በዝዋይ ሐይቅ ደሴቶች መጥታ በዚያ ቆይታ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

ዮዲት ትግራይ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን አቃጥላ ስትመለስ “አዲ ነፋስ” የተባለ ቦታ ስትደርስ ዓውሎ ነፋስ ተነሥቶ ከዓለት ጋር አጋጭቶ ገድሏታል፡፡ በአስከሬኗም ላይ የተወረወረው ድንጋይ ክምር ሆኖ እስከ አሁን ድረስ ይገኛል፡፡

**የዛጒዬ ዘመነ መንግሥት፡-** የአክሱም ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት የመጨረሻ ንጉሥ

የድልነዓድን ሴት ልጅን ያገባው የጦር መሪው መራ ተክለ ሃይማኖት ድል ነዓድን በጦርነት አሸንፎ ሲነግሥ የሰሎሞን ሥርወ መንግሥት በዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ተተካ፡፡

***መራ ተክለ ሃይማኖት፡-*** የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት የመጀመሪያው ንጉሥ ነበር፡፡ መናገሻ ከተማውን ከአክሱም ወደ ሮሃ የአሁንዋ ላሊበላ አካባቢ አዛወረ፡፡

**በዛጉዌ ዘመነ መንግሥት የነገሡ አራቱ ቅዱሳን ነገሥታት፡-*"ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለችና እንደ ጨለማዋ እንዲሁ ብርሃንዋ ነው፡፡"*** /መዝ.፻፴፱÷፲፪/ የጨለመውን የሀገሪቱንና የቤተ ክርስቲያንን ጉዞ የሚያበሩ ደገኛ ነገሥታትን እግዚአብሔር አስነሥቶ መልካሙን አደረገ፡፡አራቱ ቅዱሳን ነገሥታት.......

**ዐፄ ይምርሐነ ክርስቶስ ፲፻፸፯-፲፩፻፲፯(1077-1117)፡-** ከንጉሥነቱ በተጨማሪ ሃይማኖታዊ ተግባራትን ያዘወትር እና ይፈጽም ነበር፡፡ ዐፄ ይምርሐነ ክርስቶስ ባዕድ አምልኩ ያመልክ የነበሩትን ከልክሏል፡፡ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከአንድ በላይ እንዳያገባ አድርጓል፡፡ በዘመኑ የነበረው የግብጽ መሪ በዚያ ያሉትን ክርስቲያኖችን ሲበድል የዓባይን ወንዝ አቅጣጫ እንደሚቀይር አስፈራርቶ ክርስቲያኖቹን ከመከራ ታድጓል፡፡

**ንጉሥ ሀርቤ /ገብረ ማርያም ፲፩፻፲፯-፲፩፻፶፯(1117-1157)፡-** ስለ ስብከተ ወንጌል መስፋፋት የተጋ ንጉሥ ነበር፡፡ በመላ ሀገሪቱ ስብከተ ወንጌል እንዲዳረስ ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ጳጳሳት እንዲሾሙ ንጉሥ ሀርቤ የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ቢጠይቅም ፣ ጥያቄው መልስ አላገኘም ነበር፡፡

**ንጉሥ ላሊበላ ፲፩፻፶፯-፲፩፻፺፯(1157-1197)፡-** ቅዱስ ላሊበላ በነገሠባቸው ዘመናት የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን አንጾአል፡፡ ከእነዚህም አብያተ ክርስቲያናት በጣም የሚታወቅበት ከአንድ ወጥ ዓለት ተፈልፍሎ የተሠራው የሮሃው ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ቅዱስ ላሊበላ ካነጻቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዙዎቹ ከወጥ ዓለት ተፈልፍለው የተሠሩ ናቸው፡፡ ቅዱስ ላሊበላ በሀገር አመራር ዙሪያ የምታግዘው ሚስቱ መስቀል ክብራ ነበረች፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ለእነዚህ ባለውለታዎች የቅድስና ማዕረግ ሰጥታ ታስባቸዋለች፡፡

www.zeorthodox.org

**ዐፄ ነአኩቶ ለአብ፡-** የዛጉዌ ዘመነ መንግሥት የመጨረሻው ንጉሥ ነው፡፡ እጅግ በጣም መንፈሳዊ የሆነ ጾም ፣ ጸሎት ፣ ምጽዋት እና ስግደት የሚያበዛ ሰው ነበር፡፡ ከጌታችንም ቃል ኪዳን እንደተቀበለ በገድሉ ተጽፏል፡፡ እርሱም አብያተ ክርስቲያናትን አንጾአል፡፡

- እነዚህ የዛጉዌ ነገሥታት ከሀገር መሪነቱ ጎን በፈጸሚቸው መንፈሳዊ ተግባራት ቤተ ክርስቲያን የቅድስና ማዕረግ ሰጥታቸዋለች፡፡

**ማጠቃለያ፡-** ቤተ ክርስቲያናችን በተደጋጋሚ መከራ ደርሶባታል፡፡ ነገር ግን የሃይማኖት ፍቅር በነበራቸው ነገሥታት አማካኝነት ልታገግም ችላለች፡፡ በተለይም በዛጒዌ ዘመነ መንግሥት እስከ አሁን ድረስ የቱሪስት መስሕብ የሆኑት አብያ ክርስቲያናት ታንጸዋል፡፡

**ተግባር፡-** አራቱ ቅዱሳን ነገሥታት የሀገር መሪ ከመሆናቸው ባሻገር የቤተ ክርስቲያን ፍቅር ያላቸውና ዘወትር ለቤተ ክርስቲያን የሚለፉ እንደ ነበሩ፡፡ ሁሉ እኛም ዕውቀት፣ሥልጣን፣ ክብር፣ ሀብት ወዘተ  በእግዚአብሔር ፊት ምንም ማለት እንዳልሆነ ተገንዝበን ለመንፈሳዊ ተግባር መፋጠን ይገባናል፡፡

**መዝሙር፡-**

ዕቀቡኒ አበውየ እም አፈ አንበሳ ወተኩላ

ነአኵቶ ለአብ ይምርሐ ገብረማርያም ወላሊበላ

ጥያቄዎች፡-

1. ለአክሱም ዘመነ መንግሥት መዳከም እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት ምን ምን ናቸው? አብራሩ፡፡
2. በዛጉዌ ሥርወ መንግሥት የመጀመሪያው ንጉሥ ማን ይባላል?
3. ከዛጉዌ ሥርወ መንግሥት አራቱ ቅዱሳን ነገሥታት ተብለው የሚጠቀሱት እና ቅድስት ቤተክርስቲያን ያከበረቻቸው ነገሥታት እነማን ናቸው?
4. በዓለም ድንቅ ሥራነቱ ተመዝግቦ በከፍተኛ ደረጃ የቱሪስት መስሕብ የሆነው ከአንድ ወጥ ዐለት ተፈልፍሎ የተሠራው ቤተክርስቲያን ማን ይባላል? ያሠራውስ ማን ነው? የት ይገኛል?

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
# (ከ፮ኛው እስከ ፲፫ኛው መ/ክ/ዘ) — (ሦስት)
# ዐሥራ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች በተሰዓቱ ቅዱሳን የተመሠረተው ገዳማዊ ኑሮ ዳግም ስለማንሰራራቱ እና ስለ አራቱ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አባቶች ታሪክና ሥራ ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ ፤ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጕድጓድ ተቅበዘበዙ፡፡"*** /ዕብ.፲፩፥፴፯-፴፰/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያ ታሪክ››፤ አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ሉሌ መልአኩ

**መግቢያ፡-** ባለፈው ትምህርታችን ስለ አክሱም መንግሥት መዳከም ተምረናል፡፡ የአክሱም መንግሥት በዮዲት ጉዲት ለአርባ ዓመታት ያህል በደረሰበት ጥቃት የነበረውን ኃይል ካጣ በኋላ ዳግመኛ ለመመለስ በማንሠራራት ላይ ሳለ በዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ተተክቷል፡፡ የዚህ ዕለት ትምህርታችን ደግሞ በዘጠኙ ቅዱሳን የተጀመረው እና በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረው የገዳማዊነት እና የብሕትውና ኑሮ ዳግም ማንሠራራቱንና በመካከለኛው ፣ በደቡብ በምዕራብ እና ምሥራቅ ሀገሪቱ መስፋፋቱን እንመለከታለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የብሕትውና ኑሮ፡- ባሕታዊ ማለት ብቸኛ ፣ የራሱ የሆነ ኃብት የሌለው እና ከምኞት ኑሮ የራቀ፣ ጤዛ ልሶ፣ ድንጋይ ተንተርሶ የሚኖር ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ***"ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ ፤ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጕድጓድ ተቅበዘበዙ፡፡"*** ዕብ.፲፩፥፴፯-፴፰ በማለት እንደገለጣቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አባቶች፤ አባቶቻችን ከሰው ተለይተው በዱር ፣ በበረሐ የአራዊትን ድምፅ ሳይፈሩ፣ ፈተናዎችን በጾም፣ በጸሎት እና በስግደት ድል የሚያደርጉበት የብሕትውና ኑሮን የተማሩት

ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ /ማቴ. ፬፥፩-፲፩/ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሕይወታቸውን በብሕትውና እየኖሩ ወንጌልን በሀገሪቱ ያዳረሱ ብዙ ቅዱሳን አባቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም በዐሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩት ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡

**ምንኩስናና ገዳማዊ ኑሮ፡-** በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ አዲስ እና በሥርዓተ ገዳም የተጀመረው ይህ ሕይወት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዘጠኙ ቅዱሳን ነው፡፡ በኢትዮጵያውያን አባቶች ሲስፋፋ ኖሮ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የሚጠቅም ማዕከልነትን በመያዝ በዐሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ አዲስ አንሰራራ፡፡ በዚህ ታሪክ ግንባር ቀደም ከሆኑት የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

**አባ ዮሐኒ፡-** በዐሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን የደብረ ዳሞ አበምኔት የነበሩ ቅዱስ ናቸው፡፡ በመንፈሳዊ ተጋድሎዋቸው እና በእውቀታቸው የተመሰከረላቸው አባት ስለነበሩ ታላላቅ አባቶችን በቆብና በትምህርት ወልደዋል፡፡ ከእነዚህም የሐይቁ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ፣ የደብረ ሊባኖሱ አቡነ ተክለ ሃይማኖት………. ይጠቀሳሉ፡፡

**አባ ኢየሱስ ሞዓ ፲፪፻፲፩-፲፪፻፺፪(1211-1292 ዓ.ም)፡-** አባ ኢየሱስ ሞዓ በ፲፪፻፲፩ (1211)ዓ.ም ከእናታቸው እግዚአ ክብራ እና አባታቸው ዘክርስቶስ ተወለዱ፡፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ አጎታቸው መንፈሳዊ ትምህርትን አስተማሩአቸው፡፡ በመቀጠል ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ሄዱ፡፡ ሌሊቱን በስግደትና በጸሎት፤ ቀኑን እህል በመፍጨት፣ እንጨት በመልቀም፣ ውኃ በመቅዳት፣ አባቶችን በመታዘዝ በትሕትና ያሳልፉ ነበር፡፡

አባ ኢየሱስ ሞዓ ገዳሙን በሥራ ከማገልገል በተጨማሪ የቁም ጽሕፈት ዐዋቂ ስለ ነበሩ የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍትን በብራና ላይ ጽፈዋል፡፡ ከዚያም ተመልሰው የሐይቅ እስጢፋኖስን ገዳም እና መንፈሳዊ ትምህርት ቤትን መሥርተዋል፡፡ ሐይቅ እስጢፋኖስ በርካታ የቤተ ክርስቲያናችንን አባቶች መነኮሳትን ያፈራ ገዳም ሲሆን ፤ የተደራጀ የሥነ መለኮት ት/ቤት እንደነበር ምሁራን ይጠቅሳሉ፡፡

www.zeorthodox.org

**አባ ተክለ ሃይማኖት ፲፪፻፲፭-፲፫፻፲፫(1215-1313 ዓ.ም)፡-** ከእናታቸው እግዚእ ሐረያ እና ከአባታቸው ጸጋ ዘአብ በ፲፪፻፲፭(1215) ዓ.ም ተወለዱ፡፡ በትግራይ ክልል የሚገኙትን ተሰዓቱ ቅዱሳን የመሠረቷቸውን ገዳማት የጎበኙ ሲሆን ሥርዓተ አስኬማን ከአቡነ ዮሐኒ ተቀብለዋል፡፡ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በታላቁ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ነው፡፡

ከትምህርታቸውም መልስ የዜጋመል ማርያም እና ደብረ አሰቦ ገዳምን እንደ ገና አጠናክረዋል፡፡ በርካታ ጣዖት ያመልኩ የነበሩ ሕዝቦችን አስተምረው በማጥመቅ ክርስትና እንዲቀበሉ አድርገዋል፡፡ ስብከተ ወንጌልን በሀገራችን በማስፋፋታቸውም ***"የኢትዮጵያ ሐዋርያ"*** የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ጳጳሳት በቀሩባቸው ሰፊ ዘመናት በቅዱስ ሚካኤል ተቀብተው የጳጳስን ተግባር ሲያከናወኑ የቆዩ ታላቅ የቤተ ክርስቲያናችን ባለውለታ ቅዱስ አባት ናቸው፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም አብዝተው ይጸልዩ የነበሩ ሲሆን፤ አንድ እግራቸውን በዚህ ምክንያት ቢያጡም በእግዚአብሔር ክንፍ ተሰጥቶአቸው ጸሎታቸውን ሳያቋርጡ ቆይተው በ፲፫፻፲፫(1313) ዓ.ም. ዐርፈዋል፡፡

**አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ፲፪፻፸፫-፲፫፻፶፪**(1273-1352 **ዓ.ም**)፡- አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ከልጅነታቸው ጀምሮ መንፈሳዊ ትምህርትን የተማሩት ከአጎታቸው ከአባ ዳንኤል ነው፡፡ በርካታ የጣዖት ማምለኪያ ስፍራዎችን በትምህርተ ወንጌል አፍርሰው ሕዝቡን ወደ ክርስትና የመለሱ ታላቅ አባት ናቸው፡፡ ኤርትራ ውስጥ ሰራዬ በተባለ ቦታ በስማቸው የሚጠራ ገዳምን መሥርተዋል፡፡ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ በጣም የሚታወቁት ቅዳሜን እንደ እሑድ ሰንበት ተደርጋ እንድትከበር በማድረጋቸው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በተነሣባቸው ስደት ወደ አርመን ሲጓዙ የመርከብ መሳፈሪያ ስላልነበራቸው የለበሱትን ቆዳ በባሕር ላይ በማንጠፍ ተሻግረዋል፡፡ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ በዚያው በአርመን እያስተማሩ ቆይተው ዐርፈዋል፡፡ አባ ኤዎስጣቴዎስ በርካታ ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ወንጌል በሀገራችን እንዲስፋፋ ያደረጉ አባት ናቸው፡፡ የአባታችንን ዓጽም በዐፄ ዮሐንስ አንደኛ ዘመን ፲፮፻፶፱-፲፮፻፸፬/1659-1674/ ዓ.ም በአንድ አርመናዊ ኤጲስ ቆጰስ አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- የብሕትውና ኑሮ በሀገራን በዘጠኙ ቅዱሳን አማካኝነት ቢጀመርም በመካከል ተፈጥረው በነበሩት እንደ ዮዲት ወረራ እና የአክሱም መንግሥት መዳከም ምክንያት ከሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በቀር ወደ ሌላው አልተስፋፋም ነበር፡፡ ከዐሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ግን የተለያዩ ገዳማት ተገድመዋል፤ የብሕትውና ኑሮም ተስፋፍቷል፡፡ በዚህ ጊዜ ገዳማትን ካስፋፉት አባቶችም በቀዳሚነት የሚጠቀሱት አቡነ ኢየሱስ ሞዓ፤ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እና አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ናቸው፡፡
- ከሰው ተለይቶ ያለ ምንም ምቾት ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖሩት ኑሮ ዛሬም በዘመናችን አለ፡፡ አባቶቻችን በበረኃ ሆነው ለእኛ እና ለሀገራችን በአጠቃላይ ለዓለም ሁሉ እግዚአብሔር ሰላም እና ጤናን ይሰጥ ዘንድ ይለምናሉ፡፡ እግዚአብሔርም ስለ እነርሱ ሲል ይምረናል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- አባቶቻችን ከወገኖቻቸው እና ከሥጋቸው ምቾት ይልቅ እግዚአብሔርን እንደ ወደዱ ሁሉ እኛም እግዚአብሔርን ከሁሉም በፊት ማስቀደም አለብን፡፡ አባቶቻችን ይታዘዙ እና በትሕትና ይኖሩ እንደነበር ሁሉ እኛም ታዛዥ እና ትሑት መሆን ይጠበቅብናል፡፡

**መዝሙር፡-**

አባ አቡነ መምህርነ አባ ተክለ ሃይማኖት /ኢየሱስ ሞዓ፣ ኤዎስጣቴዎስ/

እም አእላፍ ኅሩይ አብ አባ አቡነ ተክለ ሃይማኖት/ኢየሱስ ሞዓ ፣ ኤዎስጣቴዎስ /

**ጥያቄዎች፡-**

1. የብሕትውና ኑሮ ሲባል ምን ማለት ነው? ከቃሉ ትርጉም ጀምሮ አብራሩ፡፡
2. ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በማን እና መቼ ነው?
3. ከአራቱ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አባቶች፤ አባ ዮሐኒ፣ አባ ኢየሱስ ሞዓ፣ አባ ተክለሃይማኖት፣ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፤ ሁለቱን አባቶች መርጣችሁ ታሪካቸውንና ሥራዎቻቸውን (ለቤተክርስቲያን ያበረከቱትን ተግባራት) ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ከ፳ኛው እስከ ፲፰ኛው መ/ክ/ዘ) — (አራት) ዐሥራ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፦-** ተማሪዎች ስለ መካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎት ታሪክ እና በወቅቱ ስለተከሠቱት ውዝግቦች ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፦-** *"እንግዲህ፥ ልጄ ሆይ፥ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል። የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም። ደግሞም በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን፥ እንደሚገባ አድርጎ ባይታገል፥ የድሉን አክሊል አያገኝም። የሚደክመው ገበሬ ፍሬውን ከሚበሉት መጀመሪያ እንዲሆን ይገባዋል። የምለውን ተመልከት፤ ጌታም በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይሰጥሀ።" ፪ኛ ጢሞ. ፪፥፩-፯*

**ተጨማሪ ምንባባት፦-** ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያ ታሪክ››፤ አቡነ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፤ ሉሌ መልአኩ

**መግቢያ፦-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን በዐሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የገዳማዊ ሕይወትን ዳግም ስለመስፋፋቱ ተምረናል። ገዳማቱ የስብከተ ወንጌል ማስማርያ፣ የአስተዳደር ማስተማርያ ማዕከላት ሆነው እንደተነሡም አይተናል። ከእነዚህም ዋናዎቹ ደብረ ዳሞ እና ሐይቅ እስጢፋኖስ ነበሩ። ከእነኚህ ገዳማት የተገኙትና ቦታውን ካቀኑት መካከልም፦ አቡነ ዮሐኒ ፣ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ እና አቡነ ተክለ ሃይማኖትን አይተናል። በዛሬው ትምህርታችንም የዚህን ዘመንና የተከታዮቹን አዝማናት ታሪክ እንቀጥላለን። በቅዱሳን ጸሎት ለመፈጸም የበቃን ያድርገን።

www.zeorthodox.org

**የሳምንቱ ትምህርት፡-** በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለይም በዐሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በገዳማት እና በገዳማዊ ኑሮ የታየው መነቃቃት በተወሰኑ አካባቢ እና አበው የተገደበ አልነበረም። በአራቱም ማዕዘናተ ኢትዮጵያ የተከናወነ ነበር። ከእነኚህም የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የሰሎሞናዊው መንግሥት ዳግም ማንሠራራት የመጀመሪያው ንጉሥ ይኩኖ አምላክን ፤ ንጉሥ ዓምደ ጽዮን ተኩት። ዓምደ ጽዮን በዚህ ዘመን ከተነሡት ነገሥታት ገናና ስም ያለውና ለሀገሪቱ እና ለቤተ ክስቲያን በነበረው ፍቅር በርካታ ውለታዎችን ያስተላለፈ ነው።

**ከአክሱም ውድቀት ጋር የጠፋው የጽሑፍ ሥራ እንደ አዲስ ተነሣ።** በርካታ መጻሕፍት የተተረጎሙት፣ ወጥ ጽሑፎች እንደ አዲስ መጻፍ የተጀመረው በዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው። ገድለ ሰማዕታት ፣ ግብረ ሕማማት ፣ ዜና አይሁድ ፣ መጽሐፈ ኪዳን ፣ መጽሐፈ ግንዘት…… ከዐረብኛ ተተረጎሙ። ክብረ ነገሥት ፣ የታሪክ መጽሐፍ ፣ ገድላት ተጻፉ።

**ሊቀ ጳጳስ ከግብጽ አስመጣ።** ለዘመናት የተቋረጠው የግብጽና ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት በይኩኖ አምላክ ዘመን ከኮፕት(ግብጽ) በመጡት አቡነ ዮሐንስ እንደ አዲስ ቀጠለ። በአባቱ ዘመን የመጡት አቡነ ዮሐንስ ሲያርፉ፣ አቡነ ያዕቆብ ከኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተሹመው የመጡት በንጉሡ ዓምደ ጽዮን ጥረት ነበር።

**ሊቀ ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ እና እጨጌ አቡነ ፊልጶስ፡-** አቡነ ያዕቆብ ለሐዋርያዊ ተልዕኮ ትኩረት ስለሰጡ ዘመኑን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ልዩ ያደረገው ሐዋርያዊ ተልዕኮ በአራቱም ማዕዘን ጎመራ። አቡነ ያዕቆብ እጨጌ ፊልጶስን ***"ኢትዮጵያ ሰፊ ሀገር በመሆንዋ በአንድ ጳጳስ መወሰን የለባትም ፤ ዐሥራ ሁለት አበው ምረጥና ከአንተ ጋር አጺስ ቆጶሳት ተሹመው እናገልግል"*** አሏቸው በዚህ መሠሰረት፡- አቡነ ፊልጶስ በደብረ ሊባኖስ በእጨጌነት ተቀምጠው ፤ አቡነ አድኅኒ ዘዳሞት ፣ አቡነ ሳሙኤል ዘወገግ ፣ አቡነ ገብረ ክርስቶስ ዘድም ፣ አቡነ ኢዮስያስ ዘወጅ ፣ አቡነ አኖሬዎስ ዘሞረት ፣ አቡነ አኖሬዎስ ዘወረብ ፣ አቡነ መርቆሬዎስ ዘመርሐ ቤቴ ፣ አቡነ ቀውስጦስ ዘመሀገል ፣ አቡነ ማትያስ ዘፈጠጋር፣ አቡነ ታዴዎስ ዘጽላልሽ፣ አቡነ ዮሴፍ ዘእናርያ ተሾሙ። እነሱም በምሥራቅ ፣ በምዕራብ ፣ በደቡብ እና በማዕከላዊው የሀገሪቱ ክፍል ክርስትናን አስፋፉ።

www.zeorthodox.org

በሌላ አቅጣጫ በዘመኑ የነበሩት የሐይቅ ገዳም አበው እንደ አባቶቻቸው ገዳሙን ከማጠናከር ጎን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋትና ገዳማትን በማቅናት ተጋድለዋል። ለምሳሌ፡- አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን ያስተማረው አባ ሠረቀ ብርሃን የገዳሙን የትምህርት ማዕከልነት በማስቀጠል አቃቤ ሰዓት ነበር። አቡነ ሒሩተ አምላክ ዳጋ እስጢፋኖስን ያቀኑት ከሐይቅ ሄደው ነበር።

**የደብረ በንኮሉ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ፡-** ከአክሱም ከተማ በሠላሳ ኪሎ ርቀት የምትገኘውን የደብረ በንኮልን ገዳም የመሠረቱት አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በገዳማቸው ከነበረው የጾምና ጸሎት ተጋድሎ በተጨማሪ፣ ቦታውን ዕፀዋት በመትከል ጫካ ያደረጉ አባትም ናቸው። ደቀ መዝሙሮቻቸውን በማስተማር፣ በማመንኮስና ለሐዋርያዊ ተልእኮ በማሰማራትም ሰባቱ ከዋክብት እና አምስቱ ቅዱሳን የሚባሉትን በማፍራት ያን ዘመን ወርቃማ ያደረጉ አባት ናቸው። ሰባቱ ከዋክብት፡- ሳሙኤል ዘቆየፃ ፣ ሳሙኤል ዘጣሬጣ፣ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ ያሳይ ዘምንድባ፣ ታዴዎስ ዘባልተዋር፣ ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉብጉቤ ሲሆኑ፤ አምስቱ ቅዱሳን አሮን ዘክቱር ፣ መርቆሬዎስ ዘዳባ፣ ዘካርያስ ዘከፋ ፣ ገብረ ክርስቶስ ዘቢታንያ ፣ ዳንኤል ዘጸአዳ ናቸው። እነዚህ አባቶች በሰሜን እና በምሥራቅ ኢትዮጵያ ያገለገሉ አበው ናቸው።

**አወዛጋቢው ጋብቻ፡-** በጦርነት ድልና በመልካም ሥራዎቹ ገናና የነበረው ንጉሥ ዓምደ ጽዮን የወንድሙን ሚስት አገባ። ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ያዕቆብና እጨጌ ፊልጶስ ክርስቲያን ሆኖ ይህን መፈጸም አይገባም በሚል ተቃወሙት። ከእነርሱም ጋር በርካታ አባቶች ተባበሩ። ንጉሡም የእነዚህን አባቶች ምክርና ተቃውሞ ከድፍረት ቆጥሮት በግርፋት በእስር እና በግዞት አስቀጣቸው። በዚህ በጣም የሚታወቁት አቡነ ፊልጶስና አቡነ አሮን ናቸው። በመጨረሻም ንጉሡ ይቅርታ ጠይቋል።

**የሰንበት አከባበር ውዝግብ።** ሌላው በዚህ ዘመን የተነሣው ጉዳይ ቅዳሜ ከእሑድ እኩል ትከበር የሚለው ጥያቄ ነበር። የዚህን መቋጫ በሚቀጠለው ክፍል እናያለን። ሆኖም አቡነ አዎስጣቴዎስ ሁለቱም ሰንበታት(ቅዳሜና እሑድ) እኩል ይከበሩ ሲሉ፤ ሌሎቹ በተለይም የደብረ ሊባኖስ አበው፤ ቅዳሜ ከእሑድ እኩል አትከበርም በማለታቸው ለረጅም ጊዜ ያወዛገበ ጉዳይ ነበር። የቅዳሜ ትከበር ደጋፊዎች ቤተ ኤዎስጣቴዎስ ሲባሉ ፣ እኩል አትከበርም ያሉት ቤተ ተክለ ሃይማኖት ተባሉ።

**ግማደ መስቀል የመምጣቱ ጅምር።** ዐፄ ዳዊት የግብጽ ክርስቲያኖችን በመታደጋቸው ፤ በርካታ ነዋያተ ቅድሳትና ጌታችን የተሰቀለበት የቀኝ እጁ ያረፈበት ግማደ መስቀል በስጦታ መልክ መጣ። ንጉሡ ዐፄ ዳዊት ግማደ መስቀሉን ለመቀበል በዛሬዋ ሱዳን ድንበር ሲደርሱ ከፈረስ ወድቀው ዐረፉ። መስቀሉም ወደ ኢትዮጲያ ገባ። የቀዳሚት ሰንበት አከባበርና የግማደ መስቀሉን መግባት ታሪክ በሚቀጥሉት የትምህርት ክፍሎች እንመለከታለን።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

- ዐሥራ አራተኛ መቶ ክፍለ ዘመን በመጻሕፍት መጻፍ እና መተርጎም ፣ በገዳማት እና ስብከተ ወንጌል መስፋፋት የሚታወስ ዘመን ሲሆን አወዛጋቢ ታሪኮችንም አሳልፏል።

## ተግባር

- ተማሪዎች በአቡነ ያዕቆብ የተሾሙት ንቡራነ እድ ያስተማሩባቸውን ቦታዎች አሁን የት እንደሚገኙ ጠይቃችሁ ከተረዳችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ ግለጹ።

**ጥያቄዎች፡-**

1. በዐፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ከተፈጸሙት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዋና ዋናዎቹን ተግባራት ግለጹ።
2. በወቅቱ ሊቀጳጳስ የነበሩት አቡነ ያዕቆብ ለሐዋርያዊ ተልዕኮ ትኩረት በመስጠት ከአቡነ ፊልጶስ ጋር በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል። ለዚህ ሥራ መሠረት የሆነው ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ያዕቆብ አቡነ ፊልጶስን ያሏቸው ምን ነበር? በአቡነ ፊልጶስ እጨጌነት ለኤጲስ ቆጶስነት ተመርጠው የተሾሙትን አባቶች ዝርዝር ግለጹ።
3. ከአክሱም ሠላሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን ደብረ በንኮል ገዳም የመሠረቱት አባት ማን ይባላሉ? ከአከናወኗቸው ተግባራት ዋና ዋናዎቹን ጥቀሱ። ሰባቱ ከዋክብት እና አምሥቱ ቅዱሳን በመባል የሚታወቁት አስተምረው ያመነኮሱአቸውና በሰሜን እና በምሥራቅ ኢትዮጵያ ያሰማሩአቸውን አባቶች በዝርዝር ግለጹ።
4. ዐፄ ዓምደ ጽዮንን በአበው ያስወቀሳቸው እና እነዚህን አባቶች ስለተቃወሟቸው በእስርና በግዞት እስከመቅጣት ያደረሳቸው ጉዳይ ምን ነበር?
5. ጌታችን የተሰቀለበት ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እና በማን ጥረት መጣ?
6. ስለ ሰንበት አከባበር ውዝግብ አብራሩ። በውዝግቡ የተከፋፈሉት ወገኖች መጠሪያ ማን ማን ይባላሉ?

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
# (ከ፰ኛው እስከ ፲፰ኛው መ/ክ/ዘ) — (አምስት)
# ዐሥራ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀጣይ ታሪክ ይገነዘባሉ፤ በተለይም በዘመኑ ስለነበሩት ታላቅ የቤተክርስቲያን ሊቅና አባት ስለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ታሪክና ሥራዎች ያውቃሉ፡፡ በመምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣልና፡፡ ከኃይል ወደ ኃይል ይሄዳሉ የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል፡፡"*** /መዝ. ፹፬፥፯/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት››፤ በዲ/ን ሰሎሞን ዮሐንስ ፣ ‹‹የቤተክርስቲያን መረጃዎች›› በዲ/ን ዳንኤል ክብረት

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን በዐሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስለገዳማዊ ሕይወት፣ ስለስብከተ ወንጌልና ስለቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ ዳግም መስፋፋት ተምረናል፡፡ ስለቀዳሚት ሰንበት አከባበርና ጌታችን የተሰቀለበት ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን ታሪክ የመጀመሪያ ክፍል አይተናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም በዚህ ዘመን  የተነሳውን አባ ጊዮርጊስን ታሪክ እና ሥራዎቹ ላይ ትኩረት አድርገን እንማራለን፡፡

አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር በቅዱሳን ጸሎት ከታሪኩ ፍሬ የምናፈራበትን ትምህርት አግኝተን መልካሙን ገድል ለመፈጸም የበቃን ያድርገን አሜን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት - አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፡፡

**ትውልዱና እድገቱ፡-** አባ ጊዮርጊስ አባቱ ሕዝበ ጽዮን እናቱ እምነ ጽዮን ይባላሉ፡፡ አባቱ በመጀመያ የትግራየ በኋላ ደግሞ የሰግላ/አሁን በደቡብ ወሎ የሚገኘው ጋሥጫ/ ገዥ ነበረ፡፡ የቤተክርስቲያን ሊቅ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ያደረበት በቤተ መንግሥት በነበረችው ሥዕል ቤት የሚያገለግል ካህን ነበር፡፡ እናቱ ወለቃ /ዛሬ ደቡብ ወሎ፣ ቦረና የነበሩ መኳንንት ወገን የሆነች ናት፡፡ አባ ጊዮርጊስ ከእነዚህ የእግዚአብሔር ወዳጆች በ፲፫፻፶፯(1357) ዓ.ም በጋሥጫ የተወለደ ብቸኛ

ልጃቸው ነው፡፡ እናቱ በታላቁ ሰማዕት ስም ጊዮርጊስ አለችው፡፡ የመጻሕፍት እና የድጓ ሊቅ ከነበረው አባቱ የመጀመሪያ የቤተክርስቲያን ትምህርት ተማረ፡፡ ከዚያም አባቱ ከጳጳሱ ዘንድ ወስዶ ዲቁና እንዲሾም አድርጎታል፡፡

***ወደ ሐይቅ ለትምህርት፡-*** መሔድ ጊዮርጊስ በዕድሜ ከፍ ሲል ሐይቅ እስጢፋኖስ ለትምህርት ሄደ፡፡ በዚያን ጊዜ በገዳሙ የነበረው አባት አባ ሠረቀ ብርሃን ይባላል፡፡ አባ ሠረቀ ብርሃን ጥልቅ ዕውቀትና ፍጹም መንፈሳዊነት የነበረው አባት ነው፡፡ ከዚህ አባት መማር ታላቅ ዕድል ነበር፡፡ ጊዮርጊስ በገዳሙ ትምህርቱን ቢቀጥልም ከታሪኩ እንደምንረዳው ትምህርት አልያዝልህ ብሎት ተቸገረ፡፡ ነገር ግን ያዕቆብ ***"ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል።"*** እንዳለ ተስፋ ሳይቆርጥ በጸሎት እግዚአብሔርን በመለመንና የእመቤታችንን ምልጃ በመማጸን ተጋ፡፡ አባ ጊዮርጊስ ዕውቀት ስለተሠወረው ሁልጊዜ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ሥር እየተንበረከከ ይጸልይ ነበር፡፡ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃ ፣ መንፈስ ቅዱስ እውቀት ገለጠለትና ፣ ጎበዝ ተማሪ ሆኖ ትምህርቱን መከታተል ቻለ፡፡

***ሊቁ ጊዮርጊስ በመምህርነት፡-*** በአስደናቂ ትምህርቶቹ ፣ በድርሰቱና በቅድስናው የሚታወቀው ጊዮርጊስ በፍጥነት ትምህቱን ያዘ፤በሐይቅ እስጢፋኖስ የሚያውቁት መነኮሳት ሁሉ በትምህርቱና በዕውቀቱ ይደነቁበት ነበር፡፡ የሚደነቅ አስተማሪም ሆነ፡፡ ዝናውን የሰሙ ብዙዎችም ወደ እርሱ ለመማር ይመጡ ነበር፡፡ በዘመኑ የነበሩት ንጉሥ ዐፄ ዳዊት ልጆቻቸውን እንዲያስተምርላቸው ወደ ቤተ መንግሥት ወሰዱት፡፡ ከእነዚህም ለቤተ ክርስቲያን እና ለሀገር የሚጠቅም ሥራ የሠሩት የዐፄ ዳዊት የመጀመሪያ ልጅ ቴዎድሮስ እና የመጨረሻ ልጅ ዘርዓ ያዕቆብ ይጠቀሳሉ፡፡ ንጉሡ በልጆቻቸው ባዩት የዕውቀትና የመልካም ጠባይ ለውጥና እድገት በሊቁ ቅድስናና ዕውቀት ተማርከው ሴት ልጃቸውን እሌኒን ሊድሩለት ፈለጉ፡፡ ሆኖም የሊቁ ጊዮርጊስ ምርጫ ምንኩስና ስለነበር ይህንን ጥያቄ አልተቀበለውም፡፡

***ክህነትና ምንኩስና፡-*** ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ከግብጻዊው ጳጳስ ከአቡነ በርተለሜዎስ ቅስና ተቀበለ፡፡ በመቀጠልም ወደ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ገብቶ ምንኩስና ተቀበለ፡፡ በእውነተኛ የምንኩስና ሕይወት የኖረው አባ ጊዮርጊስ ሕይወቱን፡- ወንበር ዘርግቶ በማስተማር ፣ አስደናቂዎቹን ድርሰቶችን በማዘጋጀት ፣ በጾምና በጸሎት ተጠምዶ በንጽሕና በማገልገል ፣ ለእውነተኛው ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን ጥብቅና በመቆም የኖረ አባት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

***ሥራዎቹ፡-*** የአባ ጊዮርጊስን ሥራዎች ለመዘርዘር ሳምንታዊው ክፍለ ትምህርት አይበቃም፤ ሆኖም በጥቅሉ የሚከተሉት ናቸው ፡-

- **በትምህርቱ፡-** የቅዱስ ያሬድን ድርሰቶች ያስተማረና ያስፋፋ ሲሆን ፤ ከዚህ በተጨማሪም በርካታ መነኮሳት ፣ ሊቃውንትና ሀገር መሪዎችን አፍርቷል፡፡ ከእነዚህም ነገሥታቱ ቴዎድሮስና ዘርዓ ያዕቆብ ይጠቀሳሉ፡፡
- **ከአርባ በላይ ድርሰቶች አዘጋጅቷል፡፡** ከእነዚህም መጽሐፈ ሰዓታት የመሰሉት የአገልግሎት መጻሕፍት ሲሆኑ፤ መጽሐፈ ምስጢር፣ ውዳሴ መስቀል፣ ፍካሬ ሃይማኖት፣ መጽሐፈ አርጋኖን የቀሩትም በዘመኑ በተነሡ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ለቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጥብቅና የቆመባቸውና መሠረታዊ ትምህርቶችን ያስተላለፈባቸው መጻሕፍት ናቸው፡፡
- **በእውነተኛ ሕይወት የሚኖር እንደመላእክት በጸሎት እና በጾም የሚጋደልም አባት ነበር፡፡** ለዚህም ነው የሃያ አራት ሰዓታት የጸሎት መጻሕፍት ያዘጋጀው፡፡ አባ ጊዮርጊስ ቀጥተኛ አባት ነበርና በዘመኑ በቅዳሴ ሰዓት ቁርባን ሲሰጥ ሌላው ሕዝብ ወደ ቅድስት ሄዶ ሲቀበል ለንጉሡ እና ንግሥቲቱ ግን ወደ ቀሙበት ሄደው ያቆርቧቸው ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ ተራ ደርሶት ሲቀድስ ድርገት ላይ ንፍቁ ካህን ‹‹ንጉሡንና ንግሥቲቱን ሄደን እናቁርብ›› አሉት፡፡ ‹‹ለምን?›› አለ፡፡ ‹‹ንጉሥ ስለሆኑ ነው›› የሚል መልስ ተሰጠው፡፡ ቅዱሱ አባ ጊዮርጊስም ቅዱስ ቁርባኑን እያሳየ ***“ንጉሠ ነገሥት ውእቱ ሥጋ ወደሙ ለክርስቶስ - ንጉሠ ነገሥት የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ነው፡፡”*** አለ፡፡

በመጨረሻም በጋስጫ አካባቢ እራሱ ከአንድ ዐለት ፈልፍሎ በሠራው ገዳም በተጋድሎ መኖር ጀመረ፣ ከተማሪዎቹ አንዱ ዐፄ ይሥሐቅም ቤተ ክርስቲያን አሠራለት፡፡ አባ ጊዮርጊስ በእውነተኛ መንፈሳዊነት ኖሮ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፬፻፲፯ ዓ.ም ዐረፈ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ከ፲፫፻፶፯ እስከ ፲፬፻፲፯ ዓ.ም የኖረው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በቅድስና ሕይወት ፣ በመምህርነት ፣ በርካታ መጻሕፍት በመጻፍና ለቤተ ክርስቲያን ጥብቅና በመቆም የኖረ አባት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

**ተግባር፡-** በተጠቀሱት መጻሕፍት ያለውን ዝርዝር ታሪክ አንብቡ፡፡

**ጥያቄዎች:-**

1. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ መቼ፣ የት ተወለደ? እናትና አባቱ ማን ይባላሉ?
2. አባ ጊዮርጊስን ከፊደል ቆጠራ አንሥቶ የመጀመሪያውን የቤተክርስቲያን ትምህርት ያስተማረው ማነው? ከዚያ በኋላ ዕድሜው ከፍ ሲል ለትምህርት የሄደው የት ነው? መምህሩ ማን ይባላሉ?
3. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ዕውቀት የተገለጠለት እንዴት ነው? አብራሩ።
4. አባ ጊዮርጊስ ልጆቻቸውን እንዲያስተምርላቸው ወደ ቤተመንግሥታቸው የወሰዱት ንጉሥ ማን ይባላሉ? ካስተማራቸው የንጉሡ ልጆች ሁለቱን ጥቀሱ።
5. ስለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ሥራዎች ዋና ዋናዎቹን በመጥቀስ አብራሩ።
6. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ያረፉት መቼ ነው?

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
# (ከ፮ኛው እስከ ፲፫ኛው መ/ክ/ዘ) — (ስድስት)
# ዐሥራ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎተ ቀጣዩን የመካከለኛውን ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይረዳሉ፤ በተለይ ዐሥራ አምስተኛውን መቶ ክፍለ ዘመን ልዩ ከሚያደርጉት ታሪካዊ ክስተቶች ዋና ዋናዎቹን ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሥራዎች ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው፡፡"*** ፪ኛ ቆሮ.፲፩፥፳፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያ ታሪክ››፤ በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) ፤ ‹‹የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት››፤ በዲ/ን ሰሎሞን ዮሐንስ ፣ ‹‹የቤተክርስቲያን መረጃዎች››፤ በዲ/ን ዳንኤል ክብረት፡፡

## መግቢያ፡-

ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን በዐሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽና በዐሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ የተነሣውንና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ታላቅ ክሥተት በመሆን ጉልህ ሥራ የሠራውንና በቅድስናው የተመሰከረለትን የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን ታሪክና ሥራዎች ዐይተናል፡፡

በዛሬው ትምህርታችንም የተከታዩን ዘመን ታሪክ እንቀጥላለን፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዐሥራ አምስተኛውን መቶ ክፍለ ዘመን ልዩ ከሚያደርጉት ዋና ዋናዎቹ፡- የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት መልካምና አወዛጋቢ ታሪካዊ ክሥተቶች ናቸው፡፡ ለዚህ ርእሰ ጉዳይ ዋና ትኩረት በመስጠት እና ሌሎች በክፍለ ዘመኑ የተከናወኑ ታሪኮችንም በመጨመር እናያለን፡፡ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር በቅዱሳን ጸሎት ከታሪኩ ለመማርና መልካሙን ገድል ለመፈጸም የበቃን ያድርገን አሜን፡፡

www.zeorthodox.org

**ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ዐፄ ይስሐቅ**

እስከ ፲፬፻፳፮(1426) ዓ.ም ወንድማማቾች ነገሥታት ለአጫጭር ጊዜያት ሀገሪቱን መርተዋል፡፡ በእነዚህ ነገሥታት ዘመን የተከናወኑ ዋና ዋና የቤተ ክርስቲያን ታሪኮችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ይዞታ ተብሎ በትክክል አገልግሎት ላይ ያልዋለውን መሬት ፣ ለድሆች ያከፋፈለው ዐፄ ቴዎድሮስ ቀዳማዊ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ተማሪ ነበር፡፡ በቅዱስ ጋብቻ እና በታረመ ሕይወት በመኖሩ ያገኘውን ቅድስና በሰኔ ፳፱ ቀን የሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር ይገልጣል፡፡

**ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ**

ከ፲፫፻፺፱(1399) እስከ ፲፬፻፷(1460) ዓ.ም የኖረው ዘርዓ ያዕቆብ ፤ በመጀመሪያ ከአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በሕፃንነቱ ፣ ከዚያም አክሱም ሄዶ ከአንድ መነኩሴ ዘንድ ትምህርቱን ተምሯል፡፡ የደብረ ቢዘኑ አባ ፊልጶስም እንዳስተማሩት ገድለ ፊልጶስ ይተርካል፡፡ በዘመኑ ባህል የሥልጣን ተቀናቃኞች የሚቀመጡበት ግሽን አምባ ውስጥም ለተወሰኑ ጊዜያት ኖሯል፡፡ ከ፲፬፻፳፮(1426) ጀምሮ ለሠላሳ አራት ዓመታት የነገሠው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ካከናወናቸው ተግባራት የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- **በዓላትን ማስከበሩ፡-**በዘመኑ ሠልጥኖ የነበረውን ጥንቆላንና ደስቅ የተባለውን ጣዖት አምልኮ ለማስቀረት፣ ሕዝቡ በቤተ ክርስቲያን ተሳባስቦ የሚማርባቸውን በዓላት እንዲከበሩ አድርጎአል፡፡
- **ግማደ መስቀሉን ማስገባቱ፡-** ዐፄ ዳዊት ጌታችን ኢየሱስ የተሰቀለበትን ግማደ መስቀሉን ለመቀበል ስናር ሄደው በዚያ ከሞቱ በኋላ የተቋረጠው መስቀሉን ወደ ኢትዮጵያ የማስገባት ጥረት ተቋርጦ ነበር ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እንደነገሠ ስናር ሄዶ በማስመጣት በሕልም በተረዳው መሠረት ግማደ መስቀሉን በመስቀልኛ ቦታ - በግሽን ማርያም በክብር እንዲቀመጥ አድርጎአል፡፡
- **ወጥ ድርሰቶች ተጻፉ ፣ ከውጭ ቋንቋዎችም ተተረጎሙ፡-** ዘመነ ዘርዓ ያዕቆብ ከዘመነ አክሱም እና ከዐፄ ዓምደ ጽዮን ዘመን በኋላ ሦስተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን ያሰኘው ተብሎአል፡፡ ምክንያቱም በራሱ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና በሌሎች ሊቃውንት በርካታ መጻሕፍት ተተርጉመዋል፣ አዲስ ተጽፈዋል፣ ተዘጋጅተዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ከገድላት ገድለ ተክለ ሃይማኖት ፣ ገድለ ፊልጶስ ፣ የተስዓቱ ቅዱሳን ገድሎች…… ፤ ከመልኮች መልክአ ማርያምና መልክአ ኢየሱስ ፤ ከትርጉም ተአምረ ማርያም ፣ ስንክሳር ፣ ፍትሐ ነገሥት ይጠቀሳሉ፡፡
- **የሥርዓት መወሰንና ማስከበር፡-** ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ የኖረው የቀዳሚት ሰንበት

www.zeorthodox.org

መከበር ውዝግብ በደብረ ቁስቋም ጉባኤ ተወሰነ፡፡ ማተብ ማሰር፣ የመስቀል ምልክት ማድረግ ፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን ንስሐ አባት እንዲኖረው ፣ ቅዳሜና እሑድ እንዲያስቀደስ ፣ በእየ አጥቢያው ቤተ መጻሕፍት እንዲቋቋም ግዴታ መሆኑ በዘመኑ የተደነገጉ ሥርዓቶች ነበሩ፡፡

- **ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋት፡-** በዘመኑ አቡነ ሚካኤልና አቡነ ገብርኤል የተባሉ ሁለት ጳጳሳት ፣ አባ ዮሐንስ የተባለ አንድ ኤጲስ ቆጶስ አስመጥቶ ፤ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት ጥረት አድርጓል፡፡ እያንዳንዱ ካህን የበለጠ መማር ካልቻለ ገዳም ገብቶ እንዲማር ወይም ክህነቱ እንዲሻርና ካህን በመሆኑ የሚያገኘው ርስት እንዲቀር ያወጀውም ለዚህ ነበር፡፡

ይህን ሁሉ በማድረጉ በመልካም የሚነሣው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከአባ እስጢፋኖስና ከተከታዮቻቸው ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ፣ በወሰዳቸው ከባድ እርምጃዎች የሚነሡ አወዛጋቢ ታሪኮችም አሉ፡፡

አባ እስጢፋኖስና ልጆቹ ፤ ‹‹ሥርዓተ ምንኩስና ይከበር፣ ለንጉሡ አንሰግድም›› በማለታቸው ፣ መከራ መቀበላቸውን ስለ ራሳቸው ሲጽፉልን ፤ ዘርዓ ያዕቆብና በእርሱ በኩል ያሉት ደግሞ ‹‹አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቹ ለእመቤታችንንና ለመስቀል የሚሰጠው የጸጋ ስግደት አይገባም›› በማለታቸው መወገዛቸውን ያብራራሉ፡፡ በመሠረቱ ለቅዱሳን የሚሰጠውን የሚገባ ክብር ፣ ስግደትን ጨምሮ መቃወም ከኦርቶዶክሳዊነት የወጣ ትምህርት ነው፡፡ ይህም ሆኖ በአካላዊ ጉዳት የተፈጸመው ቅጣት ተመጣጣኝነት የሌለውና ከዘመነ ዘርዓ ያዕቆብ ፲፩፻(1100) ዓመታት ቀድሞ በአረማውያኑ የሮም ነገሥታት ከሚፈጸመው ቅጣት ጋር ይመሳሰላል፡፡

የዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጨረሻው ንጉሥ ዐፄ ናዖድ ነበሩ፡፡ ይህ ወቅት በቤተ ክርስቲያን የዘመን አቆጣጠር የሰባተኛው ሺሕ ማብቂያ የስምንተኛው ሺሕ መጀመሪያ ነበር፡፡ ንጉሡ ከስምንተኛው ሺሕ ከውኃው አታጠጣኝ ከእህሉም አታብላኝ፡፡ ይሉ ነበርና መስከረም ላይ ፲፭፻፩(1501)ኛው ዓ.ም ከመጀመሩ በፊት ነሐሴ ፯ ቀን ፲፭፻ ዓ.ም ዐረፉ ይባላል፡፡

## ማጠቃለያ

www.zeorthodox.org

- ዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በድርሰት፣ በሥርዓትና በሐዋርያዊ አገልግሎት እድገት የታየበት ዘመን ነው፡፡
- በሰንበት አከባበር ላይ የተነሣው ክርክር ሲቋጭ ፤ የደቂቀ እስጢፋኖሳውያን አከራካሪ ታሪክ የተከሠተበትም ነው፡፡

# ተግባር

✍ ስለተማራችሁት ታሪክ ተወያዩ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. የቤተክርስቲያን ይዞታ ነው እየተባለ በትክክል አገልግሎት ላይ ያልዋለውን መሬት ለድሆች ያከፋፈለ፣ በቅዱስ ጋብቻ በአንዲት ሚስት ተወስኖ በታረመ ሕይወት የኖረ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ማን ይባላል? የዚህ ንጉሥ መምህር ማን ይባላል?
2. ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የኖረበት ዘመን ከመቼ እስከ መቼ ነው? ለስንት ዓመታት ኢትዮጵያን በንጉሥነት አስተዳድሮአል?
3. ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ያናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራት እየጠቀሳችሁ አብራሩ፡፡
4. የዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጨረሻው ንጉሥ ማን ነበሩ? እኚህ ንጉሥ የሚታወቁበትን ነገር ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
# (ከ፯ እስከ ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን)- (ሰባት)
# ዐሥራ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ አብነት ትምህርት ቤት አመሠራረት፣ ዓይነትና ደረጃዎች እንዲሁም ያበረከቱትን አስተዋጽዖ ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *“ ከእነርሱ ርቆ ደቀ መዛሙርትን ለየ፥ ጢራኖስም በሚሉት በትምህርት ቤት ዕለት ዕለት ይነጋገር ነበር፡፡ ”* /የሐዋ.፲፱፥፱/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› ፤ በሉሌ መልአኩ

**መግቢያ፡-** ባለፉት ተከታታይ ትምህርቶቻችን በመካከለኛው ዘመን የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አጥንተናል፡፡ የዕለቱ ትምህርት የሚሆነው የአብነት ትምህርት ቤቶችን ታሪክ እና አከፋፈል ማጥናት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### 1. የአብነት ትምህርት ቤት ታሪክ

በዓለማችን ከነበሩት ቀደምት የትምህርት ማዕከላት የመጀመሪያውን ቦታ የሚይዙት ሃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የነቢያት ልጆች የሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ነበሩ፡፡ /፪ኛ.ነገሥ.፮፥፩-/ አይሁድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን የሚያስተምሩባቸው ጥንታዊ ትምህርት ቤቶችም ነበሩ፡፡ /የሐዋ.፳፥፴፬/ በክርስትናው ዓለም በታሪክ ታዋቂ የትምህርት ማዕከላት የነበሩት የእስክንድርያ እና የአንጾኪያ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም መጽሐፍ ቅዱስን ሲተረጉሙና ክርስትናን ሲያስተላልፉ ኖረዋል፤ የእነዚህ ትምህርት ቤቶች ተጽዕኖ በመላው የክርስትና ዓለም እና በዘመናውያኑ የትምህርት ተቋማትም አለ፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ከሁሉም የወሰደችው በጎ ልምድ እና በራስዋ ሊቃውንት ያደራጀችው

www.zeorthodox.org

የትምህርት ሥርዓት አላት፡፡

የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶችም፡- አብነት ፣ የወንበር ትምህርት ቤት፣ ጉባኤ ቤት በሚል መጠሪያ ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደተጀመሩ ትውፊታዊው ታሪክ እና ግዙፋኑ ቅርሶች ያረጋግጣሉ፡፡ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር በመጡት ሌዋውያን እንደተጀመረ የሚነገርለት የኦሪት ትምህርት ቤት የወንበር መምህራንን እያተካካ እስከ ክርስትና ደርሷል፡፡ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንና ተሰዓቱ ቅዱሳን ግእዝ የተማሩትና ቋንቋውን በማደራጀት መጻሕፍት መተርጎም የቻሉት ከነበሩት ትምህርት ቤት ሊቃውንት ነው፡፡ እነርሱም የምሥራቁን ክርስቲያናዊ የትርጉምና የትምህርት ስልት ከመጻሕፍት ጋር አበርክተዋል፡፡ እነ ቅዱስ ያሬድ የተገኙትም ከዚህ ትምህርት ቤት ነው፡፡

የቅዱስ ያሬድ መነሳት ትምህርት ቤቶቹን ቀይሯቸዋል ፤ የመጽሐፍ ትምህርት ቤት የነበረው የአክሱም ትምህርት ቤት የትምህርት ስልቱና ዓይነቱ ተሻሻለ፡፡ የዜማ ፣ የቅኔ እና የአቋቋም ትምህርቶች በየዘርፋቸው ተጀመሩ፡፡ በኋላም ከአክሱም ሥልጣኔ መውደቅ ጋር ትምህርት ቤቶቹም ተዳከሙ፡፡

በመካከለኛው ዘመን የተነሡት አበው በተለይም አባ ኢየሱስ ሞዓ እና አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ለትምህርት ቤቶቻችን ዳግም ትንሣኤ የዘሩባቸው ናቸው፡፡ አባ ኢየሱስ ሞዓ በቤተ መጻሕፍት በማደራጀት ሐይቅ ላይ የጀመሩት የትምህርት ስልት ከነበረው የተወለደ ቢሆንም ብዙ መምህራንን በማፍራት እና ከመንፈሳዊው ትምህርት ጎን የአስተዳደር ትምህርትን ማካተቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡

የአብነት ትምህርት ቤቶች ሌላው ልዩ ጊዜ የጎንደር ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ በዚህ ዘመን የተነሡት ሊቃውንት ትምህርት ቤቶቹን አሁን ባላው መልክ አደራጅተዋል፡፡ ለምሳሌ እነ አዛዥ ጌራ ወርቅ የአቋቋምን ምስክር ፣ መምህር ኤስድሮስ ትርጓሜን አሁን ባለው መልክ አደራጅተዋል ፡፡ እንደ አሁኑ ዘመናዊ ትምህርት ባልተስፋፋበት ጊዜ በኢትዮጵያ የነበረው ትምህርት ሲካሄድ እና ሲመራ የነበው ሃይማኖታዊ በሆነው ሥርዓተ ትምህርት በአብነት ትምህርት ቤት ነው፡፡ አስተማሪዎቹም ***"የኔታ"*** ተማሪዎቹ ደግሞ ***"ቆሎ ተማሪዎች"*** ይባሉ ነበር፡፡ እነዚህም ተማሪዎች ለብርድ መከላከያ ደበሎ ከበግ ቆዳ የሚሠራ ይደርባሉ፡፡ ከቤተሰቦቻቸው ርቀው ስለሚኖሩ እና ስንቅ ስለሚያልቅባቸው ***"በእንተ ስማ ለማርያም"*** በማለት እየለመኑ ቁራሽ እንጀራ የሚያጠራቅሙበት አቁፋዳ እና የውሻ ማባረሪያ ዱላ /በትር/ አላቸው፡፡ መኖርያቸውም የሳር ክዳን ያላቸው ትንንሽ ጎጆዎች ሲሆኑ ቤቶቹ ከትንሽነታቸው የተነሣ ጎጆ ውስጥ የሚገባ ሰው ማጎንበስ ይኖርበታል፡፡

**2. የአብነት ትምህርት እርከኖች**

***ሀ. ፊደል ቤት፡-*** ሆሄያትን ከመለየት በመጀመር እስከ ዳዊት እና የመጻሕፍት ምንባባትን

www.zoorthodox.org

ያካትታል፡፡

**ለ. ዜማ ቤት፡-**የቃል ትምህርቶችን ከውዳሴ ማርያም ጀምሮ ይማሩበታል፡፡ የቅዳሴ ዜማ፣ጾመ ድጓ፣መዋሥዕት፣ዝማሬ፣አቋቋምን ያጠቃልላል፡፡

**ሐ. ቅኔ ቤት፡-**የግእዝ ሰዋስው በማጥናት ቅኔ የሚቀኙበት ነው፡፡ ይህ ክፍል የመጻሕፍትን ትርጉም ለመማር መሠረታዊ ነው፡፡

**መ. መጽሐፍ ቤት፡-**በዚህ ክፍል ብሉያት፣ሐዲሳት፣ሊቃውንት እና መጻሕፍተ መነኮሳት ይተረጎማሉ፡፡

**3. የአብነት ትምህርት ቤቶች ያደረጉት አስተዋጽዖ**

- የቤተ ክርስቲያንና የሀገር ትምህርት በጎ ባህልና ትውፊት እንዲጠበቅ አድርገዋል፡፡
- ፊደል ፣ ቅኔ እና ሥነ ጽሑፍን አበርክተዋል፡፡
- የዕውቀት ማዕከላት በመሆን ለሀገርና ለቤተ ክስቲያን የሚጠቅሙ ቅዱሳንን ፣ ነገሥታትንና ሊቃውንትን አፍርተዋል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

የአብነት ትምህርት ቤቶች ለሀገራችን እና ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ንባብ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ ቅኔ እና መጻሕፍት ቤት የሚባሉ ክፍሎች ያሉ ሲሆን፤ የቆሎ ተማሪዎች ቁራሽ እየለመኑ እና በትሕትና ተከባብረው ሲማሩ ይስተዋላሉ፡፡ በቆሎ ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ተከባብረው የሚኖሩ ሲሆን እንግዳ ሰው ሲመጣ እግሩን ለማጠብ ይሽቀዳደማሉ፡፡ ይህ ሥርዓት እና ትምህርት ብዙ ዘመናትን ተሻግሮ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡

## ተግባር፡-

የቆሎ ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ረኀብን፣ በሽታን እና መራቆትን ሳይፈሩ ቃለ እግዚአብሔርን እንደሚማሩ ሁሉ እኛም ከዘመናዊው ትምህርት ጎን ለጎን አብነት ትምህርትን መማር ይጠበቅብናል፡፡

www.zeorthodox.org

በቆሎ ትምህርት ቤት ያለውን ትሕትና አብነት በማድረግ እኛም ከጓደኞቻችን እና ከቤተሰባችን ጋር በመከባበር ይገባል፡፡

ለቤተ ክርስቲያናችን እና ለሀገር ታላቅ ቅርስ የሆኑ ትምህርት ቤቶች፤ በአሁኑ ሰዓት በአቅም እጦት ምክንያት ችግር እያጋጠማቸው እየተበተኑ ስለሆነ በጸሎታችሁ ጊዜ ትምህርት ቤቶቹንና ተማሪዎቹን አስቧቸው፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. **በክርስትናው ዓለም ቀደምትና ታዋቂ ትምህርት ቤቶች የነበሩት እነማን ናቸው?** ዐበይት ሥራዎቻቸውን ግለጹ፡፡
2. በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቶች የሚታወቁበትን ልዩ መጠሪያዎች ግለጹ፡፡
3. በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች እንዴትና በየትኛው ዘመን ተጀመሩ?
4. በመካከለኛው ዘመን ከተነሡት አባቶች በተለይም የኢትዮጵያን ትምህርት ቤቶች ዳግም ትንሣኤ ዘርተውባቸዋል በመባል የሚታወቁትን አባቶች ስም ግለጹ፡፡
5. አባ ኢየሱስ ሞዓ በዘመናቸው ያደራጁት ትምህርት ቤት የት ነበር? ትምህርት ቤቱን ልዩ የሚያደርገው ምን ነበር?
6. የአብነት ትምህርት እርከኖች ወይም የትምህርት ቤቶቹ የአከፋፈል ደረጃዎች ምን ምን ናቸው? በየደረጃዎቹ የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች አብራሩ፡፡
7. የአብነት ትምህርት ቤቶች ካደረጉት አስተዋጽዖዎች ዋና ዋናዎቹን አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ጠፍተው የተገኙት

# ዐሥራ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች በትምህርቱ ከተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ይገነዘባሉ፤መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"ጠፍቶ ነበር ተገኘ"*** / ሉቃ. ፲፭÷፳፬/

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** /ሉቃ.፲፭÷፫-፴፪/

## *መግቢያ፡-*

ጌታችንና መድኃኒችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠፍተው ስለተገኙ ሦስት ነገሮች ምሳሌ መስሎ አስተምሮናል። በዛሬው ትምህርታችን የእነዚህን ጠፍተው የተገኙት ሦስት ነገሮች መንፈሳዊ ትርጉምና በሕይወታችን ያላቸውን ትምህርት እናያለን።

## ትምህርቱ

### *የፈሪሳውያንና የጻፎች ማንጎራጎር*

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱን ለማንም ልዩነት ሳያደርግ ይሰጥ ነበር። በደካማ ጠባያቸው ፣ በኃጢአተኝነታቸውና በኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛነት ከማኅበረሰቡ የተገለሉም ትምህርቱን ሊሰሙት ይመጡ ነበር። እርሱም ኃጢአተኞች ንስሓ እንዲገቡ ፣ ድሆች እንዲመገቡ ፣ ሕሙማን እንዲፈወሱ ያደርግ ስለነበር። ***"ቀራጮችና ኃጢአተኞችም ሁሉ ሊሰሙት ወደ እርሱ ይቀርቡ ነበር።"*** /ሉቃ.፲፭÷፩/ ነገር ግን ብዙዎች ጻፎችና ፈሪሳውያን ለምን ኃጢአተኞችን ይቀበላል ብለው አንጎራጎሩበት። /ሉቃ.፲፭÷፪/ ክርስቶስ ኃጢአትን እንጂ በኃጠአት የወደቀውን ሰው አይጠላም። እንዲያውም ለንስሓ ይጠራዋል።

www.zeorthodox.org

### የጌታችን ምሳሌያዊ ትምህርቶች

1. የጠፋው በግ

ይህ በግ የጠፋው በመንገድ ስሕተት ነው። ከዘጠና ዘጠኙ በጎችና ከእረኛው መንጎች ተለይቶ መንገድ ሳተ። በዚያውም ጠፋ። ሆኖም እረኛው ፈልጎ አገኘው፤ ተሸክሞም ወደ በረቱ ቀላቀለው። የጠፋው በግ አዳም ነው። የፈለገውም ክርስቶስ ነው። ዘጠና ዘጡኙ ያጠፉትም መላእክት ናቸው። እኛ መንገድ ስተን የምንሄድበት ወቅት አለ፡፡ ሆኖም ቸር እረኛችን በትምህርት እና በፍቅሩ

ትክክለኛውን መንገድ ስተን ከጠፋንበት ወይም ከገባንበት ጉድጎድ ሊያወጣን ከተሳሳትንበት መንገድ ሊመልስን ይፈልገናል።

2. የጠፋው ድሪም

ይህ ድሪም የጠፋው በቸልተኝነት ነው። የድሪሙ ባለቤት የሆነችው ሴት የት እንዳስቀመጠችው አታውቅም። ሆኖም ከሌሎች ዐሥር ድሪሞች ተለይቶ ጠፍቷል። መፍትሔው መፈለግ ነበር። ሴትዮዋ ቤትዋን ሁሉ በርብራ ፈለገችው አገኘችውም።

በቸልተኝነታችን የምናጣው ብዙ ነው። በቸልተኛ አስተዳደግ ልጆ ች ይበላሻሉ። በቸልተኛ ካህናት ምእመናን ይጠፋሉ። እኛም በቸልተኝነታችን የትምህርት ውጤታችን ሊበላሽ ይችላል። በቸልተኛነት የሚጠፉ ብዙ ነገሮች አሉ። ሆኖም መፍትሔው ጌታ እንደነገረን

ሀ. ማጽዳት ነው። ይህም ማለት ንስሓ መግባት እና ራስን ማንጻት ነው።

ለ. መፈለግ። ከወዴት እንደ ወደቅንና የት ላይ እንዳጠፋን መፈለግ። ከቤተ ክርስቲያን የወጡትንም በስብከት መፈለግ ነው።

3. የጠፋው ልጅ

ሁለት ልጆች የነበሩት ሀብታም ሰው ነበር። አንድ ቀን ታናሽ ልጁ ***"ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ስጠኝ"*** አለው። አባቱ ከሰጠው በኋላም ሩቅ አገር ሄደ፤ ከአባቱ የወሰደውንም ገንዘብ በከንቱ አባከነውም። ብዙ ጓደኞችን ያዘ። በሂደትም ገንዘቡን ጨረሰ። ገንዘቡ ሲያልቅም በጣም ተቸግሮ ስለተራብ ለሚበላው ምግብ ልመና ጀመረ። ነገር ግን ገንዘብም ሆነ ሥራ አላገኘም። በኋላም አሳማ አርቢ አሳማዎችን ሊጠብቅለት ቀጠረው። ከመራቡም የተነሣ የአሳማ ምግብ ሊበላ ይመኝ ነበር። አሳማዎቹ ሲበሉ አይቶም፣ ***"እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሙያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ። ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና÷አባቴ ሆይ÷ በሰማይና በፊትህ በደልሁ ወደፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ።"*** ብሎ አሰበ።

www.zeorthodox.org

ከረጅሙ ጉዞ በኋላም አባቱ ቤት ደረሰ። አባቱ ከሩቅ አይቶትም÷ ከጠፋበት ቀን ጀምሮ ይጠብቀው ነበርና አቅፎ ሳመው፤ ***"እነሆ ይህ ልጄ ጠፍቶ ነበር ተገኝቶአል"*** አለ። ልጁም ***"ልጅህ ልባል አይገባኝም ከባሮችህ እንደ አንዱ ቁጠረኝ"*** አለው።

አባቱ ግን ሳይቆጣ በፍቅርና በይቅርታ አገልጋዮቹን ***"ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፣ ለእጅ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ፤ የሰባውንም ፍሪዳ አምጥታችሁ እረዱለት÷ እንብላም ደስም ይበለን፤ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ሕያው ሆኖአል ፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም ።"***

አላቸው፤ ደስም አላቸው።

## ማጠቃለያ

የጠፋው በግ መንገድ ሲስት፣ የጠፋው ድሪም የት እንደተቀመጠ አልታወቀም። የጠፋው ልጅም በጥጋቡ የሄደ ትእቢተኛ ሰውን ይመስላሉ። ሆኖም በትጉሁ እረኛ ምክንያት ሁሉም ጠፍተው አልቀሩም ተገኝተዋል። ለመገኘት ፍቃድን መስጠት ከእኛ ይጠበቃል።

የጠፋው ልጅ አባካኝ ልጅ ነበር። ከቤተሰቡ ገንዘብን ወስዶ ያጠፋውም ለዚህ ነበር። ስሕተቱ ከአባቱ ቤት መኮብለሉ ብቻ ሳይሆን ገንዘቡን ማባከኑና ግድ የለሽነቱም ነበር።

ሁላችንም ስሕተት እንሠራለን። ይህ አባት የልጁን መመለስ ይጠባበቅ እንደነበረም÷ እኛም ጥፋታችንን አውቀን በንስሐ ስንመለስ እግዚአብሔር መመለሳችንን ይጠብቃልና - ይቅር ይለናል።

ነገር ግን እኛ ኃጢአታችንን በማመን እንደጠፋው ልጅ ***"በድያለሁ"*** ብለን ለካህናት መናዘዝም ይገባናል። የእግዚአብሔር ቃል ***"በአንድ ኃጢአተኛ መመለስ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።"*** / ሉቃ.፲፭÷፲/ ያለውም ለዚህ ነው።

## ተግባር

- የተሳሳቱትን ወደ እውነት ለመመለስ ጥረት አድርጉ።

www.zeorthodox.org

# ዘመነ አስተርእዮ

# ዐሥራ ስምንተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።"*** / ዮሐ.፪÷፲፩/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** /ማቴ ፫፣ ማር.፩፣ ሊቃ. ፫÷፣ ዮሐ ፩÷፳፱-፴፬/

## መግቢያ፡-

በግእዝ ‹‹አስተርእዮ›› የሚለው ቃል ቀጥተኛ የአማርኛ ትርጉሙ ‹‹መገለጥ›› ማለት ነው። እግዚአብሔር በብዙ መንገድ ተገልጧል።

የመጀመሪያው የእግዚአብሔር መገለጥ በፍጥረቱ ነበር። ***"እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤"*** / ሮሜ.፩÷፲፱-፳/

እግዚአብሔር በብዙ መንገድ ራሱን ለቅዱሳን ገልጦአል። በሕልም፣በራእይ፣በሰውና በመላእክት፣ድምፁን በማሰማትም ተገልጦ ነበር።***"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥"*** / ዕብ.፩÷፩/

የእነኚህ መገለጦች ምሳሌነትና አስፈላጊነት ግን አምላክ በሥጋ ለመገለጡ ትንቢት የተነገረባቸው፣ ምሳሌ የተመሰለባቸው ናቸው። ዋናው አስተርእዮተ እግዚአብሔር የአንድ ልጁ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ራሱን መግለጥ ነው። ወልድ በመገለጡ፡-

www.zeorthodox.org

1. ስለ እግዚአብሔር በትክክል አውቀናል። ***"መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።"*** /ዮሐ.፩÷፲፰/
2. የዲያብሎስ ሥራ ፈርሷል። ጠላታችን ዲያብሎስ በእባብ አድሮ ዓለምን አስቶ ነበር። ክርስቶስ በሥጋ ማርያም አድሮ ዓለምን አዳነ። የዲያብሎስንም ሥራ ሻረ። ***"ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ።"*** ፩ኛ.ዮሐ.፫÷፱
3. ከኃጢአት ድነን በጽድቅ ለመኖር ጸጋን አግኝተናል።***"ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር***

*ጸጋ ተገልጦአልና፤ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤"* ቲቶ ፪÷፲፩-፲፫

በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት የክርስቶስ መገለጥ በታላቅ ክብር ይታሰባል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም ከልደት እስከ ነነዌ ጾም ያለውን ጊዜ ዘመነ አስተርእዩ ወይም የመገለጥ ወራት ብላ ታስበዋለች፡፡ የዛሬው ትምህርታችንም ስለዚህ ወቅት ያስተምረናል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

**ጌታችን ከእመቤታችን ሲወለድ በሥጋ ተግለጦአል፡፡**

እረኞቹ መላእክት የክርስቶስን መወለድ ሲገልጡላቸው እንዲህ ብለው ነበር፡፡***"እንግዲህ እስከ ቤተ ልሔም ድረስ እንሂድ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን የሆነውን ነገር እንይ ተባባሉ፡፡"*** ሆኖም ይህን መገለጥ ሰዎች ሁሉ አልተረዱትም፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን እረኞች ሲሰግዱና ሲያመስግኑ ፣ አረጋዊው ስምዖን ሲተንብይ ፣ ነቢይት ሀና ስትመሰክር ….. 'ብልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር፡፡" ሉቃ.፪÷፲፱ እና ፶፩

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ሠላሳ ዓመቱ ራሱን አልገለጠም፡፡ ***"ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር"*** /ሉቃ.፫÷፳፫/

**በጥምቀት የተገለጠው፡፡**

የዘመነ ብሉይ የመጨረሻው ነቢይ ፣ የሊቀ ካህኑ የዘካርያስ እና ኤልሳቤጥ ልጅ ፣ ዮሐንስ ስለ ንስሐ እየሰበከና እያጠመቀ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ነበር፡፡ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ እየሄዱ ንስሐ ይገቡ፤ይጠመቁም ነበር፡፡ እርሱም ያስተምራቸው ነበር፡፡ ለሚጠይቁትም መልስ ይሰጥ ነበር፡፡ እርሱ ክርስቶስ መስሏቸው የጠየቁትም ነበሩ፡፡ እርሱም ***"እኔ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፡፡ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት ነበር፡፡ የእግሩን ጫማ ልፈታ የማይገባኝ ነው ያልኳችሁ ይሄ ነው፡፡ እርሱም በውኃና በመንፈስ ያጠምቃችኋል፡፡ እኔ በበረሐ ለጌታ መንገድን አቅኑ ብሎ የሚጮኽ ድምፅ ነኝ"*** አላቸው፡፡ ጌታ ራሱን ለሕዝቡ ከሚገልጥበት ዘመን ስድስት ወር ቀደም ብሎ መጥምቁ ዮሐንስ ተነሣ፡፡ ሕዝቡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲቀበሉና እንዲዘጋጁ መንፈቀ ዓመት ቀድሞ መንገድ ጠርጓል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሠላሳ ዓመት ሲሞላው በዮሐንስ እጅ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ሄደ፡፡ ዮሐንስ ግን እኔ ባንተ ልጠመቅ ይገባኛል ብሎ ከለከለው፡፡ ጌታችን ግን" ***አሁንስ ፍቀድልኝ***

www.zeorthodox.org

***እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና*** "አለው፡፡ማቴ.፫÷፲፭ ዮሐንስም አጠመቀው፡፡ ጌታችን ተጠምቆ ከውኃ ሲወጣም÷ሰማያት ተከፈቱ፡፡

1. መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳያ ከሰማይ ወረደ፡፡
2. ይህ የምወደው ልጄ ነው እርሱንም ስሙት የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀበት ዕለት እግዚአብሔር በአንድነት በሦስትነቱ ተገለጠ፡፡ እግዚአብሔር አብ ስለ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በመመስከር ተገለጠ፡፡ ወልድ በዮርዳኖስ ባሕር በመጠመቅና በአባቱ እየተመሰከረለት በሥጋ ሲገለጥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል በወልድ ላይ በማረፍ ተገለጠ፡፡

በዚህም ጌታችን አምላክነቱን በመግለጥ የሰው ልጆችን በትሕትና ማገልገል ጀመረ፡፡ የተጠመቀበት አንዱ ምክንያትም ራሱን አባቱንና መንፈስ ቅዱስን ለመግለጥ ነበር፡፡ ሌላው ምክንያት ደግሞ ምሳሌ ሊሆነንና ትንቢቶችን ለመፈጸም ነበር፡፡

በእኛ ቤተክርስቲያን በዓለ ጥምቀት ጥር ፲ እና ፲፩ ሲከበር! ከልደት በኋላ ያለውን ወቅትም እስከ ጾመ ነነዌ ዘመነ አስተርእዮ የመገለጥ ዘመን ብለን እናከብረዋለን፡፡

በምዕራብውያን (Epiphany) መገለጥ ተብሎ ይከበራል፡፡ ይህም መገለጥ የአምላክ ሦስትነት ፣ የጌታ ማስተማር በገሀድ መውጣት የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው፡፡

### የምልክቶች መጀመሪያ፡፡

ሌላው የመገለጥ በዓል ቃና ዘገሊላ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀንና ሌሊት ከጾመ በኋላ የዲያብሎስን ፈተናና ኃይል ድል አደረገልን፡፡ ከዚያም ወደ እናቱ ቤት ወደ አደገበትም መንደር ወደ ገሊላ ተመለሰ፡፡ ሁለቱንም ቀናት ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፡፡ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ እንድርያስ፣ ያዕቆብ ናትናኤል፣ ፊልጶስ በእርሱ አምነው ተከተሉት፡፡ ይሁዳም በዚህ ወቅት እንደተጠራ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ያስረዳሉ፡፡ በሦስተኛው ቀንም በገሊላ በምትገኘው ቃና በተባለች መንደር ሰርግ ነበር፡፡ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ እና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተጠርቶ በሰርጉ ቤት ተገኘ፡፡ በሰርጉ የታደሙት እንግዶች ሳይስተናገዱ ወይን አለቀባቸው፡፡ ሰዎቹም በጣም አዘኑ፡፡ በዚህ ጊዜ እመቤታችን ወደ ጌታ ሄዳ ***"የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው፡፡"*** ዮሐ. ፪÷፫ ለሰዎቹም የሚላችሁን አድርጉ አለቻቸው፡፡ እርሱም ጋኖቹን ውኃ ሙሉ ብሎ ውኃውን ወይን አድርጎ ቀየረው፡፡ ይህ የምልክቶች መጀመሪያ ነበር ***"ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ፡፡"*** ዮሐ. ፪÷፲፩ በዚህ ዕለት ፡-

1. እናቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሚላችሁን አድርጉ ብላ ሁሉን ቻይ ጌታ መሆኑን የገለጠችበት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

2. ጌታችን ከተጠመቀ በኋላ የፈጸመው የምልክቶች መጀመሪያው ቀን ነው።

3. ክብሩን ለደቀ መዛሙርቱ ለመጀመሪያ የገለጠበትና ያሳመነበት ቀን ነው።

የቃና ዘገሊላ ተአምር ጥንተ ዕለት የካቲት ፳፫ ነው። ሆኖም ወደ ጥር ፲፪ ተዛውሮ ይከበራል። ምክንያቱም፡- የመገለጥ በዓል ስለሆነ ቃናን ከውኃ በዓል ከጥምቀት ጋር ለማክበር ነው።

## ማጠቃለያ

ከዚህ ትምህርት የሚከተሉትን ነጥቦች እንማራለን፡-

ንስሐ፡- መጥምቁ ዮሐንስ "***መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ"*** በማለት አስተምሮአል። ንስሐ ከልባችን በመጸጸት ኃጢአትን መተው፣ ለካህን (ንስሐ አባት) መናዘዝና ላለመመለስ መወሰንም ነው። በዚህም በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እናገኛለን።

**ትሕትና፡-** ዮሐንስ እንደገለጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ (ከመጥምቁ ዮሐንስ) ይበልጣል፥ ብቻም ሳይሆን ጌታውና አምላኩም ነበር። የሰማይና የምድርም ፈጣሪ ነው። ነገር ግን እርሱ ወደ ዮሐንስ ሄዶ ሲጠመቅ ትሕትናን ሊያስተምር ነበር። ለዚህም ነው ***"ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናል"*** ያለው። ከጌታ ትሕትናን ከዮሐንስ መታዘዝን ተምረናል።

**በምሳሌ ማስተማር፡-** ጌታችን በቃል ብቻ አላስተማረንም፤ በተግባርና በቃልም ምሳሌ በመሆን አስተማረን እንጂ። በዚህም በዕለታዊ ኑሮአችን መልካም ምሳሌ እንድንሆን አርኣያ ሆኖናል።

**አስተርእዮ፡-** መገለጥ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ሦስትነት ፣ የጌታችን ለሕዝቡ መገለጥ ፣ በቃና የተደረገው የመጀመሪያ ተአምራት ናቸው። እነዚህ በሙሉ በምድረ እስራኤል ራሱን ዝቅ አድርጎ የተወለደው አምላክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን የገለጠባቸው ናቸው።

## ተግባር

ክርስቶስን በማስተማር ፣ በሕይወታችሁ የእርሱ መሆናችሁን በማሳየትና በሚቻለው ጥበብ ግለጡት።

www.zeorthodox.org

ጥያቄዎች፡-

1. ‹‹ አስተርእዮ›› የሚለው የግእዝ ቃል የአማርኛ ትርጉም ምንድነው?
2. የመጀመሪያው የእግዚአብሔር መገለጥ በምን ይታወቃል? በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በመጥቀስ አብራሩ።
3. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዘመነ አስተርእዮ ወይም የመገለጥ ወራት ብላ የምታስበው ከመቼ እስከ መቼ ያለውን ጊዜ ነው?

4. እግዚአብሔር በአንድነት በሦስትነቱ የተገለጠበት ዕለት ምን ተብሎ ይታወቃል? የዚህን መገለጥ መነሻና አጠቃላይ ሁኔታ በዝርዝር አብራሩ።
5. በቤተ ክርስቲያናችን ይህ በዓል ምን ተብሎ ይጠራል? የሚከበርበት ዕለትስ መቼ ነው?
6. ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ የፈጸመው ተአምር ምንድነው? የት?

www.zeorthodox.org

# ትንቢተ ዮናስ

## ዐሥራ ዘጠነኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ተማሪዎች ከነቢዩ ዮናስ ታሪክ፤ እግዚአብሔርን ስለመታዘዝ፣ በንስሐ ስለመጸለይ እና ስለ ኃጢአታችን ስለመጾም እንዲሁም በንስሐ፣ በጾምና በጸሎት የሚገኘውን በረከት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "***በመከራዬ ሳለሁ ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ እርሱም ሰማኝ*** ዮና. 2÷3

**ምንባብ፡-** ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢተ ዮናስን በሙሉ አንብቡ

**መግቢያ፡-** በዛሬው ትምህርታችን ትንቢተ ዮናስን እናጠናለን።

**ነነዌ፡-** በጢግሮስ ወንዝ ዳርቻ በናምሩድ ተመሠረተች። ይህች ቦታ በዘመናችን ኢራቅ ተብሎ በሚጠራው ሀገር ስትገኝ ሞሱል ትባላለች። በዙሪያዋ ረጅም ግንብ ያላት ታላቅ ከተማ ነበረች። ከጌታችን ልደት ዘጠኝ መቶ ዓመታት በፊት ፤ አንድ መቶ ሃያ ሺሕ ሕዝብ ይኖርባት ነበር።

ሆኖም ሕዝቡ በኃጢአት የሚኖሩ ነበሩ። እግዚአብሔር የአማቴ ልጅ ዮናስን ***"ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ፥ ክፉታቸውም ወደ ፊቴ ወጥቶአልና በእርስዋ ላይ ስበክ።"*** ዮና.፩÷፪ አለው። የነነዌ ሰዎች ከእግዚአብሔር ርቀው ለረጅም ጊዜ ኖሩ÷አምላካቸውን እግዚአብሔርንም ረስተው በብዙ ኃጢአቶች ተጠመዱ። እግዚአብሔር ግን ፍጹም አልረሳቸውም፣ ከጥፋታቸው ተመልሰው እንዲድኑና ወደ እውነተኛው እውቀት እንዲመጡ ይፈልግ ነበር። ሁሌም ከአጠገባቸው አልተለየም።

የነነዌ ሰዎች ለራሳቸው ጣዖታትን ፈጥረዋል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ያላቸው መሠረተ እምነት እና አመለካከትም የተዛባ ነበር። በቀጥተኛ መንገድ በእርሱ እንዲያምኑ ፣ ለእግዚአብሔር የማይቻለው አልነበረም። ነገር ግን ስሙን እንዲያውቁ፣ ክብሩን እንዲያወድሱና በቀና አምልኮ እንዲኖሩ በነቢያት ትምህርት ጠራቸው።

www.zeorthodox.org

### ነቢዩ ዮናስ፡-

ዮናስ ማለት ርግብ ማለት ነው። ዮናስ በገሊላ ውስጥ ከምትገኘው ከጋትሔፌር የተነሣ ነቢይ ነው። ፪ኛ.ነገሥ.፲፬÷፳፭። አባቱ አማቴ ይባላል።

ከትንቢተ ዮናስ ውጭ በ፪ኛ ነገ.፲፬÷፳፫-፳፭ ላይ ብቻ ስለ ዮናስ ተጠቅሶአል፡፡ ከዚህ ጥቅስ ዮናስ የነበረው በዳግማዊ ኢዩርብዓም ዘመን ፯፻፹፫-፯፻፵፫(783-743) መሆኑን እንረዳለን፡፡ ዮናስ ከመጀመሪያዎቹ የሥነ ጽሑፍ ነቢያት አንዱ ነው፡፡

ነቢዩ ዮናስ ትንቢት የተናገረው በአሦራውያን ዋና ከተማ በነነዌ ነበር፡፡ ዮናስ በነነዌ ያስተማረው በራብዓዊ ስልምናሶር በነገሠበት ዘመን ፯፻፹፩-፯፻፸፪(781-772 ቅ.ል.ክ) ነበር፡፡ ዮናስ ከትውልድ ሀገሩ ወጥቶ በአሕዛብ ሀገር የእግዚአብሔርን ቃል የሰበከ ብቸኛ ነቢይ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. የመጽሐፉ ዓላማ

ትንቢተ ዮናስ ከእስራኤል ወደ አሕዛብ የተላከ የብሉይ ኪዳን መልእክት ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያለውን ፍቅር ያስረዳል፡፡ መጽሐፉ የነቢዩን የአገልግሎት ሕይወት ይገልጻል፡፡

የነብዩ ታሪክ ስለ ክርስቶስ ይነግረናል፡፡ ዮናስ ሦስት መዐልትና ሦስት ሌሊት በዓሣ አንበሪ ሆድ አድሯል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ማደሩን ያመለክታል፡፡ ማቴ.፲፪÷፴፱-፵፩፤ ሉቃ.፲፩÷፳፱-፴፡፡ ከነቢያት መካከል ለክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ በቀጥታ የተጠቀሰ ዩናስ ብቻ ነው፡፡ ወደ አሐዛብ የሆነው የዩናስ ተልእኮ የመሲሕ ተልእኮ እና አድኅኖት ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም መሆኑን ያመለክታል፡፡

## 2. አከፋፈሉ

መጽሐፈ ዮናስ በአምስት ይከፈላል፡፡

1. ምዕራፍ.፩÷፩-፫ እግዚአብሔር ዮናስን ወደ ነነዌ ላከው፤ ዮናስ ኮበለለ፡፡
2. ምዕ ፩÷፬-፲፯ የዮናስ ወደ ቴርሴስ መኰብለልና የተከተለው እግዚአብሔር እጅ፡፡
3. ምዕ ፪÷፩-፲ ዮናስ በከርሠ አንበሪ የጸለየው ጸሎት፡፡
4. ምዕ ፫÷፩-፱ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ለዩናስ እንደገና መምጣቱ፡፡
5. ምዕ ፫÷፲፣፬÷፲፩ በእግዚአብሔር ምሕረት የዮናስ አለመደሰትና የእግዚአብሔር ተግሣጽ፡፡

### 3. ታሪኩ

ዮናስ ነነዌ በኃጢአትዋ ልትጠፋ ሲፈረድባት ሕዝቡን ለንስሐ እንዲጠራ በእግርዚአብሔር ተላከ፡፡(፩÷፩) ዮናስ ግን እግዚአብሔር መሐሪ ስለሆነ ከጥፋት ቢያድናቸው ውሸታም እባላለሁ ብሎ ፈርቶ በጀልባ ከነነዌ ወጣና ከእግዚአብሔር ፊት ሸሸ፡፡(፩÷፪-፫)

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ታላቅ የነፋስ ሞገድ አስነሣ ባሕሩም ተናወጠ በመርከብዋ የነበሩት ለሕይወታቸው ፈሩ፣ እጅግም ተሸበሩ፤ ሁሉም ወደ አምላክ ጮኹ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ዮናስ ከመርከቡ ውስጠኛ ክፍል ተኝቶ ነበር፡፡ የመርከቡ መሪ ግን ዮናስ ተነሥቶ እንዲጸልይ ቀሰቀሰው፡፡ በመርከብዋ የነበሩት በአንድ ሰው ኃጢአት ይህ አግኝቶናልና ማን እንደሆነ እርስ በርሳችን እጣ እንጣጣል አሉ፡፡(ዮና.፩፥፬-፯)

እጣው በዮናስ ላይ ወደቀ፤ ምን በደል እንደሠራ ጠየቁት፡፡ ዮናስም ከእግዚአብሔር ፊት እንደ ኮበለለ፣ በርሱ ምክንያት ነዉጡ እንደመጣ ቢጥሉትም ሞገዱ ጸጥ እንደሚል ነገራቸው፡፡ ሰዎቹ ግን ወደ ምድሩ ሊመለሱ አጥብቀው ቀዘፉ ሆኖም ሞገዱ አየለባቸው፡፡(ዮና.፩፥፰-፲፫) እግዚአብሔር በንጹሕ ደም እንዳይፈርድባቸው ጸልየው ጣሉት፡፡ ባሕሩም ጸጥ አለ፡፡ ሰዎቹም እግዚአብሔርን ፈርተው መሥዋዕት አቀረቡ፡፡(፩፥፲፬-፲፮)

እግዚአብሔርም ዮናስን የሚውጥ ታላቅ ዓሣ አሰናዳ፡፡ ዮናስንም ዋጠው፤ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ነበር፡፡ ዮናስ በዓሣው ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም መለሰለት፡፡ እግዚአብሔርም ዓሣውን አዘዘው ዮናስንም በየብስ ላይ ተፋው፡፡ (ዮና.፪፥፩-፲፩)

ጌታ እግዚአብሔር ዮናስን ወደ ነነዌ ተመልሶ በሕዝቡ ኃጢአት በሦስት ቀን ትጠፋለች ብሎ እንዲናገር ላከው፡፡ ዮናስም የታዘዘውን ፈጸመ፡፡ ይሄን የሰሙ የነነዌ ሰዎች ጾም ዓወጁ፤ ማቅ ለብሰውም አለቀሱ፡፡ የነነዌ ንጉሥ ከዙፋኑ ወርዶ ማቅ ለበሰ፤ አመድ ነሰነሶም ተቀመጠ፡፡ ከአዋቂ እስከ ሕፃን እንስሳት ጭምር ለሦስት ቀን እንዲጾሙ አዘዘ፡፡ ከክፉ መንገዳቸው መመለሳቸውን ያየ ጌታ መአቱን መለሰ፡፡ (ዮና.፫፥፩-፲)

ዮናስ ግን በዚህ ደስ አልተሰኘም ፤ እግዚአብሔር የነነዌን ሕዝብ አጠፋለሁ ብሎ አላጠፋቸውምና ከከተማው ወጥቶ ዳስ ሠርቶ ተቀመጠ፡፡ እግዚአብሔር የቅል ዛፍ አብቅሎ፤ ዮናስን ከፀሐይ የሚከልለው ማረፊያ ጥላ አዘጋጀለት፡፡ ሲነጋ ቅሉን ትል በልቶት ወደቀ፡፡ ዮናስ ተቆጣ መሞትንም ተመኘ በቁጣ አማረረ፡፡ እግዚአብሔርም፤ አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምህባት ላላሳደግሃትም፣ በአንድ ሌሊት ለበቀለች፣ በአንድ ሌሊትም ለደረቀችው፣ ቅል አዝነሃል፡፡ እኔስ ቀኛቸውንና ግራቸውን የማይለዩ ከመቶ ሃያ ሺህ የሚበልጡ ሰዎችና ብዙ እንስሳት ላሉባት ለታላቂቱ ከተማ ለነነዌ አላዝንምን አለው፡፡ (ዮና.፬፥፩-፲፩)

www.zeorthodox.org

**4. ዮናስ የክርስቶስ ምሳሌ ነው ፦**

እግዚአብሔር ዮናስን ወደ ነነዌ ሰዎች ላከው፤ የነነዌ ሰዎችም ንስሐ ገብተው ዳኑ፡፡ በተመሳሳይም እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሳ አንድያ ልጁን ላከ፤ ሥጋን ተዋሕዶ ሰው ሆነ፥ስለ

ዓለም ሞቶ ተነሣ÷ላመኑበትም የዘላለም ሕይወት ሰጠ፡፡

ዮናስን ወደ ባሕሩ መጣል መርከበኞቹን በሙሉ ከሞት ጥፋት አድኗል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሰቀል ለዓለም ከዘላለም ሞት መዳንን አድሏል፡፡

ዮናስ በዓሣ ነባሪው ሆድ ሦስት ቀንና ሌሊት አድሮ ወጥቷል፤ በሕይወት ኖሯል፡፡ አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ ጌታችን በመስቀል ላይ ሞቶ፤ ሦስት ቀንና ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ፤ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል፡፡ ሕያው ሆኖ የዘላለምን ሕይወት ሰጥቶናል፡፡

በዮናስ ጸሎት የሞትን ድል መነሳትና ዳግም ልደትን የሚያስተምር ግልጽ መልእክት አለ፡፡ ***"በሲኦልም ሆድ ውስጥ ሆኜ ጮኽሁ÷ቃሌንም አዳመጥህ...በምድርና በመወርወሪያዎችዋ ለዘላለም ተዘጋሁ፤አንተ ግን አቤቱ አምላኬ÷ሕይወቴን ከጉድጓዱ አወጣህ፡፡"*** ዮና.፩÷፪-፯ ይሄንንም ከጌታችን ሞት እና ትንሣኤ ጋራ በማነጻጸር ለቅዱሳን ሐዋርያቱ ያላቸውን አስተውል፡፡***"...የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች አልፎ ይሰጣል÷የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል÷ ለአሕዛብም አሳልፈው ይሰጡታል÷ይዘብቱበትማል÷ይተፉበትማል÷ይገርፉትማል÷ይገድሉትማል÷በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው፡፡"*** ማር.፲÷፴፫-፴፬

## ማጠቃለያ

**እግዚአብሔር** መሐሪ ነው፡፡ ሕዝቡ እንዲጠፋ አይፈልግም፡፡ ስለዚህም መልእክቱን በነቢያትና መምህራን እየላከ በኃጢአታችን እንዳንጠፋ ያሳስበናል፡፡ በኀጢአት እንኳን ሆነን የንስሐ ጊዜ ይሰጠናል፡፡ ዮናስን ወደ ሕዝቡ የላከው የነነዌ ሰዎችን ከጥፋት ለማዳን ነበር፡፡ ከኃጢአታቸው ሲመለሱም ማራቸው፡፡

**የነነዌ ሰዎች ንስሐ በጾምና ጸሎት ነበር**፡፡ ንጉሡ ሕዝቡ እንዲጾሙ አዝዞአል፡፡ ይህም ከልብ የሆነ ጾምና ጸሎት የእግዚአብሔርን ልብ የሚያራራና ምሕረትን የሚያመጣ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

**የትም ብንሆን ከእግዚአብሔር አንደበቅም**፤ የእርሱን ጥሪ ሰምተን ልንመልስ ይገባል፡፡ ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት ለመሸሽም ሞክሯል ግን አልቻለም፡፡ እግዚአብሔር ልናደርገው የሚፈልገውን መፈጸም ይገባናል፡፡

www.zeorthodox.org

**እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በነቢያት ቃል ያዘጋጅ ነበር**፡፡ በተጨማሪም ብዙ ምልክቶች እና ትንቢቶችን በመግለጥ የዓለምን ድኅነት እንዲጠብቁ አድርጓል፡፡ የትንቢቱን መፈጸም (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን) የተጠባበቁና ያመኑም ድነዋል፡፡

## ተግባር ፡-

1. በእኛ ያለውን የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ እና ሓላፊነታችንን እንወጣ፡፡
2. ተማሪዎች ስሕተታችሁን በማረም የቀና ሕይወት ለመኀዝ፤ ተስፋ መቁረጥን ከእናንተ አርቁ፤
3. ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ ልብ ሊኖረን ይገባል፡፡
4. እግዚአብሔር ቀጥቷቸው መልካም ያገኙና የዳኑ ቅዱሳንን ታሪክ አስረዱ፡፡
5. እግዚአብሔር ምሕረቱን እና ትዕግሥቱን ለሰዎች ከሚያሳይባቸው ሁኔታዎች የተወሰኑትን ግለጡ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. ነነዌ በየት የምትገኝ ከተማ ነች?
2. ወደ ነነዌ የተላከው ነቢይ ማን ይባላል?
3. ነቢዩ ወደ ነነዌ ሰዎች የተላከበት ምክንያት ምንድነው?
4. ወደ ነነዌ የተላከው ነቢይ ምን ደረሰበት? ምክንያቱን እና አጠቃላይ ታሪኩን አብራሩ፡፡
5. የነነዌ ሰዎች ከእግዚአብሔር ቅጣት የዳኑት በምንድነው? አብራሩ፡፡
6. ዮናስ የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ይገልጻል፡፡ ምሳሌነቱን በማብራራት ግለጽ፡፡

www.zeorthodox.org

# ጾም እና አስፈላጊነቱ

# ሃያኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለጾም ጥቅምና መንፈሳዊት ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ጾምን ቀድሱ ጉባኤውንም አውጁ፡፡"*** ኢዩ ፪÷፲፭

**ምንባባት፡-** ማቴ.፬÷፩-፲፩ ፣ዳን. ፲÷፫

## መግቢያ፡-

ጾመ ተከለከለ ማለት ሲሆን፣ ከምግብና መጠጥ ለተወሰነ ሰዓታትና ከቅባት ምግቦች ደግሞ በጾም ወቅት መከልከል ነው፡፡ ክርስቲያኖች ሁሌም መጾም ያለባቸው ክፋት፣ ኃጢአትና ክፉ ምኞቶችም አሉ፡፡

ጾም የሥጋ ፍላጎቶችን በማዳከም የነፍስን ፍቃድ ለመፈጸም የምንችልበት ነው፡፡ ጾም የመንፈሳዊ እድገት መንገድ ነው፡፡ ከመንፈሳዊ እድገት ጋር ያልሆነ ጾም የምግብ ለውጥ ብቻ ነው፡፡

ሁዳዴ በመባል የሚታወቀው ዐቢይ ጾም ከሰባቱ አጸዋማት አንዱ ነው፤ ጌታችን አርባ ቀንና አርባ ሌሊት የጾመው ስለሆነም እንጾመዋለን፡፡

በዛሬው ትምህርታችንም ጾም በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ጠቀሜታና መንፈሳዊ ይዘቱን እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

ጾም በመንፈሳዊ ሕይወታችን አስፈላጊው ተግባር ሲሆን፤ በብሉይ ኪዳን በጾም ብዙ መንፈሳዊ ሥራ የሠሩ የእግዚአብሔር ሰዎችን እናገኛለን፡፡

www.zeorthodox.org

ለምሳሌ :-

- ሙሴ ዐሥርቱን ትእዛዛት ከእግዚአብሔር ከመቀበሉ በፊት አርባ ቀንና ሌሊት ጾሞአል፡፡ ዘጸ. ፴፬
- ዳንኤል በዓለም ወደፊት የሚፈጸመውን ሲገለጽለት በጾም ነበር፡፡ዳን.፲÷፫
- ነኅምያ ስለ ኢየሩሳሌም ጥፋት ሲሰማ ጾሟል፡፡ ኑኃ.፩
- ዳዊት ይጾም ነበር፡፡ ***"ነፍሴን በጾም አስመረርኳት"*** መዝ. ፻፰/፻፱÷፳፬
- ኢሳይያስ ይጾም ነበር፡፡ ስለጾምም አስተምሮአል፡፡ (ኢሳ.፶፰÷፫)

- ነቢዩ ኤልያስ አርባ ቀንና ሌሊት ጾሞአል፡፡ ፩ኛነገ.፲፱÷፰
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እስኪራብ በበረሐ አርባ ቀንና ሌሊት ጾሟል፡፡ ማቴ.፬÷፩-፲፩ በተራራው ስብከትም ስለ ጾም አስተምሮአል፡፡ /ማቴ.፮÷፲፮-፲፰/ ዲያብሎስ እንዴት እንደሚሸነፍ ***"ይህ ወገን በጸሎትና ጾም ካልሆነ ሊወጣ አይችልም"*** /ማር.፱÷፳፱/ብሎናል፡፡
- በሐዋርያት ሥራ ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ስትጾም እናነባለን፡፡/የሐዋ.ሥ.፲፫÷፫-፬/
- የቤተ ክርስቲያን አባቶች ለእኛ በደረሱን ጽሑፎቻቸው ስለ ጾም ጥቅም ጽፈዋል፣ ደንግገዋልም፡፡

## ጾምና መንፈሳዊ እድገት

ጾም የነፍሳችንን ፈቃድ ለመፈጸም የሥጋን ፍላጎት ለማሸነፍ የምንፈጽመው ተግባረ ነፍስ ነው፡፡ በሕይወታችን በሥጋ ክፉ አምሮትና መንፈሳዊነት መካከል ትግል አለብን፡፡

ለዚህም ነው! ቅዱስ ጳውሎስ ***"ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና÷ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉት አትችሉም፡፡"*** ያለው ገላ.፭÷፲፯

ሶርያዊው ይስሐቅ ***"በኃጢአትና ምኞቶቹ የሚፈጸም መንፈሳዊ ትግል ሁሉ በጾም መጀመር አለበት በተለይም ይህ ትግል ከውስጣዊ ኃጢአት /ምኞት/ ጋር ከሆነ "*** ይላል

**ከምግብ መካከል ጎን ለጎን መንፈሳዊ እድገት መኖር አለበት፡፡**

የሥጋ ጾም ከልብ ንጽሕና ፣ ከነፍስና ከሥጋ ቅድስና ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚህም ጋር አንድ ቅዱስ ***"በኃጢአትና በግፍ ተይዘን ከምግብ በመከልከል ብቻ ከጾምን÷ የሥጋችን መጾም ብቻ አይጠቅመንም÷ ውድ የሆነውን ተግባር እናረክሰዋለን፡፡ ስለዚህም የውጭ ሰውነታችን እንደሚጾም ውሳጣዊ ሰብእናችንንም መቆጣጠር እና ከሚጎዱት ነገሮች በመቆጠብ ጾማችንን ከክፋት፣ ካለመታመን፣ ከጥላቻ በማንጻት እውነተኛ ማድረግ አለብን፡፡*** ብሏል፡፡

**የጾምና የጸሎት አለመነጣጠል፡፡** www.zeorthodox.org

ቅዱሳን ጾምን በጠንካራ ምሽግ ፣ ጸሎትን ደግሞ በጠንካራ ምሽግ ውስጥ ያለ ሰው በሚያጠቃበት መሣሪያ ይመስሉታል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎት ከጾም ጋር በኅበረት ሲፈጸም እንመለከታለን፡፡

የነነዌ ሰዎች ጾም ፣ የአስቴር ጾም እና አይሁድ ከጥፋት ለመዳን የጾሙት ጾም ሁሉ ከጸሎት ጋር ነበር፡፡ ዮና.፪ አስቴር ፬-፫ ያገኙት መልስና ውጤቱም ጾም ከጸሎት ጋር ያለው አንድነት ማሳያ ነው፡፡

## ጾምና ምጽዋት አይነጣጠሉም

ጾም ከፍቅርና ቸርነት ጋር የተያያዘ ነውና፣ ጿሚዎች ሲራቡ ለድሆችና የሚበሉት ለሌላቸው በጾም የተዉትን ምግብ እና ሌላም ለነዳያን የሚያስፈልገውን ይመውታሉ። እግዚአብሔርም ለነብዩ ለኢሳይያስ *"እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን?.... እንጀራህን ለተራብ ትቆርስ ዘንድ÷ ስደቶኞችን ድሆችን ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ፤የተራቆተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፤ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን? የዚያን ጊዜ ብርሃን እንደ ንጋት ይበራል÷ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል÷ ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል÷ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ይጠብቅሃል።"* /ኢሳይ.፶፰÷፮-፰/

## ማጠቃለያ

ጾምና ጸሎት ራስን መግዛትን ለማዳበርና ለመንፈሳዊ እድገት የሚያስፈልጉ፣ የማይነጣጠሉ ተግባራዊ አምልኮቶች እና የጽድቅ መሣሪያዎች ናቸው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሊሆነን ጾሟል። እኛም ምሳሌውን ተከትለን መንፈሳዊ መሣሪያዎችንን ልንታጠቅ ይገባል።

## ተግባር

♣ የጾም ፈተናዎች እንዴት እንደሚታለፉ ተወያዩ።

**ጥያቄዎች፡-**

1. ጾም ማለት ምን ማለት ነው? ከትርጉሙ ጋር ምንነቱንና አፈጻጸሙን አብራሩ።
2. በብሉይ ኪዳን በጾም መንፈሳዊ ሥራ ከሠሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ሦስቱን በመጥቀስ አብራሩ።
3. ሁዳዴ በመባል የሚታወቀውን ዐቢይ ጾም የምንጾመው ለምንድነው?

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ቄርሎስ

# ሃያ አንደኛ ሳምንት

***የትምህርቱ ዓላማ፡-*** *ተማሪዎች የቅዱስ ቄርሎስን ታሪክ ያውቃሉ፤ ከሕይወቱና ሥራዎቹ ቤተ ክርስቲያንን ስለመጠበቅ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡*

***የሚጠና ጥቅስ፡-*** ***"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።"*** የሐዋ.፳፥፳፰፡፡

***ተጨማሪ ምንባባት፡-*** ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንታሪክ ከልደት እስከ ፳፻ ዓ.ም/ ገጽ 178፤ Patrology: Father Tadros Malaty. ‹‹ሃይማኖተ አበው፤››

## መግቢያ፡-

ከ375(8)— 444 ዓ.ም የኖረው ቅዱስ ቄርሎስ፡- ዓምደ ሃይማኖት ፤ ቅዱስ ፤ ሊቅ ፤ የቤተ ክርስቲያን ጠበቃ በሚሉት ቅጽል ስያሜዎች በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ይጠራል፡፡ ቤተ ክርቲያናችንም ***የዓለም መምህር*** ትለዋለች፡፡ ይህ የአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አባት ቅዱስ ቄርሎስ ከአይሁድ፣ ከአረማውያንና ከመናፍቃን ጋር የታገለ የሃይማኖት አባት ነው፡፡

የኤፌሶን ጉባኤ ሰብሳቢ እርሱ ነበር፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ የነገረ መለኮት ትምህርት ታላቅ ሊቅ ሲሆን፤ የቤተ ክርስቲያንን ቃላት ያዳበረ ምሁርም ነበር፡፡ ከዕውቀቱ ጎን በቅድስናውም የተመሰከረለት አባት ነው፡፡

በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መሰደድ፣ በፈላስፋዋ ሂፓቲያ ሞት እና በኤፌሶን ጉባኤ አካሄድ አወዛጋቢ ታሪኮች ምክንያት ከተለያዩ ወገኖች ጥያቄዎች ይነሣሉ፡፡ ለመሆኑ ቅዱስ ቄርሎስ ማነው ? …..እኛስ ከታሪኩ ምን እንማራለን? የሚሉትን ነጥቦች ይህ ትምህርት የሚዳስሳቸው ጉዳዮች አድርገን መርጠናቸዋል፡፡ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተዋልና ጥበብን ይስጠን አሜን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

ስሙ፡-በግሪክ እና ኮፕት ኪሪሊዮስ፣ሲሪል፣በግእዝ ቄርሎስ ተብሎ ይጠራል፤ መምህር(አለቃ)

ማለት ነው፡፡

## ትውልድ እና እድገቱ

ቀድሞ ቴዎዶስየስ ተብላ በምትጠራ ፤ በዛሬዋ ኢል መኻላ ኢል ኩብራ በተባለችው ከተማ አካባቢ በግብጽ ተወለደ:: እናቱ በልጅነቱ ሞተች፡፡ አጎቱ (የእናቱ ወንድም) ቴዎፍሎስ አሳደገው፡፡ ቴዎፍሎስ በእስክንድርያ የነበረ ካህን ሲሆን በኋላ ፓትርያርክ ሆኗል፡፡

ከዐሥራ ሁለት እስከ ዐሥራ አራት ዓመቱ የቋንቋ አገባብ ተማረ፤ እስከ ሃያ ዓመቱ የዘመኑን የንግግር ጥበብ አጠና፡፡ ከዚያም ለአምስት ዓመታት በግብጽ ገዳማት በገዳማዊ ሕይወት ኖረ፡፡ በዚያም በርካታ መጻሕፍትን አንብቧል፡፡

## አገልግሎቱ

ቄርሎስ ጥሩ አንባቢ እና አስተማሪ ነበር፡፡ ይህን የሚያውቀው አጎቱ ወደ እስክንድርያ አስመጣው:: በዚያም በንባብ እና በትምህርት ማገልገል ጀመረ፡፡ በእውቀቱ እና በንጽሕናው የሚደሰትበት አጎቱ -ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ክህነት ሰጠው፡፡ በአገልግሎቱም በርትቶ ማስተማር ቀጠለ፡፡

## የኦክ ጉባኤ

በ፬፻፪(402) ዓ.ም በኦክ የተደረገው ጉባኤ ታላቅ ስሕተት የተሠራበት ጉባኤ ነበር፡፡ ቄርሎስ ከአጎቱ ጋር እስክንድርያን ወክለው ተገኙ፡፡ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ በስሕተትና በሐሰት ግዝት ካስተላለፉት ጋር ተባበረ፡፡ ይህም የቴዎፍሎስ ያልተገባ ድርጊትና በንግሥቲቱ ተጽዕኖ ነበር፡፡ ሆኖም ቅዱስ ቄርሎስ ፬፻፲፯(በ417)ዓ.ም ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቅድስና መዓርግ በመስጠት ስሕተቱን አርሟል፡፡

## ፕትርክና

ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ በ፬፻፲፪(412) ዓ.ም ሞተ፡፡ በወቅቱ በእስክንድርያ የነበረው ትውፊት አዲስ ፓትርያርክ የሚሾመው በኃላፊው ፓትርያርክ ኑዛዜ መሠረት ነው፡፡ የነበረው ፓትርያርክ እከሌን ሹሙት ብሎ ከመሞቱ በፊት ይናዘዛል፡፡ ያንን አባት ይሾሙታል፡፡ በዚህ መሰረት ፓትርያርክ ቴዋፍሎስ ቄርሎስ እንዲተካው ተናዞ ነበር፡፡ እርሱ ጥቅምት ፲፭ ቀን ዐርፎ ቅዱስ ቄርሎስ ጥቅምት ፲፰ ቀን ተተካ፡፡

የቅዱስ ቄርሎስ ዘመነ ፕትርክና የመጀመሪያዎቹ ሥራዎች በእስክንድርያ ከገነኑት አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ጋር መታገል ነበር፡፡ እነዚህም በዋናነት ሦስት ነበሩ፡-

www.zeorthodox.org

*1. ኖቫቲስቶች*

ከ፪፻፶(250) ዓ.ም ጀምሮ የነበረው የሮም ጳጳስ በመፍራት ለጣዖት የሠዉ ክርስቲያኖችን ተቀበለ፡፡ ይህን ኖቫቲና ተከታዮቹ ተቃወሙት፡፡ የዚህ እንቅስቃሴ ተከታዮች መሪያቸው ኖቫቲ በሰማዕትነት ሲሞት ወደ ተለያየ ቦታ ተሰደዱ፡፡ ዋና መነኻርያቸውም እስክንድርያ ነበረች፡፡ የንስሐን ትምህርትና የእግዚአብሔርን መሐሪነት የዘነጉ ናቸው፡፡ በቴዎፍሎስ ዘመነ ፓትርክና በቸልታ የታለፉ ሲሆን በቄርሎስ ዘመነ ፓትርክና ዋነኛ ኃይሎች ሆነው ወጡ፡፡ የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን አቋቋሙ፡፡ ይህ ድርጊት ቤተ ክርስቲያንን የሚከፋፍል በመሆኑ ቄርሎስ አጥብቆ ተቃውሞ፡፡ ቤተ ክርስቲያናቸውን ዘጋው፡፡

*2. አይሁድ*

ከታላቁ እስክንድር ዘመን ፫፻፴(330 ዓ.ዓ ቅልክ) ጀምሮ አይሁድ በእስክንድርያ ይኖሩ ነበሩ፡፡ በዘመነ ክርስትናም በተለይም በ፸(70) ዓ.ም ኢየሩሳሌም በጥጦስ ባድማ ስትሆን ፤ ከአይሁድ ዋና መነኻሪያዎች አንድዋ እስክንድርያ ነበረች፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ በፓትርክና እንደተቀመጠ ክርስትናን በበጎ የማይመለከቱት አይሁድ ከክርስቲያኖች ጋር የነበራቸው አለመግባባት አይሎ ክርስቲያኖችን መግደል እና አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠል ጀመሩ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ድርጊቶቻቸው በትዕግሥት ታለፉ፡፡ ቄርሎስ የአይሁድን ስሕተት በትምህርት ብቻ ለማረም ሞከረ፡፡ ሆኖም የአይሁድ ጭፍን ጉዞ እየባሰ መጣ፡፡ አደጋው በማየሉም አይሁድ ከእስክንድርያ እንዲወጡ ተደረገ፡፡

*3. አረማዊነት*

ጣዖት አምልኮንና የግሪክን (በተለይም ኒዎ ፕላቶኒዝምን) መሠረት ያደረገ ትምህርት እና አምልኮ በእስክንድርያ ነበር፡፡ እነዚህም ሰይጣናዊ አምልኮ ፣ ኮከብ ቆጠራ እና የመሳሰሉትን ሕዝቡን በማለማመድ እና በማስፈጸም የታወቁ ነበሩ፡፡ ከእነዚህም የኒዮ ፕላቶኒዝም ፣ የሒሳብ ፣ ኮከብ ቆጠራ  መምህርት የነበረችው ሂፓቲያ ከ፫፻፶-፬፻፲፭(350-415) ዓ.ም ትጠቀሳለች፡፡ ይህች ሴት በሮም ሕግ የተከለከለውን ጣዖት አምልኮ ከመፈጸምዋም ባሻገር የከተማዋን ገዥ (ኦሬተስ) በመምከር ከፓትርያርክ ቄርሎስ ጋር አጋጪቻቸው፡፡ ይህ ነገር በሕዝቡ ዘንድ ሲሰማ ከፍተኛ ቁጣ ቀሰቀሰ፡፡ ጴጥሮስ በተባለ አናጉንስጢስ መሪነት በዐቢይ ጾም የተነሣው ሁከት ሂፓትያን በጥንታዊው የጣዖት ማምለኪያ በመግደል ተጠናቀቀ፡፡ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መዛግብት እንደሚጠቁሙት ቄርሎስ በቁጣ የተነሣሣውንና በግድያ የተፈጸመውን ኢ ክርስቲያናዊ ድርጊት ተቃውሞ ነበር፡፡ ሆኖም ከእርሱ ፈቃድ ውጪ በሕዝባዊ ቁጣ ተመርቶ ድርጊቱ ተፈጸመ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ቄርሎስ አረማዊነትን የታገለው በጽሑፍ እና በትምህርት ነበር፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ በገዳማዊ ሕይወቱ በብዛት ካነበባቸው መጻሕፍት አንዱ የቀጳዶቅያ አበው ጽሑፎች (በተለይም

የቅዱስ ባስልዮስን) ነበር፡፡ በተቃራኒውም የአሕዛብን ፍልስፍናም አጥንቷል፡፡ በዚህ መሠረት ከቀጰዶቂያ አባቶች ጋር ወደ ውዝግብ የገባውና አረማዊነትን ለመመለስ ጥሮ ያልተሳካለት ንጉሥ ጁልያን ከ፫፻፷፩-፫፻፷፫(361-363)ዓ.ም አረማዊነትን ደግፎ ክርስትናን ተቃውሞ ያስጻፋቸው ሦስት መጻሕፍት ነበሩት፡፡ እነኚህ መጻሕፍት ለማንሰራራት ለሚጥረው አረማዊነት ማጣቀሻዎች ነበሩ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ለእነዚህ መጻሕፍት በምክንያታዊ አቀራረብ የመለሰባቸው ሠላሳ ክፍል ያለው መጽሐፍ ጽፏል፡፡

እነዚህ የቅዱስ ቄርሎስ የመጀመሪያዎቹ የዘመነ ፓትርክና ፈተናዎች ነበሩ፡፡ የቅዱስ ቄርሎስን ስም በዓለም አብያተ ክስቲያናት ታሪክ ያገነነው የኤፌሶን ጉባኤ ነው፡፡ ይሄንን ለመረዳት የሚከተሉትን ታሪካዊ ሂደቶች ማየት ያስፈልጋል፡-

**መንበረ ቁስጥንጥንያ፡፡** በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመን እንደ አዲስ በተቋቋመችው ከተማ ቁስጥንጥንያ ንስጥሮስ ተሾመ ፡፡ በምንኩስናው ሕይወቱ የተመሰገነው ንስጥሮስ በቁስጥንጥያ ተሹሞ ጥቂት እንደቆየ ‹‹እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ***ወላዲተ አምላክ*** አትባልም›› የሚለውን ትምህርት ደግፎ አ ስተማረ፡፡ በዚህ ምክንያት ከቁስጥንጥያ ክርስቲያኖች ተቃውሞ ተነሣ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ይህንን ተቃውሞ ለንስጥሮስ ሁለት የጽሑፍ መልእክቶች ላከ፡፡ የሮሙ ፓትርያርክ ሲላስቲን ፣ የአንጾኪያው ወዳጁ ዮሐንስ ቢመክሩትም ንስጥሮስ ስሕተቱን አልተቀበለም፡፡ ይህ ውዝግብ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሆነና ንጉሡም ገብቶበት በኤፌሶን ጉባዔ ተጠራ፡፡

**ነገረ ክርስቶስ፡፡** ንስጥሮስ ‹‹አምላክ ከሰው አይወለድም፤ ድንግል ማርያም የወለደችው ክርስቶስን ነው እንጂ አምላክን አይደለም›› አለ፡፡ ይህም ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ሁለት አካል አለው ፤ ወደ ሚል መደምደሚያ አደረሰው፡፡ ይህም ሐሳብ ሁለት ባሕርይ (Duaphysis) በሚል ቃል ሲገለጥ አምላክ በሰው አደረበት የሚል ድምዳሜ ላይ አደረሰ ፡፡ ይህን የተቃወሙ የመሰላቸው አንዳንዶችም በተቃራኒው መለኮት ሥጋን፡- ውጦታል መጦታል ሲሉ (Monophysis) የሚለውን ቃል ተጠቀሙ፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ ግን ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ ሆነ ሲል (Miaphisis) የሚለውን ሐሳብ እና እውነተኛ መሠረተ እምነት አቀረበ፡፡ ይህም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እምነት መሆኑ ተረጋገጠ፡፡ የንስጥሮስ ትምህርት በእስክንድርያ ጉባኤ ተወገዘ እና ባለ ዐሥራ ሁለት አንቀጽ ውሳኔ አሳልፎ ለንስጥሮስ ተላከለት ፤ ይህንንም አልተቀበለውም፡፡

www.zoorthodox.org

**ጉባኤ ኤፌሶን፡፡** ይህ ጉባኤ ሦስተኛው ዓለም አቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ይባላል፡፡ ከላይ ያየነውን የንስጥሮስን የተሳሳተ ትምህርት ያወገዘ ጉባኤ ነው፡፡

ከጉባኤው በኋላ የነበረው ከንስጥሮስ ተከታዮች ፣ ከሐሳቡ ደጋፊዎች እና ቄርሎስን በጉባኤው

ምክንያት ከሚቃወሙት ጋር የተደረገ ትግል ነበር፡፡ በተለይም አንጾኪያውያን በብርቱ ተቃውሞ በቄርሎስ ላይ ተነሥተው ነበር፡፡ እርሱም በቃል እና በጽሑፍ መልሶአል፡፡ ከእነኚህም የአንጾኪያው ዮሐንስ የቄርሎስን ሐሳብ ተቀብሎ በ፬፻፴፫(433) ዓ.ም ደብዳቤ ጽፎለታል፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ በተከታዮቹ እና በንስጥሮሳውያኑ ያለው ትግል በክፉ ቢተረጎምበትም፤ እርሱ ግን፡- ***"ሰላምን እወዳለሁ ጠብና ግጭትን እጠላለሁ ሁሉንም ሰው እወዳለሁ ያለኝን ሀብትና ንብረት ሁሉ ለወንድሜ ሰጥቼ ቁስሉን መፈወስን ብችል በደስታና ያለማቅማማት አደርገው ነበር፡፡ ነገር ግን እምነት እና በጎ ምግባርን በተመለከተ .... የምንወደው ከሆነ ከክፋት ጋር እንዴት ተስማምተን መቀጠል እንችላለን? እኔም እምነትን የሚጎዳ ማንኛውንም ነገር ያለማጉረምረም እቀበላለሁ ....የንስጥሮስ ፍቅር በእኔ ዘንድ ምሉዕ ነው፡፡ እኔ የምወደውን ያህል ንስጥሮስን የሚወድ የለም፡፡ እንደ ክርስቶስ ትእዛዝ .......እውነትን ለመናገር ከፈራን ለነፍሳችንም ለሥጋችንም ደኅንነትን አያመጣልንም"*** አለ፡፡

## ሥራዎቹ

ቅዱስ ቄርሎስ በርካታ ጽሑፎችን ያዘጋጀ ምሁር የቤተ ክርስቲያን አባት (ፓትርያርክ) ነው፡፡ በወቅቱ ሁኔታ መነሻነትና በአባትነቱ በርካታ መጻሕፍትን አዘጋጅቷል፡፡ መጻሐፍቱን እንደሚከተለው መድበን እናያቸዋለን፡-

**ለቤተ ክርስቲያን ጥብቅና የቆመባቸው መጻሕፍት፡-** ለጁልያን ሦስት ጸረ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ጽፎ ነበር ፤ ቄርሎስ መልስ የሆኑ ሠላሳ መጻሕፍትን አዘጋጅቷል፡፡

**ትርጓሜ መጻሕፍት፡-** አብዛኛዎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በእስክንድርያ ትምህርት ቤት የትርጉም መንገድ ተርጉሟቸዋል፡፡

**በዶግማ ጉዳዮች ላይ ለተነሡ ክርክሮች የተሰጡ መልሶች፡-** በቅድስት ሥላሴ ፤ በክርስቶስ ባሕርይ (ሁለት አካል፣ ሁለት ባሕርይ ለሚለው የንስጥሮስ ኑፋቄ)፣ በእመቤታችን የአምላክ እናትነት ላይ ......... ለሚነሡ ክርክሮች መልስ የሰጠባቸው መጻሕፍት አሉ፡፡

**መልእክታት እና ስብከቶቹም፡-** በልዩ ልዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የተጻፉ ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ከእነዚህም መጻሕፍት መካከል የነገረ ሃይማኖት ትምህርቶቹ በተጻፉበት ክፍለ ዘመን ፣ በዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል፡፡ ለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያን ከአራቱ የመጽሐፍ ቤት ትምህርቶች በሊቃውንት ዝርዝር የቅዱስ ቄርሎስን መጽሐፍ በትርጓሜ ቤት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ አስገብታ የምታስተምረው፡፡

በመጨረሻም ቅዱስ ቄርሎስ በ፬፻፵፬(444) ዓ.ም ዐረፈ፡፡

*ምን እንማራለን*

1. *ራስን በትምህርትና በዕውቀት ለአገልግሎት ማዘጋጀት፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ በቀጥተኛ ትምህርት ፣ በንባብ እና እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጠው በመለመን በእውቀት አድጎ በተሻለ ግንዘቤም መጥቆ የተገኘ አባት ነበር፡፡ እውቀት በቀጥተኛው የትምህርት መስክና በግል ጥረት በንባብም ይገኛል፡፡*
2. *ጽናት፡፡ ቄርሎስ የተካው ቴዎፍሎስን ነው፡፡ ቴዎፍሎስ ደግሞ ለእስክንድርያ የበላይነት ሲል የማይገቡ ነገሮችን የፈጸመ ነው፤ በሌላው አቅጣጫ አንጾኪያ እና የእስክንድርያ ልዩነት አለ፡፡ ይሕ ሁሉ የተዛባ ዕይታ እና ትርጉም የሚያሰጥበት ቢሆንም ቅዱስ ቄርሎስ ስሕተቱን በስሕተትነት ከመቃወምና እውነቱን ከመግለጥ አላደከመው ነበር፡፡ እንዲያውም በጽናት ገፋበት፡፡ ቢዘገይም ሰዎች እውነቱን መረዳታቸው አልቀረም፡፡ እኛም ስለ እውነተኛው ትምህርት የምናደርገውን ትግል አውቀው በሚያጣምሙ፣ ባልገባቸው እና የተለየ ዓላማ ባላቸው ተቃውሞ ሲደርስብን እንዳንዝል ያስተምረናል፡፡*
3. *ራስን ማረም፡፡ ብዙዎችን የሚያርሙ ሰዎች ለራሳቸው ጊዜ አይሰጡም፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ከዚህ በተለየ መልኩ የሠራቸውን ቀደምት ስሕተቶች በሚገባ አርሞአል፡፡ ለምሳሌ ቄርሎስ ቴዎፍሎስን ተከትሎ በኦኩ ጉባኤ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ለማውገዝ ቢገኝም በኋላ ይህንን ስሕተቱን ተረድቶ ስሕተቱን በማረም ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቅድስና መዓርግ ሰጥቷል፡፡ እኛም በሰዎች ወይም በራሳችን የምንሠራቸው ስሕተቶች ይኖራሉ፡፡ በጊዜ ማረም አስተዋይነት ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፦* ***"ስለዚህ እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፤ ነፋስን እንደሚጎስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም ፤ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ፡፡"*** *፩ኛ ቆሮ.፱፥፳፮-፳፯* ***"እንደተገለጠልኝም ወጣሁ ምናልባትም በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም ሮጬ እንዳልሆን...ዋኖች መስለው ለሚታዩ....አስታወቅኋቸው፡፡"*** ገላ.፪፥፪
4. *በቀናው መንገድ ለማረም መጣር፡፡ ቄርሎስ ከአገረ ገዢው አሪተስ ፣ ከንስጥሮስ እና ከሌሎች ጋር በነበረው ትግል አግባብነት ያላቸውን መንገዶች ተጠቅሞ ሌሎችን ለማረም ጥረት አድርጓል፡፡ በአካል እና በደብዳቤ በመጠየቅ ሲጀምር ከዚያም ለማረም በጥብአት ሲጓዝ አይተነዋል፡፡ ሌሎችን ለማረም በምናደረገው ጉዞ መንፈሳዊው እና ሕጋዊውን መንገድ መከተል እውነትም ብልህትም ነው፡፡*

www.zoorthodox.org

## ማጠቃለያ

ከ፫፻፸፭-፬፻፵፬(375-444) ዓ.ም የነበረው ቅዱስ ቄርሎስ የነገረ መለኮት ምሁር ፣ የቤተ ክርስቲያን ጠበቃ ፣የእውነት መምህርም ነበር፡፡

## ተግባር

♣ ለትምህርትና ለአገልግሎት ትኩረት ስጡ፡፡

በእግዚአብሔር የተጠሩና የልጁን የጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን አርአያዊ መልክ በኑሮና በቃል መስለው የኖሩትን ቅዱስ የሚል የግብር ስያሜ በቤተ ክርስቲያን ይሰጣል፡፡ በዚህ መሠረትም ቅዱስ ቄርሎስ በጥንታውያን ኦርቶዶክስ ፣ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ እና በሮም ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ቅዱስ ተብሎአል፡፡ /ሮሜ.፰፥፳፱-፴/

ኦሬተስ በወቅቱ የግብጽ ሀገረ ገዥ የነበረ የአውግስጦስ ቄሳር እንደራሴ ነው፡፡ ከቅዱስ ቄርሎስ ጋር የነበረው አለ መግባባት የጀመረው ቄርሎስ እንደ ተሾመ ነው፡፡ በተለይም በኖቫቲስቶች እና በአይሁድ የወሰደው እርምጃ የርሱን ሥልጣን እንደመጋፋት አስቆጥሮበት ነበር ፡፡ ይህ ልዩነት የጎላው አይሁድ በከተማዋ ታላቅ ስብሰባ ሲያደርጉ እና ኦሪስተስ ለዐዋጅ ሲቀመጥ የቅዱስ ቄርሎስ የቅርብ ሰው በምስጢር ለመታዘብ መገኘቱ አይሁድን ሲያስቆጣ ኦሪስተስ እንደ ሥልጣን ማሳያ በአደባባይ አስገረፈው፡፡ አይሁድም በቁጣ ክርስቲያኖችን ገደሉ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ገዳዮቹ ወይም አይሁድ ከእስክንድርያ እንዲወጡ ጠየቀ፡፡ ኦሪስተስ በነገሩ ስላልተስማማ ከንጥርያ ገዳም የመጡ መነኮሳት እና ክርስቲያኖች ኦሪስተስን ተቃወሙ፡፡ በዚህ መካከል አሞንዮስ የተባለ መነኩሴ የወረወራት ድንጋይ ኦሪስተስን ክፉኛ አቆሰለችው፡፡ ኦሪስተስም መነኩሴውን አስገደለ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ የመነኩሴውን አስከሬን በቤተ ክርስቲያን በማስቀመጥ እና ከሰማዕታት ዝርዝር በመቁጠሩ በኦሪስተስ እና በቅዱስ ቄርሎስ መካከል ያለው ልዩነት ሰፋ በመጨረሻም ሁለቱም የየራሳቸውን ደብዳቤ ለቴዎዶስዮስ ፪ኛ ጻፉ፡፡ የሂፓቲያ ሚና ተብሎ የታሪክ ሰነዶች የሚያነሡት ይህንን ልዩነት ተጠቅማ ኦሪስተስን ጸረ ቤተ ክርስቲያን ምክር መምከርዋ ነው፡፡

www.zoorthodox.org

**ጥያቄዎች፡-**

1. ‹‹ቄርሎስ›› የሚለውን ስም ትርጉም ግለጽ፤ ቅዱስ ቄርሎስ የተወለደው በየት ሀገር ነው? ያሳደገው ማን ነው?
2. ቅዱስ ቄርሎስ የማን ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ነበር ? ቅዱስ ቄርሎስ በሰብሳቢነት

የመራው ታላቅ ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ምን ይባላል? ይህ ጉባኤ የተካኼደበት ምክንያት ምን ነበር? በጉባኤው ስለተላለፈው ውሳኔ አብራሩ፡፡

3. ቅዱስ ቄርሎስ በዘመነ ፓትርክናው የመጀመሪያ ጊዜያት ያጋጠሙት ዋና ዋና ፈተናዎች እና ስለአደረጋቸው ትግሎች ሦስቱን በመጥቀስ አብራሩ፡፡
4. ቅዱስ ቄርሎስ ያረፈበት ዘመን መቼ ነው?

www.zeorthodox.org

# ሰዓታት

# ሃያ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ሰዓታት ጸሎት ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እነሆ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ፥ በአምላካችን ቤት አደባባዮች የምትቆሙ እናንተ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁላችሁ፤ በሌሊት በቤተ መቅደስ ውስጥ እጆቻችሁን አንሡ፥ እግዚአብሔርንም ባርኩ።"*** መዝ.፻፴፫(፻፴፬)፩-፪፡፡

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፤ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም

**መግቢያ፡-** እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምላክዋን የምታመልክባቸውና የምታመሰግንባቸው የማኅበር ጸሎቶች፣ ምሥጋናዎች፣ አጽዋማትና በዓላት አሉ፡፡ ከእነዚህም ማሕሌት፣ ቅዳሴ፣ ንግሥ፣ የሰርክና የነግሕ ጸሎት የምንላቸው ይገኙበታል፡፡ ሰዓታትም ቤተ ክርስቲያን ለአምላክዋ የምታቀርበው ምሥጋና፣ ጸሎትና ምልጃ ያለበት የጸሎት ዓይነት ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለ ሰዓታት አጀማመርና ይዘት እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**ስያሜው**

‹‹ሰዓታት›› የሚለው ቃል በየሰዓቱ የሚደረስ ማለት ነው፡፡ ሃያ አራቱን ሰዓታት ከፋፍሎ ለጸሎት የሚያዘው መጽሐፍ ያለው ይዘትም ይህንኑ ያመለክተናል፡፡ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም (Horologium, Hours, Oris የሚባሉ) ለተመሳሳይ አገልግሎት የሚውሉ መጻሕፍት አሉ፡፡

www.zeorthodox.org

በኢትዮጵያ ሰዓታት የሚባሉ ሁለት መጻሕፍት አሉ፡፡ አንዱ ከውጭ የተተረጎመ ሲሆን ሁለተኛው በሀገር ውስጥ የተደረሰ ነው፡፡ በየገዳማት እና አድባራቱ አገልግሎት የሚሰጠው መጽሐፍ በሀገራችን ሊቃውንትና ቅዱሳን አበው የተደረሰ ነው፡፡

የመዓልትና የሌሊት ሰዓታት የሚባሉ ሁለት ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ በኋላ የታወቀውና በብዛት የሚደረሰውም የሌሊት የሰዓታት ጸሎት ነው፡፡ ይህ ጸሎት በብዙ ገዳማትና አድባራት በዐቢይ ጾምና ፣ በፍልሰታ እንዲሁም በጥቂት ገዳማትና አድባራት ከዓመት እስከ ዓመት ሳይቋረጥ ሰዓታት

ይቆማል፡፡

**መቼና እንዴት ተጀመረ ?**

ሰዓታት በዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው፡፡ ሆኖም በረጅሙ የሰዓታት ጸሎት የሚደረሱ አንዳንድ ክፍሎች በሌሎች ሊቃውንት የተደረሱም አሉበት፡፡

ከአአትብ ጀምሮ እስከ ሚካኤል ሊቀ መላእክት መጨረሻ ድረስ ያለው የአባ ጊዮርጊስ ድርሰት ነው፡፡ ከኖኀ ሐመሩ ጀምሮ ያለው በየጊዜው በሌሎች የተደረሰ ነው፡፡ ለኖኀ ሐመሩን ፣ የእመቤታችንን ሰብሐተ ፍቁር ፣ ተፈሥሒ ማርያምን ፣ ለአዳም ፋሲካሁ ፣ አ ርጎርጎተ ሕሊናን ዐፄ ልብነ ድንግል ደርሰውታል፡፡ የቅዱሳንና የመላእክት ስብሐተ ፍቁርም በየጊዜው እየተደረሰ የተጨመረ ነው፡፡

የሰዓታት ድርሰት በግጥም መልክ የተዘጋጀ ግሩም መጽሐፍ ነው፡፡

**የሰዓታቱ ክፍል**

የሌሊት ሰዓታት ክፍል ሦስት ነው፡፡ ይኸውም፡-

1ኛ/ አአትብ ወእትነሣአ

2ኛ/ ሚካኤል ሊቀ መላእክት

3ኛ/ ለኖኀ ሐመሩ ነው፡፡

መስተብቁእ በየ ምዕራፉ እየተገባ ይጸለያል፡፡ በዚህ ክፍል ለነጋድያን ፣ ለገበሬ ፣ ለመንገደኞች ፣ ለሕሙማን ፣ ለነገሥታት ፣ ለሙታን ፣ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች ለምእመናን ይጸለይበታል፡፡

መጽሐፈ ሰዓታት በግእዝ፣ በዕዝልና በአራራይ ተቀላቅሎ የተዘጋጀ ዜማ ሲሆን፤ የሚበዛው አራራይ ዜማ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን የምሥጋና መንገድ አብዝቶ ያሳያል፡፡ ያመሰግናልም፡፡ እመቤታችንን በሰፊው ሌሎች ቅዱሳንንም በአማላጅነታቸው በመማጸን ያመሰግናል፡፡

ከሰዓታት በኋላ ተአምራት ከነመርገፎቻቸው ተብሎ ፤ ኪዳን ይደርሳል፡፡ ይህ መንፈስን ማራኪ የሆነ ድርሰት ከስድስት ክፍለ ዘመናት በላይ አስቆጥሯል፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

በሀገራችን ቤተ ክርስቲያን ያለው ሰዓታት በአባ ጊዮርጊስ ተዘጋጀ፡፡ ለእግዚአብሔር የአምልኮ ምሥጋና ለቅዱሳን የጸጋ እና የሚገባቸውን ምሥጋና ያቀርባል፡፡ ጸሎትና ተማጽኖም ያቀርባል፡፡

## ተግባር፡-

ከቤተሰብ ጋር በመመካከር ሰዓታት ተሳተፉ።

☸ መምህር መጽሐፈ ሰዓታት አምጥተው ይዘቱንና አከፋፈሉን ለተማሪዎች ያሳዩአቸው።

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ቅድስት ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን ከምታመልክባቸው እና ከምታመሰግንባቸው የማኅበር ጸሎቶችና ምሥጋናዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ግለጹ።
2. ‹‹ሰዓታት›› ማለት ምን ማለት ነው? ስለዓይነቱና አገልግሎቱ ምንነት አብራሩ።
3. ሰዓታት በስንት ይከፈላል? በስፋት የሚታወቀውና በብዛት የሚደርሰው የትኛው የሰዓታት ጸሎት ነው?
4. በሀገር ውስጥ የተደረሰው እና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የዋለውን መጽሐፈ ሰዓታት አብዛኛውን ክፍል ያዘጋጀው ማነው?
5. የሌሊት ሰዓታት ክፍሎች ስንት ናቸው? አብራሩ።

www.zeorthodox.org

# ምስጢረ ሥላሴ

# ሃያ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ ፡-** ተማሪዎች የእግዚአብሔርን አንድነት እና ሦስትነት ምስጢር ያውቃሉ፤ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" እኔና አብ አንድ ነን "*** ዮሐ.፲÷፴

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ.፫÷፲፮-፲፯፣፳፰ኛ ቆሮ.፲፫÷፲፬

**መግቢያ፡-** በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ከመሠረተ እምነቶች የመጀመሪያው ምስጢረ ሥላሴ ነው፡፡ ሥላሴ ሦስትነት ማለት ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔር በአካል ፣ በስም እና በግብር ያለውን ሦስትነት የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችን እነዚህን እንመለከታለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### የእግዚአብሔር አንድነት፡-

እግዚአብሔር አንድ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት የምናምነው በአንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ብዙ አማልክት የሉንም ፤ ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ ***" ነአምን በአሐዱ አምላክ -በአንድ አምላክ እናምናለን "*** ስትል ትመሰክራለች፡፡ ***"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ"*** ብለን ስናጠናቅቅም ***" አሐዱ አምላክ - አንድ አምላክ አሜን "*** የምንለውም አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር አንድ መሆኑን ለመመስከር ነው፡፡ የቅድስት ሥላሴ አንድነት በምንድነው ?

1. **በመለኮት** (በአገዛዝ) አንድ ነው፡፡ ሦስቱም ልዩነት በሌለው መለኮታዊ አንድነት ፈጥረው ይገዛሉ፡፡
2. **በሥልጣን** የአብ የሆነ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ያልሆነ ሥልጣን የለም፡፡ ለዚህ እንደ ምሳሌ የክርስቶስ ትንሣኤ ያለውን አንድነት እንይ፡፡ ጌታችን ስለ ትንሣኤው ከመሞቱ በፊት ሞቶ እንደሚነሣ ሲገልጥ ***"እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፡፡ ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ፡፡"*** አለ፡፡ ዮሐ.፲÷፲፰ በሌላም ቦታ አብ አስነሣው ተብሎ ለማለት ***"እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነሣው"*** በሐዋ ሥ. ፬÷፲ ተብሎአል፡፡መንፈስ ቅዱስ አስነሣውም ተብሎም ተጽፎአል፡፡ ***"ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ"*** ሮሜ

www.zeorthodox.org

፰÷፲፩ ከዚህም የሥልጣናቸውን አንድነት እናስተውላለን፡፡

3. **በፈቃድ፡-** በአብ ልብነት አስበው በወልድ ቃልነት የሚናገሩ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት የሚኖሩ ናቸው፡፡ የአንዱ የሆነ የሌላው ያልሆነ ፈቃድ የለም፡፡ ለዚህም ክርስቶስ ***"የላከኝን ፈቃድ ልፈጽም መጥቻለሁ፡፡"*** ዮሐ.፮÷፴፯ ያለው በዚህም መሠረት በመፍጠር፣ ፍጥረቱን በመመገብ እና በማሳለፍም አንዲት ፈቃድ፣ሥልጣን እና አገዛዝ አላቸው እንጂ፡፡
4. **በሕልውና፡-** (መኖር ማለት ነው፡፡) የሰማይና የምድርን ሕልውና በቅድስት ፈቃዳቸው በጽንኢት ሥልጣናቸው የሰጡ ቅድስት ሥላሴ፤ ከጊዜ በፊት የነበሩ ሕያዋን ዓለምን አሳልፈው የሚኖሩ ዘላለማውያን ናቸው፡፡ በዚህ መሠረትም አንዱ ከሌላው ተለይቶ የነበሩበት ጊዜ አልነበረም፤ አይኖርምም፡፡ ***"ከአብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርኩ፡፡"*** ዮሐ.፰፥፶፰

ከዚሁም ጋር አብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሕልው ነው፡፡ ወልድም በአብ እና በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስም በአብ እና በወልድ ህልው ነው፡፡ አንዳቸው በሌላቸው ይኖራሉ፡፡ "እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ ፡፡ " ዮሐ ፲፬÷፲

የተለያየ ህልውና ወይም አኗኗር አለ፡፡ ቅዱስ አውግስቲን ግኡዝ ፍጥረታት፣ ከዕፀዋት፣ ዕፀዋት ከእንስሳት፣እንስሳት ከሰው፣ሰው ከመላእክት በህልውና እንደሚለያዩ ፣ የእግዚአሔርም ህልውና ከእነዚህ የረቀቀ ነው ይላል፡፡

በዚህና በመሳሰሉት እግዚአብሔር አንድ ነው፡፡ በቅዳሴ ማርያምም ***"ሦስቱ ስም አንዱ እግዚአብሔር ነው"*** ቁጥር ፶፬፡፡ አማልክቶቻቸው ብዙ የሆኑ በጣዖት እንደሚያመልኩ አረማወያን.... ከአንድ በላይ አማልክት እንደሚያመለኩ ሦስት አማልክት አንልም፡፡ ***"መለኮት ግን አብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስም ነው፡፡ አንድ አምላክ አንዲት መንግሥት አንዲት ሥልጣን አንዲት አገዛዝ ነው"*** እግዚአብሔር በመመለክ፣በሥልጣን ፣ በአገዛዝ በፍቃድም አንድ ነው፡፡

አንድ ገጽ አንድ አካል ብለው እንደሚያምኑት እና የእግዚአብሔርን አንድነት እንደካዱትም በገጽ በስም እና በግብርም አንድ ነው ብለን አናምንም፡፡ አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ ነው፡፡ ብለን እናምናለን፡፡ በሰይጣን ተንኮል እንዳንሳሳት የሚጠነቀቅልን እግዚአብሔር ሦስትነቱ በመጽሐፍ ፣ በፍጥረታት እና በተሰጠን አእምሮ እንድንረዳ አድርጎአል፡፡

www.zeorthodox.org

## የእግዚአብሔርን ሦስትነት የሚያስረዱ ጥቅሶች፡-

- ***"የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች ÷ የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ ፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች ፡፡"*** መዝ ፻፲፯(፻፲፰)÷፲፭-፲፮
- ***"እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም÷እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም÷***

***እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ ሰላምንም ይስጥህ፡፡"*** ዘኁል. ፮÷፳፬-፳፮ ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር ማለቱ ሦስትነትን ለመግለጥ ነው፡፡

- ***" የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ÷የእግዚአብሔርም ፍቅር ÷የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችንም ጋር ይሁን፡፡"*** ፪ኛ ቆሮ ፲፫÷፲፬ ብሎ ቅዱስ ጳውሎስም ሦስትነት አስተምሮዋል፡፡
- ***"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር"*** ኢሳይ. ፮÷፫ ሦስት ጊዜ ቅዱስ ማለቱም ለአብ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡
- ***"መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይምጣል ÷የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፡፡ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡"*** ሉቃ ፩÷፴፭ ወልድን ***የእግዚአብሔር ልጅ*** ብሎ ÷ መንፈስ ቅዱስ ብሎ ሦስተኛውን አካል ÷**ልዑል** ብሎ አብን እየጠቀሰ ቅዱስ ገብርኤል አስተምሮዋል፡፡

**የቅድስት ሥላሴን አንድነት እና ሦስትነት የሚያስረዱ ምሳሌዎች፡-**

1. **ሰው፡-** ሰው በነፍሱ ሦስትነት አለው፡፡ ልብነት(ዕውቀት)፣ ቃልነት(ተናጋሪነት) እስትንፋስነት(ሕያውነት )፤ ሰው ሲፈጠር ሦስቱም አብረው ተሰጥተውታል፤ አይቀዳደሙም፡፡ሥላሴም በአብ ልብነት ያስባሉ፣በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ይኖራሉ፡፡ ሰው እግዚአብሔርን በዚህ ስለሚመስለውም የፈጠረው እግዚአብሔር ***" ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር አለ፡፡"*** ዘፍ ፩÷፳፮
2. **ፀሐይ እና እሳት፡-** ሁለቱም ሙቀት፣ አካል እና ብርሃንነት አላቸው፡፡ በአንዱ እግዚአብሔርም ሦስትነት አለ፡፡ ነገር ግን ሦስት እሳት ሦስት ፀሐይ እንደማንል እግዚአብሔርም በግብር፣በአካል እና በስም ሦስትነት አለው፤ ነገር ግን አንድ እግዚአብሔር ነው፡፡
3. **አቶም (Atom)፡-** አንድ አቶም (Atom) ኒውትሮን (neutron) ፣ ፕሩቶን (proton) ፣ ኤሌክትሮን (electron) አሉት፡፡ ሦስቱም በዓይን አይታዩም፡፡ ኃይል ሲሰጡ ግን ያታወቃሉ፡፡ ስለ እግዚአብሔር አንድነት ሦስትነት የማንማረውንም በዚህ ምሳሌነት መረዳት እንችላለን፡፡ በአንዱ እግዚአብሔር ሦስትነት አለ፤ እግዚአብሔርንም በፍጥረቱ እና በሥራው እናውቀዋለን እንጂ በሥጋ ዐይናችን አናየውም፡፡ የነዚህ ሁሉ ምሳሌነት ምሉዕ መገለጫ ሆነው÷ሳይሆን አባቶቻችን "ምሳሌ ዘየሐጽጽ-ጐዶሎ ምሳሌ" እንደሚሉት ለእኛ ለማስረዳት የተመሰሉ ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

1. የምናመልከው አባታችን እግዚአብሔር አንድ ነው፡፡ አንድነቱም በመለኮት በሥልጣን በፍቃድ እና በህልውና ነው ፡፡ እንዲሁም ሦስትነቱ በአካል፣በግብር እና በስም ነው፡፡
2. በአብ ልብነት ያስባሉ ፤ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፤በመንፈስ ቅዱስ ሕያዋን ይሆናሉ፡፡

## ተግባር

- ✎ የተሰጡአችሁን ጥቅሶች አንብቡ፡፡
- ✎ ያልገባችሁን ከመምህራን ጠይቁ እርስ በእርስም ተወያዩ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት፤ ከመሠረተ እምነቶች የመጀመሪያው ‹‹ምስጢረ ሥላሴ›› የሚያመለክተው ምንድ ነው?
2. አምላካችን እግዚአብሔር አንድ መሆኑን ለመመስከር ምን እንላለን?
3. የቅድስት ሥላሴ አንድነት በምን ይገለጣል? ሦስትነቱስ? አብራሩ፡፡
4. የእግዚብሔርን ሦስትነት የሚያስረዱ ጥቅሶችን ከመጽሐፍ ቅዱስ በተማራችሁት መሠረት እየጠቀሳችሁ ግለጹ፡፡
5. የቅድስት ሥላሴን አንድነት እና ሦስትነት የሚያስረዱ (የተሟሉ መገለጫ እና ምሳሌዎች ባይሆኑም) ምሳሌዎቹን በማቅረብ አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ልባሞቹና ሰነፎቹ ደናግል

# ሃያ አራተኛ ሳምንት

*ዓላማ፡-* ተማሪዎች ስለ የመንፈሳዊ ሕይወት ዝግጁነት፣ እምነትና መልካም ሥራ አስፈላጊነት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

የሚጠና ጥቅስ፡-*"ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት"* /ማቴ.፳፭፥፵፩/

## መግቢያ፡-

ምሳሌ ቀለል ተደርጎና መልእክት ለማስተላለፍ የሚቀርብ የማስተማሪያ የማመላከቻ መንገድ /ዘዴ/ ነው፡፡ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ምሳሌዎችን ለደቀ መዛሙርቱ በደብረ ዘይት ነግሮአቸዋል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም አንዱን እናያለን፡፡ ከነዚህ ምሳሌነት በኋላም ጌታችን ስለምጽአትና ስለ ፍርድ ቀን ነግሮአቸዋል፡፡ በክብሩ ሲገለጥም በሕያዋንና በሙታን ይፈርዳል፡፡

## ትምህርቱ

መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ አሥር ቆነጃጅትን ትመስላለች፡፡ ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች አምስቱም ልባሞች ነበሩ፡፡ ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙም ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ይዘዋል፡፡ ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉም አንቀላፉ /ተኙ/፡፡ እኩለ ሌሊትም ሲሆን፤ እነሆ ሙሽራው ይመጣል፣ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ፤ የሚል ሁካታ ሆነ፡፡ በዚያን ጊዜም ቆነጃጅቱ ሁሉ ተነሡና መብራታቸውን አዘጋጁ፡፡

ሰነፎቹም ልባሞቹን፡- ‹‹*መብራታችን ሊጠፋብን ነው፤ ከዘይታችሁ ስጡን*›› አሉአቸው፡፡

ልባሞቹ ግን፡- ‹‹*ምናልባት ለእናንተና ለእኛ ባይበቃስ፤ ይልቅስ ሄዳችሁ ግዙ*›› አሉአቸው፡፡

ሰነፎቹ ሊገዙ በሄዱ ጊዜ ሙሽራው መጣ፡፡ አስቀድመው ለመብራታቸው ዘይት የያዙትና የተዘጋጁት ገቡ፣ ደጁም ተዘጋ፡፡ ከረፈደ በኋላ ዘይት ሊገዙ የሄዱት ሰነፎች ተመልሰው መጥተው ***ክፈትልን*** አሉ፡፡እርሱ ግን ***"እውነት እላችኋለሁ፣ አላውቃችሁም"*** አለ፡፡

***ስለዚህ ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ፡፡***

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ከዚህ ምሳሌ የሚከተለውን እንማራለን፡፡

### ዝግጁነት

ከአምስቱ ልባሞች ደናግላን በመጨረሻው ሰዓት የምናገኘውን ዕድል እንዳናጣ በተሰጠን ጊዜና ዕድል በመጠቀም አስቀድመን መዘጋጀት እንዳለብን እንማራለን፡፡ ሰነፎቹ ከሙሽራው ጋር ያልገቡት ተጨማሪ ዘይት ይዘው ስላልተዘጋጁ ነበር፡፡ ይህ ምሳሌ ጌታችን በመግቢያው እንደነገረን የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው፡፡

- ሙሽራው ክርስቶስ ነው፡፡
- ልባሞቹ ደናግላን በቅድስና፣ ሕገ እግዚአብሔርን በመጠበቅና፣ እርሱን በማምለክ፣ ችግረኞችን፣ በመርዳትም የሚኖሩ ቅዱሳን ምሳሌ ናቸው፡፡
- ሰነፎቹ ቆነጃጅትም የቅድስና ኑሮ የሌላቸውና ለእግዚአብሔር መንግሥት ራሳቸውን ያላዘጋጁ ናቸው፡፡
- የሙሽራው መምጣትም የጌታ ዳግም ምጽአት ነው፡፡
- መብራቱ እምነት ዘይቱ የምግባራቸው ምሳሌ ነው፡፡

ከዚህ በኋላም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ ሲመጣ ምን እንደሚደረግ ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሮአቸዋል፡፡ ***"እናንተ የአባቴ ብሩካን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፤ ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታሥሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና፡፡....እውነት እላችኋላሁ፣ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ ስንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል፡፡"***

በግራው ያሉትንም ደግሞ ***"እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ሂዱ፡፡ ተርቤ አላበላችሁኝምና፣ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና ፣ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና ፣ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፣ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና...እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል፡፡"***

www.zeorthodox.org

ለሰነፎቹ ሴቶች እንዳላቸውም እነዚህንም ***"አላውቃችሁም"*** ብሏቸዋል፡፡ ጌታ ዳግም ሲመጣ የሚክዳቸው አሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በእምነት ከመልካም ምግባርና ሥራ ጋር በመኖር የመንግሥቱ ወራሾች ለመሆን መዘጋጀት አለብን፡፡ ክርስቶስ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፤ እንደሚለንና ሲፈጥረንም የመንግሥቱ ወራሾች ሊያደርገን እንደሆነም ያስረዳናል ፡፡ በዚህ ካልኖርን ግን 'ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ የዘላላም እሳት'

እንኄዳለን ፡፡

## ማጠቃለያ

ክርስትና የተስፋ ሃይማኖት ነው፡፡ በዚህ ምድር በተሰጠን ጊዜና ዕድል ተጠቅመን በሃይማኖታችን ጸንተን በመልካም ሥራ ተግተን አስቀድመን ከተዘጋጀን ከዘላለማዊ ፍርድ እንድናለን፡፡ ተማሪዎች እንደ ልባሞቹ ደናግላን ሁሌም የተዘጋጃችሁ ሁኑ፡፡

## ተግባር

የተሰጡትን ጥቅሶች ከቤተሰብ ጋር አንብቡ፡፡

## ጥያቄዎች

1. አምስቱ ጎበዞች ደናግላን የተባሉት ለምንድ ነው? የማን ምሳሌ ናቸው?
2. አምስቱ ሰነፎች የተባሉትስ ለምንድ ነው? የማን ምሳሌ ናቸው? አብራሩ፡፡
3. አምስቱ ሰነፎች ከሙሽራው ጋር ያልገቡበት ምክንያት ምንድ ነው?
4. ሙሽራው ማን ነው? የሙሽራው መምጣት ማለት ምንድ ነው?
5. መብራቱ የምን፣ ዘይቱስ የምን ምሳሌዎች ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ገብር ኄር
# ሃያ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች፤ እግዚአብሔር ስለ ሰጠን ጸጋዎች (ተሰጥዖ) ይገነዘባሉ፤ በተሰጣቸው ጸጋ (ተሰጥዖ) ስለመጠቀም ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት የመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-"ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ፡፡"** ፪ኛ ጢሞ ፪፥፩

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ማቴ. ፳፭፥፲፬-፴

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ጌታችን ስለ ዳግም ምጽአቱ በተለያዩ ምሳሌዎች ማስተማሩን አይተናል፡፡ ከነዚህ ምሳሌዎች ስለ ታማኞች እና ሰነፍ ባርያዎች መስሎ ያስተማረው ይገኝበታል፡፡ ማቴ.፳፭፥፲፬-፴፡፡ ይህ አንቀጽ በቤተ ክርስቲያን ***"ገብር ኄር"*** ተብሎ ሲታወቅ፤ የዐቢይ ጾም ስድስተኛ ሳምንት ነው፡፡

ገብር ኄር - ታማኝ አገልጋይ ማለት ሲሆን፤እግዚአብሔርን በመታመን ስለማገልገል በተሰጠን ተሰጥዖ ተጠቅመን ውጤታማ ስለ መሆንና በታማኝነት በማገልገል ስለሚገኘው ክብርና ዋጋ እንማርበታለን፡፡

## የትምህርቱ መገለጫ

ጌታችን ስለ አንድ ባለ ጠጋና ባሮቹ ምሳሌ አስተማረ፡፡ ወደ ሌላ አገር የሚሄድ አንድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ ለእያንዳንዱ እንደየአቅሙ፤ ለአንዱ አምስት፣ ለአንዱም ሁለት፣ ለአንዱም አንድ መክሊት ሰጠና ሄደ፡፡ ባለ አምስቱ ሄዶ ነገደና አምስት ፣ ባለ ሁሉቱም ሁለት አተረፉ፡፡ ባለአንዱ ግን የተሰጠውን ቆፍሮ ቀበረው፡፡

www.zoorthodox.org

ከብዙ ዘመንም በኋላ ለእነዚያ ባሮች ጌታ የሰጣቸውን ሊቆጣጠር መጣ፡፡ ባለአምስቱና ባለ ሁለቱ ጌታቸው በሰጣቸው መክሊት ሠርተውበት ያተረፉትን ይዘው ሲቀርቡ፤ ባለ አንዱ ግን ጌታዬ ጨካኝ ነው ብሎ እንደፈራና የሰጠኝን መክሊት ምንም ሳላደርግ ባስቀምጠው ይሻላል ብሎ እንደቀበረውም ነገረው፡፡

ጌታቸውም ያተረፉትን እያንዳንዳቸውን ***"መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል***

***በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ"*** አለ፡፡

እንዲሠራበትና አትርፎ እንዲጠብቅ የተሰጠው መክሊት ሳይሠራበት የቀበረውንም ***"አንተ ክፉና ሃኬተኛ እኔ ካልዘራሁበት እንደማጭድ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፣ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር፡፡ ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት ዐሥር መክሊትም ላለው ስጡት"*** አለ፡፡ ሰነፉን አገልጋይ ወደ ውጪ አውጥተው እንዲጥሉትም አዘዘ፡፡ ***በዚያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል***፡፡

ይህ ምሳሌ ጌታችን ስለ ዳግም ምጽአቱ ሲያስተምር የተናገረው ነው፡፡ ምሳሌነቱም የባለጠጋው የክርስቶስ፤ ባሮችም ጌታችን በሰጣቸው ጸጋ፣ ዕውቀት፣ ሀብት፣ መንፈሳዊ በረከቶች የተጠቀሙና ያልተጠቀሙ ሰዎች ምሳሌ ነው፡፡

## ከዚህም ምን እንማራለን?

ጌታችን ሲመጣ ለእያንዳንዳችን የሰጠንን ጸጋ ተጠቅመን በሚገባ የሠራንበትን መልካም ነገር እንደሚቀበለንና እንዲሚጠይቀን ለዚህም መዘጋጀት እንደሚገባን እንማራለን፡፡

## ማጠቃለያ

ማድረግ የሚገባንን በጠቅላላው እንዲህ ከተገነዘብን የምንፈጽምባቸውን መንገዶች እንይ ፦

1. **እግዚአብሔር የተለያዩ ስጦታዎችን ሰጥቶናል፡፡** በተፈጥሮ የተሰጠን ዕውቀት፣በጥምቀትና ሜሮን የተቀበልነው ጸጋ፣ የምንቆርብባትና የምንማርባት ቤተ ክርስቲያን፣ ካህናትና መምህራን፣ የሚወዱንና የሚንከባከቡን ቤተሰቦቻችንና ወዳጆቻችንን መልካም ምክራቸውን ከሰማናቸውና በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው ከእግዚአብሔር የተሰጡን ስጦታዎች /መክሊቶችም/ ናቸው፡፡ በመጽሐፍ ***"ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ፡፡"*** ፪ኛ ጢሞ ፪÷፩
2. **ተሰጥዎቻችንን እንጠቀምባቸው፤** ከላይ የተጠቀሱትን እና ዕውቀታችንን፣ ተሰጥዖዎቻችንን በአግባቡ ተጠቅመን፣ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወታችንን በቀና መንገድ ብንመራና ብናሳድግ እግዚአብሔር ***"አንተ ታማኝ በሰላም ወደ ጌታህ ደስታ ግባ"*** ይለናል፡፡ በበለጠውም ይሾመናል÷ያከብረናልም፡፡
3. **ጌታችን *ሥራችንን* ሊመዝን የሚመጣበት ጊዜ አለ፡፡** ***"ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው፡፡"*** ማቴ. ፳፭÷፲፱ ተብሎ እንደተመሰለ ሁሉንም ስለሥራው ዋጋ ሊሰጥ ጌታችን ይመጣል፡፡ ***"እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፡፡"*** ራዕ. ፳፪÷፲፰ እንዲል፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የሚታይ፣ የሚመሰገንም ሥራ ልንሠራና ዋጋችንን ጌታችን እንደሚከፍለን አምነን

www.zeorthodox.org

ልንሠማራ ይገባል፡፡

4. እግዚአብሔር በሰጠን ጊዜ በዕድሜአችን በአግባቡ ከሠራንበት፣ ከተማርን፣ ለቤተሰባችን ከታዘዝንና ከተመረቅን በእግዚአብሔር ፊትም በእውነትና በትጋት ካገለገልን በነገው ሕይወታችን *"በጥቂት ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ፡፡"* ማቴ. ፳፭÷፳፩ እና ፳፫ በማለት እንደሚባርከንና ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሀገር እና ለሕዝብ ጠቃሚ ሰው እንደሚያደርገንም መገንዘብ አለብን፡፡
5. **ታዛዥነት** ሌላው ከዚህ ምሳሌ የምንማረው መታዘዝን ነው፡፡ ሁለቱ ሰዎች የጌታቸውን ትእዛዝ አክብረው በተሰጣቸው መክሊት ሠርተው ሲያተርፉ ሦስተኛው ግን የተሰጠውን ትእዛዝ ሳይፈጽም መክሊቱን ቀብሮ ከመቆየቱም በላይ በስንፍናው ጌታውን የወቀሰ ነው፡፡ ይሄም የማይታዘዙ እንቢተኛ ልጆችን ይመስላል፡፡ ካለመታዘዝ በቅንነት ወደ መታዘዝ እንድንመጣ፤ በትሕትና የተባልነውንና የተማርነውን ወደ መፈጸም እንድንመለስ ያስተምረናል፡፡

# ተግባር

1. የሰንፍና ምክንያቶችን አስወግዱ፡፡
2. ታዛዦች ሁኑ፡፡
3. የተሰጣችሁንና ያላችሁን በረከት እወቁ! እግዚአብሔርን አመስግኑበት! አድንቁ! ተጠቀሙበትም፡፡

**መዝሙር**

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ይጠብቀኛል
በዕረፍት ውኃ በለምለም መስክ እኔን ይመራኛል፡፡

www.zeorthodox.org

ጥያቄዎች፡-

1. ጌታ ‹‹ አንተ በጎ ታማኝ ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ›› የተባሉት አገልጋዮች ባለ ስንት መክሊቶቹ ናቸው? እንዲህ የተባረኩት የተመሰገኑት ምን ስለአደረጉ ነው?
2. መክሊቱ እንዲወሰድበት እና ወደ ውጪ እንዲጣል የተፈረደበት የተቀጣው አገልጋይ በምን ምክንያት ነው?
3. እግዚአብሔር የሰጠን(ጸጋ) ስጦታዎችን ዘርዝሩ፡፡

# ሆሣዕና በአርያም

# ሃያ ስድስተኛ ሳምንት

ዓላማ፡- ተማሪዎች ቤተ ክርስቲያናችን የምታከብራቸው ሆሳዕና እና ሰሙነ ሕማማት ምንነት፣ ታሪክና አፈጻጸም ያውቃሉ፤ በዚህ መሠረትነት በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ስለመኖር ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

የሚጠና ጥቅስ፡- *‹‹ ሆሳዕና በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው፡፡››* ዮሐ.፲፪÷፲፫

## መግቢያ

ሆሳዕና መድኃኒት ማለት ነው፡፡ ከኒቆዲሞስ ረቡዕ እስከ እሑድ ያሉት ቀናት በቤተ ክርስቲያን የሆሳዕና መዝሙር እና ምንባብ የሚሰማባቸው ፤ ትምህርትም የሚሰጥባቸው ቀናት ናቸው፡፡

ጌታችን ዓለምን ለማዳን ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ÷ ሕፃናትና አዋቂዎች የዘመሩት ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ይታሰባል፡፡ አራቱ ወንጌላውያንም ይሄንኑ ታሪክ ጽፈውልናል /ማቴ.፳፩÷፩-፲፯፣ማር.፲፩÷፲-፩፣ ሉቃ.፲፱÷፳፰-፵ ዮሐ.፲፪÷፲፪-፲፱/፡፡ ይህን የሆሳዕና ቀን *‹‹ከፋሲካ በፊት ስድስተኛው ቀን››* /ዮሐ.፲፪÷፩/ ብሎ ዮሐንስ ገልጦታል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን አባቶችም ይሄንኑ የወንጌል ቃል በሚገባ አጥንተው በዓሉን በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሠርተውልናል፡፡

ጌታችን አልአዛርን ከሙታን ካስነሣ በኋላ የአይሁድ አለቆች በከፍተኛ ቅናት ሊገድሉት ፈልገዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ እየተማከሩ ሳለ ነው ጌታችን ረቡዕ አልዓዛርን አስነሥቶት እሑድ እየሩሳሌም የገባው፡፡ ዮሐ.፲፩÷፵፫-፶፯ ሕዝቡና ሕፃናት ግን የዓለሙን ንጉሥና መድኃኒት በክብር ተቀብለውታል፡፡

www.zeorthodox.org

➯ በዛሬው ትምህርታችንም በዚሁ በዓል ተመሥርተን እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአይሁድ በዓለ ፋሲካ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ በከተማይቱ በዓል ለማክበር የተሰበሰበው ሕዝብ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱን ሰምቶ ሊቀበለው ወጣ፡፡

## ሆሳዕና

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳም ከመውጣቱ በፊትም ሁለት ደቀ መዛሙርቱን « ***በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ÷ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ። ማንም እንዳች ቢላችሁ፡-ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ወዲውም ይሰዳቸዋል።*** » ማቴ. ፳፩÷፪-፫

ደቀ መዛሙርቱ እንደታዘዙት ሄደው አህያዋንና ውርንጫዋን አገኙ። ፈትተው ሲመጡም የአህዮቹ ጌታ በጠየቃቸው ጊዜ ጌታ መፈለጉን ነግረውት ሰደዳቸው። ጌታችን በውርንጫይቱ (በአህያዋ ግልገል ላይ) ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ። ሕዝቡ ልብሳቸውን የዘንባባ ዝንጣፊና የሌሎች ዛፎች ቅርንጫፍ(ቅጠል) እየቆረጡ መንገድ ላይ በማንጠፍ ተቀበሉት።

ሕፃናትም «***ሆሳዕና በአርያም በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው።*** » እያሉ ዘመሩ። ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ ጌታችንና መድኃኒታችን የመረጣቸው ቅዱሳን ሐዋርያት የሆነውን በመጀመሪያ አላስተዋሉም ነበር። በኋላ ግን ነቢያት ቀድመው ተንብየው እንደነበርና ያም መፈጸሙን አስተዋሉ።

መዝሙረኛው ነቢዩ ዳዊት « ***ከሕፃናትና ከሚጠቡ አፍ ምሥጋናን ለራስን አዘጋጅህ*** »መዝ. ፰÷፪ ሲል ቀድሞ ተንብዮ ነበር። በነቢዩ ዘካርያስም «***ለጽዮን ልጅ፦ እነሆ÷ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉኣት*** »ትን. ዘካር. ፱÷፱ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ።

## ሕማማት

ጌታችን ስለእኛ መከራ ተቀብሎ እንዳዳነን የምናስብበት ሰሞን ነው። ***«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።»*** ዮሐ. ፫÷፲፮ ተብሎ እንደተጻፈ። አምላካችን ለእኛ ያለውን ፍጹም ፍቅር የገለጠበትና ያዳነበት ሰሞን ስለሆነ ይሄንኑ ፍቅር በማሰብ በጾም፣በጸሎት በስግደት እናከብረዋለን። ቤተ ክርስቲያናችንም የሐዘን ምልክት የሆኑ ምንጣፎችና መጋረጃ በማድረግ ፍቅሩንና ሕማማቱን በሐዘን ትገልጣለች።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

- ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመጨረሻ ጊዜ የገባበት ሰንበት ከመስቀሉ በፊት ያለችው ሰንበት ናት። የአይሁድ መምህራን ጌታችንን ብዙ ሕዝብ ሲከተለው ስላዩ ቀኑ። ይኽ ቅናትም ሊያድናቸው የመጣውን የዓለም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመስቀል አሳልፎ ለመስጠት አበቃቸው።

- የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ምንም እንኳ መጻሕፍት አዋቂዎች ቢሆኑና ስለክርስቶስ የተባለውን ቢያውቁም ለክብራቸው ሲሉና ቅንዓት ዓይናቸውን አሳውሮት ጌታችንን መቀበልና ማመን አልቻሉም።
- በዚህም የሐሰት ክስ በክርስቶስ ላይ በማቅረብ ዓርብ ዕለት ሰቀሉት። ጌታችን ግን ክሳቸውንና ተንኮላቸውን አውቆ በሞቱና በትንሣኤው ሞትን ይሽር ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ።
- ከሆሳዕና እሑድ በኋላ ያለው ሳምንት ***‹‹ሰሙነ ሕማማት››*** የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራና ሞት መታሰቢያ ቀናት ናቸው።

## ተግባር

- ሆሳዕና የምስጋና በዓል ነው። በቤተ ክርስቲያን ተገኝታችሁ አክብሩ።
- ሆሳዕና የመፈታት በዓል ነው። የንስሐ አባት ጋር መነጋገር ያልጀመራችሁ ወጣቶች የቤተሰብን ንስሐ አባት ወይም ከመምህር ጋር በመነጋገር ንስሐ አባት ያዙ።

**ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር፡-**ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው! እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት ብቻ ለዚህ በቂ ነው። ስለ እኛ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል።***"እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን።"*** ፩ኛ ዮሐ ፬÷፲፱። የፈጠረን እኛ ሳንወደው አስቀድሞ እርሱ ስለወደደን ነው። ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ የፈጠረን በራሱ መልክና ምሳሌ ነው።

እርሱ እኛን የፈጠረን ሁሉንም ነገር ካዘጋጀልን በኋላ ነው።ሰማይ ጣሪያ እንዲሆነን ከፍ ሲያደርግልን ምድርንም በላይዋ ላይ እንድንራመድ ለእኛ አስተካክሎልናል። እርሱ ብርሃንን፣ ውኃን፣ አትክልቶችንና ገነትን አዘጋጅቶልናል። ከዚህ በኋላ እኛን ፈጠረን። በኃጢአት ስንወድቅም የድኅነትን መንገድ አዘጋጅቶልናል። ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ይመሩን ዘንድ ነቢያትን ወደ እኛ ልኮልናል፤ የምናስብበትን ኅሊና ቸሮናል፤ ከዚህ በተጨማሪ አርቀን እናስተውል ዘንድ የሚያስረዳንን የተጻፈ ሕግ ሰጥቶናል።

www.zeorthodox.org

ሥጋን እንዲለብስ ግድ ያለውም የእኛ ፍቅር ነው።እርሱ ይህን የእኛ ሥጋ የለበሰው ሊቀድሰው ነው። እርሱ ስለ እኛ ሲል ሕግን በመቀበል ሰዎች እግዚአብሔርን የመፍራት መልክ እንዲኖራቸው አድርጎ በማቅረብ አባቱ እግዚብሔር አብን አስደስቷል። ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣም ስለ እኛ ሲል ሞቷል።***"ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆነ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤....."*** ፩ኛ ጴጥ.፫÷፲፰።

እርሱ በመስቀል ላይ ሳለ ፍቅርን የሚያድል አምላክ ነበር። እርሱ የዓለሙን ኃጢአት በመሸከም በደሙ አጥቦልናል፣ እርሱ ምንም ኃጢአት ሳይኖርበት ስለ እኛ ኃጢአት ሲል እንደ

ኃጢአተኛ ተቆጥሮአል፡፡ ይህን በማድረጉም በእኛ ፋንታ መላውን ካሣ ከፍሎአል፡፡ ስለ እርሱ *▪... በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው፡፡▪* (ዮሐ.፲፫÷፩) ተብሎ ተጽፎአል፡፡እንዲህም ተብሎ ተጽፎአል፡- *▪ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም፡፡▪*ዮሐ.፲፭÷፲፫፡፡

ስለ ወደደንም እንዲህ ብሎናል፡፡ *▪ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤.... ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፡፡▪*ዮሐ.፲፭÷፲፭ ወንድሞቼ ብሎም ጠርቶናል፡- *▪...በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው፡፡▪*ዕብ.፪÷፲፯፡፡ እኛም የሰማዩ አባት ልጆች ሆነናል፡- *▪የእግዚአብሄር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፤...▪*፩ኛ ዮሐ.፫÷፩፡፡ ፍቅሩን ሊያሳየን ስለ ፈለገም እንዲህ ብሎናል፡- *▪እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡▪*ማቴ ፳፰÷፳ *▪ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡት በዚያ በመካከላቸው እሆለናሁ፡፡▪*ማቴ.፲፰÷፳፡፡ ፍቅሩ በጥበቃው፤በእንክብካቤውና በማንኛውም ነገር ለእኛ በሚያደርገው አመራር ውስጥ ታይቶአል፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ‹‹ሆሳዕና›› ማለት ምን ማለት ነው? በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ስለ ሆሳዕና መዝሙር እና ምንባብ የሚስማባቸው ጊዜያት መቼ ናቸው?
2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ከመውጣቱ በፊት ሁለት ደቀ መዝሙሮቹን ያዘዛቸው ምንድ ነው?
3. ስለ ‹‹ሆሳዕና›› በዓል ታሪክና ሁኔታ በዝርዝር አብራሩ፡፡
4. ሰሙነ ‹‹ሕማማት››ን የምናከብረው ለምንድን ነው እንዴት ይታሰባል?

www.zeorthodox.org

# ትንሣኤ

# ሃያ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚሰጣቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ‹‹አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና እንደተናገረ ተነሥቶልና›› /ማቴ.፳፰፥፭-፮/

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ማቴ.፳፰፥፩-፰፣ ማር፥፲፮፥፩-፰፣ሉቃ፥፳፬፥፩-፲፣ ዮሐ፥፥፩-፲፰

## መግቢያ፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን በሞቱ ሽሮ ተነሥቷል፡፡ ትንሣኤ የዓለም ድኅነትና ተስፋ የተገኘበት ነው፡፡ በየዓመቱ በደማቅ ሁኔታ የሚከበረውና የድኅነታችን ዓዋጅ የተነገረበት ትንሣኤ ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ማወቅ ያለብንን መሠረታዊ ትምህርቶች እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**፩. ከተዘጋ መቃብር - መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ተነሥቷል፡፡**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ተነሣ፡፡ እንደ አልዓዛር መግነዝ ሊፈታለት የመቃብር ድንጋይ ሊንከባለልለት አላስፈለገውም፡፡ የመግነዙ ጨርቅ ተቀምጦ ክርስቶስ ግን በዚያ አልነበረም፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስ ያረጋገጡልን መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል መነሣቱን ነው፡፡ ***"ስምዖን ጴጥሮስም ተከትሎት መጣ ወደ መቃብሩም ገባ፤ የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ፥ደግሞም በራሱ የነበረውን ጨርቅ ለብቻው በአንድ ስፍራ ተጠምጥሞ እንደ ነበረ እንጂ ከተልባ እግሩ ልብስ ጋር ተቀምጦ እንዳልነበረ አየ። በዚያን ጊዜ አስቀድሞ ወደ መቃብር የመጣውም ሌላው ደቀ መዝሙር ደግሞ ገባ፥ አየም፥ አመነም፤"*** ዮሐ.፳፰፥፮-፰

www.zeorthodox.org

መልአኩ ድንጋዩን አንከባሎ መቃብሩን ለቅዱሳት አንስት ሲያሳያቸው ጌታ በመቃብሩ ስፍራ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ጌታችን በመንፈቀ ሌሊት ድንጋይ አንሡልኝ ሳይል ተነሥቶ ነበር፡፡ መልአኩ በታላቅ መናወጥ ድንጋዩን ያንከባለለው፤ ለሴቶቹ የትንሣኤውን ምሥራች ፤ ለሚጠብቁት ወታደሮች የክርስቶስን ግርማ ለማሳየት ነው፡፡ ***"እነሆም፥ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ***

***የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ።ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ። መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው። እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ።"*** ማቴ.28፡2-6

### ፪. ትንሣኤውን በመጀመሪያ ያዩትና ያበሰሩት ሴቶች ናቸው፡፡

ሌሊት ሳይነጋ መግደላዊት ማርያም ወደ መቃብር ስፍራ ሄደች፡፡ ክርስቶስ ግን በመቃብር አልነበረም፡፡ መግደላዊት ማርያም ከሌሎች ሴቶች ጋር ዳግመኛ ስትመለስ ጌታችን በመንፈቀ ሌሊት ከመቃብር ተነሥቶ ነበር፡፡ ይህንኑ ተመለከቱ፡፡ መግደላዊት ማርያም አዝና በመቃብር በር ላይ ቆማ ታለቅስ ነበር፡፡ መላእክትን በክርስቶስ መቃብር ራስጌና ግርጌ ዝቅ ብላ አየች፡፡ እነርሱም ስለምን ታለቅሻለሽ አሉዋት፡፡ እርስዋም ጌታዬን ወስደውታል፤ ወዴት እንዳኖሩት አላውቅም አለች፡፡ ዘወር ስትልም ጌታችን ‹‹ስለምን ታለቅሻለሽ?›› አላት፡፡ እርስዋም ክርስቶስ መሆኑን ሳታውቅ ተመሳሳይ መልስ ሰጠች፡፡ ጌታችን ማርያም ሲላት አወቀችውና እግሩ ስር ወደቀች፡፡ እርሱም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሄዳ ትንሣኤውን እንድታበስር ላካት፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች መግደላዊት ማርያም በፍቅር ፣ በእምነትና በትዕግሥት ጌታዋን ስለፈለገች ከሁሉ ቀድማ የክርስቶስን ትንሣኤ አየች፡፡ ዮሐ.፳÷፲፩-፲፰ ***"ከሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን ማልዶ በተነሣ ጊዜ÷ አስቀድሞ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለመግደላዊት ማርያም ታየ።"*** ማር.፲፮÷፱፡፡

ሴቶችም ወደ መቃብሩ ሥፍራ ተመለከቱ፤ መልአኩ እንደነገራቸውም ጌታችን በዚያ አልነበረም፡፡ ይህን በመስማታቸው እጅግ ተደስተው ሄዱ፡፡ በመንገድም ክርስቶስ ተገለጠላቸው፡፡ መልካሙን የትንሣኤ ዜናም ለደቀ መዛሙርቱ አበሰሩ፡፡

### ፫. ጌታችን በማኅበር ትንሣኤውን የገለጠባቸው ጊዜያት

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በተለያየ መንገድ ተግልጦል፡፡ ክርስቶስ ትንሣኤውን ለአርባ ቀናት በብዙ መንገድ ሲገልጥ ነበር፡፡***"ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው÷ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው"*** /የሐዋ.፩÷፫/ ከእነዚህ መገለጦች የጎላውና በማኅበር የተገለጠው ሦስት ጊዜ ነው፡፡ እነርሱም፡-

ሀ. እሑድ ጠዋት ደቀ መዛሙርቱ በዝግ ቤት ተሰብስበው ሳሉ፡፡(ዮሐ.፳÷፲፱-፳፩)

ለ. በሳምንቱ እሑድ ይህ ዳግማዊ ትንሣኤ የምንለው ነው፡፡ በዚህ ቀን ሐዋርያው ቶማስ አካሉን የዳሰሰበት ዕለት ነው፡፡ (ዮሐ.፳÷፳፮-፳፱)

ሐ. በጥብርያዶስ ባሕር - በቤተ ክርስቲያን አግብዖተ ግብር ይባላል፡፡ (ዮሐ.፳፩÷፩-፳፭)

www.zeorthodox.org

**፬. የክርስቶስ ትንሣኤ የሙታን ትንሣኤ በኩር ነው።**

‹‹በኵር›› ***መጀመሪያ ማለት ነው።*** የትንሣኤያችን በኵር (*መጀመሪያ*) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ***‹‹እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶቹም ይበተኑ የሚጠሉትም ከፊቱ ይሽሹ››*** (*መዝ.፷፯፥፩*) እንደተባለ *መድኃኒታችን* ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና *መቃብርን* ድል አድርጎ እንደሚነሣ በትምህርት ከገለጸ በኋላ በተግባር አሳይቶናል። ***‹‹ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ›› ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ››*** (ዮሐ.፲፥፲፯፲፰) ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ትንሣኤው በቃል አስተምሮ አልቀረም። የትንሣኤያችን በኵር ሆኖ በተግባር ገለጠልን እንጂ ***‹‹ መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው፦ እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስ እንድትሹ አውቃለሁና እንደተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም የተኛበትን ሥፍራ ኑና እዩ››*** (ማቴ.፳፰፥፭) ተብሎ እንደተጻፈ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቶአል። (ማር.፲፮፥፮፤ ሉቃ.፳፬፥፯)

በዚህም የትንሣኤያችን በኵር ሆነ ፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ብኵርና ሲያስተምር ***"አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል።"*** /፩ኛ ቆሮ.፲፭፥፳/ አለ። በሌላም ***ሥፍራ ‹‹ ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና››*** (፩ኛ ተሰ.፬፥፲፬) ተብሎ ተጽፎአል።

ሌሎች ቢነሡ አሥነሺ ይፈልጋሉ። ከተነሡ በኋላም ኖረው ሞተዋል። ክርስቶስ ግን በራሱ ፈቃድና ኃይል ተነሣ፤ዳግመኛ ሞት የሌለበትን ትንሣኤ ተነሥቶ በኩራችን ሆነ።

***የተነሣው በክቡር አካል ነው።***

ልጆች ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ***"ሰማያዊ አካል አለ፥ ምድራዊም አካል አለ፤ ነገር ግን የሰማያዊ አካል ክብር ልዩ ነው፥ የምድራዊም አካል ክብር ልዩ ነው።"*** /፩ኛ ቆሮ.፲፭፥፵/ እንዳለው ሁለት ዓይነት አካላት አሉ። የክብር አካል መብልና መጠጥ አያስፈልገውም። አይራብም÷አይጠማም። በክብር አካል ድካም የለም፣ አይታመምም፤ አይሞትምም፤ ሕያው፣ መንፈሳዊና ክቡር አካል ነው። ፍጥረታዊው አካል ግን ይራባል፣ ይጠማል፣ ይሞታል፣ ኃጢአት ሊሠለጥንበት ይችላል። በዚህ ምድር የምንኖረውና የምንሞተውም በፍጥረታዊው አካል ነው። የምንነሣውም በመንፈሳዊ አካል ነው። ***"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል÷ባለመበስበስ ይነሣል ፤ በውርደት ይዘራል÷ በክብር ይነሣል። በድካም ይዘራል÷ በኃይል ይነሣል ፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።"*** ፩ኛ ቆሮ.፲፭፥፵፬

**ክርስቶስ የተወለደው የእኛን ዓይነት አካል ይዞ ነው። ከኃጢአት በስተቀር እኛን መስሎ**

www.zeorthodox.org

ባሕርያችንን ወረሰ፡-“ ***የሰው ልጅ”*** ተብሎ አዳነን፡፡ እንደ ሰው ከሕፃንነት ጀምሮ በጥቂት አደገ፡፡ (ሉቃ.፩፥፹) ***“ተርቧል”*** (ማቴ.፬፥፪) ተጠምቷል (ዮሐ.፲፱፥፳፰) ደክሞት ያውቃል (ዮሐ.፬፥፮) ተኝቷልም (ማቴ.፰፥፳፬)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣው በክቡር አካል ነው፡፡ በተዘጋ በር መግባት እና ከተዘጋ ቦታ መውጣት፤ የተነሣው በክብር አካል እንደሆነ ግልጽ ማረጋገጫዎች ነው፡፡***“ደጆቹ ተዘግተው ሳለ ”*** ዮሐ. ፳፥፲፱ ና ፳፮ በትንሣኤውም ከታተመ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ወጥቶአል፡፡

እኛ በክብር አካል የምንነሣ ከሆነ÷የክርስቶስ ትንሣኤ ምን ያህል ይልቃል? እኛ የእርሱን ትንሣኤ መስለን በክብር ስለምንነሣበት ግልጥ ትምህርትን የጻፈልን ቅዱስ ጳውሎስ በፊልጵስዮስ መልእክቱ ፫፥፳፩ ላይ እንዲህ ጽፎአል፡፡***“ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል፡፡”***

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ መግነዝ ፍቱልኝ፣ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ተነሥቷል፡፡ የክርስቶስ ትንሣኤ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጠው ለቅዱሳት አንስት በተለይም ለማርያም መግደላዊት ነው፡፡

ክርስቶስ የትንሣኤያችን በኩር ነው፡፡ በእርሱ ትንሣኤ ልቦናና ትንሣኤ ዘለክብር እናገኛለን፡፡***“ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል፡፡”*** (ሮሜ ፰÷፲፩)

ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን የተዋሐደው ክርስቶስ ከኃጢአት በቀር እኛን መስሏል፡፡ የተነሣውም በከበረው አካል ነው፡፡ ክቡር አካል ከፍጥረታዊው አካል በክብር በኃይልና ባለ መሞት ይለያል፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- ስለ ትንሣኤው መሠረታዊ ትምህርቶችን ከመምህራን ጠይቁ፡፡

### ጥያቄዎች

1. የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጠው ለማን ነው? የጌታችንን ትንሣኤ እንድታበስር ወደ ደቀ መዛሙርቱ የተላከችውስ ማን ናት? የላካት ማን ነው?
2. መልአኩ በታላቅ መናወጥ ድንጋዩን ያንከባለለው ለምንድን ነው? ይህንን የሚያስረዳ

ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ በማቅረብ አብራሩ፡፡

3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ (በማኅበር) በተለያየ መንገድ ተገልጦአል፡፡ የተገለጠበትን ጊዜ እና ሁኔታ አብራሩ፡፡
4. የክርስቶስ ትንሣኤ የትንሣኤያችን በኲር (መጀመሪያ) ነው ሲባል ምን ማለት ነው? በጥቅስ ማስረጃ እያቀረባችሁ አብራሩ፡፡
5. ‹‹ የክብር አካል›› እና ‹‹ፍጥረታዊ አካል›› አንድነትና ልዩነት አስረዱ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን - መግቢያ

## ሃያ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን በመግቢያ ደረጃ መሠረታዊ ዕውቀትን ያገኛሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ጥበብ ቤትዋን ሠራች ፥ ሰባቱንም ምሰሶዎችዋን አቆመች፡፡"*** ምሳ. 9፡1

**ምንባባት፡-** ‹‹ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት›› (ሊቀ ጉባኤ አበራ በቀለ)

**መግቢያ፡-** ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚባሉት ረቂቁን (የማይታየውን) የእግዚአብሔር ጸጋ በሚታይ መንፈሳዊ አገልግሎት የምንቀበልባቸው ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ሲሆኑ በቁጥርም ሰባት ናቸው፡፡

የመዳናችን ምስጢር በእምነት ብቻ የሚፈጸም ሳይሆን ቃለ እግዚአብሔርን ሰምቶ በማመን ፣ ቃሉን ሰምቶ በማድረግና ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን በመፈጸም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሠረታዊነትም ቃለ እግዚአብሔር እና ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመዳናችንና ለመቀደሳችን ሲባል ከአንድ ጌታ የተሰጡ ናቸው፡፡

በጠቅላላው ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ሕይወትን የሚያስገኙ ፣ የአገልግሎትና የአንድነትን ጸጋ የሚያሰጡ እና የፈውስ ጸጋ የሚገኝባቸው በመባል በሦስት ምድብ ይከፈላሉ፡፡ ከእነዚህም አራቱ አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸሙ ፣ ሦስቱ ደግሞ በተደጋጋሚ የምንፈጽማቸው ናቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### 1. ጸጋ እና ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን

**"እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና ፤ ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ፡፡"** እንዲል ጸጋ በክርስቶስ ሰው መሆን የተገኘ እና በእርሱ ላመኑት ሁሉ ያለዋጋ የሚሰጥ ስጦታ ነው፡፡ /ዮሐ.፩፥፲፮-፲፯/

የሙሴን ሕግ ያከበረና የጠበቀ በሕይወት እንደሚኖር ተነግሯል፡፡ ነገር ግን ከሰው ወገን የሙሴን ሕግ የጠበቀ ባለመኖሩ ሰው ሁሉ ከሞት ፍርድ አላመለጠም፡፡ ሕግ ሰውን ከኃጢአት የማላቀቅ ኃይል የለውምና፡፡ **"ጻድቅ የለም አንድስ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም ፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል ፥ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል ፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም ፥ አንድስ ስንኳ የለም፡፡ "** /ሮሜ.፫፥፲፩/

www.zeorthodox.org

በክርስቶስ የተገኘው ጸጋ ግን በክርስቶስ ቤዛነት የሚገኝ **የኃጢአት ሥርየትና እርቅ ነው**፡፡ ፍጡር ከፈጣሪ ጋር መታረቁ የመጀመሪያው የጸጋ ውጤት ነው፡፡ /ሉቃ.፲፰፥፲፩-፳፬/ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በኃጢአት ምክንያንት የመጣውን ሞት መደምሰስ ነው፡፡ በክርስቶስ ሞት የተገኘው ጸጋ የዘላለምን ሕይወት ያሰጣል፡፡

ጌታችን ከሰው ልጅ የሚያገኘው ጥቅም ሳይኖር እንዲያውም ሰው የፈጣሪውን ቃል ተላልፎ በመበደሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖ ሳለ እርሱ ግን በዓይነ ምሕረቱ ተመልክቶ የቸርነት ሥራን ማድረጉ አምላካችን ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህ የሚያስደንቀው አምላካዊ የፍቅር ሥራ ሁሉ ጸጋ ይባላል፡፡ ጸጋንም ጸጋ ያሰኘው ከቸሩ እግዚአብሔር ያለ ምንም ዋጋ ለሰዎች ደኅንነት በነፃ የሚሰጥ ስለሆነ ነው፡፡ ከኃጢአት እና ከሞት ድነን ከመንፈሳዊ ልደት እስከ ዘላለማዊ ሕይወት መንግሥተ ሰማያት ድረስ በነፍስ በሥጋ የሚደረግ ረድኤተ እግዚአብሔር ሁሉ ጸጋ ማለት እንደሆነ እናምናለን፡፡

ይህንን በክርስቶስ የመጣውን የጸጋ ስጦታ ሁሉ የምንቀበለው በእምነትና ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም ነው፡፡ ከጌታችን የሚሰጠንን ጸጋ በምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ለመቀበል እንድንችል የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያስፈልገናል፡፡ ***"... በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ፦ ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ፡፡"*** /፩ኛ.ቆሮ.፲፪፥፫/ እንዲል የጸጋን ትርጉም በመከተል የምንገነዘበውና በስጦታ ለመቀበል የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያው ጸጋ እግዚአብሔር ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

በመስቀል ላይ በፈሰሰው የክርስቶስ ደም ማለትም የእግዚአብሔር ጸጋ የሰው ልጆች ኃጢአት ተደምስሶ ዓለም ሁሉ እንደዳነ አምነናል፡፡ ይህ አንድ ጊዜ የተፈጸመው የማዳን ሥራና ጸጋው ለሁሉም ሰው የተሰጠ ቢሆንም ተቀባይ ከሌለ ደግሞ መሰጠቱ ብቻ በቂ አይሆንም፡፡ ስለዚህ ጸጋን ለማግኘት አምኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን መቅረብ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚታደልበት መንገዱ እና የሚገኝበት ቤት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ በዚያ ውስጥ በሚደረገው ጸሎትና በልዩ ልዩ ምስጢራት አማካኝነት ጸጋ ይገኛል፡፡

www.zeorthodox.org

## 2. የምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አከፋፈል

### ሀ. አዲስ ሕይወትን የሚያሰጡ ምስጢራት

በዚህ ምድብ የሚመደቡት ምስጢረ ጥምቀት፣ ምስጢረ ሜሮን እና ምስጢረ ቁርባን ናቸው፡፡ ሰው ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወትን የሚጀምርባቸው እና ክርስቲያናዊ ሕይወትን የሚያስገኙ (ክርስቲያን የሚያሰኙ) በመሆናቸው በዚህ ምድብ ተካተዋል፡፡

እነዚህ ምስጢራት ለአዲስ አማኝ (ለሕፃናት) በአንድ ጊዜ በተከታታይ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ ከመካከላቸውም ምስጢረ ጥምቀትና ምስጢረ ሜሮን አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸሙ ሲሆኑ ፤ ምስጢረ ቁርባን ግን ወደፊት በንስሐ እየታደስን የምንቀበለው ምስጢር ነው፡፡

### ለ. የአገልግሎትና የአንድነትን ጸጋ የሚያሰጡ ምስጢራት

በዚህ ምድብ የሚገኙ ምስጢረ ክህነትና ተክሊል ናቸው፡፡ በዚህ ምድብ መካተታቸውም ከራሳቸው አልፎ ለሌሎች የሚተላለፍ መንፈሳዊ አገልግሎትንና ሓላፊነትን የሚያመለክቱ በመሆናቸው ነው፡፡ ክህነት የሚቀበል ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን መንፈሳዊ አባት ሆኖ ለማስተማርና ምእመናንን ለማገልገል ነው፡፡ የካህን ሓላፊነት በሌሎች መዳን ላይ ያተኮረ ስለሆነ የካህኑ የጽድቅ ሥራ የሚለካው በሚያበረክተው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በመሆኑ ነው፡፡

በተክሊል የሚጋቡ ሁሉ አንዱ ለሌላው የሚያስፈልገውን አገልግሎት የመስጠትና የሥጋና የመንፈስ አንድነታቸውንም የማጽናት ሓላፊነት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ልጆችን የማሳደግና የማስተማርን ተግባርና ሓላፊነት ስለሚወጡ በአንድ ወገን ተመድበዋል፡፡ እነዚህ ሁለቱም ምስጢራት አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡

### ሐ. የፈውስ ጸጋ የሚገኝባቸው ምስጢራት

በዚህ ዓለም ላይ ስንኖር በሚያጋጥሙን ልዩ ልዩ ፈተናዎች ነፍሳችን በኃጢአት ፣ ሥጋችን ደግሞ በደዌ ይያዛሉ፡፡ ስለዚህ ከእነዚህ የነፍስና የሥጋ ደዌያት የሚፈውሱን ምስጢራት፡- ምስጢረ ንስሐ እና ምስጢረ ቀንዲል ከአገልግሎታቸው አንጻር በዚህ ምድብ ተመድበዋል፡፡ ለነፍሳችን ቁስል መዳኛ ምስጢረ ንስሐ ለሥጋችን መዳኛ ደግሞ ምስጢረ ቀንዲል የተዘጋጁልን ሲሆኑ፤ ሁለቱም የሚደገሙ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ጸጋ በክርስቶስ ሰው መሆን የተገኘ እና በእርሱ ላመኑት ሁሉ ያለ ዋጋ የሚሰጥ ስጦታ ነው ፡፡
- የእግዚአብሔር ጸጋ የሚታደልበት መንገዱ እና የሚገኝበት ቤት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡
- ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ሕይወትን የሚያሰጡ ፣ የአገልግሎትና የአንድነትን ጸጋ የሚያሰጡ እና የፈውስ ጸጋ የሚገኝባቸው በመባል በሦስት ይከፈላሉ፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

ሁሉም ምስጢራት የሚፈጸሙልን በካህናት ነው፡፡

ከንስሐ አባታችሁ ጋር ስለምስጢራቱ አፈጻጸም ተወያዩ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ምስጢረ ቤተክርስቲያን ምንድን ናቸው? ቁጥራቸው ምን ያህል ነው በስንት ምድብ እና ምን በመባል ይከፈላሉ?
2. ከምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸሙትን እና በተደጋጋሚ የሚፈጸሙትን ብዛታቸውን እና ማንነታቸውን በመለየት ግለጹ፡፡
3. በክርስቶስ የተገኘው ጸጋ ምንድን ነው? አብራሩ፡፡
4. በክርስቶስ የተገኘውን(የመጣውን) የጸጋ ስጦታ ልንቀበል የምንችለው እንዴት ነው? ጸጋውንስ ለመቀበል ምን ያስፈልገናል?

www.zeorthodox.org

# ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን - ምስጢረ ጥምቀት

# ሃያ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች በምስጢረ ጥምቀት የምናገኘውን መንፈሳዊ ሕይወትና አንድነት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ያልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም"*** /ዮሐ.፫፥፭/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት›› (ሊቀ ጉባኤ አበራ በቀለ)፣ ‹‹ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን›› (ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ)

**የሳምንቱ ትምህርት፡-** **የቃሉ ስያሜ እና ትርጉም፡-** ጥምቀት ‹‹አጥመቀ›› ከሚለው ግሥ የወጣ ነው፡፡ ፍቺውም መንከር ፣ መዝፈቅ ማለት ነው፡፡ መላ አካልን በውኃ ውስጥ በማስገባት የሚፈጸም ነው፡፡ ጥምቀት በደልን ሁሉ የሚደመስስና በመንፈስ ቅዱስ እንደገና እንድንወለድ የሚያደርገን የመጀመሪያው የእምነትና የጸጋ ምስጢር ነው፡፡ ይህም የሚፈጸመው ካህኑ ውኃውን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሲባርከው ነው፡፡ /ማቴ.፳፰፥፲፱/

**ጥምቀት የአዲስ ሕይወት እና የእድገት መጀመሪያ ነው፡፡** አንድ ሰው ሕይወት ለመጀመር መወለድ እንዲሁም ማደግ እንደሚያስፈልገው ፤ በመንፈሳዊ ሕይወታችንም መንፈሳዊ ልደትን የምናገኘው በጥምቀት ነው፡፡ መንፈሳዊ ዕድገትንም በምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን እናገኛለን፡፡ ጥምቀት ለክርስቲያናዊ ሕይወት የመጀመሪያው መግቢያ በር ነው፡፡ በዚህ መግቢያነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ማኅበር ካልተቀላቀልን ሌሎቹን የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት መሳተፍ አይችልም፡፡ ምሥጢረ ጥምቀት ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንን አንድነት የምንጀምርበትን ፣ አዲስ ሕይወትን የሚያሰጥ ፣ ክርስቲያናዊ ሕይወትን የሚያስገኝ ምሥጢር ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ከክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ ጋር መተባበር ነው፡- ***"የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቅምን?...."*** /ሮሜ.፮፥፫/ በእምነትና በጥምቀት ትንሣኤ ልቡናን እናገኛለን፡፡ ስለዚህም ክርስቶስን በሞቱ ከመሰልነው በትንሣኤውም እንመስለዋለን፡፡ /ሮሜ.፮፥፭/ ከክርስቶስ ጋር መሞትና መቀበር ማለት የኃጢአት ፍላጎታችንን መጋደልና መዋጋት ከዓለምም ደስታ መለየት ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ የተጠመቅን ክርስቲያኖች አሮጌውን ሰውነታችንን ማለትም የኃጢአት ሥራችንን ትተን በክርስቶስ እንደ አዲስ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ተወልደን አዲስ ሕይወትን

መኖር ይገባናል፡፡

**የምስጢረ ጥምቀት አመሠራረት፡-** የጥምቀት መሥራች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ አመሠራረቱም በትምህርትና በተግባር ነው፡-

**ሀ. በትምህርት፡-** የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረው አንድነት የሚመሠረተው እንዲሁም ዘላለማዊ መንግሥተ እግዚአብሔርን ለመውረስ የሚችለው በጥምቀት እንደሆነ በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተናግሯል፡፡ ***"ከውኃና ከመንፈስ ያልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም"*** /ዮሐ.፫፥፲፰/ ***"ሂዱና በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዛሙርቴ አድርጉዋቸው......."*** /ማቴ.፳፰፥፲፱/

**ለ. በተግባር፡-** ***" ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ....፡፡"*** /ማቴ. ፫፥፲፫/

**ትንቢት፡-** *ጥምቀት የሚጀመርበትን ዮርዳኖስን ቀድሞ ያየው ዳዊት፡-* ***" ባሕር አየች ሸሸችም ፥ ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ"*** መዝ.፻፲፫(፻፲፬)፥፫ ሲል፤ ሕዝቅኤልም በጥምቀት የምናገኘውን ቀድሞ መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት እንዲህ ብሏል፡- ***"ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ፥ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ፡፡ አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ፡፡ መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም አስሄዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ፡፡"*** ሕዝ.፴፮፥፳፭

**ምሳሌ በብሉይ ኪዳን፡- የሚከተሉት በዘመነ ብሉይ የተፈጸሙ ክሥተቶች ፤ ለሐዲስ ኪዳን እንደ ምሳሌ ነበሩ፡፡ መምህር ያብራሩላቸው፡-**

- የኖኅ መርከብ፡- ፩ኛ ጴጥ.፫፥፳-፳፩፣ ግዝረት፡- ቆላ.፪፥፲፩፣ እስራኤልን ሲመራቸው የነበረው ደመና፡- ፩ኛ ቆሮ.፲፥፩-፪

**የጥምቀት ዓይነቶች፡-** ጥምቀት አንዲት ናት ***"አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት.."*** / ኤፌ.፬፥፬-፭/ የጥምቀት ዓላማና ባሕርይ አንድ ቢሆንም ፤ ሦስት ዓይነት ጥምቀት አለ፡፡

1ኛ. **በመንፈስና በውኃ መጠመቅ፡-** ይህ የልጅነት ጥምቀት የምንለው ነው፡፡

2ኛ. **በመንፈስ ቅዱስና በእሳት የሚሆን ጥምቀት፡-** ሐዋ. ፩፥፭

3ኛ. **የደም ጥምቀት፡-** የክርስትናን ትምህርት በመማር ላይ እንዳሉ ወይም ተምረው አምነው ከመጠመቃቸው በፊት ያለዚያም ሁሉንም ሳያውቁት ባጋጣሚ ምክንያት ክርስቲያኖች በሰማዕትነት ሲያልቁ በማየታቸው ተመስጠው ‹‹የእነዚህ ሰዎች አምላክ እውነት ነው›› ብለው በድንገት በሰማዕትነት የሚሞቱ ሰዎች ደማቸው እንደ ጥምቀት ይሆንላቸዋል፡፡

**የጥምቀት *ዕድሜ*፡-** በቤተ ክርስቲያን ጥንትም ሆነ አሁን የጥምቀት ዕድሜ አልተወሰነም፡፡ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሕጻናትን በአርባ እና በሰማንያ ቀናቸው ጀምሮ ይጠመቃሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ነገር ግን ሕፃኑ ለሞት የሚያሰጋ ከሆነም ፣ በአጋጣሚ ቀናት አሳልፈው ቢመጡ ቤተ ክርስቲያን ወደ እርሷ የመጡትን አትመልስም፡፡ ሕፃናትን ለማስባረክ ወደ ቤተ እግዚአብሔር መውሰድ በብሉይ ኪዳንም የተጠቀሰ ነው፡፡ /ዘጸ.፲፫÷፪/

***የሚታይ አገልግሎት፡-*** የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ጸጋ እግዚአብሔርን የሚያስገኙት በሚታይ አገልግሎት አማካኝነት ነው፡፡ እነዚህ የሚታዩ አገልግሎቶችም የካህናት ጸሎት፣ ቡራኬዎች፣ እንዲሁም ተጠማቂው ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረገ ማጥመቁ ናቸው፡፡

***የማይታይ ጸጋ፡-*** የማይታይ ጸጋ የምንለው በመጠመቃችን የምናገኛቸው መለኮታዊ ጸጋዎች ናቸው፡፡ እንደ ግኡዝ ነገር በአካላዊ ስሜቶቻችን ልናውቃቸው የማንችላቸውንና በእምነትና በቃል ኪዳኑ ተመሥርተን የምቀበላቸውን ነው፡፡ ጥምቀት የክርስትና እምነት ምሥጢር ነው፤ የመዳናችን ጸጋ ነው፡፡ የመዳናችን ምስጢር በክርስቶስ ነው ፤ ጥምቀት ደግሞ ከአዳኛችን ጋር አንድ ያደርገናል፡፡ ከእርሱ ጋር አንድ ከሆንን የመዳንን ጸጋ ከኃጢአት ቁስል የመፈወስን ሀብት እናገኛለን፡፡ ሐዋ.፪÷፴፰ በተጨማሪም፡- ዳግመኛ መወለድ (ዳግም ልደት) ዮሐ.፫÷፫-፭፣ ቲቶ.፫÷፭፤ ድኅነት ማር.፲፮÷፲፮፤ ቅድስና ኤፌ. ፭÷፳፭፣ ገላ.፫÷፳፯ … እናገኛለን፡፡ በእነዚህና በሌሎችም መለኮታዊ ጸጋዎች አማካኝነት ዓለማዊ አስተሳሰባችን ይወገዳል ፣ አዲስ ልቡና እናገኛለን ፣ መንፈሳዊ ሕይወታችን ይጠነክራል፡፡ በዚህና በመሳሰሉት መንገድ በክርስቲያናዊ ሕይወታችን ውስጥ ለውጥ ይታያል፡፡ በጸጋ ውስጥ መሆናችንንም በዚህ እናውቀዋለን፡፡ ***"ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ"*** ብሎናልና፡፡ ማቴ.፯÷፳

**ማጠቃለያ፡-** ጥምቀት ቃሉን በቁሙ ስንፈታው መነከር ማለት ነው፡፡ በጥምቀት የእግዚአብሔርን ልጅነት ሥልጣናችን ይመለስልናል ፣ የኃጢአት ሥርየት እናገኛለን ፣ አዲስ ሕይወትም እንጀምራለን፡፡ ጥምቀት የተመሠረተው በጌታችን በኢየሱስ ሲሆን በዘመነ ብሉይ የተነገሩ ትንቢት እና ምሳሌዎች ነበሩት፡፡

**ተግባር፡-** በጥምቀት ያገኘነውን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የመሆን ጸጋ ከኃጢአት በመራቅ እንጠብቀው፡፡

***ጥያቄዎች፡-*** www.zeorthodox.org

1. ጥምቀት ምንድነው? የሚፈጽመው ማን ነው? እንዴት ይፈጸማል? ጥምቀትን የመሠረተው ማን ነው? አመሠራረቱም በትምህርት እና በተግባር ነው ሲባል ምን ለማለት ነው? አብራሩ፡፡
2. የጥምቀት ዓላማና ባሕርይ አንድ ቢሆንም ሦስት ዓይነት ጥምቀት እንዳለ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንረዳለን፡፡ ምን ምን ናቸው? ግለጹ፡፡
3. ምስጢረ ጥምቀት ሲፈጸም የሚታዩት አገልግሎቶች ምን ምን ናቸው? የምናገኘው የማይታየው ጸጋስ ምን ድነው?

# ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን - ምስጢረ ሜሮን

# ሠላሳኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለምስጢረ ሜሮን ምንነትና አፈጻጸም፤ እንዲሁም በምስጢረ ሜሮን የምናገኘውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያውቃሉ፤ መምህሩ ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስና ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እናንተም ከቅዱሱ ቅብዐት ተቀብላችኋል ሁሉንም ታውቃላችሁ፡፡ …ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ፡፡"*** /፩ኛ ዮሐ.፪፥፳-፳፯/

**ምንባብ፡-** ‹‹ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት›› (ሊቀ ጉባኤ አበራ በቀለ) ፣ ‹‹ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን›› (ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ)

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**የቃሉ ስያሜ እና ትርጕም፡-** ቅብዐ ሜሮን ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና የሚረጋገጥበት የምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን መገልገያና ማስፈጸሚያ ፤ የሀብተ መንፈስ ቅዱስ መስጫ እና መቀበያ ፤ የልጅነት መታወቂያ ዓርማና ማኅተም ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ቅብዐ ሜሮን የአንድ ቤተ ክርስቲያን ሉዐላዊነት መግለጫና የክብር ምልክትም ነው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ሲወጣ መንፈስ ቅዱስ እንደ ወረደና የባሕርይ ልጅ መሆኑ እንደታወቀ ፤ እንዲሁም ተጠማቂዎች ከተጠመቁ በኋላ ሳይውሉ ሳያድሩ በምስጢረ ሜሮን አማካኝነት ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ መወለዳቸው ይረጋገጣል፡፡

www.zeorthodox.org

**የምስጢረ ሜሮን አመሠራረት፡-**

ምስጢረ ሜሮንን የመሠረተ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን የሚሰጥ እርሱ ብቻ ነው፡፡ ዮሐንስ እንደ መሠከረ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ማጥመቅ የሚችለው እርሱ ብቻ ነውና፡፡ /ሉቃ.፫፥፲፮/ ለቅዱሳን ሐዋርያትም የሚያጽናና ጰራቅሊጦስን እንደሚልክላቸው ተስፋ ሰጥቷቸው ነበር፡፡ /ዮሐ.፲፬፥፳፮/ ከዕርገቱ በኋላ በአሥረኛው ቀን በተስፋው መሠረት መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው፡፡ በመንፈስ ቅዱስም አጠመቃቸው፡፡ /ሐዋ.፩፥፭፣፪፥፩-፬/ ዛሬም በምስጢረ ሜሮን ለተጠማቂዎች የሚሰጠው ለሐዋርያት የተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው፡፡

**ሜሮን በብሉይ ኪዳን፡-** በብሉይ ኪዳን በተቀደሰው ቅባት የመቅደሱ ንዋያተ ቅዱሳት እንደሚቀቡና እንደሚከብሩ፣ የተለዩም የተቀደሱ እንደሚሆኑ ተጽፏል፡፡ ***"…የመገናኛውንም ድንኳን የምስክሩን ታቦት ገበታውንም ዕቃውንም… ሁሉንም ትቀድሳቸዋለህ ቅድስተ ቅዱሳንም ይሆናሉ፤ የሚነካቸውም ሁሉ ቅዱስ ይሆናል፡፡"*** /ዘጸ.፴፥፳፪-፴/ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለዩና የተመረጡ ሰዎች በዚህ ቅዱስ ቅብዐት ይከብሩ ነበር፡፡ ***"በክህነትም ያገለግሉኝ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን ቅባቸው ቀድሳቸውም፡፡"*** /ዘጸ.፴፥፴/

**በሐዲስ ኪዳን፡-** ቅዱሳን ሐዋርያት በአንብሮተ እድ (እጅን በመጫን) መንፈስ ቅዱስን ያሳድሩ ነበር፡፡ **"እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ ገና አልወረደም ነበርና፡፡ በዚያ ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ፡፡"** /ሐዋ.፰፥፲፯፣፲፱፥፭-፯/

እንደ ብሉይ ኪዳኑ ቅብዐት ሰዎችን ለእግዚአብሔር የተለዩ፣ ለአገልግሎቱም የተመረጡና የተቀደሱ ብቻ ለማድረግ ሳይሆን ሁሉንም የሚቀድሰው መንፈስ ቅዱስ በሐዲስ ኪዳን ለመሰጠቱም ጭምር ምሳሌነት አለው፡፡ ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ቅዱስ ቅብዐት ሲል አማኞችን የሚቀድሰውና ለአማኞችም የተሰጠው መንፈስ ቅዱስን ያሳያል፡፡ **"እናንተም ከቅዱሱ ቅብዐት ተቀብላችኋል ሁሉንም ታውቃላችሁ፡፡ …ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ፡፡"** ፩ኛ ዮሐ.፪፥፳-፳፯፣ ፩ኛ ቆሮ.፩፥፳፩-፳፪

**የሚታይ አገልግሎት፡-** በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት ከጥምቀት ጋር ተያይዞ የሚፈጸም ነው፡፡ የአቀባቡም ሥርዓት ሕፃን ከሆነ(ከሆነች) በክርስትና አባት (እናት) እቅፍ እንዳለ ነው፡፡ አዋቂ እንደ ሆነ ደግሞ ከመጠመቂያው ወጥቶ ቆሞ ካህኑ በአውራ ጣቱ ***"እቀብዐከ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ"*** እያለ በትእምርተ መስቀል ያትመዋል፡፡ የሚቀቡትም ሕዋሳት፡-

- ግንባሩን፡- አእምሮው የተባረከና ብሩህ እንዲሆን
- ዓይኖቹን፡- ዓይኖቹ የእግዚአብሔርን እውነት እንዲያዩ
- ጆሮዎቹን፡- የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ
- አፍና ከናፍሩን፡- እውነት እንዲናገር፣ የእግዚአብሔርን ጥበብ እንዲማር
- ደረቱን፡- በልቡ ቅን እንዲያስብ፣ ቅን እንዲሆን
- እግሮቹን፡- ለመልካም ሥራ እንዲፋጠኑ
- በጠቅላላ መላ ሰውነቱ የእግዚአብሔር ማደሪያ እንዲሆን ሠላሳ ስድስት ቦታ ይቀባል፡፡

www.zeorthodox.org

በቅብዐ ሜሮን የሚቀደሱ አዳዲስ ክርስቲያኖች ብቻ አይደሉም፤ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ ካለቀ በኋላ፣ ንዋያተ ቅዱሳት አገልግሎት የሚሰጡት በሜሮን ከከበሩ በኋላ ነው። አንድ ጊዜ በሜሮን ከታተሙ በኋላ ተራ ሥጋዊ ተግባር አይሠራባቸውም።

**የማይታይ ጸጋ፡-** ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ስንቀበል አይታይም ፤ በምንሠራው ሥራ ይገለጣል እንጂ። መንፈስ ቅዱስ የተቀበለ ምእመን የመንፈስ ቅዱስ ሀብታት ያድሩበታል። ***"የእግዚአብሔር መንፈስ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ የምክርና የኃይል መንፈስ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል።"*** /ኢሳ.፲፩÷፪/

**ማጠቃለያ፡-** መንፈስ ቅዱስን መቀበል ቀላል ነገር አይደለም። እኛን ለማዳን ክርስቶስ በተቀበለው ሕማምና ሞት የተገኘ ታላቅ ጸጋ ነው። እንዲያው በከንቱ ወይም በአጋጣሚ የመጣ አይደለምና። እንዲህ ካሰብን የእግዚአብሔርን ፍቅርና ውለታ ረሳን ማለት ነው።

**ተግባር፡-** ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ መከረን የዚህን ዓለም አምሮት ወደ ጎን ትተን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወደ ፊት እንገሥግሥ። "**በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ**" /ገላ.፭÷፳፭/

**ጥያቄዎች፡-**

1. ቅብዐ ሜሮን ምንድ ነው?
2. ምስጢረ ሜሮንን የመሠረተ ማን ነው? ምክንያቱ ግለጹ።
3. ስለሜሮን በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን አፈጻጸሙን እና አገልግሎቱን አስረዱ።
4. ምስጢረ ሜሮን ከጥምቀት ጋር ተያይዞ ሲፈጸም በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ካህኑ ተጠማቂውን የሚያትመው ምን እየለ ነው? የሚቀቡት ሕዋሳት (የሰውነት አካላት) ምን ምን ናቸው? ለምን?

www.zeorthodox.org

# ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን- ምስጢረ ቁርባን

# ሠላሳ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለምስጢረ ቁርባን ያውቃሉ፤ ከክርስቶስ ጋር የሚኖረንን ዘለዓለማዊ አንድነት ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና፡- ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት አለ፡፡ እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፡- ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈስሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፡፡"*** /ሉቃ.፳፪÷፲፱-፳ ፣ ማቴ.፳፮÷፳፮/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት›› (ሊቀ ጉባኤ አበራ በቀለ) ፣ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን (ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ፤ ያልታተመ)

**መግቢያ፡-** ስለ ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን መማር የጀመርነው ትምህርት በመቀጠል፤ በዛሬው ትምህርታችን ምስጢረ ቁርባንን እናያለን፡፡

ምስጢረ ቁርባን፡- ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት በመስቀል ላይ መሥዋዕት ሆኖ በመሞቱ ፣ የዓለምን ኃጢአት አስወግዶ የዘላለም ሕይወትን ያስገኘበት የመዳናችን መሠረት ነው፡፡ የጸጋችን ሁሉ ምንጭ የሆነውን የቅዱስ ሥጋውንና የክቡር ደሙን የማዳን ጸጋ የሚያመለክት ታላቅ የክርስትና ሃይማኖት ምስጢር ነው፡፡

ቁርባን በአንድ በኩል ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን መሥዋዕት ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበትን ፣ የምንዋሐድበትን ሁኔታ የሚያሳይ ምስጢር ነው፡፡ በጥምቀት ጊዜ ከምስጢረ ሜሮን ቀጥሎ በአንድ ጊዜ የሚፈጸም ሲሆን፤ አንድ ሰው ንስሐውን ከፈጸመ በኋላ፣ ተክሊል ሲፈጽም፣ ሥልጣነ ክህነት ሲቀበል ቅዱስ ቁርባን ይቀበላል፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ቁርባን የምስጢራት ሁሉ ዘውድ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**የቃሉ ትርጉም፡-** ቁርባን በዕብራይስጥ፣ በሱርስት፤ መባዕ፣ ስጦታ፣ አምኃ ማለት ነው፡፡ በጽርዕ ቋንቋ ***"አምላካዊት ሱታፌ፣ አምላካዊት ደስታ"*** የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህም እንደ ኦሪቱ ቁርባን ሰው ለእግዚአብሔር ያቀረበውን ስጦታ ብቻ የሚያመለክት አይደለም፡፡ በሐዲስ ኪዳን እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ ለሰዎች ድኅነት ለዓለም ሁሉ ያለዋጋ እንዲሁ በቸሮታ የሰጠውን በሥጋና በደም የመጣውን የልጁን ስጦታ ያስገነዝባል፡፡

**ቅዱስ ቁርባን በምሳሌ፡-** በጠቅላላው የኦሪት መሥዋዕት ለወንጌሉ መሥዋዕት ምሳሌነት ቢኖረውም ዋና ዋናዎቹን ብቻ እንመለከታለን፡፡

- ሊቀ ካህናት መልከ ጼዴቅ ለአብርሃም መስተንግዶ ያቀረበው ኅብስትና ወይን የክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌ ሆኗል፡፡ /ዘፍ.፲፬፥፲፰/
- **"ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል፡፡"** ተብሎ እንደ ተነገረ እሥራኤል ሥጋውን በልተው ደሙን ረጭተው በግብጽ ከወረደው መቅሰፍት የዳኑበት የፋሲካ በግ የመሲህ መሥዋዕትነት ምሳሌ ነው፡፡ /ዘጸ. ፲፪፥፩-፶፩/
- ሕዝበ እሥራኤል በምድረ በዳ ሳሉ በተአምራት ከሰማይ የወረደላቸው አርባ ዓመት ሙሉ የተመገቡት መና ምንም እንኳን ከሞት ባያድንም በተአምራት በመገኘቱ ለሥጋውና ለደሙ ምሳሌ ሆኗል፡፡ /ዮሐ.፮፥፵፱/

**ቅዱስ ቁርባን በትንቢት፡-*"እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ÷ ወደ ውኃ ኑ÷ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም፤ኑ ያለ ገንዘብ ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ፡፡"*** /ኢሳ.፶፭፥፩-፪/ ***"ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፤ በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ፤ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡"*** ይህ ስለ ወንጌል መሥዋዕት መነገሩ የኦሪት መሥዋዕት በኢየሩሳሌም ከተማ ብቻ በቤተ መቅደስ ይደረግ ስለነበረ ነው፡፡

## የምስጢረ ቁርባን አመሠራረት፡-

**በትምህርት፡- "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፡፡" ዮሐ.፮፥፶፬**

**በተግባር፡-** ከሕማማቱና ከሞቱ በፊት በዋዜማው ሐሙስ ማታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጢረ ቁርባንን መሥርቶታል፡፡ በዚያን ወቅት የኦሪት የፋሲካ በግ የሚሠዋበት ጊዜ በመሆኑ ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የኦሪትን መሥዋዕት አሳልፎ መሥዋዕተ ወንጌልን መሥርቷል፡፡ በዚያም ምሽት የኦሪቱ የበግ መሥዋዕት አበቃ ፤ ከእንግዲህ እውነተኛው የእግዚአብሔር በግ ይሠዋል፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ቁርባን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያደረገው አዲስ ቃል ኪዳን ነው፡፡ **"እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና፡- ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት አለ፡፡ እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፡- ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈስሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፡፡"** /ሉቃ.፳፪፥፲፱-፳፣ ማቴ.፳፮፥፳፮/ በክርስቶስ የአዲስ ኪዳን ደም ኃጢአታችን ተወግዶልናል ÷ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀናል ÷ የእግዚአብሔርን ልጅነት አግኝተናል ፤ እግዚአብሔርም አባት ሆኖን የመንግሥቱ ወራሾች አድርጎናልና - አዲሱ ኪዳን እጅግ የላቀ ነው፡፡

## የቅዱስ ቁርባን አማናዊነት፡-

ጌታችን "ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፡፡ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡" /ዮሐ.፮፥፶፭-፶፮/ ብሎ እንዳስተማረ፤ የምንቀበለው ሥጋ እና ደም እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው፡፡ ለመሥዋዕት የምናቀርበው ኅብስትና ወይን በጸሎተ ቅዳሴ አማካኝነት የኅብስቱና የወይኑ ባሕርይ ሳይለወጥ ፤ ኣርዓያውና መልኩ ፣ ጣዕሙና ልምላሜው ሳይለወጥ ሥጋ መለኮት እንዲሁም ደመ መለኮት ይሆናል እንጂ ተራ መታሰቢያ አይደለም፡፡

"ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት" የሚለው የጌታችን ቃል በመጀመሪያ ደረጃ ወደ እርሱ ሥጋነት የተለወጠውን ኅብስት እንዲሁም ወደ እርሱ ደምነት የተለወጠውን ወይን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ለመታሰቢያ አድርጉት ማለት፡- ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ከገባንበት ዋናው ነገር በምናስቀድስበትና በምንቆርብበት ጊዜ የበደላችንና የኃጢአታችንን ስርየት ያገኘንበትን ÷ ከእግዚአብሔር ጋር የታረቅንበትን የክርስቶስን ሕማምና ሞት ማስታወስ ነው፡፡

መታሰቢያ የተባለው ስለ ሕማምና ሞቱ መሆኑንን ከቅዱስ ጳውሎስ እንማራለን፡፡ "ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ÷ ቈርሶም፡- እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፡፡ እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፡- ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው ፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፡፡ ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና፡፡" /፩ኛ. ቆሮ.፲፩፥፳፫-፳፱/ በፍሬ ቅዳሴ *" ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሳኤከ ቅድስተ ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ - አቤቱ ሞትህንና ቅድስት ትንሣኤህን እንናገራለን እርገትህንና ዳግም መምጣትህንም እናምናለን፡፡"* እያልን የምንጸልየው ይህንኑ ለማረጋገጥ ነው፡፡

አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም በመሆኑና ተራ መታሰቢያ ባለመሆኑ ራሳችንን በንስሐ መርምረን መቀበል እንደሚገባ ይኸው ሐዋርያ፤ "ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት፡፡ ሰው ግን ራሱን ይፈትን÷ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና÷ ይጠጣልምና" በማለት ያስጠነቅቃል፡፡ /፩ኛ. ቆሮ. ፲፩፥፳፯-፳፱/

www.zeorthodox.org

## በቅዱስ ቁርባን የሚገኝ ጸጋ

የኃጢአት ሥርየት፡-"... ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡" ብሏል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ የኃጢአት ስርየት ከተገኘ ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅና ሰላም

ይወርዳል፤ እርቅ ከተገኘ ደግሞ ሌሎቹ ስጦታዎች ይጨመራሉ። ኃጢአታቸው የተተወላቸው ሰዎች ብፁዓን ናቸውና። /መዝ.፴፩÷፩/

**ከክርስቶስ ጋር በኅብረት መኖር፡-** ***"ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።"*** /ዮሐ.፮÷፶፮/

**ከነፍስ ረኃብና ጥም መዳን፡-** ***" የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምን ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም።"*** ዮሐ.6፡35 *ሥጋው* ወደሙ እውነተኛ መንፈሳዊ ምግብ ነውና።

**በእኛ ያለ አንድነት እና ፍቅር ይጠናከራል፡-** ***"የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቈርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? አንድ እንጀራ ስለሆነ÷ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና።"*** ፩ኛ ቆሮ.፲÷፲፮-፲፷

## ማጠቃለያ፡-

የጌታችን ቅዱስ *ሥጋ*ና ክቡር ደም ቅዱስ ቁርባን ተብሎ ይጠራል። የተሰጠን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቅዱስ *ሥጋ*ውንና ክቡር ደሙን የሚበሉትና የሚጠጡት ሁሉ ስርየተ ኃጢአት፣ ከክርስቶስ ጋር ኅብረትን ያገኛሉ። ከነፍስ ረኃብና ጥም ይድናሉ፤ ክስቲያናዊ አንድነት እና የዘለዓለምን ሕይወት ይቀዳጃሉ።

## ተግባር፡-

- ቅዱስ ቁርባን በጸሎተ ቅደሴ አማካኝት የሚለወጥ በመሆኑ ሥርዓተ ቅዳሴን በአንቃዕዶ ኅሊና ልንሳተፍ ይገባል።
- ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁን አንድነት አጽኑ።

www.zeorthodox.org

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ምስጢረ ቁርባን የመዳናችን መሠረት ነው፤ ሲባል ምን ማለት ነው? ምክንያቱን አብራሩ።
2. ቁርባን ማለት ምን ማለት ነው?
3. ቁርባን መቼ እና እንዴት ይፈጸማል?
4. ስለ ቅዱስ ቁርባን በኦሪት(ብሉይ ኪዳን) የተገለጸውን በሦስት ምሳሌዎች በማቅረብ አብራሩ።

5. ምስጢረ ቁርባንን የመሠረተልን ማን ነው? በወንጌል የተቀመጡትን ጥቅሶች በማስረጃ በማቅረብ አብራሩ፡፡
6. የምንቀበለው ቅዱስ ቁርባን አማናዊ ነው፤ ሲባል ምን ማለት ነው? በማስረጃ አብራሩ፡፡
7. ‹‹ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት›› የሚለውን የጌታችንን ቃል ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ፡፡
8. ቅዱስ ቁርባን በመቀበል የምናገኛቸውን ጸጋዎች ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን - ምስጢረ ንስሓ
# ሠላሳ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ተማሪዎች ስለ ምስጢረ ንስሐና አፈጻጸሙ እንዲሁም ስለምናገኘው የእግዚአብሔር ጸጋ ያውቃሉ፤ ከዚያም ሰዎች ሁሌም ኃጢአታቸውን አምነው ፣ ለመታረምና ለማቆም ፈቃደኛ በመሆን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደሚገባቸው ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፦** *"ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሓ ግቡ ተመለሱም "* የሐዋ.ሥ ፫÷፲፱

**መግቢያ፦** ምስጢረ ንስሓ በሚታየው ሐዘን፣ ኑዛዜና ቀኖና፤ የማይታየው ስርየተ ኃጢአት የሚሰጥባት ናት። ስለሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን በተከታታይ በጀመርነው ትምህርት መሠረት በዛሬው ትምህርታችን ስለ ምስጢረ ንስሐ እንማራለን።

## የሳምንቱ ትምህርት፦

‹‹ንስሐ›› ቃሉ - ተነስሐ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ፤ ቀጥተኛ ትርጉሙም **ተጸጸተ ፣ ተመለሰ** ማለት ነው። ንስሐ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው። ንስሐ ለእርቅ የተዘረጋ የእግዚአብሔር እጅ ነው። ንስሐ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ስለራሳችን ንጽሕና ሲባል ኃጢአትን መተው ነው።

**የምስጢረ ንስሓ አጀማመር፦** የተጀመረው በአዳም መጸጸት በእግዚአብሔር ምሕረት ሲሆን፣ ጌታችን በወንጌል በሦስት ቦታዎች ምስጢረ ንስሐን ከክህነት ጋር አጣምሮ መሥርቶታል።

1. ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ ካለው በኋላ ጌታችን ‹‹ ***በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል። በምድር የምትፈታው ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።*** ›› ማቴ ፲፮ ÷፲፱ ሲል ቃል ገብቶለታል።
2. ለደቀ መዛሙርቱ ቃል ሲገባላቸውም *"....**እውነት እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት በሰማይም የታሰረ ይሆናል÷ በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።**"* ማቴ ፲፰÷፲፰ ፣
3. ከትንሣኤው በኋላም የሚጠብቃቸውን አብይ ተልዕኮ ሲነግራቸው*"**አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኃለሁ አላቸው። ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፦ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።***

www.zeorthodox.org

*ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።"* /ዮሐ. ፳÷፳፩-፳፫/ ፣

በዚህ *መሠረት "ንስሐ ግቡ "* ብሎ በማስተማር ከሰባቱ ምሰሶዎች አንዱ የሆነውን ምስጢረ ንስሐን ከነአስፈጻሚዎቹ የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የንስሐ ሂደቶች የሚከተሉት ናቸው፡- በመጀመሪያ በኃጢአት በማዘን ፣ በመጸጸት እና በመናዘዝ እግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ ይገባል፡፡ ተነሳሒው(ዋ) ለካህኑ ተናዘው ቀኖናቸውን ሲፈጽሙ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ፡፡ ከዚያም በካህኑ ምክርና ፍትሐት (ይፍታህ ወይም ይፍታሽ) ከተባሉ በኋላ ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ይጀምራሉ፡፡

## የእውነተኛ ንስሐ መገለጫዎች፣

- ለተፈጸመው ኃጢአት ከልብ ማዘን (መዝ.፯÷፪-፯)
- ወደ ኃጢአት ላለመመለስ ቁርጥ ውሳኔ መወሰን (የጠፋው ልጅ ሉቃ.፲፭)
- በእግዚአብሔር ይቅር ባይነትና ምሕረት ማመን ፣ ፩ኛ. ዮሐ. ፩÷፱
- ጌታ "*ሂዱ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ "* ሉቃ ፲፯÷፲፬ እንዳለን ለካህን መናዘዝ ፡፡
- ከኃጢአት ምክንያቶች መጠበቅ፡፡ መዝ. ፩÷፩-፫
- ሌሎችን ሳይከሡ እውነታውን ብቻ መናገር፡፡
- ዳዊት ነቢዩ ናታንን እንደሰማው የካህኑን ምክር ማዳመጥና መቀበል፡፡ ፪ኛ ሳሙ.፲፪÷፲፩-፲፫
- ቅጣትን ለመቀበል መዘጋጀት ፪ኛ ሳሙ. ፲፮÷፱-፲፬ ; ዕብ.፲፪÷፯

**ንስሓ ለማን ነው ?** ንስሓ የበደለ ሁሉ በየዕለቱ ሊፈጽሙት የሚገባ ምስጢር /አገልግሎት/ ነው፡፡

**በማን ይፈጸማል?** ንስሓ በተናዛዡ ኃጢአተኛ እና በካህኑ ብቻ የሚፈጸም ሲሆን ፤ ሥልጣነ ክህነት የሌለው ንስሓ አይቀበልም፡፡

**እንዴት ይፈጸማል ?** ተነሳሒው ወደ ካህኑ ቀርቦ ኃጢአቱን ይናዘዛል፡፡ ካህኑም ምክርና ቀኖና /ቅጣት - ስግደት፣ ምጽዋት፣ ጾም፣ ከምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለተወሰነ ጊዜ መከልከል......../ ለምክንያተ ድኅነት ይሰጡታል፡፡ ተነሳሒው የተታዘዘውን ከፈጸመ በኋላ ፍትሐት ዘወልድ (የንሥሓ ጸሎት) ይጸለይለታል ፤ ከምእመናን ጋር እንዲቆጠርም የጌታችንን ሥጋና ደም ይቀበላል፡፡

www.zeorthodox.org

**ሁለም ኃጢአት ይቅር ይባላል ?** መጽሐፍ ቅዱስ፡- የቱንም ያህል ከባድ ኃጢአት ይሰረያል ይለናል፡፡ "*ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል"* ማቴ. ፲፪÷፴፩ " *ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፣ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን፣ እንደ አመዳይ ትነጻለች፣ እንደ ደምም ብትቀላ*

***እንደ ባዘቶ ትጠራለች።"*** ኢሳ.፩÷፲፰ እግዚአብሔርም ሁሉንም ለመቀበልና ይቅር ለማለት ዝግጁ እንደሆነ ተምረናል "***ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም"*** ዮሐ. ፮÷፴፯ ለእኛ ትምህርት እንዲሆነን የተጻፉት የአባቶቻችን ታሪኮችም ይሄንኑ ያስገነዝቡናል። **ለምሳሌ፡-** መዝሙረኛው ዳዊት ከባድ ኃጢአት ቢሠራም ይቅር ተብሏል። ቅዱስ ጴጥሮስም ጌታን አላውቀውም ካለ በኂላ በንስሓ ተመልሶዋል። ማቴ.፳፮÷፷፱-፸፭ ጌታችን ለሰቀሉት እንኳ ይቅርታ አድርጓል።

***በሚታየው አገልግሎት በምስጢረ ንስሓ የምንቀበለው የማይታይ ጸጋ አለ።***

***የሚታይ አገልግሎት፡-*** የተነሳሒው በካህን ፊት መናዘዝ ፣ የካህኑ ቀኖና መስጠት እና ጸሎት ፣ ተነሳሒው የሚፈጽመው ቅጣት የሚታየው አገልግሎት ነው።

***የማይታይ ጸጋ፣*** ከኃጢአት መፈታት (ስርየተ ኃጢአት) ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ፣ ያጣነው መንፈሳዊ ሀብት መመለሱ ደግሞ የማይታየው ጸጋ ነው።

***ማጠቃለያ፣*** ንስሐ ለሁሉም ጠቃሚና አስፈላጊ ምስጢር ስለሆነ፣ ዕለት ተዕለት ልንፈጽመው የሚገባ ሲሆን ÷ ቅዱስ ቁርባን በመቀበል ከአምላካችን ጋር በአንድነት እንድንኖር ያደርገናል። ያስፈልገናልም።

**ተግባር፡-** ሁል ጊዜም ንስሓ መግባትና መቁረብ አለብን፤ ዛሬውኑ ንስሓ እንግባ ፣ የንስሓ አባት ይኑረን።

## ኑዛዜ እና ጸጸት /ንስሐ/

በቤተ ክርስቲያን ትምህርትና በክርስቲያናዊ ኑሮ ኑዛዜ ከልብ የሆነ እውነተኛ የጸጸት ውጤት ነው። ከጸጸት የተለየ ኑዛዜ፣ ትረካ እንጂ ኑዛዜ አይደለም። ኑዛዜ ስለበደልነው በደል በፍጹም እምነት የምናቀርበው የጸጸት ውጤት ነው።

ጸጸት ራስን መክሰስ እና በራስ ላይ መፍረድ ያንንም መቀበል ነው። እውነተኛው ጸጸት ከልብ ይጀምራል። አንድ ሰው ክፉ ሥራውን ሲተው - ጠባዩንም ያርማል ፣ እንጂ ***በደለኛ ነኝ!*** ብሎ መናገር ወይም መደጋገም ብቻ አይደለም። ራሱን ክዶ ከልብ ተጸጽቶ ንስሓ የገባ ከእግዚአብሔርም ሆነ ፣ ከሰው ማንኛውንም ቅጣት ሲቀጣ ፣ ይገባኛል! ይላል።

www.zeorthodox.org

ሲቀጡ ማጉረምረም ያለመጸጸት ማረጋገጫ ነው። ጸጸት የኃጢአት ውጤቶችን በተቻለ መጠን መተው ሲሆን ፤ በሌሎች ያደረግነውን ፍትሕ አልባ ድርጊት ማረምም ነው። ለዚህም ነው ዘኬዎስ ***"ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደሆንኩ አራት እጥፍ እመልሳለሁ።"*** ያለው ሉቃ.፲፱÷፱ አንተም የወሰድከውን መልስ የበደልከውን ካስ። ሳይክሱና የወሰዱትን ሳይመልሱ መጸጸት ብቻውን በቂ

አይደለምና፡፡

ጸጸት፣ ትሑት ልብ ይፈልጋል፡፡ ለራሱ ልዕልናና ለክብሩ የሚጨነቅ ሰው አይጸጸትም፡፡ ሁሌም ራሱን የሚከላከል፣ ለክፉ ድርጊትና ለንግግሩ መከላከያ በማቅረብ የሚሟገት ሰው ጸጸት የለውም፡፡ ክብሩ ከንስሓ ይመልሰዋልና ፡፡ ካህኑ ተነሳሒው መጸጸቱን ሲያይ ***"እግዚአብሔር ይፍታህ"*** ይለዋል ፣ ***"ይፍታህ"*** የሚባለው በኃጢአቱ የተጸጸተ ነውና፡፡ መበደሉን በፍፁም ያመነ ፣ ኀሊናው የሚወቅሰው፣ ጠባዩ ይታረማል፣ ከልቡ ይጸጸታልም፡፡ በተቃራኒው ራሱን በመከላከልና በማሳመን ብቻ የሚኖርም ከኃጢአቱ ጋር ይኖራል፣ ለዚህ ሰው ኃጢአቱ ምን ያህል ከባድ ቢሆንም አይረብሸውም፡፡ የሰዶም ሰዎች ዓይናቸው ታውሮ የሎጥን ቤት ደጃፍ ለማግኘት ሲፈልጉ ደከሙ የተባለው ለዚህ ነበር፡፡ ዘፍ.፲፱÷ አንድ ሰው መሳሳቱን ካላመነ እንዴት ይጸጸታል? ሳይጸጸትስ እንዴት ይናዘዛል ? በሰማያዊው ሥልጣን ያልተፈታስ እንዴት ከእግዚአብሔር ይታረቃል ? ኃጢአትን ማመን የመጀመሪያ ደረጃ÷ ኑዛዜ ቀጣዩ ነው፡፡ እውነተኛ ኑዛዜና ኃጢአትን አለማመን በጣም ይለያያሉ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ‹‹ንስሐ›› ማለት ምን ማለት ነው? አብራሩ፡፡
2. ምስጢረ ንስሐ መቼና እንዴት ተጀመረ?
3. ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጢረ ንስሐን በወንጌል በሦስት ቦታዎች ከክህነት ጋር በማጣመር መሥርቶታል፡፡ እየጠቀሳችሁ አብራሩ፡፡
4. የእውነተኛ ንስሐ መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?
5. ስለ ምስጢረ ንስሐ፤ ‹‹የሚታየው አገልግሎት›› ምንድነው? እንዲሁም በሚታየው አገልግሎት የምንቀበለው ‹‹የማይታይ ጸጋ›› ምንድ ነው? አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን - ምስጢረ ክህነት

# ሠላሳ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ሥልጣነ ክህነት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም፡፡"*** / ዕብ. ፭÷፬/

**ምንባብ፡-** ‹‹ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት›› (ሊቀ ጉባኤ አበራ በቀለ) ፣ ‹‹ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን›› (ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ ፤ ያልታተመ) ፣ ‹‹ትምህርተ አበ ነፍስ›› (ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ)

**መግቢያ፡-** ምስጢረ ክህነት የአገልግሎትን ጸጋ ከሚያሰጡ ምስጢራት አንዱ ነው፡፡ ክህነት በእግዚአብሔርና በምእመናን መካከል ተገኝተው የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትእዛዝ ለመፈጸምና ለማስፈጸም፤ አማኞችን ለመጠበቅ ለመምከርና ለማስተማር፤ እንዲሁም ለመጸለይና ለመባረክ፤ በጠቅላላው ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለመፈጸም እንዲችሉ ለማድረግ ለተመረጡ ሰዎች በጳጳሳት ጸሎትና አንብሮተ እድ የሚሰጥ መንፈሳዊ መዓርግንና ሥልጣንን የሚያስገኝ ከፍተኛ የጸጋ ምስጢር ነው፡፡

**የሳምንቱ ትምህርት፡-** በግእዝ ቋንቋ "ተክህነ" አገለገለ ከሚለው ግስ የወጣ ነው፡፡ አገልግሎቱም ለሃይማኖት ብቻ ነው፡፡ ክህነት የሥልጣኑ ስም ሲሆን አገልጋዮቹ ካህናት ይባላሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ካህናት የአገልግሎት ሥልጣን የሚቀበሉት ከመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ይህም የክህነት ሹመት - ምስጢረ ክህነት ይባላል፡፡

*አመሠራረት፡-* በብሉይ ኪዳን የነበረው ሥርዓተ ክህነት ለአዲስ ኪዳኑ የክህነት አገልግሎትና ምስጢር መሠረትነት አለው፡፡ የብሉይ ኪዳኑ ክህነት ለአንድ ወገን ብቻ ተሰጠ፣ እንስሳትን ያቀርቡ የነበሩ ናቸው፡፡ ዘጸ.፳፰-፴፣ ዘኁ.፩÷፶፣ ፫÷፳፣ ኢያ.፲፬÷፬

በሐዲስ ኪዳን የክህነትን ምስጢር የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በደሙ ቤተ ክርስቲያንን ከመሠረተ በኋላ ከትንሣኤው አያይዞ ለሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን ሰጥቷቸዋል፡፡ "...

www.zoorthodox.org

**ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፡- መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።"** /ዮሐ.፳፥፳፪/

**የሐርያት ሥልጣነ ክህነት መተላለፍ** /Apostolic succession/፡- የክህነት ሥርዓት ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን እየተላለፈ ደርሷል። ቅዱሳን ሐዋርያት በዘመናቸው ሥልጣነ ክህነት ይሾሙ ነበርና ። /ሐዋ.፲፬፥፳፩/

ይህ የሥርዓተ ክህነት ደንብ ዛሬም ሐዋርያዊውን ትውፊት ጠብቃ ለኖረችው ቤተ ክርስቲያን መመሪያ ነው። ጌታችንም **"እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ"** ብሎ ለሐዋርያት የተናገረው ለጊዜው ለእነርሱ ቢሆንም ፍጻሜው ግን አስከ ዛሬ ድረስና እስከ ዓለም ፍጻሜ ለምትቆየው ለሐዋርያዊቷ ቤተ ክርስቲያን እና ለአገልጋዮቿ ነው። /ማቴ.፳፰፥፳፰/

## የክህነት አገልግሎት

**በቃል ለማስተማር እና የቅድስና መንገድ ለማሳየት፡-** በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ከግሪክ የመጡት አይሁድ በኢየሩሳሌም ኖረው በነበሩት ላይ በመስተንግዶ ምክንያት አንጎራጎሩባቸው። ***"አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው። የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። ወንድሞች ሆይ ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን ፤ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።"*** /ሐዋ.፮፥፩-፬/ የክህነት ዋናው አገልግሎት ማስተማር ነው። እግዚአብሔር በሆሴዕ አድሮ ካህኑን፤ ‹‹***ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ፤ የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ።***›› /ሆሴ.፬፥፮/ ብሎ የወቀሰው የካህኑ ዋና ሓላፊነት በቃልና በተግባር ማስተማር በመሆኑ ነው። ***እውቀትን ጠልተሃል*** የሚለው ቃል፣ ***የአምላክህን ሕግ ረስተሃል*** *የሚለውን* ተግባራዊውን የማስተማር ግዴታና ሓላፊነት *ያመለክተናል*።

www.zeorthodox.org

**የሕዝቡን ኃጢአት ለማስተስረይ፡-** የኦሪት ካህናት የሕዝቡን ኃጢአት እንዲያስተሰርዩ በእግዚአብሔር ታዘው ነበር። /ዘሌዋ.፲፮፥፯-፴፬/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን ሲሰጥ በመጀመሪያ ለጴጥሮስ፤ ‹‹***የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።***›› /ማቴ.፲፮፥፲፱/ ብሎት ነበር። በኋላም ለዐሥራ ሁለቱም ሐዋርያት ***"እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል። "*** /ማቴ.፲፰፥፲፰/ ብሏቸው ነበር። ይህንኑ የክህነት አገልግሎት

ከትንሣኤው በኋላ የበለጠ ግልጽ አድርጎ ሰጣቸው፡፡ ‹‹*ኢየሱስም ዳግመኛ፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና- መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው፡፡*›› /ዮሐ.፳፥፳፩-፳፫/ በዚህ መሠረትም ከክህነት አገልግሎቶች አንዱ ስርየት ኃጢአት ማስጠት ነው፡፡

***መንጋውን ለመጠበቅና ለማስማራት፡-****"ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው፡፡ አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፡፡ ግልገሎቼን አሰማራ አለው፡፡ ደግሞ ሁለተኛ፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው፡፡ አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፡፡ ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው፡፡ ሦስተኛ ጊዜ፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው፡፡ ሦስተኛ፡- ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና፡- ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፡፡ ኢየሱስም፦ በጎቼን አሰማራ፡፡"* /ዮሐ.፳፩፥፲፭-፲፯/ በግልገል፣ በጠቦትና፣ በበግ የተመሰሉ ወጣንያን ፣ ማዕከላውያንና ፍጹማን ወይም ልጆች፣ ጎልማሶች እና አረጋውያን ናቸው፡፡ መንጋውን በሃይማኖት፣ በምግባር፣ በጸጋቸው ማሰማራት እና ከአጋንንት ፣ ከኃጢአት ፣ ከክፉው ዓለምና ከመናፍቃን መጠበቅ የክህነት አገልግሎት ነው፡፡

## የክህነት ማዓርጋት

**ጳጳስ፡-** ሥልጣነ ክህነት በምልዓት በጽጽስና ይገኛል፡፡ ጳጳስ ሐዋርያትን መስሎ አክሎ ይሠራል ያገለግላል፡፡ ሥልጣነ ክህነት ይሰጣል ፣ ቅብዓ ሜሮን ይባርካል፣ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ይባርካል፡፡

**ቄስ፡-** ክህነት ከመስጠት በስተቀር የተቀሩትን ምስጢራት ይፈጽማል፡፡

**ዲያቆን፡-** በምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሱንና ቄሱን ይራዳል እንጂ ራሱን ችሎ ምስጢራትን አያከናውንም፡፡

## ክብረ ክህነት

www.zeorthodox.org

***መለኮታዊ ጥሪ ነው፡-*** /ማር.፫፥፲፫-፲፭/ ማንም ሰው ለክርስቶስ ምስክር ለመሆን ተጠርቶአል፤ ማንም ሰው ግን ካህን ለመሆን ጥሪ የለውም፡፡ ጥሪው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰዎች አይደለም ፤ ይህም በረድኤተ እግዚአብሔር ለነፍስ የሚሰማ ጥሪ ነው፡፡ ይህ ጥሪ በመጀመሪያ በቤተ ክርስቲያን ወይም በጳጳስ በኩል ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ውሳጣዊ ሥራ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ጥሪ የደረሰው ሰውም ምንም ዓይነት ማምለጫ ሳይኖረው ካህን ወደ መሆን ይደርሳል፡፡ ‹‹*እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም፡፡*›› /ዕብ.፭፥፬/

የክህነት አገልግሎት የሙያ አገልግሎት ባለመሆኑ የመለኮታዊ ጥሪ አስፈላጊነት ግድ ይሆናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በምልዐት ስለዚህ ይናገራል፡፡ ከሳሙኤል፣ ከኤርምያስ፣ ከኢሳይያስ ከአሞጽና ከሌሎችም ታሪክ እንደምንረዳው የብሉይ ኪዳን ነቢያት ሁሉ በእግዚአብሔር የተጠሩ ነበሩ፡፡

መለኮታዊ ምርጫ ነው፡- *"በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፤ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ፡፡ በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ ከእነርሱም ዐሥራ ሁለቱን መረጠ ደግሞም ሐዋርያ ብሎ ሰየማቸው፡፡"* /ሉቃ.፮፥፲፪-፲፫፣ ሐዋ.፲፫፥፫፣ ገላ.፩፥፲፭/

ሹመት ነው፡- *"ከዚህም በኋላ ጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድ ወዳለው ከተማና ሥፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው፡፡"* /ሉቃ.፲፥፩/

የተቀደሱ ናቸው፡- *"ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው፤ እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ፡፡"* /ዮሐ.፲፯፥፲፱/

መጋቢ ናቸው፡- *"እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምስጢር መጋቢዎች ይቁጠረን፡፡ እንደዚህም ሲሆን በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል፡፡"* /፩ኛ ቆሮ.፬፥፩-፪፣ ሉቃ.፲፪፥፵፪/

## ክህነት ከመቀበል በፊት የሚገባ ዝግጅት

በሃይማኖት በኩል፡- የጸና ሃይማኖት ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ፣ *መንፈሳዊ ቅናት*

በምግባር፡- ቅድስና እና ንጽሕና ፣ ትዕግሥትን ገንዘብ ማድረግ ፣ ለመማር ዘወትር ዝግጁ *መሆን*

## ተግባር፡-

- ካህናት አባቶችን አክብሩ፡፡
- የእግዚአብሔርን ጥሪ ማንም ቀድሞ መገመት አይችልም ፤ በንጽሕናና በእውቀት ለአገልግሎት ራሳችሁን አዘጋጁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ምስጢረ ክህነት ምንድነው ?ትርጉሙን አገልግሎቱን ግለጹ፡፡
2. በሐዲስ ኪዳን ምስጢረ ክህነትን የመሠረተው ማን ነው? እንዴት መሠረተው? የጥቅስ ማስረጃ በማቅረብ አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

3. ስለ ክህነት አገልግሎት ዋና ዋናዎቹን በመጥቀስ አብራሩ፡፡
4. የክህነት መዓርጋት ምን ምን ናቸው? ተግባራቸውንም ግለጹ፡፡
5. የሥልጣነ ክህነት ክብር ምን ምን ናቸው? በዝርዝር ግለጹ፡፡
6. ሥልጣነ ክህነት ከመቀበል በፊት መደረግ የሚገባቸው ዝግጅቶች በሃይማኖት እና በምግባር ምን ምን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን - ምስጢረ ተክሊል

# ሠላሳ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *ተማሪዎች ስለ ክርስቲያናዊ ጋብቻ ምንነት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡*

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል÷ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው፡፡"*** */ማቴ.፲፱÷፫-፯/*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** *‹‹ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት›› (ሊቀ ጉባኤ አበራ በቀለ) ፣ ‹‹ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን›› (ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ፤ ያልታተመ)*

***መግቢያ፡-*** *ተክሊል ማለት **"ተክለለ"** ተቀዳጀ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ነው፡፡ በጋብቻቸው ጊዜ ሙሽራው እንደ ንጉሥ ሙሽራይቱ እንደ ንግሥት ሆነው አክሊል ይቀዳጃሉና ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ምስጢረ ተክሊል የሙሽራውንና የሙሽሪትን የጋብቻ ቃል ኪዳን በሃይማኖት የሚያጸና ፣ የጋብቻን ግዴታ ለመወጣት የሚያስችል ፣ በፍቅር የሚያስተሳስር ፣ ዘላቂ አንድነትን የሚያስገኝ ከቅዱስ ቁርባን ጋር የሚሰጥ የጸጋ ምስጢር ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ይህንኑ እናያለን፡፡*

## ***የሳምንቱ ትምህርት፡-***

*ጋብቻ ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን ፍቅርና አንድነት ምሳሌ የሆነ ታላቅ ምሥጢር መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል፡፡ /ኤፌ.፭÷፴፩/*

www.zeorthodox.org

*ምስጢረ ተክሊል ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት እስከ ዘለዓለም ድረስ በጋብቻ በአንድነት ይኖሩ ዘንድ በኦርቶዶክሳዊ ካህን የሚፈጸም ቅዱስ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህም ቅዱስ ሥርዓትና ምስጢር ሁለቱ ተጋቢዎች አንድ ይሆናሉ፡፡* ***"ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል ÷ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው፡፡"*** */ ማቴ. ፲፱÷፫-፯/*

*ቅዱስ ጳውሎስም ይህንን የባል እና የሚስትን አንድነት ምስጢር፤* ***"ይህ ምስጢር ታላቅ ነው"***

በማለት ፤ እንዲሁም "**መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን**" በማለት የጋብቻን ቅዱስነት መስክሯል። /ኤፌ.፭÷፴፪፣ ዕብ.፲፫÷፬/

ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚፈጸም ዘላለማዊ አንድነት ነው ፤ ይህም አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት አድርጎ ሰውን በመፍጠሩ ይታወቃል። /ዘፍ.፪÷፲፰-፳፬፣፩ኛ. ቆሮ.፯÷፪/

ብዙ ዓይነት የጋብቻ ሥርዓት አለ። በዋናነትም ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ብለን እንለያቸዋለን። ዓለማዊዎቹ በባህላዊ እና መንግሥታዊ ሥርዓት የሚፈጸሙት ሲሆኑ መንፈሳዊ ጋብቻ የምንለው በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የሚፈጸመውን ነው። ጋብቻ መንፈሳዊ በረከቶች አሉት። ይህንን በትዳር የሚገኘውን መንፈሳዊ በረከት ማግኘት የሚቻለውም እግዚአብሔር ሲፈቅድ ነው።

## የጋብቻ አመሠራረት

ጋብቻን የመሠረተው ልዑል እግዚአብሔር ነው። አመሠራረቱም አዳምን እና ሔዋንን በመፍጠር ነው። ***" እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው "*** ዘፍ.፩÷፳፯ ‹‹***እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት። ..... እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት። አዳምም አለ፦ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።*** /ዘፍ.፪÷፲፰፣፳፩÷፳፬/

ጌታችን የመጀመሪያውን ተአምር በሰርግ ቤት ፈጸመ። /ዮሐ02÷፩-፲፪/፣ ስለ ጋብቻ ሲያስተምርም ለአዳምና ለሔዋን የተሰጠውንና የተፈቀደውን የጋብቻ ሕግ አጸና። /ማቴ.፲፱÷፬-፱/

## የጋብቻ ዓላማዎች፡-

www.zeorthodox.org

**ለመረዳዳት፡-"** ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" /ዘፍ.፩÷፲፰/ ለሰው ልጆች ብቸኝነት ከባድ ሕይወት ነው። በሐሳብ ፣ በኑሮና በስሜት መደጋገፍ የሚቻለው - ረዳት ሲኖር ነው። ለዚህ ነው ንጉሥ ሰሎሞን፡-***" ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል። ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት።"*** /መክ.፬÷፱-፲/ የሚል ምክር የሰጠው። እግዚአብሔር ሰዎች እንዲረዳዱ ካዘጋጃቸው አንዱና ዋነኛው ተቋም ጋብቻ ነው ፤ ወይም የጋብቻ አንዱና ዋናው

ዓላማ መረዳዳት ነው፡፡ ***"እግዚአብሔርም አለ.....የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት፡፡"*** /ዘፍ.፪÷፲፰/

***ዘር ለመተካት፡-*** በጋብቻ አማካኝነት ወላጆች ልጆችን በማፍራት በእግዚአብሔር የሥነ ፍጥረት ሥራ ውስጥ ተባባሪ ያደርጋቸዋል፡፡ **"ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት"** የሚለው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በቀጥተኛ መልኩ የሚፈጸመው በጋብቻ ነው፡፡ /ዘፍ.፩÷፳፯/ **"እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው ÷ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው፡፡"** /መዝ. ፻፳፮(፻፳፯)÷፫/ **"ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ናት ፤ ልጆችህ በማዕድህ ዙሪያ እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው፡፡ እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንዲህ ይባረካል፡፡"** /መዝ.፻፳፯(፻፳፰)÷፫/ እንደሚል ልጆች ከእግዚአብሔር የሚሰጡ በረከቶች ናቸው፡፡

ምን አልባት በጋብቻ ውስጥ ልጅ የማይወለድበት አጋጣሚ ቢፈጠር ፣ ከጸሎት ጋር የሚቻለንን ጥረት በማድረግ ***"የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን"*** ማለት ይገባል፡፡ የጋብቻ ዋና ዓላማ መረዳዳት ሲሆን ዘር መተካት ሁለተኛው ነው፡፡ በልጅ አለመኖር ብቻ ፍቺ አይፈጸምም፡፡

***ከዝሙት ለመጠበቅ፡-*** የጋብቻ ሦስተኛ ዓላማ ከአመንዝራነት ለመጠበቅና የሥጋ ፍትወትን ለመቆጣጠር ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ከዝሙት ጠንቅ ከሚመጣው ደዌና የመንፈስ ጭንቀት ለመዳን ቅዱስ ጋብቻ መፍትሔ ነው፡፡ **"...ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ፡፡"** /፩ኛ ቆሮ.፯÷፰/

## የክርስቲያናዊ ጋብቻ መገለጫዎች፡-

***አንድነት፡-*** ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው የጋብቻ ትምህርት አንድ ለአንድ /monogamy/ የሚባለውን ነው፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ያዘጋጀው አንድ አዳምን ለአንዲት ሔዋን ነው፡፡ በሥርዓተ ተክሊል እና በቅዱስ ቁርባን ሁለት የነበሩት ተጋቢዎች በክርስቶስ አንድ ይሆናሉ ፤ ስለዚህም ወደ ፊት አንድ እንጂ ሁለት አይባሉም፡፡ **"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡፡"** /ኤፌ.፭÷፴፩/

***ዘላቂነት፡-*** ጋብቻ ሁለቱ ጥንዶች ያለ መለያየት እስከ ዕድሜያቸው ፍጻሜ በአንድነት የሚቆዩበት ሕይወት ነው፡፡ ምናልባት ሊለያዩባቸው ከሚችሉት ምክንያቶች አንዱ ዝሙት ነው ፤ ይህም የመለያያ ምክንያት የሚሆነው የቅዱሱን ጋብቻ ቅድስና ስለሚያሳድፈው ነው፡፡ ነገር ግን ኃጢአቱን የሠራው ወገን ንስሐ ከገባና ይቅር ከተባባሉ አብረው እንዲቀጥሉ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች፡፡ ሁለተኛው ፍቺ ሊፈጸም የሚችልበት ምክንያት ከሁለት አንዳቸው እምነታቸውን (ሃይማኖታቸውን) የለወጡ ከሆነ ነው፡፡ ሦስተኛው ጋብቻ የሚፈርስበት ምክንያት ባል ወይም ሚስት ከሁለት አንዳቸው በሞት ሲለዩ ነው፡፡

***ፍሬ ማፍራት፡-*** በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት በቅዱስ ጋብቻ ሕይወታቸውን የሚመሩ ጥንዶች

www.zeorthodox.org

በርካታ ፍሬዎችን ያፈራሉ፡፡ ፍሬዎቻቸውም፡- ፍቅር ፣ በጎነት ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሁም ልጆች ናቸው፡፡

**ማጠቃለያ፡-** *የጋብቻ ሕይወት ጥንዶች በንጽሕናና በቅድስና ሆነው በጋራ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በመምራት ክርስቲያናዊ ተጋድሎን እየፈጸሙ ራሳቸውን ለመንግሥተ እግዚአብሔር የሚያዘጋጁበት ሕይወት ነው፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔርን ሊያገለግሉ፣ ሀገርን የሚጠቅሙ ልጆችን ወልደው በአግባቡ በማሳደግ በሥርዓት የሚያንጹበት ሕይወት ነው፡፡ ስለዚህ ከጋብቻ በፊት ይህንን ሓላፊነት ለመወጣት በቂ ሥነ ልቡናዊ፣ መንፈሳዊ እንዲሁም ቁሳዊ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡*

**ተግባር፡-** ለተክሊል ለመብቃት ራሳችሁን ከፈተና ጠብቁ፡፡

**ጥየቄዎች፡-**

1. ‹‹ተክሊል›› ማለት ምን ማለት ነው ?ስያሜው የተሰጠበትን ምክንያት አስረዱ፡፡
2. ‹‹ምስጢረ ተክሊል›› ምንድን ነው? በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስረጅ ጥቅስ በማቅረብ አበራሩ፡፡
3. ጋብቻን የመሠረተው ማነው? እንዴት መሠረተው?
4. የጋብቻ ዓላማዎች ምን ምን ናቸው? አብራሩ፡፡
5. ቅድስት ቤተክርስቲያን ጋብቻ በአንድ ወንድ እና በአንዲት ሴት መካከል የሚፈጸም መሆኑን ታስተምራለች፡፡ ይህ ክርስቲያናዊ ጋብቻ መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን - ምስጢረ ቀንዲል
# ሠላሳ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ሕሙማን ስለ ሚፈወሱበት ምስጢር መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-***"ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች(ካህናት) ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩበት፡፡ የእምነት ጸሎትም ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሳዋል ፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል፡፡"* /ያዕ.፭፥፲፬-፲፭/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት›› (ሊቀ ጉባኤ አበራ በቀለ) ፣ ‹‹ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን›› (ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ፤ ያልታተመ)

**መግቢያ፡-** ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ምሥጢረ ቀንዲል ነው፡፡ ምስጢረ ቀንዲል - የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው የጌታችንን አዳኝነት የሚያሳየን ነው፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ የሰዎችን ደዌያት ሊያስቀርና ሕሙማንን ሁሉ ሊፈውስ እንደመጣ ወንጌል ታስተምረናለች፡፡ (ሉቃ.፬፥፲፮-፳፪) በዚህ ሳምንት ትምህርታችን፡- በምስጢረ ቀንዲል ለሕሙማን የሚፈጸመውን ማዳን ፣ የምስጢሩን አጀማመር እና አፈጻጸም እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**ቀንዲል፡-** ቀጥታ ትርጉሙ በዘይት የሚሠራ **መብራት** ማለት ነው፡፡ ምስጢሩ ሲፈጸም መብራት ስለ ሚበራ ከዚህ በመነሣት የተሰጠው ስያሜ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

**የምስጢረ ቀንዲል አመሠራረት፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ምስጢር መሥርቶታል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በደዌያትና በአጋንንት ላይ ሥልጣን ሰጥቷቸው ነበር፡፡ /ሉቃ.፲፥፩-፱/ ዐሥራ ሁለቱንም ደቀ መዛሙርት ሲልካቸው የተጀመረውን የቀንዲል ፈውስ ወንጌላዊ ማርቆስ፤ ***"ብዙ ሰዎችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው፡፡"*** ማር.፮፥፲፫ በማለት ገልጾልናል፡፡ ይህን የተቀበሉትም ከጌታ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡ ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ ***"እንዲሁ ሰው ሁሉ እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምስጢር መጋቢዎች ይቁጠረን፡፡"*** ፩ኛ. ቆሮ.፬፥፩ ያለው፡፡ ጌታችን የሠራቸው ሁሉ በወንጌል አልተጻፈም (ዮሐ.፳፩፥፳፭) በሐዋርያው ትውፊት

ከተላለፉልን አንዱም ምስጢራትን ሐዋርያት ከጌታ እንዳገኙት የሚያስረዳው ነው፡፡

**ቀንዲል**፡- ሁሉም (የምሥራቅ እና የምዕራብ) አብያተ ክርስቲያናት በዚህ ምስጢር ማዳንና ክብር ይስማማሉ ያምኑበታልም፡፡

**የምስጢረ ቀንዲል አገልግሎት፡-** ምስጢረ ቀንዲል ካህናት በጸሎትና በመቀባት ፤ ለሕመምተኛው የእግዚአብሔርን የምሕረት ጸጋ የሚጠይቁበት የሥጋና የነፍስ ድኅነት የሚገኝበት አገልግሎት ነው፡፡ ይህ ምስጢር ሲፈጸም ሕመምተኛው በሥጋና በነፍስ የሚድንበትን ሰማያዊ ጸጋ ለመቀበል መዘጋጀቱንና መፍቀዱን ቤተ ክርስቲያን ሕመምተኛውን በመጠየቅ ታረጋግጣለች፡፡ ሐዋርያው ያዕቆብ "***ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች(ካህናት) ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩበት፡፡ የእምነት ጸሎትም ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል፡፡***" ያዕ.፭÷፲፬-፲፭ ካለን በመነሳት የሚከተሉትን ነጥቦች እናያለን፡-

- የዚህ ምስጢር ተጠቃሚዎች ሕሙማን ናቸው፡፡
- ይህን ምስጢር መፈጸም የሚችሉት ሕሙማን ናቸው፡፡
- የሚፈጸምበት መንገድም ***"በጸሎት"*** ነው ፡፡
- በምስጢረ ቀንዲል የሚታየው አገልግሎት በተቀደሰው ቅባት ይፈጸማል ፡፡
- ውጤቱም መልካም ጤናና ስርየተ ኃጢአት ማግኘት ነው፡፡

**አፈጻጸሙ፡-** በቤት ፣ በሆስፒታል ፣ በቤተ ክርስቲያንም ይፈጸማል፡፡ ካህኑ መብራት አብርቶ የመጽሐፈ ቀንዲል ጸሎት አድርሶ በመስቀል ምልክት ይቀባዋል፡፡

## በሚታይ አገልግሎት ያለው የማይታየው ጸጋ

**የሚታይ አገልግሎት**፡- የቀንዲል ቅባት ፣ ጸሎቱ ፣ ካህኑ ፣ በአጠቃላይ ሕመምተኛው ድኅነትን እንዲያገኝ በካህኑ አማካኝነት የሚፈጸመው ሥርዓት የሚታየው አገልግሎት ናቸው፡፡

www.zoorthodox.org

**የማይታየው ጸጋ**፡- ሕመምተኛው የሚያገኘው የነፍስና የሥጋ ድኅነት የማይታየው ጸጋ ናቸው፡፡

**ይህ ምስጢር አንዳንድ ሰዎችን ለምን አያድንም?**

- ኃጢአታቸውን ስላልተናዘዙ ሊሆን ይችላል፡፡
- እምነት ስለ ሌላቸውም (የእምነት ጉድለት ስላለባቸውም) ሊሆን ይችላል፡፡
- እግዚአብሔር መስቀሉን እንዲሸከሙ በመፍቀዱ ይሆናል፡፡
- እግዚአብሔር በሞተ ሥጋ ወደ እርሱ የሚጠሩበት ጊዜ እንደደረሰ ስለአወቀ ወይም ደዌ

ዘእሴት ሆኖላቸው ሰማያዊ ዋጋ እንዲቀበሉበት ፈቅዶ ይሆናል፡፡

### ስንታመም ማድረግ ያለብን ምንድነው ?

ወደ ካህናት ሄደን ንስሐ መግባት ፣ ቅባቱን እንዲቀቡን / ቀንዲል እንዲያደርጉልን መጠየቅ እና ጸሎት ማስደረግ ሲሆን ፤ ወደ ሐኪም መሔድና መመርመር፣ በሐኪሙ የታዘዘልንን መድኃኒትም ከጸሎት ጋር በአግባቡ መውሰድም ተገቢ ነው፡፡ በምናገኘው ለውጥ እግዚአብሔርን እናመስግን፡፡

## ማጠቃለያ:-

1. ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አዳኝ ነው፡፡ በእምነታችን ጸንተን፤ ትእዛዛቱን አክብረን መንፈሳዊ ሕይወታችንን ጠብቀን ከእርሱ ጋር እንሁን፤ በእርሱ ፍቅር እንኑር መመኪያተን አለኝታና ጠባቂያችን እርሱ ነውና፡፡
2. ዓለም እውነተኛና ፍጹም መድኃኒት የላትም፡፡ ፍጹም መድኃኒት ሊሰጠን የሚችለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ነው ክርስትና የደስታ ምንጭ የሆነ ሃይማኖት ነው የምንለው ፣ ታመንም እንኳ ተስፋ አንቆርጥም፡፡
3. የእግዚአብሔር ቃል፣ ጸሎት፣ ቅዱስ ቁርባን፣ ቀንዲል ሆነ በመላእክት በተከበበችው ቤተ ክርስቲያን መሳተፍም ሆነ የቅዱሳኑ በረከት ፈውስና መድኃኒት ይሆናሉ፡፡ ሰዎች በጸበል እንደሚፈወሱም በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአል፡፡ በተግባር ሲፈጸምም በየቀኑ እናያለን፡፡

## ተግባር፡-

- ♣ ስትታመሙ ጸልዩ አባቶችን በመጥራትም ጸሎት ተቀበሉ፡፡
- ♣ በሕመም ለሚሰቃዩ ጸልዩላቸው፡፡

**ጥያቄዎች፡-** www.zeorthodox.org

1. ምስጢረ ቀንዲልን የመሠረተው ማን ነው? አስረጂ ጥቅሶችን በማቅረብ አብራሩ፡፡
2. የምስጢረ ቀንዲል አገልግሎት ምንድነው? እንዴት ይፈጸማል?
3. በምስጢረ ቀንዲል የሚታየው አገልግሎት ምንድነው? በዚህ አገልግሎት የሚገኘው የማይታየው ጸጋ ምንድ ነው?

# ቅዱስ ጊዮርጊስ

## ሠላሳ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ጽኑ እምነት፣ ተጋድሎና ሰማዕትነት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸው ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፤ በክፍል ውስጥ ገለጻ ያደርጋሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል÷ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል*** " ዮሐ.፲፬÷፲፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ገድለ ጊዮርጊስ

**መግቢያ፡-** ቅዱስ ጊዮርጊስ በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ ፣ የክርስትና ሰማዕት ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ሰማዕታት የሚል መዓርግ ሰጥታዋለች። ገድሉ እንደሚነግረንም ከሃያ እስከ ሃያ ሰባት ዓመቱ ድረስ እውነተኛውን የክርስትና ትምህርት አስተምሮአል። በዚህ የተነሣ ብዙ መከራ የደረሰበት የእምነት አርበኛ ነው።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ከሠላሳ በሚበልጡ ሀገሮች እንደ አገር ጠባቂ የሚታመን ሲሆን ፤ ከእነዚህም ሀገራችን ኢትዮጵያ ፣ እንግሊዝ ፣ ሩሲያ እና ጀርመን ይገኛሉ። የምሥራቅ አውሮጳዋ ሀገር ጆርጂያም መጠሪያ ስያሜዋን ከቅዱሱ ስም ወስዳለች። የዩናይትድ ስቴት አሜሪካ ጦር ጠባቂ ተደርጎ ከመቆጠሩም በላይ ፣ ከከፍተኛዎቹ የጦር ሜዳሎች አንዱ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም የተሰየመ ነው። በዛሬው ትምህርታችንም የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስን ዜና ገድል እንማራለን። በረከቱ ይደርብን የአምላከ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቸርነት አይለየን አሜን።

## ትምህርቱ፡-

www.zeorthodox.org

### ትውልዱና እድገቱ

ቅዱስ ጊዮርጊስ ቀጰዶቅያ በሚባል ሀገር ከክርስቲያን ቤተሰብ ተወልዶ በምግባር እና በሃይማኖት አደገ። አባቱ ዞሮንቶስ አንስታስዮስ እናቱ ደግሞ ቴኦብስታ ይባላሉ። አባቱ በመካከለኛው ምሥራቅ ከቀጰዶቅያ ሲሆን የሮም ዜጋና የቄሣሩ የዲዮቅልጥያኖስ ከፍተኛ ባለሥልጣን ነበር። ዕድሜው ሲደርስም የአባቱን ሹመት ለመቀበል ወደ ንጉሡ ሄደ።

**ዲያብሎስ ያደረበት ዘንዶው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ተሸነፈ**

ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ በሚተርኩ በሁሉም አገሮች ታሪክና ገድል የሚከተለው ዜና ይገኛል፡፡ በዚያን ዘመን በመካከለኛው ምሥራቅ የቤይሩት አካባቢ ሰዎች አረማውያን ስለነበሩ፤ ደራጎን የሚባል ሰይጣን ያደረበት ዘንዶ ያመልኩ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ለዘንዶው በየጊዜው አንዳንድ ሴት ልጅ በየተራ ይገብሩለት ነበር፡፡ ሁሉም ከደረሳቸው በኋላ የአገረ ገዥው ተራ ይደርሳል፡፡

አገረ ገዢውም ሴት ልጁን (አንዳንዶች ደግሞ ሴት አሽከሩን ይላሉ) ወስዶ ለዘንዶው በተዘጋጀለት ቦታ አስቀመጣት፡፡ ዘንዶው ከመድረሱ በፊት ቅዱስ ጊዮርጊስ በዚያ ቦታ ሲያልፍ ልጅቷን አይቶ ለምን እንደታሰረች ጠየቃት፡፡ እርስዋም ሁሉንም ነገረችው፤ አስከትላም ዘንዶው እሱንም እንዳይበላው ከዚያ እንዲርቅ መከረችው፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ የሰይጣን ማደሪያ የሆነውን ዘንዶ እንደማይፈራው እየነገራት ሳለ ዘንዶው /ደራጎኑ/ መጣ፡፡ ምላሱንም እያውለበለበ አንገቱን አስግጎ ጊዮርጊስን ሊበላው መጣ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስም በሥላሴ ስም በትእምርተ መስቀል ሲያማትብ የድራጎኑ ኃይል ደክሞ መርዙም ጠፍቶ ወደቀ፡፡

ወዲያውኑ ልጅቷን ከታሰረችበት ፈትቶ እሷ በታሰረችበት ገመድና በመቀነቷ የዘንዶውን አንገት አሰረው፡፡ ከዚያም ልጅቷ እየሳበችው ወደ ከተማ ይሄዱ ጀመር፡፡ ዘንዶውንም ያየ ሰው ሁሉ እየሸሸ ገሚሱ ዛፍ ላይ ይወጣ ጀመር፡፡ ገሚሱ ደግሞ ወደ የቤቱ እየገባ በየስርቻው ተደበቀ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስም ሰዎቹን ሁሉ ሰብስቦ እንዳይፈሩ አደፋፈራቸው፡፡ በክርስቶስ አምነው የሚጠመቁ ከሆነ እሱ ዘንዶውን እንደሚገድለው አረጋገጠላቸው፡፡ ዘንዶውንም በጦር ወግቶ ገደለው፡፡ የዘንዶውንም ሬሳ ወደ ዱር ወስደው ጣሉት፡፡ ያን ዕለት ከአገረ ገዥው ጋር ዐሥራ አምስት ሺሕ ሰዎች አምነው ተጠመቁ፡፡

**የንጉሡ ዓዋጅ እና የቅዱስ ጊዮርጊስ መልስ**

በወቅቱ የነበረው ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ሰውን ሁሉ በተለይም በመንግሥቱ ውስጥ ይሠሩ የነበሩትን ክርስቲያኖች ጣዖት እንዲያመልኩና ለጣዖታት እንዲሰዉ ያስገድድ ነበረ፡፡ ጊዮርጊስም ይህን አይቶ አዝኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ የተመሰከረለት ክርስቲያን እንደመሆኑ ወደ ሀገሩ ተመልሶ በሰላም መኖር ይችል ነበር፡፡ ሆኖም በወንጌል ***"እንዲት ገና ቀርታሃለች፤ ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው.........እውነት እላችኋለሁ፥ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ቤትን ወይም ወላጆችን ወይም ወንድሞችን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን የተወ ፥ በዚህ ዘመን ብዙ እጥፍ በሚመጣውም ዓለም የዘላለምን ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም አላቸው።"*** /ሉቃ.፲፰፥፳፪-፴/ ያለውን የጌታችንን ቃል አስቦ ሀብቱን ንብረቱን ለድኾች አከፋፈለ ፡፡

www.zeorthodox.org

*‹‹በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ እኔም በሰማያዊው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፡፡››* /ማቴ.፲፥፴፪/ የተባለውን ቃል ለመፈጸም ቅዱስ ጊዮርጊስ ወደ ዲዮቅልጥያኖስ ፊት ቀርቦ ክርስቲያን መሆኑን ፣ ሰው ሁሉ ጣዖት እንዲያመልክ የወጣውን ዓዋጅ እንደማይቀበልና በኢየሱስ ክርስቶስ በሙሉ ልብ እንደሚያምን ገለጠለት፡፡ ንጉሡም ቅዱስ ጊዮርጊስን አባቱ ከነበረው እጅግ የበለጠ ሹመት እንደሚሰጠው ተስፋ ሰጥቶ፤ ጊዮርጊስ ክርስቶስን እንዲክድ፣ በጣዖት እንዲያመልክና ለጣዖት እንዲሠዋ አባበለው፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን ጣዖት የሰው እጅ ሥራ ስለሆነ በእሱ ፈጽሞ እንደማያመልክ ሳይፈራ መሰከረ፡፡

## የሰማዕትነት ተጋድሎ

ቅዱስ ጊዮርጊስ በማባበል እንዳልተሳካለት የተገነዘበው ንጉሥ በልዩ ልዩ የማሰቃያ መሣሪያ በጭካኔ እያሰቃዩ ወደ አምልኮ ጣዖት እንዲመልሱት ሹማምንቱን አዘዘ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን ያወረዱበትን ስቃይ በትዕግሥት አሸነፈ፡፡ ስለ ጌታችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት እና አዳኝነትም አብዝቶ መመስከሩን ቀጠለ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በስቃዩና በመከራው ያበረታውና ከቁስሉም ይፈውሰው ስለነበር ብዙ ሰዎች ይህን እያዩ ክርስቲያን ሆኑ፡፡

ከዚያም ንጉሡ ጠንቋይ አስጠራና ኃይለኛ መርዝ አጠጥቶ እንዲገድለው አዘዘ፡፡ ጠንቋዩም ወዲያው የሚገድል መርዝ በጥብጦ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ሰጠው፡፡ ጊዮርጊስም በመስቀልኛ ባርኮ መርዙን ጠጣው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***“ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉዋቸዋል.......... የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ፡፡”*** /ማር.፲፮፥፲፯-፲፰/ እንዳለው ቅዱሱ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ፊቱ ፈክቶ ሲያበራ ታየ፡፡ በዚህ ጊዜ ጠንቋዩ በቅዱስ ጊዮርጊስ አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ እና መስክሮ በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡

በዚህ የተበሳጨው ንጉሠ ነገሥት ዲዮቅልጥያኖስ በብዙ ስቃይ ሰማዕቱ ጊዮርጊስ እንዲሞት አደረገ፡፡ ሆኖም ቅዱስ ጊዮርጊስ በእግዚአብሔር ኃይል ተነሥቶ እየተዘዋወረ ያስተምር ጀምር፡፡ ብዙ ተአምራትም እያደረገ ሕዝቡን ወደ ክርስቶስ ማረከ፡፡ በአንድ ወቅት ልጅዋ ሕመምተኛ ከሆነባት አንዲት ደሃ ቤት ወስደው ቅዱሱን አሰሩት፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ የታሰረበት ምሰሶ ለመለመ፡፡ ሕመምተኛዋን ልጅ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከሕመሟ ፈወሳት፡፡ የእናቷም ቤት በበረከት ተሞላ፡፡ በዚህ ጊዜ ያቺ ድሃ እናት በቅዱስ ጊዮርጊስ አምላክ አመነች፡፡

www.zeorthodox.org

ንጉሡም የሚያደርገውን ቢያጣ በሰላም ወደ ሰማዕቱ ቀርቦ ‹‹ለጣዖት የሠዋህ ዕጣንም ያጠንክ እንደሆነ ልጄን እድርልሃለሁ›› በማለት ያባብለው ጀመር፡፡ ጊዮርጊስም በንጉሡ ሐሳብ የመስማማት ዝንባሌ ያሳየ መሰለ፡፡ ንጉሡም በዚህ እጅግ ተደስቶ ቅዱስ ጊዮርጊስን ወደ ቤተ መንግሥቱ

ከአስገባው በኋላ ንጉሡ የከተማውን ሕዝብ ሊሰበስብ ወደ ውጭ ወጣ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ሆኖ እየጮኸ ወደ ፈጣሪው ይጸልይ ጀመር፡፡ ንግሥቲቱም ሲጸልይና መዝሙራትን ሲዘምር ስታይ የሚናገረውን እንዲያብራራላት ጠየቀችው፡፡ ቅዱሱም ስለ ክርስቶስ ወንጌል አስተማራት፤ እርሷም በትምህርቱ ልቧ ተነክቶ በክርስቶስ አመነች፡፡ ንጉሡ በዚህ ነገር ይበልጥ ተበሳጭቶ ንግሥቲቷ ሚስቱ ወዲያውኑ በሰይፍ ተቀልታ እንድትሞት አደረገ፡፡

ጣዖት አምላኪው ንጉሥ ለማሰቃያ በተዘጋጀ መሣሪያ (መንኮራኩር) የቅዱስ ጊዮርጊስ ሥጋ እና አጥንት እንዲፈጭ እና አመድ ሆኖ እንዲበተን አዘዘ፡፡ በዚሁም መሠረት ቅዱስ ጊዮርጊስን በምስማር ጫማ ! በማስኬድ፣ በጋለ ብረት ላይ እርቃኑን አስረው በማስተኛት፣ ከሥር እሳት እያነደዱ ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስን ክደህ ጣዖት አምልክ›› አሉት፡፡

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው ምሥክር ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን ሀይማኖቱን አልካደም፡፡ ወታደሮቹ የታዘዙትን ለመፈጸም የቅደሱን ሰውነት ቆራርጠው በክፋል በክፍል ካደረጉ በኋላ በተዘጋጀው መሣሪያ /ማሽን/ ፈጭተው ደብረ ይድራስ በተባለ ተራራ ላይ በተኑት፡፡ ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ፤ ለጌታው ለኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሱን አሳልፎ የሰጠው ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን እንደ እምነቱ ጌታችን ተገልጦ ምድር የቅዱሱን አካላት አንድም ሳታስቀር እንድትሰበስብ አዘዘ፡፡ የቅዱሳን የራስ ፀጉራቸው እንኳ እንዲጠፋ የማይፈልግ እግዚአብሔር ቅዱስ ጊዮርጊስን ከሞት አስነሥቶ ለስሙ እንዲመስክር በአሕዛብ ነገሥታት ፊት አቆመው፡፡ በወንጌል ***‹‹በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ÷ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል››*** /ዮሐ. ፲፬÷፲፪/ ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረ፤ በጌታችን ያመነው ቅዱስ ጊዮርጊስም እንደ ጌታውና እንደ አምላኩ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ተነሥቶ አመድ አድርገው የበተኑትን ወታደሮች ቀድሞ ደረሰና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ አምላክነት እና አዳኝነት መመስከር ጀመረ፡፡ በዚህ መንፈሳዊ ተጋድሎውም ብዙዎቹ የሮም ወታደሮች፣ ሕዝቡም ‹‹በቅዱስ ጊዮርጊስ አምላክ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን›› ብለው በሰማዕትነት ዐረፉ፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስ በሕዝቡ ፊት ቆሞ ጣዖታቱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠፉ በከፍተኛ ድምፅ ጮኸ፡፡ ወዲያውኑ እሳት ከሰማይ ወርዶ ጣዖታቱን አቃጠላቸው ፤ መሬትም ተከፍታ የጣዖታቱን አገልጋዮች ዋጠቻቸው፡፡ ይህ የጣዖት ፍቅር ያደረበት ንጉሥ በቅዱስ ጊዮርጊስ እጅግ ተናዶ ልዳ በሚባል ሥፍራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለመጨረሻ ጊዜ አንገቱ በሰይፍ ተቀልቶ (ተቆርጦ) እንዲሞት አደረገ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለሰባት ዓመታት ብዙ መከራዎችን በመታገስ ተጋድሎ ሚያዝያ 23 ቀን በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለደው ቅዱስ ጊዮርጊስ ከ20-27 ዓመቱ መንፈሳዊ ተጋድሎን ፈጽሞአል፡፡ በክርስትና መንፈሳዊ ሥራዎች የሚሠሩት በወጣትነት ዘመን ነው፡፡ ***‹‹ጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ››*** /መክ.፲፪፥፳/

ቅዱስ ጊዮርጊስ በሦስተኛው መቶ ክፍል ዘመን የነበረ የክርስቶስ ምስክር (ሰማዕት) ነው፡፡ ሁለት ጊዜ ሞቶ የተነሳ ሲሆን ፤ ብዙ መከራዎችን በእምነት የተቀበለ ነው፡፡ ጌታችን ‹‹***እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥኃለሁ››*** /ራእ.፪፥፲፩/ እንዳለው በመታመኑ የሕይወትን አክሊል ተቀብሏል፡፡ ለእግዚአብሔር የሚኖረን ታማኝነት በማንኛውም ሁኔታ የሚገለጥ ሊሆን ይገባዋል፡፡

የሚገድልን መርዝ ፣ የገንዘብን ፍቅር ፣ የኃጢአትን ግብዣ በእምነት ድል አድርጎ ቅዱስ ጊዮርጊስ ብዙ ተአምራትን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ፈጽሟል፡፡ እኛም በእምነት የምንጠይቀውን እንድንቀበል ቅዱስ ጊዮርጊስ አርዓያችን ነው፡፡

## ተግባር

- ገድለ ጊዮርጊስን እና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን በማንበብ፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን በመጠየቅ ከቅዱስ ጊዮርጊስ የወጣትነት ሕይወት ተማሩ፡፡

| ***መዝሙር - 1*** | ***ትርጉም*** |
|---|---|
| ጊዮርጊስ ኃያል(2) መስተጋድል | ጊዮርጊስ ኃይለኛ ተጋዳይ ነው |
| ገባሬ ተአምር ኮከበ ክብር(2) | ተአምራት ያደረገ ባለ ብዙ የኮከብ ክብር ነው |

***መዝሙር - 2***

የከበረ ስሙን እንድታስከብር (ዘማሪት ፋንቱ ወልዴ)

***ጥያቄዎች፡-***

www.zeorthodox.org

1. የቅዱስ ጊዮርጊስ እናትና አባት ማን ይባላሉ? ሀገሩ የት ነው? የነበረበት ዘመን መቼ ነው?
2. ቅዱስ ጊዮርጊስ በነበረበት ዘመን፤ ጣዖት በማምለክ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስን እና እምነቱን በመጥላት ያሰቃየው እና እንዲገደል ያደረገው ንጉሥ ማን ይባላል?
3. ቅዱስ ጊዮርጊስ ያደረገውን ተጋሎ፣ የፈጸመውን ተአምራት ከተማራችሁት፣ ተጨማሪ መጻሕፍት በማንበብ እና የቤተ ክርስቲያን መምህራንን በመጠየቅ ጥናት አድርጋችሁ ጽሑፍ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡ (መምህር ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጋቸው)

# ዕርገት

## ሠላሳ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**:- ተማሪዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ስለመነሣቱ፣ ከዚያም ስለ ዕርገቱ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸው ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**:-***"ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ።"*** /ዮሐ.፲፮÷፳፰/

**ተጨማሪ ምንባባት**:- ማር.፲፮÷፲፱-፳፣ ሉቃ.፳፬÷፶-፶፫፣ የሐ.ሥ.፩÷፮-፲፩፣ዮሐ.፲፮÷፳፰-፳፫/

**መግቢያ**:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሠላሳ ሦስት ዓመታት በምድር ተመላልሷል፡፡ በ30 ዓመቱ ተጠመቀ፤ ለሦስት ዓመታት አስተማረ፡፡ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ ቤዛ ሆነልን፡፡ በመስቀል ላይ ሞቶ በተቀበረ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ተገለጠላቸው፡፡ ዛሬም ከማረጉ በፊት ከተነሳ በኋላ ስላስተማራቸው ትምህርቶች እና ደቀ መዛሙርቱን ያዘዛቸውን ትዕዛዛት እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት:-

**ከዕርገቱ በፊት**፡-ጌታችን ከዕርገት በፊት ሓዋርያትን ወደ ቢታንያ ጠርቶ የሚከተሉትን ትእዛዝና ሓላፊነቶች ሰጣቸው፡፡

1. ***ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ*** ፡፡ ማር ፲፮÷፲፭
2. ***ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ፡፡*** የሐዋ.ሥ ፩÷፭
3. ***እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁቸው… አስተምሯቸው፡፡*** ማቴ.፳፰÷፲፱-፳
4. ***"እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"*** የሐዋ.ሥ ፩÷፰

www.zeorthodox.org

ሐዋርያት በወንጌል ለመስበክ እና በስሙ ለማጥመቅ  ወደ ዓለም ሲወጡ ፣ እንደሚገረፉ ወደ ነገሥታት የፍርድ አደባባይም እንደሚያወጧቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነገሯቸዋል፡፡ እስከ መጨረሻው የጸና ግን ይድናል፡፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆንና መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ኃይልን እንደሚያገኙም ጌታችን ቃል ገብቶላቸዋል፡፡

***ታሪኩ፡-*** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በአርባኛው ቀን ደቀ መዛሙርቱን በቢታንያ ወደምትገኘው ደብረ ዘይት ወሰዳቸውና ባረካቸው፡፡ ተሰብስበው ትምህርቱን እየሰሙም ***ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ፡፡ ወደ ሰማይም ዐረገ፤ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረው፡፡*** ደቀ መዛሙርቱ ክርስቶስ ወደ ዐረገበት ቀና ብለው እየተመለከቱ ሳለ ሁለት መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው በአጠገባቸው ቆመው፤ ***"ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይሄ ከናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው፡፡"*** ደቀ መዛሙርቱም ጌታ ካረገበት ከደብረ ዘይት እግዚአብሔርን እያከበሩ እያመሰገኑ ተመለሱ፡፡ እንደታዘዙት መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉም ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩ፡፡

***ቦታው፡-*** ጌታችን ያረገው አልዓዛርን ከሞት ባስነሣበት በቢታንያ ነው፡፡ ይህ ቦታ ከከተማው ጭንቅንቅና ጫኸት ወጣ ያለ ነው፡፡ ይህም ከተጨናነቀውና ሁከት ከበዛበት ዓለም በጸጥታና የሰማዩን ጌታ በማሰብ ብቻ ዕርገትን የምናስብበበትን የተረጋጋ ሕይወት እንድንመርጥ ያስገነዝበናል፡፡

***ጊዜው፡-*** ሕያው ሆኖ ራሱን ለደቀ መዛሙርቱ ካሳየበት ከትንሣኤው ከአርባ ቀናት በኋላ ነው፡፡ ሐዋርያትና ሌሎቹ የክርስቶስ ቤተ ሰቦች ከዚህ በፊት የማያውቁት አዲስ ሕይወትና ልምድ እያዩ ነበር፡፡ በመሆኑም ትንሣኤና ዕርገት የስብከታቸው ዋና ማዕዘን ነበር፡፡ ሕዝቡም ከዚህ በፊት የማያውቁት አዲስ ነገር ነው፡፡ ሕዝቡ ሁሉ የሚያውቀው እያንዳንዱ ሰው ‹‹ይወለዳል ይሞታልም›› የሚለውን ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለዓለም አዲስ ሕይወት ሰጠን፡፡ እርሱም ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ማለት ነው፡፡

## ከምድር በተቃራኒ ወደ ሰማይ መሄድ

አዳምና ሔዋን ከበደሉ በኋላ ከገነት ተሰደዱ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው ሁሉ ሲሞት ሥጋው ወደ መቃብር ነፍሱ ወደ ሲዖል ይሄድ ነበር፡፡ ይህንንም የምድር መንገድ ብለን እንጠራው ነበር፡፡ ነቢዩ ንጉሥ ዳዊት ሊሞት ሲዘጋጅ ልጁን ሰሎሞንን ጠርቶ የንግሥና ሓላፊነቱን አስረክቦት ሥልጣኑን ከሰጠው በኋላ፤ ***"እኔ የምድሩን ሁሉ መንገድ እሄዳለሁ"*** ፩ኛ.ነገሥ.፪÷፪ ብሎታል፡፡ ጌታችን በሥጋ ተገልጦ ድኅነት ሳይፈጸምልን በፊት የሰው ልጆች ሁሉ መንገድ የምድር መንገድ ነበር፡፡ ጌታችን በሐዲስ ኪዳን ***"በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤"*** ዮሐ.14፡2 እንዳለን የገነትን በር ዳግመኛ ከፍቶልናል፡፡ ወንበዴው ‹‹***በመንግሥትህ አስበኝ***›› ባለው ጊዜ ጌታችን፤ ‹‹***ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ***›› ያለው ለዚህ ነበር፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ ታላቅ ተስፋ አዘጋጅቶልናል፡፡ ይህ በዳዊት ***የምድር መንገድ*** ካለው ይለያል፡፡ በጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማይሻር ቃል

www.zeorthodox.org

የተነገረን፤ ‹‹*ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ*›› የሚል ዘላለማዊ ተስፋ አለን፡፡

## የቅዱሳን ሕይወት

ቤተ ክርስቲያን በምድር የሰማይ ኑሮ የኖሩ በርካታ ቅዱሳን አሏት፡፡ የቅዱሳኑ ሕይወት የሚነግረን ጊዜያዊና ሓላፊ የሆነውን የምድሩን መንገድ ዘለዓለማዊ በሆነው በሰማያዊው መንገድ እንድንቀይር ነው፡፡ (መምህር ልጆች የሚያውቋቸውን ቅዱሳን ሕይወት እንዲተርኩ ያድርጉ፡፡) የቅዱሳን ሕይወት በሰማይ ያለውን እግዚአብሔርን በማመን የጥልቁን ጨለማ ሰይጣንን መካድ ነው፡፡ የቅዱሳን ሕይወት ኃጢአትን በጽድቅ ቀይሮ መኖር ነው፡፡ ቅዱሳን ይህንን በክርስቶስ ቸርነት የተገኘ ኑሮ ሕይወታቸው አድርገውት ሰማያዊውን ኑሮ በምድር አሳዩ፡፡

የእግዚአብሔር ልጆች ይህ ለእኛም የተከፈተ መንገድ ነው፡፡ ***"ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤"*** /ቲቶ.፪÷፲፩-፲፫/ ለዚህ ነው ዘማሪው ንጉሥ ዳዊት ***"ወደ ላይ ዓረግህ፥ ምርኮን ማረክህ፥ ስጦታንም ለሰዎች ሰጠህ፥"*** /መዝ.፷፰÷፲፰/ ያለው፡፡ የሰማዩ መንገድ የተከፈተልን እኛ በጽድቅና በቅድስና እንድንመላለስ ታድለናል፡፡

## ማጠቃለያ

መንፈሳዊ በዓላት መታሰቢያ ከመሆን በላይ ሱታፌ ናቸው፡፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓላት ስናከብር በበዓሉ ክርስቶስ የሰጠንን ኃይልና ጸጋ እናስባለን፡፡ እያንዳንዳችን በዚህ በተሰጠን የልጅነት ሀብትና ክብር ‹‹አለሁ›› ብለን ራሳችንን በመመርመር ለመንፈሳዊ እድገት መዘጋጃ ናቸው፡፡ ይህን በማድረግ ራሳችንን በጸሎትና በንስሓ ካዛጋጀን በዓላት ተራ አከባበር ብቻ ሳይሆኑ ሃይማኖታዊ ሱታፌዎችም ይሆናሉ፡፡

ጌታ ከተነሣ በኋላ በአርባኛውን ቀን ሐዋርያትን እያስተማረና እያዘዘ ቆየ፡፡ የሚያገኛቸውንም መከራ ነገራቸው፡፡ የሚጸና ዘላለማዊ ሕይወት እንደሚያገኙም ቃል ገባላቸው፡፡ በደብረ ዘይት ሐዋርያት ሰብስቦ አስተማራቸውና ባርኳቸው ዐረገ፡፡

www.zeorthodox.org

ከዓለም ርኩሰት ፣ ዝሙት ፣ ሐሰት ፣ ጥላቻና ክፉ ሥራ ርቀን ከእግዚአብሔር ጋር በመሆን የምናገኘውን ጣፋጭ ሕይወት በእምነት እንቅመሰው፡፡ ያኔ ቅዱሳን በምድር የኖሩትን ሰማያዊ ሕይወት እናረጋግጣለን፡፡

እንደ ክርስቲያን ምስክሮች ልንሆን ተጠርተናል፡፡ ምስክርነትም መናገር ብቻ ሳይሆን ትዕዛዛቱን መጠበቅ ነው፡፡ ‹‹***ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ፤***›› /ማቴ.፳፰÷፳/

በዚህ ምድር ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛውን ሕይወት የኖረ በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር ሐዘንና ስቃይ የሌለበትን ዘላለማዊ ሕይወት ይመራል።

## ተግባር

ምድራዊ ኑሮን በሰማያዊ ኑሮ ለውጠው የኖሩትን የአባ ሙሴ ጸሊም እና የዘኬዎስ ታሪክ አጥንታችሁ አቅርቡ።

በኢየሩሳሌም መቆየት ምን ዓይነት መንፈሳዊ ትርጉም አለው? ጠይቃችሁ ጽሑፍ በማዘጋጀት በሚጥለው ሳምንት በክፍል አቅርቡ።

***ጥያቄዎች፡-***

1. ጌታችን መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ሐዋርያትን ወደ ቢታንያ ጠርቶ የሰጣቸው ትእዛዞችና ሓላፊነት ምን ምን ናቸው?
2. ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ወደ ቢታንያ ጠርቶ የባረካቸው ቦታ ማን ተብሎ ይታወቃል? ይህን ያደገው ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በስንተኛው ቀን ነው? በቦታው ምን ተደረገ ?

www.zeorthodox.org

# ጰንጠቆስጤና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች

# ሠላሳ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**:- ተማሪዎች የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ምን እንደሆነ፤ መንፈስ ቅዱስ በአማንያን ሕይወት ያለውን በጎ ተጽዕኖ ያውቃሉ፤መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ።

**የሚጠና ጥቅስ**:-*"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር ፣ ደስታ ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት ፣ ራስን መግዛት ነው።"* ገላ. ፭÷፳፪-፳፫

**ተጨማሪ ምንባብ**:- ኤፌ.፩÷፲፯-፲፰፣ ገላ.፭÷፳፪-፳፫፣ ሮሜ.፬÷፲፯

**መግቢያ**፡- መቶ ሃያው የክርስቶስ ቤተሰቦች (ዐሥራ ሁለት ሐዋርያት፣ ሰባሁለቱ አርድዕትና ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት እንስት) እመቤታችን ባለችበት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉበት ዕለት ጰንጠቆስጤ ይባላል።

በዛሬው ትምህርታችን ስለጰንጠቆስጤ ቀን፣ ታሪክ እና ስለሐዋርያት አገልግሎት አጀማመር እናያለን። ከዚሁም ጋር ይህንን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስንቀበል ሊታይብን ስለሚገባው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች እንማራለን።

መምህር በምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን በሚታይ አገልግሎት ስለሚገኘው የማይታይ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተማሩትን ይከልሱላቸው።

## የሳምንቱ ትምህርት

### ጰንጠቆስጤ

ጰንጠቆስጤ ሃምሳኛው ቀን ማለት ነው። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉበት ዕለት ክርስቶስ በተነሣ በሃምሳኛው ቀን ስለነበረ ነው። ደቀ መዛሙርቱ በማርቆስ እናት ቤት ተሰብስበው ነበር። እመቤታችንና ሌሎችም ከእነርሱ ጋር ነበሩ። አንድ መቶ ሃያ ያህሉም በአንድ ልብ ይጸለዩ ነበር ።

www.zeorthodox.org

#### የመንፈስ ቅዱስ መውረድ

በድንገትም እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ የነበሩበትን ቤት ሞላው። በእያንዳንዳቸውም ላይ መንፈስ ቅዱስ በእሳት ላንቃ አምሳያ ወረዳባቸው። በተለያየ ቋንቋ መናገር ጀመሩ።የአይሁድን በዓለ ፋሲካ ለማክበር የተሰበሰቡና ከተለያዩ ሀገሮች የመጡ ሰዎች ነበሩ፤ በየራሳቸው ቋንቋ ሲናገሩ ሰምተው ተደነቁ።

**የመጀመሪያዎቹ አገልግሎቶች**

አንዳንዶቹ ግን የወይን ጠጅ ጠጥተዋል ብለው አጉረመረሙ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ከዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ጋር ተነሥቶ የተሰበሰቡትን አስተማረ፡፡ አሁን የሚያዩትና ከዚህ በፊት የተመለከቱት በሙሉ በነቢያት የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን አስረዳቸው፡፡ ከዳዊት መዝሙርም ስለክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት የተነበየውን ጠቅሶ አስተማረ፡፡ ምን እናድርግ? ሲሉትም ***"ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፡፡"*** አላቸው፡፡ በዚህ ቀን ሦስት ሺሕ ሕዝብ አምኖ ተጠመቀ፡፡ ሁሉም በወንድማማችነት፣ በኅብረትና በጸሎት አንድ ልብ ሆነው መኖር ጀመሩ፡፡ ይህም ክርስቶስ እንዲህ ሲል የነገራቸው ፍጻሜ ነበር፡፡***"የመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉኣቸዋል፣በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ በአኛ ቋንቋ ይናገራሉ፡፡"*** ማር.፲፮÷፲፯-፲፰ ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ፣ ወንጌልን ሰበኩ፣ ስለ ክርስቶም መሰከሩ፡፡ ዓለም አልተገባቸውምና - ታሰሩ፣ ተፌዘባቸው፣ ተገረፉ፣ ተንገላቱ፤ እነርሱ ግን በስሙ መከራ በመቀበላቸው ደስተኞች ነበሩ፡፡ እስከ ሞትም ታምነው መሰከሩለት፡፡

**የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ**

ትክክለኛ ክርስቲያንን ስታስተውሉ፤ ክርስቲያን ካልሆነውና በስም ብቻ ክርስቲያን ከሆነው ሰው በአስተሳሰቡ፣በጠባዩና በአኗኗሩ ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡

በእውነተኛ ክርስቲያኖች ዘንድ የሚታዩት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የሚባሉት ናቸው፡፡ አሁን የምንነጋገርባቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ፡- በገላትያ የተጠቀሱት "***የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው፡፡›››*** ገላ. ፭÷፳፪ -፳፫ እና በኤፌሶን የተገለጠው ***"የክብር አባት….እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ፡፡ ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንደሆነ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ፤ ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤"*** /ኤፌ ፩÷፲፯-፲፰/ ናቸው፡፡

(ሀ) **በገላትያ መልእክት ምዕ.** ፭÷፳፪-፳፫ **የተገለጡት ፍሬዎች** እነኚህ በኔና በእናንተ ውስጥ ያሉ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ናቸው፡፡ ይሄም አስተሳሰባችንን፣ ፍላጎቶቻችንን፣ ጠባያችንና ኑሮአችንን የሚዳስስ ነው፡፡ እነዚህ ፍሬዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ፍቅር**፡- የጽድቅ ሁሉ መሠረት *ነው፡፡* ***"ፍቅር ይታገሣል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፣ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፣ የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣***

www.zeorthodox.org

***አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥርም፣ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፣ ሁሉን ይታገሣል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል፡፡››*** ፩ኛ ቆሮ ፲፫÷፬-፯

**ደስታ፡-** የክርስትና ዋና ግብ የሰው ልጅ ደስታ ነው፡፡ ወንጌል ማለትም "የምስራች" — "የደስታ ዜና" ማለት ነው፡፡ ***"በጌታ ደስ ይበላችሁ፡፡"*** ፊልጵ. ፬÷፬

**ሰላም፡-** ከደስታ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ***"የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት"*** ሮሜ ፲፬÷፲፯ ፍቅርና ደስታ በአማንያን ልቦና ሰላምን ይሠጣሉ፡፡

**ትዕግሥት፡-** በንዴት ምክንያቶች አለመቆጣት፣ መረጋጋት፣ ሌሎች የሚያደርጉትን ክፉ ድርጊት መቻልና ማለፍ፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን፣ ፈተናዎችን በተረጋጋ መንፈስ ሆኖ በማስተዋል በመቀበል፤ በጸሎት ጸንቶ ችግሮቹን ለማቃለል ፈተናዎችን ለማለፍ መፍትሔ መፈለግ ጥረት ማድረግ ናቸው፡፡ ጌታችን ትዕግሥትን በትክክል ያሳየን ምሳሌያችንም ነው፡፡

**ቸርነት፡-** የቁጣ ተቃራኒ ነው፡፡ **"እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት፤ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፤ በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፤ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ"** ሮሜ.፲፩÷፳፪ ***"እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፣ ምሕረትን፣ ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ የዋህነትን፣ ትዕግሥትን ልበሱ፡፡*** ቆላ ፫÷፲፪

**በጎነት፡-** ቸርነት ለበጎነት ያዘጋጀናል፤ ***"ወንድሞቼ ሆይ፣ በበጎነት ራሳችሁ እንደተሞላችሁ ዕውቀትም ሁሉ እንደሞላባችሁ፣ እርስ በርሳችሁም ደግሞ ልትገሠጹ እንዲቻላችሁ ስለ እናንተ ተረድቼአለሁ፡፡"*** /ሮሜ ፲፭÷፲፬/

**እምነት፡-** ትክክለኛ እምነት የበጎ ሕይወት መሠረት ነው፡፡ ***"ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና፡፡"*** ዕብ.፲፩÷፮

www.zeorthodox.org

**የውሃት፡-** የውሃት አንድ ሰው ጥፋተኛ መሆኑንም እያወቀን አለመፍረድ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዋህ እንድንሆን ሲያስተምረን፡፡ ***"ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፡፡"*** ብሎአል፡፡

***ራስን መግዛት፡-*** ኃጢአት ከመሥራት ራስን መግዛት (መጠበቅ) ነው፡፡ ***"ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፣ በበጎነትም ዕውቀትን፣ በዕውቀትም ራስን መግዛትን፣ ራስንም በመግዛት መጽናትን፣ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፣ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፣***

*በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።"* ፪ኛ ጴጥ ፩÷፫

(ለ) **በኤፌሶን ፩÷፲፯-፲፰ የተገለጠው ፍሬ** በእውነተኛው ክርስቲያናዊ ሰብዕና ጥበብና መገለጥ አሉ። እነዚህም አንድ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔር እንዲመሰክርና በእግዚአብሔር ክብርና ጸጋ እንዲኖር ያስችሉታል። ይህም በምድር ሰማያዊ ሕይወትን እንዲያጣጥም ያደርጉታል ማለት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጠውም ***"የክብር አባት....እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንደሆነ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤"*** ኤፌ ፩÷፲፯-፲፰

## ማጠቃለያ

(1) ስንጠመቅ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል ከታዘዝንና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የቀና ሕይወትና ኅብረት ካለን ከላይ የተገለጡት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የእኛ ይሆናሉ።

(2) በቤተ ክርስቲያን ያለፉትን ቅዱሳን ስንመለከት ታላላቅ በረከቶችን ሲቀበሉና የመንፈስ ቅዱስን ፍሬዎች በሕይወታቸው ሲያፈሩ እናስተውላለን። ለዚህም ነው ሻማ ከሥዕሎቻቸው ስር የምናበራው። ሻማና ጧፍ ከተጋገረ ቅባት ይዘጋጃሉ። ቅባቱ (ዘይቱ) የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። እሳቱ ሲቃጠል፣ ቅባቱ ይቀልጣል። ብርሃንም ይገኛል። (ማለትም ከመልካም ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ይገኛል።)

## ተግባር

- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን በሕይወት ግለጡ።

***ጥያቄዎች:-***

1. አንድ መቶ ሃያው የክርስቶስ ቤተሰቦች እነማን ናቸው?
2. አንድ መቶ ሃያው የክርስቶስ ቤተሰቦች መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉበት ቀን ምን ይባላል? ትርጉሙን እና በዕለቱ የተደረገውን ግለጹ።
3. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ምን ምን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ዐፄ ካሌብ እና ሀገረ ናግራን
# ሠላሳ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች በሀገረ ናግራን ስለነበሩ ክርስያኖች እና ስለደረሰባቸው መከራ ታሪክ ያውቃሉ፤ በማንኛውም ደረጃ እና ሁኔታ ላይ ሆኖ መልካም ነገርን ማድረግ፣ የተቸገሩትን መርዳት ማዳን፣ ማገልገል እንደሚገባ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና፤ ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቁጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና።"*** */ሮሜ.፲፫፥፫-፩/*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ‹‹የናግራን ሰማዕታት›› በዲ/ን ዳንኤል ክብረት

**መግቢያ፡-** የዛሬው ትምህርታችን ዓለም አቀፋዊ ታሪክ ስላለው አንድ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ነው። ይህ ንጉሥ ዐፄ ካሌብ ይባላል። ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተጨማሪ የሮማ ካቶሊክና ኦርቶዶክሳውያን የቅድስና ማዕረግ ሰጥተው ያከብሩታል።

## የሳምንቱ ትምህርቱ

### ናግራን አይሁድና ክርስትና

ናግራን እስከ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ በደቡብ ዐረቢያ የሚገኝ የኢትዮጵያ ግዛት ነበር። በአካባቢው ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ ክርስቲያኖች ይኖሩ ነበር። /ገላ.፩÷፯/።

እነዚህ ክርስቲያኖች ቀድሞ በአክሱም ግዛት ሥር ነበሩ። በተለይም ዐፄ ካሌብ በነገሠበት ጊዜ በደቡብ ዐረቢያ የነበረው የአኩስም ግዛት ተስፋፍቶ ዛፍርና ናግራን በተባሉ ቦታዎች የመንግሥት ሠራዊት ነበር።

www.zeorthodox.org

የአኩስም መንግሥት በአካባቢው ከነበረው ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ተግባር ባሻገር ክርስትናን ለማስፋፋትም ከፍተኛ ጥረት ያደረግ ነበር። ነገር ግን በዙሪያው ያሉት ጣዖት አምላኪዎችና አይሁድ ይህንን የአኩስም ግዛትና የክርስትናን መስፋፋት በብርቱ ይቃወሙት ነበር።

ጥጦስ በ፸(70) ዓ.ም ኢየሩሳሌምን ሲያጠፋ የተሰደዱ አይሁድ በደቡብ ዐረቢያ በብዛት ሰፍረው ነበር። በየጊዜውም /በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን/ ቁጥራቸው እየጨመረ ኃይላቸው እየጠነከረ መጣ።

የኢትዮጵያን መንግሥት ያልተቀበሉት የአካባቢው ገዥዎች ይሁዲነትን ተገን አድርገው እንቅስቃሴ ጀመሩ። በአይሁድና በክርስቲያኖች መካከልም ውዝግብ እየከረረ መጣ የአካባቢው የአኩስም ወኪል መሪ ዱሕን ዋስ /ፊንሐስ/ ክርስትናን ትቶ ወደ ይሁዲነት ተቀየረ።

### በክርስቲያኖች የደረሰው መከራ

የዚህም ምክንያት ራሱን ቻለ መንግሥት ለመመሥረት በነበረው ፍላጎት መሆኑን ታሪክ ጸሐፊዎች ይስማሙበታል። ሃይማኖቱን የለወጠው ፊንሐስ በ፭፻፲፰/፲፱(518/19) ዓ.ም ላይ በክርስቲያኖች ላይ በጠላትነት ተነሣ። በዚሁ ዓመትም አራት ሺሕ ሁለት መቶ ሃምሳ ክርስቲያኖችን አረደ። አብያተ ክርስቲያናትንም አፈረሰ።

ከዚያም ናግራን ከተማን ከብቦ በዚያ የነበሩትን ክርስቲያኖች ያስጨንቅ ጀመር። ሁኔታውን በሰላም ለመፍታት ያሰቡት የናግራን ክርስቲያኖች የሰው ሕይወት እንዳይጠፋና እነርሱም በሰላም እንደሚገብሩለት ቃል ገብተውና አስገብተው ከተማውን ከፈቱለት። ፊንሐስ ለጊዜው በቃሉ ከረጋ በኋላ መንግሥቱ ሲደላደልለት ክርስቲያኖችን ማረድና አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠል ጀመረ።

በናግራን ከተማ ጉድጓድ አስቆፍሮ እሳት እያነደደ ክርስቶስን አንክድም ያሉትን ሁሉ በእሳቱ ውስጥ እየጨመረ ፈጃቸው። የናግራን ገዢና 95 ዓመት ሽማግሌ የነበረውን ጊሩት ***« ይህን ሁሉ ያመጣብህ ክርስቶስን ማመንህ ነውና ካድ »*** ሲል ጠየቀው። ሽማግሌው ጊሩት ግን ***«አታላዮች ይክዱሉ እንጂ መንግሥታት ውላቸውን እና ማሃላቸውን ፣ሃይማኖታቸውንም አሁን አንተ ይህቺን ከተማ አላጠፋትም ብለህ እንደካድክ አይክዱም»*** ሲል መለሰለት። በዚህም ጊሩት አንገቱን ተከልሎ (ተቆርጦ) ዐረፈ።

### የክርስቲያኖች መልስ

በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው ግፍ በመላው ክርስቲያኑ ዓለም ሲሰማ ድንጋጤን ፈጠረ። የሮሙ ንጉሥ ጁስቲያን ፩ኛ ለግብጹ ፓትርያርክ ጢሞቴዎስ ሦስተኛ ፭፻፲፰-፭፻፴፭/518-535/ ዓ.ም የኢትዮጵያን ንጉሥ ለምነው ክርስቲያኖችን እንዲያድኑ ደብዳቤ ጻፈላቸው።

www.zeorthodox.org

በደቡብ ዐረቢያ የነበሩ ክርስቲያኖችም ለዐፄ ካሌብ የድረሱልን ጥሪ አሰምተው ነበር።

### የዐፄ ካሌብ ዝግጅት

ሥልሳ መርከቦች ከየወደቡ ተሰበሰቡ። ሰባ ታላላቅና ታናናሽ መርከቦች በአዶሊስ ወደብ ተገነቡ። 120000 ሠራዊት ታጥቆ ተዘጋጀ። በአጠቃላይ የጦርነት ዝግጅቱ አንድ ዓመት ያህል ወሰደ። አንድ መቶ ሃያ ሺሕ ሠራዊት በ240 መርከቦች ተጭኖ ገበዛን በሚባል ከጥንቷ አዱሊስ ብዙ በማይርቅ ወደብ ላይ በተጠንቀቅ ቆመ።

ከጉዞው በፊት ዐፄ ካሌብ ወደ አክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ጸሎት አደረገ፡፡ /የጸለየው ጸሎት ግንቦት ፳(20) በሚነበበው ስንክሳር ተጽፏል፡፡/ ከዚያም ወደ አባ ጰንጠሌዎን ዘንድ ሄዶ በጸሎታቸው እንዲያስቡት ጠየቃቸው፡፡ በ፭፻፳፫(523) ዓ.ም ከበዓለ ጰራቅሊጦስ በኋላ ሠራዊቱ ከገበዛን ወደብ ተንቀሳቀሰ፡፡

ፊንሐስ የአክሱምን ጦር አመጣጥ ስለተረዳ የደቡብ ዐረቢያን ወደቦች በሰንሰለት አጠራቸው፡፡ ሠራዊቱንም በተጠንቀቅ ወደቡ ላይ  አስቀመጠ፡፡

የዐፄ ካሌብ ሠራዊት ንክሃ በተባለ ወደብ ደረሰ፡፡ ዐፄ ካሌብ ከመርከቦቹ ዐሥራ ሁለቱን ለይቶ በመውሰድ ወደ ምሥራቅ ተጉዞ በሌላ ወደብ ለማረፍ አቀደ፡፡ ፊንሐስ ሁኔታው ስለገባው ጦሩን ወደዚያ አቅጣጫ አንቀሳቀሰ፡፡ በዚህ መሐል የኢትዮጵያ ጦር በምግብና በንጹሕ ውኃ እጥረት መንገላታት ጀመረ፡፡ በውቅያኖሱ አጠገብ የሰፈረው የፊንሐስ ጦርም ሙቀቱን መቋቋም አቃተው፡፡

## ጦርነትና ድል

ዐፄ ካሌብ ወደ ምሥራቅ በወሰዳቸው ዐሥራ ሁለት መርከቦች አማካኝነት ከፊንሐስ ጦር ጋር ውጊያ ገጥሞ መሬት ላይ ለመድረስ ቻለ፡፡ የፊንሐስን ሠራዊትም ወደኋላ እንዲያፈገፍግ አደረገው፡፡

በዚህ ጊዜ የፊንሐስ ሠራዊት በሁለት ወገን ተወጠረ፡፡ ከምድርና ከባሕር በሁለት በኩል የተወጠረው ፊንሐስ መሸነፉን ሲረዳ ወደመሐል ዐረቢያ ተራሮች ሸሸ፡፡ ዐፄ ካሌብ በድል አድራጊነት ወደ ዛፋር ከተማ ገባ፡፡ አብያተ ክርስቲያናትን እንደገና እንዲታነጹ አደረገ፡፡ ሕዝቡንም አጽናና ፡፡

አስዋ የተባለውን በትውልዱ ሂምርያት በእምነቱ ክርስቲያን የሆነውን በአካባቢው ገዢ አድርጎ ሾመው፡፡

በአካባቢውም የተወሰነ የንጉሡ ሠራዊት እንዲሰፍር አድርጎ ወደ አኩስም ተመለሰ፡፡

### ዳግመኛ ጦርነት ተቀሰቀሰ

ፊንሐስ የንጉሥ ካሌብን መመለስ ሲሰማ ከተደበቀበት ወጥቶ ኃይሉን በማስተባበር ክርስቲያኖችን ለመውጋት ተነሣ፡፡ በቦታው ከሰፈረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር መዋጋት ጀመረ፡፡ ጉዳዩ በአክሱም ቤተ መንግሥት ሲሰማ ዐፄ ካሌብ ለሁለተኛ ጊዜ በ፭፻፳፭(525) ዓ.ም ወደ ዐረቢያ ዘመተ፡፡ በዚህ ጦርነት ፊንሐስ ከሁለት ወገን ተወጠረ፡፡ ከውስጥ በዛፋር ከሚገኘው የኢትጵያ ጥብቅ ጦር ጋር፣ ከባሕር በኩል ደግሞ ከንጉሥ ካሌብ ጦር ጋር ገጠመ፡፡

የንጉሡ ሠራዊት አለቃ አብርሃ ደግሞ ዐሥር ሺሕ ሠራዊት ይዞ ሃድረማውት በሚባል ወደብ በኩል በመግባት ሌላ ውጊያ ከፈተ፡፡ በዚህ ጊዜ ፊንሐስ ፈጽሞ ተስፋ ቆረጠ፡፡ እናም ወደ ቀይ ባሕር ጋልቦ ራሱን ባሕር ውስጥ አስጥሞ ሞተ፡፡ የፊንሐስ ሠራዊት ፈጽሞ ድል ከሆነ በኋላ አብርሃ

www.zoorthodox.org

የአካባቢው ገዢ ሆኖ ተሾመ፡፡

ሥርዓተ ንግሡ በዛፋር በነበረችው በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ፡፡ ዐፄ ካሌብም በዛፋር ከተማ አርባ ሦስት ቀናት ተቀምጦ መንግሥቱን አረጋጋ፡፡ አምስት ሺሕ ሠራዊት በቦታው ትቶ በአርባ አራተኛው ቀን ወደ አኩስም ተመለሰ፡፡ ይህ የሀገረ ናግራን ሰማዕታት በዓል በቤተ ክርስቲያናችን ግንቦት ፳(20) ቀን ይከበራል፡፡

ዐፄ ካሌብን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አክብራ ታስባቸዋለች፡፡ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም በጥቅምት (October 27) ቀን በየዓመቱ ታከብራቸዋለች፡፡

## ማጠቃለያ

ዐፄ ካሌብ በስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡ ኢትዮጵያዊ መሪ ናቸው፡፡ ጥበበኛ ንጉሥ ፣ ባለድል የጦር መሪና ዓለምን ትተው የመነኑ ባሕታዊ ናቸው፡፡ ግፈኞችን ታግለው ድል ያደረጉት ዐፄ ካሌብ በመልካም ሥራቸው የተከበሩና የቅድስና መዓርግ የተሰጣቸው ታላቅ የኢትዮጵያ መሪ ነበሩ፡፡

### ተግባር

ለቃላችሁ ታማኝ ሁኑ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ሀገረ ናግራን የት ይገኛል የማን ግዛት ነበር?
2. በናግራን ክርስቲያኖች ላይ የደረሰባቸው መከራና ምክንያቱ ምን ነበር?
3. በናግራን የነበሩትን ክርስቲያኖች የድረሱልን ጥሪ ሰምቶ ያዳናቸው ማን ነው?
4. ስለዚህ መሪ ማንነትና የመጨረሻ ሁኔታ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# እኔነት

## አርባኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ሕይወትን ለእግዚአብሔር በማስገዛት ለሌሎች በጎ በማሰብ እና መልካም በማድረግ የሚገኘውን ጸጋና ክብር ያውቃሉ፤ በእኔነት መንፈስ የራስ ወዳድነትን ክፉ ውጤትና ውድቀት ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** **‹‹እኔ አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፡፡›› /**ገላ.፪፥፳/

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሉቃ.9 23-26

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በራሳችን በድሎቻችን ላይ ማተኮርና መመካት በፍጹም አይገባም፡፡ ይልቁንም የረዳንን የእግዚአብሔርን ስም ልናከብር ይገባል፡፡ በሕይወታችን፣ በምድርም በሆነ በሰማይ አሸናፊዎች እንድንሆን በድርጊቶቻችን ሁሉ ራስ ወዳድ እና ለእኔ ብቻ ባዮች መሆን የለብንም፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር በዛሬው ትምህርታችን ስለዚህ ጉዳይ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

‹‹እኔ›› በማለት ላይ ከማተኮር የበለጠ ሰውን የሚጎዳ ነገር የለም፡፡ ሰው ‹‹ለኔ›› ብቻ በማለት ላይ ሲያተኩር የወደፊት ዕድሉን፣ ሥራውን፣ ዕየታውንና ትርፉን ከማጣቱም በተጨማሪ ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር ያለውን አንድነትና ግንኙነት ያበላሻል፡፡ በዚህም ራሱን ያጣል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ **‹‹እኔ አልኖርም. . . ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል››** እንዳለው፡፡ ስንጠመቅ ‹‹ራሳችንን ክደን›› በክርስቶስ እና እንደ ክርስቶስ መኖርን ጀምረናል፡፡

www.zeorthodox.org

‹‹**እኔ አልኖርም**›› የሚለው ቃልም የሚያስተምረን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን ማለትን ነው፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይከተላል እንጂ የራሱን ሐሳብ ብቻ አይከተልም፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንን ፈቃዱን ማዳመጥና መከተል አለብን፡፡ ሎጥ ለራሱ ሲመርጥ አብርሃም ምርጫውን ለእግዚአብሔር ትተው ያገኙትን አስታውሱ፡፡ /ዘፍ.፲፫፥፩ እስከ ፍጻሜው ምዕራፍ/

በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ አብዛኞቹ ግጭቶችና ችግሮች መነሻቸው ‹‹እኔ-እኔ›› ማለት ነው፡፡ የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ሲመለስ ታላቅ ወንድሙ ያለውን አስታውሱ፤ **‹‹ይህን ያህል ዓመት እንደ ባርያ ተገዝቼልሃለሁ. . . ለእኔም ደስ እንዲለኝ አንድ ጠቦት አላረድክልኝም. . .››** /ሉቃ.፲፭፥፳፱/፡፡ ከወንድሙ መመለስ ይልቅ ለእሱ የሚቀርብ ስጦታ ያስደሰተው ይህ ታላቅ ወንድም ምን ያህል ራስ ወዳድ ነው?

በተመሳሳይም የራሷን ድካም ብቻ ተመልክታ የተበሳጨችው ማርታ፤ **‹‹እኔ እንድሠራ እኅቴ ብቻዬን ስትተወኝ አይገድህምን. . .››** በማለት ለራስዋ ብቻ ስትጨነቅ የእኅቷን መረጋጋት አላሰበችም ነበር፡፡ /ሉቃ.፲፥፵፣ዮሐ.፲፩፥፩-፴/

በሌላ መልኩ እኔ በማለት ያልተጠመዱ ሰዎች ሁሉንም በፍቅርና በመልካም ነገር ሲያሸንፉ፣ በእግዚአብሔር ሰላም ሲኖሩ ይታያል፡፡ አብርሃም የእግዚአብሔርን ድምፅና ፍቃድ ብቻ ይሰማና ይከተል ነበር፡፡ **‹‹አገርህን፣ ሕዝብህንና ቤተሰቦችህን ትተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ››** /ዘፍ.፲፪፥፩/ ያለውን ሰምቶ ወጣ በረከቱን ሁሉ ተቀበለ፡፡

በራስ ወዳድነት መጠመድ ግን በብዙ ኃጢአትና መንፈሳዊ ቀውስ ውስጥ ይጥላል፡፡ አዳም ለስሕተቱ ምክንያት ሲሰጥ፤ **‹‹የሰጠኸኝ ሴት አሳሳተችኝና በላሁ››** በማለት ነው፡፡ ሔዋን ከእግዚአብሔር ትምህርት ይልቅ **‹‹አትሞቱም፣ ከእርሱ በበላችሁ ቀን ዓይናችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ፡፡››** ሲል ዲያብሎስ የእኔነትን ትምህርት በክፋት አስተምሮአት ተቀበለችው፡፡ /ዘፍ.፫፥፬-፳/ በዚህ የተነሣ አዳምና ሔዋን በብዙ ኃጢአት ወድቀው እርቃናቸውን ከመሆናቸውም በተጨማሪ ሞት ተፈርዶባቸው ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

ክርስቲያን ራስ ወዳድ ከሆነው ከእኔነት አስተሳሰብ ይልቅ ራሱን በመካድ እግዚአብሔርን ያስቀድማል፡፡ ከእርሱ ይልቅ የወንድሙ እንደሚሻል ያስባል፡፡ እኛም እኔ ብቻ ከሚል ራስ ወዳድነት፣ ስግብግብነትና ከበላይነት ስሜት ወጥተን በክርስቲያናዊ አኗኗር ለሌሎች በማሰብ ከማይገባ የራስ ጥቅም ይልቅ የሌሎችን በማስቀደም አርዓያ ልንሆን ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

1. የየዕለት ሕይወታችን ‹‹የድርጊታችን መሠረቶች መልካሙ የትኛው ነው?›› ብለን በማስተዋል ለሁሉም የሚጠቅም መሆኑን እና የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በመጠየቅ መመራት ይገባዋል እንጂ፤ በራስ ወዳድነት ብቻ እኔነትን በማስቀደም መመራት የለብንም፡፡

2. በቤት፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በትምህርተ ቤትም ሆነ በማናቸውም ቦታዎች ለሰዎች መልካም ነገር ለማድረግ የምንተባበርና መልካም አሳቢዎች መሆን አለብን።

*አባሪ፡- ራስን መውደድ* (በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ)

እውነተኛውን ራስን መውደድ እግዚአብሔርን በመውደድ እንለማመዳለን። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚሆነው ለመንፈስ ቅዱስ መሣሪያነት በመሸነፍና በመታዘዝም ነው። በትሕትና እና በንጽሕና ራስን የእግዚአብሔር ማደሪያ ከማድረግ የተሻለ መንገድ የለም። አስተዋይ ሰው ራሱን የመንፈስ ቅዱስ መሣሪያ ለማድረግ እንቢ አይልም፤ ወይም የእግዚአብሔርን ጥበብ አይንቅም። በዚህ መልካምና ቀና መንገድ ራስን መውደድ ራስን በእውነት በመካድ ይገለጣል።

ራስን መካድ በተግባር ሲገለጥ ‹‹. . . ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም›› ፩ኛ ቆሮ.፲፭፥፲ እንላለን። ራስን መካድ ማለት የራስን ክብር እና ምስጋና መተው ነውና እንደ መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት፤ ‹‹**ለእኛ አይደለም አቤቱ ለእኛ አይደለም ነገር ግን ለስምህ ስለ ምሕረትህ ስለ እውነትህም ምስጋናን ስጥ።**››/መዝ.፻፲፬(፻፲፭)፥፱(፩)/ ማለት ነው።

ራስን መካድ ማለት አማኞች ምቾታቸውንና ሀብታቸውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባት ለሚያደርጉት ጥረት ማዋል ነው። /ማቴ.፮፥፩-፬፤ ሉቃ.፲፰፥፴/ ‹‹የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ።›› /ሉቃ.፲፮፥፱/ ራስን መካድ ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ባለው አንድነትና መግባባት ይገለጣል።

ክርስቲያን ከራሱ ይልቅ ለሌሎች ያደላል። ‹‹እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ. . . ።›› /ሮሜ.፲፪፥፲/ እንዲል የፍቅር መሠረት የሆነውን መከባበርን በማካፈል፣ በመሥዋዕትነትና በሥራም ልንገልጠው ይገባል። የሌሎቹን ኃጢአት ከመሸከምና ከነድካማቸው ከማቅረብም በላይ ራሱን አሳልፎ ይሰጣል። ነገር ግን ሌሎች በተሳሳተ ዓለማዊ መንገድ ራሳቸውን ይወዳሉ። ለመገንባት ሲሞክሩ እያፈረሱት፣ ሲያቃኑት ያጡታል።

ጌታችን ‹‹ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል። ነፍሱን ስለእኔ የሚያጠፋት ያገኛታል።›› ያለው ለዚህ ነው። /ማቴ.፲፥፴፱/ ምድራዊ ክብርን ለእግዚአብሔር ክብር ሲሉ የናቁ፣ በሰዎች ሲናቁ ራሳቸውን በትክክል ያገኙ እና ራስን መገንቢያ ትክክለኛ መንገድ የገባቸው ናቸው። መነኮሳት በመንፈስ ተወልደው ጌታችንና ሌሎችን ለማገልገል ራሳቸውን መሥዋዕት አድርገው የቀረቡ ምሳሌዎቻችን ናቸው። ከቅዱስ ጴጥሮስም ጋር ጌታቸውን ‹‹**ሁሉን ትተን ተከተልንህ**›› ይሉታል። /ማቴ.፲፱፥፳፯/ በትክክል ራሱን የሚወድ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር በጠበበው መንገድ ሲሔድ መስቀሉን ተሸክሞ ነው።

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች፡-***

1. ራስ ወዳድነት እና ለ‹‹እኔ›› ማለት ውጤቱ ምንድነው? ሐሳባችሁን ግለጹ፡፡
2. ክርስቲያን የሚሰማው ድምፅ፣ የሚከተለው ፈቃድ፣ የሚያከብረው ትእዛዝ የማንን መሆን አለበት?

- ለዚህ ምሳሌ እና አስረጂ የሚሆን ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመውሰድ አብራርታችሁ ግለጹ፡፡ (መምህር ተማሪዎች በጽሑፍ እንዲያቀርቡና በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጓቸው)

www.zeorthodox.org

# ዜማ

# አርባ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ዜማ በሰው ልጆች ላይ ያለውን መልካም እና ክፉ ተጽዕኖ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ"* /ኤፌ.፭፥፲፩/**

**መግቢያ፡-** ስለ ዜማ በሚቀጥሉት ተከታታይ የትምህርት ክፍሎች እንማራለን። ሰውና መላእክት አመስጋኝ ፍጥረታት ናቸው። ይህ ምሥጋና ደግሞ በዜማ ነው። በትንቢተ ኢሳይያስ ፣ በራእየ ዮሐንስ የተገለጡት የሰማይ ዜማዎች ይንኑ ያመለክቱናል። /ኢሳ.፮፥፪-፯ ራእ.፳ እና ፲፬/። የዜማ ጠበብትም ሰው ሁሉ ዜማ አለው ሲሉ ይህንኑ ያረጋግጣሉ። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ የዜማ አንዱ አካል የሆነውን ዘፈንን ይከለክላል። ዛሬ የምንጀምረው ትምህርት ይህንኑ ይዳስሳል።

## የሳምንቱ ዋና ክፍለ ትምህርት

### ሀ. የዜማ ፈጣሪ ልዑል እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥረው አመሥጋኝ አድርጎ ነው። እግዚአብሔር በፈጠረው መጠቀም የሰው ልጆች ስጦታ ነው። ሰውና የተፈጠረበት ዓላማም በነፍሱ በሥጋውና በመንፈሱ አምላኩን እንዲያመሠግን ነው። የሰው ልጆችን የዜማ ያህል የሚያስተባብራቸው የለም። ለዚህም ነው ዜማ እያንዳንዱን ግለሰብ ስሜት የመንካት (የመሳብ) ኃይል ያለው ነው። በዜማ ሰዎች ያዝናሉ፣ ይደሰታሉ። ሆኖም በዘጸ.፴፪ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጣዖት ለማምለክ እንደሳተ የዘመናችን ዘፋኞችም በአምልኮት ይስታሉ።

www.zeorthodox.org

### ለ. የዜማ ተጽዕኖ

1. ዜማ በሰው ሁሉ ላይ ተጽዕኖ አለው። የሰውን አስተሳሰብ ፍላጉትና መንፈሳዊ ብቃት መቀየር ይችላል። ለዚህም ነው በእግዚአብሔር እና በሰዎች መካከል ላለው ግንኙነት መዝሙር ዋና መሣሪያ የሆነው። የሰዎችን አስተሳሰብ በሰላም እና በእርጋታ ለመሙላት ያስችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው መዝሙረ ዳዊት እግዚአብሔርን የምንማጸንበትና የምናመሰግንበት የሆነው መልካም የሆነ የዜማ ተጽዕኖ ስላለው ነው። ዜማ

በዕፅዋትና በእንስሳትም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው፡፡ ሳይንሳዊ ጥናቶች ይህን አረጋግጠዋል፡፡ በዕፅዋት ዙሪያ ያለው ዜማ የተረጋጋና ሰላማዊ ሲሆን ዕፅዋቱ ጤናማና ፍሬያማ ይሆናሉ፡፡ ኃይለኛና የሚያውክ ሙዚቃ ሲሰማም ዕፅዋቱ ጤናቸው በማጣት ይደርቃሉ፡፡ በዕፅዋት ላይ ይህን ካስከተለ የበለጠ ለስሜቱ ተጋላጭ በሆነው በሰው ልጅ ላይ የሚያሳድረው በጎም ሆነ ከፉ ተጽዕኖ የባሰ ይሆናል፡፡ እናም የምትሰሙትን ዜማ መምረጥ አለባችሁ፡፡ ዜማ ተራ መዝናኛ ሳይሆን የምንጠቀምበት ወይም የምንጎዳበት ሊሆን ይችላል፡፡

2. ባለንበት ዘመን ዜማ ዋናውና ከፍተኛ ተጽዕኖ ያለው የግንኙነት መንገድ ነው፡፡ ዜማ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙትን እና በተለያየ ልሳን የሚናገሩትን በአንድነት የሚያግባባ ቋንቋ ነው፡፡ በቅኝቱ በምቱና በግጥሞቹ ሰዎች ወደ ተለያየ አቅጣጫ ይመራሉ፡፡ በተለያዩ ዜማዎች አንዱ ወደ ተመስጦ ሌላው ወደ ጭፈራ ሊያመራ ይችላል፡፡ ዜማና ግጥም የተለመዱ ራስን መግለጫ መንገዶች ናቸው፡፡ ***"በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና፤"*** ምሳ.፳፫÷፯ እንደተባለው የእያንዳንዱ ፍላጐትና ዝንባሌን ዜማ ይገልጣል፡፡

3. በርካታ ጸሐፍያንም ዜማን አስመልክተው የሚከተለውን ብለዋል ***"በግለሰብ እና በመላው ማኅበረሰብ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው፡፡" "የነፍስ ቋንቋ ነው፡፡" "በሰብእና ላይ ሥልጣን አለው፡፡" "አለአግባብ ከተጠቀምንበት ማኅበረሰብ እናበላሻለን፡፡"*** እናም ***"እንደ መርዝ ነፍስና ሥጋን እስኪያጠፋም ሊበላሽ ይችላል፡፡"*** ማንኛውም ኪነ ጥበብ የዜማን ያህል ከፍተኛ ተጽዕኖ የለውም፡፡

4. በነፍስ ላይ ያለው ተጽዕኖ፡፡ ዜማ በሰው ልጅ ላይ ያለው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡ የዜማን ያህል ሰውን በመቆጣጠር የሚወዳደር የለም፡፡ በተቃራኒውም ዜማ ከመድኃኒትና አደንዛዥ ዕፆች የከፋ ተጽዕኖም ሊያስከትል ይችላል፡፡ ነፍሳችን በመንፈሳዊው ዜማ መጥቃ ከመላእክት ዓለም ጋር አንድ ትሆናለች፡፡ ተገቢ ባልሆነ ሙዚቃ ክፉ ተጽዕኖ ደግሞ ነፍስ በተዋርዶ ከእንስሳት በታች ልትገኝ ትችላች፡፡

5. በሥጋ(ሰውነት) ላይ ያለው ተጽዕኖ፡፡ ዜማ በሰው ልጆች አካል ላይም ተጽእኖ አለው፡፡ በወታደራዊ ማርሽ ተስቦ ራስን ከመሠዋት እስከ የልብ ምትና የሕብለ ሰረሰር (ነርቭ) ሴላችን ጭምር በዜማ ይነካል፡፡ ይዝናናል፡፡ ይጎዳል ወይም ሰላም ያገኛል፡፡

www.zeorthodox.org

6. መንፈሳዊው ተጽዕኖው፡- ቤተ ክርስቲያን ዜማ በመንፈሳዊ ሕይወት ያለውን በጎ ተጽዕኖ ታምናለች፡፡ ሰማያውያን ያለማቋረጥ በዜማ ይኖራሉ፡፡ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር፣ ደስታቸውን እና ምሥጋናቸውን በዜማ ይገልጻሉ፡፡ በተቃራኒው ለኃጢአት በማነሣሣት መንፈሳዊ ኪሣራ የሚያደርሱትን የዘፈን ዜማዎችም በትምህርትዋና በዜማዋ ትቃወማለች፡፡

### ሐ. የዲያብሎስ የዜማ ብቃት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዲያብሎስ እና ውድቀቱ ሲነግረን እንዲህ ብሎናል፤ *"ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ጥበብን የተሞላህ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ። በእግዚአብሔር ገነት በዔድን ነበርህ የከበረ ዕንቁስ ሁሉ ሰርድዮን፣ ቶጳዝዮን፣ አልማዝ፣ ቢረሌ፣ መረግድ፣ ኢያስጲድ ፣ ሰንፔር፣ በሉር፣ የሚያብረቀርቅ ዕንቁ፣ ወርቅ ልብስህ ነበረ፤ የከበሮህ እና የእንቢልታህ ሥራ በአንተ ዘንድ ነበረ፤ በተፈጠርህበት ቀን ተዘጋጅተው ነበር። አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ፤ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አኖርሁህ፤ በእሳት ድንጋዩች መካከል ተመላለስህ።›› /*ሕዝቅ. ፳፰፥፲፩-፲፭/ እንደ ኪሩብ (ኢሳ.፮፥) ዲያብሎስም ዜመኛ ነበር። ይህ የመላእክት ዜማ በቁሳዊ መሣሪያዎች ወይም የሥጋን የሙዚቃ ጥበብ የሚጠቀም አልነበረም። ነገር ግን ለምሥጋና የተመረጠ ፣ ታላቅ ተስጥዖ ያለው ነበር። ዲያብሎስ ከወደቀ በኊላም ይህን አቅሙን አላጣም ለክፉ ይጠቀምበታል እንጂ፤ ሰዎች እንዲጐዱበት ከአምላካቸው እንዲጣሉበት፣ ለክፉ ሥራ እንዲጠቀሙበት ያስተምራል። ይህ የሰይጣን ሥልትም በሦስት ሊጠቃለል ይችላል።

1. ዲያቢሎስ ከፍተኛ የሆውን የዜማ ብቃት ይጠቀማል።
2. ዲያቢሎስ ዜማ በእኛ አካል ፣ ነፍስና ሥነ ልቡና ላይ ያለውን ተጽዕኖ ያውቃል።
3. ዲያቢሎስ የፍርድ ቀን መድረሱን ያውቃል። ራእይ. ፲፪፥፲፪ በመሆኑም ሙሉ አቅሙን ተጠቅሞና፣ ዜማ በሰዎች ላይ ያለውን ተጽዕኖ አውቆ በሚችለው ሁሉ ሙዚቃን ለማሳሳቻነት ይጠቀምበታል።

## ማጠቃለያ፡-

1. ዜማ በነፍስ ፣ በሥነ ልቦናና በአካላችሁ ላይ ያለውን ተጽዕኖ በመረዳት ንቁ።
2. የምትሰሙትን የዜማ ዓይነት ምረጡ። ሁሉንም ማድመጥና ወደ ውስጥ ማስቀረት ይጎዳል።
3. ዲያቢሎስ የሰው ልጆችንና ዓለምን፡- ለመጉዳት ጐጂ ሙዚቃዎችን እንዴት እንደሚለቅ ያውቅበታል።

www.zeorthodox.org

**ተግባር፡-** ስለተማራችሁት ጉዳይ ተወያዩ።

***ጥያቄዎች፡-***

1. እግዚአብሔርን አመስጋኝ ናቸው የሚባሉት ፍጥረታት እነማን ናቸው?
2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት እና የምንማጸንበት መልካም የዜማ ተጽዕኖ ያለው ክፍል ምን በመባል ይታወቃል?
3. መልካም የሆነው ዜማ በጎ ተጽዕኖ (ጥቅም) እንዲሁም መልካም ያልሆነውን ዜማ ክፉ ተጽዕኖ(ጉዳት) አብራሩ።

# ዜማ - ክፉ ወይም ጎጂ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ዘፈኖች
# አርባ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፦ ተማሪዎች ክፉ ወይመ ጎጂ ተጽዕኖ ያላቸውን ዘፈኖች ዓይነት፣ጠባይና ስልት ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ።

**የሚጠና ጥቅስ**፦ *"በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤"* /ሮሜ ፲፫÷፲፫/

**ተጨማሪ ምንባባት**፦ Music Coptic Church Canada Dioces Sunday School Curriculum Contemporary Issues; pp.63 - 75

**መግቢያ**፦ አንዳንድ ሙዚቃዎች አምልኮተ ጣዖት፣ ኃጢአትና ክፉ ምኞትን የሚያስፈጽሙ ናቸው። ክፉ ወይም ጎጂ የሆነውን ተጽዕኖአቸውንም በገሀድ ሰዎችን ለኃጢአት ምኞታቸውን ሲቀሰቅሱ፣ ጣዖት ሲያስመልኩ ማየታችን የተለመደ ነው። የዛር መናፍስትን የሚጠሩና የሚያነግሡ፣ የሥጋ ምኞትን ዝሙት ለማነሣሣት የሚቀመሩ ሙዚቃዎች እና የሙዚቃ እንቅስቃሴዎች በርካታ ናቸው።

ከእነዚህ በዘመናዊው ዓለም ያሉትን በማስቀደም እንመለከታለን፡

*ሀ. ዓለም ዓቀፋዊ ተጽዕኖ ያላቸው የሙዚቃ ስልቶች።*

**ሮክ እና ሮል**። ወይም ሮክ በመባል የሚታወቀውና ከፓፑላር ሙዚቃዎች እንደሚመደብ የሙዚቃ ባለሙያዎች የሚናገሩለት በጠንካራ ምትና የኤሌክትሪክ ጊታር የሚታጀበው ይህ ስልት ሳክስፎን የመሳሰሉትን የሙዚቃ መሣሪያዎች ይጠቀማል። ከተለያዩ ስልቶች ጋር የሚታጀበውና ብዙ ስልቶች ይህ የሙዚቃ ዓይነት በመላው ዓለም ላይ ተጽዕኖ መፍጠር የቻለ ነው። ከጣዖት አምልኮ መናፍስት መጥሪያ ሥርዓት አምልኮ የተወሰደው ይህ የሙዚቃ ስልት በኤልቪስ ፐርስሊ ወደ አውሮፓ ከዚያም በዓለም በሙሉ ተስፋፍቷል። ወጣቶችን ለኃጢአት በሚያነሣሡ ምቶችና የዘፈን ግጥሞች ዓለምን አጥለቅልቋል። ለአደንዛዥ ዕፅና ዝሙት ገበያም ታላቅ ኃይል በመሆኑ ይታወቃል።

*ፖፕ ፣ ጃዝና ሂፕ ሆፕ*። ከሮክ እኩል ከላይ ያነሣነውን ተጽዕኖ እየፈጠሩ ያሉ የዘፈን ስልቶች ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መጪው አውሬ አስጠንቅቆናል፡፡ ራእ.፲፪÷፲፪ ቅዱስ ጳውሎስም **"ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ**

www.zeorthodox.org

ይሆናሉና፤ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ዕርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ።" ፪ኛ ጢሞ.፫፥፩-፭ ሲል መክሮናል። መጪው አውሬ ሐሳቡንና መንፈሱን በሰው ልጆች ውስጥ ከሚያሰርጽባቻ መንገዶች አንዱ ፈጣኑንና ዘመናዊውን የሙዚቃ ስልት ነው።

**ለ. ባህላዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖ ያላቸው ስልቶች።**

እነዚህ የሙዚቃ ስልቶችና ምቶች በተወሰነ አካባቢ ያሉ ፣ ግፋ ካለም በሀገር ደረጃ የሚታወቁና ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ናቸው። ለዝሙትና ለኃጢአት ሰዎችን የሚያነቃቁ ሲሆኑ ፤ መናፍስት የሚጠራባቸው አንዳንዶቹም በዘፋኞቹ ላይና በሰሚዎችና በሙዚቃው ተሳታፊዎች ላይ መናፍስት ሲያነግሡ አእምሮ ሲያስቱ የሚታዩ ናቸው። ለምሳሌ፡- በሀገራችን እና በአህጉራችን አፍሪካ ሰዎችን ለዝሙት በሚቀሰቅሱ እንቅስቃሴዎች የሚታጀቡ። ምታቸውና ስልታቸውም በዚህ ቅኝት የተለመደ ባህላዊ የሙዚቃ ዓይነቶች በርካታ ናቸው። በአንዳንድ ቦታዎችም የዛር መናፍስትን የሚጠሩ ራሳቸውን በርኩስ መንፈሱ ፈረስነት የመደቡ በርካታ ዜማዎች አሉ። በከበሮ ምት ፣ በሰውነት እንቅስቃሴና በዜማና ግጥም ይዘታቸው ሰውን ወደ መናፍስቱ ዓለም የሚስቡም አሉ።

**ሐ.የዚህ ዓይነቶችን ዘፈኖች እና የዜማ ስልቶች መጽሐፍ ቅዱስ ይቃወማል።**

ምክንያቱም ***"ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።"*** ፪ኛ ቆሮ.፬፥፫-፬ እንዳለ ዘፈን ሰዎችን ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን ለጥንተ ጠላታችን ለዲያብሎስ ክብር እንዲያጎነበሱ የሚያደርግበት መንገድ ነው። ከዚሁም ጋር የሥጋ ሥራ ከተባሉትና ወደ መንግሥተ ሰማያት ከማያስገቡት ነገሮች አንዱ ***ዘፋኝነት*** ነው። ገላ.፭፥፳፩ ቅዱስ ጴጥሮስም ***"በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና።"*** ፩ኛ ጴጥ.፬፥፫ በማለት ይመክረናል።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

1. በዓለም ዐቀፍና በአካባቢያዊ የሙዚቃ ስልቶች ተጠቅሞ ዲያብሎስ ሰዎችን ያስታል፤ ከእግዚአብሔር ርቀን ወደ እርሱ እንድንሄድ ይተጋል።

2. በቅዱስ መንፈስ ወዳጅና ጸጋ መስጫ በሆነው ቅዱስ ሜሮን የከበረው ጆሮችንን የዚህ ዓይነቱን የዲያብሎስ ርኩሰት ማዳመጫ እንዳይሆን እንጠንቀቅ፡፡

## ተግባር

- በተንቀሳቃሽና ቋሚ የዘመኑ መጠቀሚያዎቻችሁ የእግዚአብሔርን ምስጋና ሙሉበት፡፡ አላስፈላጊና የጠላት ተጽዕኖ የሚያመጡ ዜማዎችን ከእናንተ አርቁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. *ሥጋዊ ፍላጎትን በማነሣሣት ወደ ኃጢአት የሚመሩ ዓለም አቀፋዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖ ያላቸውን የዘፈን ስልቶች ምሳሌ እየጠቀሳችሁ ግለጹ፡፡*
2. *የሥጋ ሥራ የተባሉትን መንግሥተ ሰማያት የማያስገቡትን ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ከተማራችሁት አስረጂ ጥቅስ በማቅረብ ግለጹ፡፡*

www.zeorthodox.org

# ተቀባይነት ያለው ዜማ

## አርባ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ መዝሙርና ተቀባይነት ስላላቸው ዜማዎች ያውቃሉ፤ መምህሩ በሚሰጧቸው ርእሶች ጽሑፍ በማዘጋጀት እያቀረቡ ያስረዳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"ሰነፍ የጥበብን ነገር አይወድድም በልቡ ያለውን ሁሉ መግለጥ ብቻ ይወዳል እንጂ"*** ምሳ.፲፰፥፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** Music Coptic Church Canada Dioces Sunday School Curriculum Contemporary Issues; pp.63 - 75

### *መግቢያ፡-*

ባለፉት ተከታታይ ሁለት የትምህርት ክፍሎች ስለ ዜማ የተማርነውን በመቀጠል፡፡ መንፈሳዊ ፣ ማኅበራዊና ግለሰባዊ ጥቅም ስላላቸው ዜማዎች እንማራለን፡፡

ተቀባይነት ያለው ዜማ የትኛው ነው? በሚለው ርእሰ ጉዳይ ብዙዎች ልዩነት ያነሣሉ፡፡ ለአንዳንዶች ዘመናዊ ሙዚቃ ከዲያብሎስ ጋር የማይገናኝ ነው በሚል አመለካከት፤ መናፍስት ጠሪዎች የሚጠቀሙበት ዜማ ብቻ ክፉ እንደሆነ ያስባሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ባህላዊ ሙዚቃዎችን ከማንነት ጋር እያያዙ መልካም ናቸው ብለው ይከራከራሉ፡፡ ለአንዳንዶች የሙዚቃው ስልት ጥሩ ወይም ክፉ የሚያሰኘው እንደሆነ ይታመናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ውስጥ ያለውና ዋናው ሐሳብ ግን የተለመደና በውስጥ የቀረን ባዕም ትክክል ብሎ ከመቀበል የሚመነጭ ነው፡፡ በዕድሜ፣ በአካባቢ፣ በዕውቀት ደረጃና በዝንባሌ ሰዎች የሚቀበሉትና የሚተውት ነገር አለ፡፡ ሆኖም እንደ ክርስትና ለሥጋዊ ፍላጎት ብቻ የሚያድረውን ራስንና አካባቢን በመካድ ለራሳችን ሳይሆን ለእግዚአብሔር መኖር ነው፡፡

ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘም ለእኛ አርአያ ይሆነን ዘንድ አባቱን ደስ አሠኘ፡፡ እኛም ***"ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል፡፡"*** ዮሐ.፲፪፥፳፭ እንደተባልን ከሥጋዊ ፍላጎታችን ከስሜቶቻችን በላይ ነፍሳችንን ለማዳን የሚያስችለንን

www.zeorthodox.org

የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳት አለብን፡፡ በእርግጥ ዜማን እግዚአብሔር ፈጠረ፡፡ ሁላችንም በዜማ አንድ ሆነን ልንገዛ፣ እግዚአብሔርነ ልናመልክና ክብርንም ልንወርስ ተጠራን፡፡ ራእ.፭፥፲-፲፭፤ ባለፉት ትምህርቶች እንዳየነውም ሰይጣን የሥጋ ፍላጎታችንን በማነሣሣት ሊያሸንፈን ዜማን አዛብቶ ይጠቀማል፡፡ የዜማ ጉዳይ ሁሉንም የሚያነጋግረውም ለዚህ ነው፡፡

ሕዝቡን ለጣዖት እና ለአጋንንት እያስገዱ፤ በሥጋ ፍቃዱ እንዲመራ እያደረጉ፤ እንደ አሮን ***"የእግዚአብሔር በዓል ነው"*** ሲሉ የሚያውጁ ለሕዝቡና ለራሳቸው ታላቅ ኃጢአት ያመጣሉ፡፡ ***"አሮንም ባየው ጊዜ (የጣዖት) መሠዊያን በፊቱ ሠራ፡፡ አሮንም ነገ የእግዚአብሔር በዓል ነው ሲል ዐወጀ፡፡ በነጋውም ማልደው ተነሥተው የሚቃጠል መሥዋዕት ሠዉ፥ የደኅንነትም መሥዋዕት አቀረቡ፡፡ ሕዝቡም ሊበሉና ሊጠጡ ተቀመጡ፥ ሊዘፍኑም ተነሡ፡፡.........ሙሴም አሮንን፦ ይህን ታላቅ ኃጢአት ታመጣበት ዘንድ ይህ ሕዝብ ምን አደረገህ? አለው፡፡"*** ዘጸ.፴፪፥፭-፳፩ ከዚሁም ጋር ***"እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ፡፡ ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው፡፡ ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም፡፡"*** ሮሜ.፰፥፭-፰ ተብሎ ተጽፎልናል፡፡

ምን ቢሆን በእግዚአብሔር ስም የምናደርገው ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት በተጻፈው ትምህርት መሰረት ሊሆን ይገባዋል፡፡ በዛሬው ትምህታችንም ለዚህ የሚረዳን አጭር ግንዛቤ ማስጨበጫ እናነሳለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

1. **ዜማ በተቻለ መጠን በነፍስ ሊመራና ቦታ ሊሰጣት ይገባል፡፡**

ብዙ የኪነ ጥበብ ባለሞያዎች ከሥጋ ደስታ በመነሣት ነፍስን ወደ ተባባሪነት ይጠሩዋታል፡፡ ሆኖም ዜማ ከመስቀሉ ሐሳብና ፍቅር ከመነጨ ሥጋን ወደ ኃጢአት አይመራም፡፡ እግዚአብሔር ሲፈጥረን ዜማን ከመሣሪያዎቹ በፊት ከልባችን እንዲነሣ አደረገው፡፡ ሲያስተምረንም ‹‹***በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ***›› አለን፡፡ ኤፌ.፭፥፲፱ ክርስቲያን እንደመሆናችን ***ከልባችን*** በሚነሣ በመዝሙር፣ በዜማ እና በመንፈሳዊ ቅኔ ***እርስ በእርሳችን*** ልንናገር ይገባል፡፡ በዚህ የሚጮህ ሙዚቃ፣ የተደራጀ ባንድ ፣ ሥጋዊ ፍላጎትን የሚያነሣሣ፣ ስሜትን የሚቀሰቅስና ወደ ክፉ መንገድ የሚመራ ድምፅ ግዴታና አስፈላጊ አይደለም፡፡ በሹክሹክታም ይሰማል፡፡ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ለአገልግሎቱ ክብርና እውነተኛነት መጨነቅ ቅድሚያ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ ለሥጋዊ ደስታ ለሥነ ልቦናዊው

www.zeorthodox.org

መማረክ ግን ትኩረት አይሰጥም፡፡ ልብን በዜማ ቃል ለእግዚአብሔር ማስገዛት ዋናው የአምልኮተ እግዚአብሔር ዓላማ ነው፡፡ ***"በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤"*** ኤፌ 5፡19 በልባችን የምንናገረው ዜማ በራሱ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምሥጋና ነው፡፡ ዘማርያን የሚያደርጉትም በልባችን ያለውን መንፈሳዊ ቅኔ በአደባባይ ወይም በጉልህ በማዜም አንዳችን ከአንዳችን ጋር እግዚአብሔርን በማመስገን በመንፈሳዊ ቋንቋ እንድንነጋር ማገልገል ነው፡፡ መንፈሰዊው ዜማ ከውጭ መጥቶ ወደ ውስጥ የሚጫን አይደለምና፡፡

ክርስቲያናዊው ዜማ ለሥጋዊ ፍላጎትና ደስታ ለዓለማዊነትና ለማያምኑ የማይስማማ ነው፡፡ በአጭሩ ቃል ስናስቀምጥ ሥጋውያን የሆኑ ዓለማውያን አይወዱትም፡፡ ሆኖም ዓለምን መውደድ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነው፡፡ ያዕ.፬፥፬ ክርስቶስ ከኃጢአተኞች ጋር መቀመጡ እውነት ቢሆንም ኃጢአት ሊሠራ ወይም ሊተባበራቸው አልተቀመጠም፡፡ ማንኛውም ዜመኛ ይህን የቃሉን እውነት ሲሻገር የክርስቶስን መስቀልና ኃይሉን እያጣ ነው፡፡

**2. ውጫዊ እይታው ዓለምን ሊመስልም አይገባውም፡፡**

‹‹ክርስቶስ ልብን እንጂ ውጪን አያይም›› በማለት በግዴለሽነት የሚከፈተው በር መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፡፡ ውስጣችን የፈጠረ እግዚአብሔር ውጫዊ አካላችንንም ፈጥሮታል፡፡ በሌሎች ሰዎች የሚታዩት ልብስ፣ ጸጉር፣ ጠባይ፣ ንግግር ሁሉ የእግዚአብሔርን ክብር ሊገልጡ ይገባል፡፡ ወደ እኛ ትኩረት ለመሳብ የሚደረጉ የሰውነት ጌጦች፣ ንቅሳቶች፣ ጸጉር ማስረዘምና ባዕድ በሆኑ ቅጥያዎች ማስዋብ በእግዚአብሔር ቃል ማመጽና የእርሱን ውብ ፍጥረት ለመጋረድ መጣር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቤት ከጣዖት ቤት ጋር አንድ ለማድረግ አንችልም፡፡ በተጨማሪም ምልክት ልናደርግ ወይም ትኩቶችን ልንስብ አልተፈቀደልንም፡፡ ***"ስለዚህም ጌታ፡፡ ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኵስንም አትንኩ ይላል፤ ሁሉንም የሚገዛ ጌታ፡፡ እኔም እቀበላችኋለሁ፥ ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል"*** ፪ኛ ቆሮ.፮፥፲፯-፲፰ በመዝሙር የሚያገለግሉም ሆኑ ስለ ዘፈን የሚከራከሩ፡፡ ተለዩ፣ ርኩስንም አትንኩ፣ ያለንን ቃል መጠበቅ፡፡ ዓለማዊውን ዘፈንና የጣዖታት መንገድ ከክርስቶስ መንገድ መለየት ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

**3. መዝሙራቱ የእግዚአብሔርን ክብር ሊገልጡ ይገባል፡፡**

እያንዳንዱ መዝሙር ክርስቶስን ሊሰብክ ይገባዋል፡፡ *በቃልም ሆነ በሥራ* እያንዳንዱ ዜማ ክርስቶስን በግልጥ ሊነግረን የእግዚአብሔርንም ክብር ሊያሳየን ይገባል፡፡ ክርስቶስን ያልሰበከና ድምፁን ያላስተላለፈ ዜማ በእግዚአበሔር ፊት አይወደድም፡፡ ***"በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፡፡ እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፥ በቃል***

*ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት"* ቆላ. ፫፥፲፯-፲፯ ለዚህ ነው የቤተ ክርስቲያን መዝሙራት ስለ ቅዱሳንና በምድር ስላሉ ሰዎች ሲያነሡ እንኳን በክርስቶስ ኃይል እንደሆነ በመግለጥ ይህን ያደረገውን እግዚአብሔርን ያከብራሉ፤ ያወድሳሉ።

4. ዘማርያን ራሳቸውን ወይም ስለራሳቸው ሊያዜሙ አይገባም።

ብዙ ቦታ እንደምናየውም በግለሰቦች ፎቶ (ምስል) የታጀቡ፣ መዝሙር መሆኑን በማይገልጡ ሥዕላት የተሸፈኑ አልበሞች ማየት የተለመደ ነው። እግዚአብሔር እንዳገነናቸው በመዘመር ታሪካቸውን ይነግሩናል። ሰማዕያኑም ያንኑ ይቀበሉታል። ጌታችን መዋዕለ ስብከቱ እንዲህ ብሎን ነበር፡- ***"እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ አልተቀበላችሁኝምም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ።"*** ዮሐ.፭፥፵፫ ክርስቶስ ይህን በማድረግ አሳየን፤ እኛም የክርስቶስ ከሆን እንዴት አይሁድ እንደሚቀበሉትና በራሱ ስም እንደሚመጣው አውሬ እንሆናለን። ቅዱስ ጳውሎስም አገልግሎቱን በዚህ አገባብ ገልጦታል። ***"ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደ ሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና፥ ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን።"*** ፪ኛ ቆሮ.፬፥፭ ሁሉም ሰውኛ ሽልማቶችና ማረጋገጫዎች ተቀባይነት የላቸውም። ወደ እግዚአብሔር ለሚደርሱ ዜማዎች ምድራዊ ክብር አያሻውም። ***ክብርን ከሰው አልቀበልም*** በሚል ልቡን ያተመ ዘማሪ መሆን አለበት። ዮሐ.፭፥፵፩-፵፪

5. የቤተ ክርስቲያንና የአባቶች የዜማ ስልትና ሥርዓት ሊጠበቅ ይገባዋል።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም በአግባብ እና በሥርዓት ታከናውናለች። ‹‹ሁሉም በአግባብና በሥርዓት ይሁን ፩ኛ.ቆሮ.፲፩፥ በመሆኑም የመዝሙር ሥርዓታችን የቅዱስ ያሬድን የዜማ ዝልትና ምልክት፣ ሰማያዊውን የዜማ ሥርዓት (ኢሳ.፮፥፪ እና ራዕ. ፭፥፬-) ይከተላል። በመዝሙር የሚገለግሉም ሆነ የሚዘምሩ ይህንን ቢከተሉ እግዚአብሔር በተፈጥሮ ከሰጠንና ከመላእክት ጋር አንድ በምንሆንበት የዜማ ክብር እንደርሳለን።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እውነተኛ ጽድቅና ንጽሕና አይደበቅም። በሐሰት የተሞላው ግን ብዙ ማስታወቂያ፣ አስረጅና ማብራሪያ ይተቀማል። እንደ መና ገዝፈው መታየት የሚሹ ቃላትን ከመጠቀም በፊት፣ ድምፅ ማጉሊያ ከመያዝ፣ መዝሙር ከመስማትና ከመዘመርም በላይ ጽድቃችን እንደማያቋረጥ ፈሳሽ ይውረድ። በዘፈናቸው መልካምነት ተሠሪውን ሲያደንቁ ሠሪውን እንዳወደሱ የሚከራከሩም፤ ቀድመው ሰውን ለሥጋ ፍቃድ ከማነሳሳት መቆጠባቸውን ያረጋግጡ። ጌታችን ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ***"የዝማሬህንም ጩኸት ከእኔ ዘንድ አርቅ የመሰንቆህንም ዜማ አላደምጥም። ነገር***

*ግን ፍርድ እንደ ውኃ፥ ጽድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ።"* አሞ.፭፥፳፫-፳፬

# ተግባር

Ø በተነሡት ርዕስ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ

***ጥያቄዎች፡-***

መምህር ተማሪዎቹን በአምስት ቡድኖች ይክፈሉዋቸው፡፡ እግዚአብሔርን የምናመሰግንበትና ደስ የሚያሰኘውን መንፈሳዊ ዜማ(መዝሙር) ምን ዓይነት መሆን እንደሚገባው፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መሠረት የሚያመለክቱትን፤ አምስት ዋና ዋና ነጥቦች፤

1. ዜማ በተቻለ መጠን በነፍስ ሊመራ እና ቦታ ሊሰጣት ይገባል፡፡
2. ውጫዊ እይታው ዓለምን ሊመስል አይገባውም፡፡
3. መዝሙራቱ የእግዚአብሔርን ክብር ሊገልጡ ይገባል፡፡
4. ዘማርያን ራሳቸውን ወይም ስለ ራሳቸው ሊገልጡ ሊያዜሙ አይገባም፡፡
5. የቤተ ክርስቲያን እና የአባቶች የዜማ ስልትና ሥርዓት ሊጠበቅ ይገባዋል፡፡

ለየቡድኖቹ አንድ አንድ ርእስ ይሰጡዋቸው፡፡ እያንዳንዱ ቡድን የተሰጠውን ርእሰ ጉዳይ በማብራራት ጽሑፍ አዘጋጅተው ያቅርቡ፡፡ በየተራ በክፍል ውስጥ ያስረዱ፡፡

www.zeorthodox.org

# ኢየሱስ ብቻ /Only Jesus/ ማን ናቸው ?
# አርባ አራተኛ ሳምንት

**ትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ራሳቸውን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ብለው የሚጠሩትን ማንነትና ታሪክ ይገነዘባሉ፤ የስሕተት ትምህርታቸውን ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎተ በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው፡፡"*** ማቴ.28፡19

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ‹‹እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን የትኛይቱ ናት?›› በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ; ‹‹አናቅጸ ጽዮን›› ብርሃኑ ጎበና፣ ገጽ.95

## መግቢያ፡-

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ባለፉት 2000 ዓመታት በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፋለች፡፡ የኑፋቄ ትምህርት በማንሣት መንጋውን ያናወጡትና የተሳሳቱ እምነቶችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስገባት ጥረት የሚያደርጉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ሆኖም በእውነተኛው ዓለት ላይ ጸንታ የተመሠረተችውና በቃለ እግዚአብሔር ተመሥርተው መንጋውን የጠበቁት አባቶች ባደረጉት ጥረት ቤተ ክርስቲያን ፈተናዎችን አልፋ ለዛሬው ደርሳለች፡፡

በዛሬው ትምህርታችን ራሳቸውን ‹‹የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን›› ብለው ስለ ሚጠሩትና ‹‹ኢየሱስ ብቻ›› በማለት የሥላሴን የአካል ሦስትነት ስለማያምኑት ክፍሎች እንማራለን፡፡ መምህር ስለምስጢረ ሥላሴ የተማሩትን ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

### ጥንተ ታሪክ

ሰባልዮስ የተባለ ሊቢያዊ በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተነሥቶ፤ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ሦስትነት ላይ የምታስተምረውን ትምህርት ተቃወመ፡፡ እግዚአብሔር በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ ስሞችና ግብሮች ቢገለጽም፤ አንድ አካል ብቻ አለው፤ አለ፡፡ በብሉይ አብ ፣ በሥጋ ሲገለጥ ወልድ ፣ በእሳት አምሳል ሲወርድ መንፈስ ቅዱስ በማለት፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣ ፣

በሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ያልተሰጠ ፣ የእግዚአብሔርን ልዩ ሦስትነት የካደ ፤ አዲስ ትምህርት አስተማረ። ይህ የሰባልዮስ ትምህርት (ሞዶሊስቲክ ሞናርኪያኒዝም) ይባላል። በነበረበት ዘመን ትምህርቱ ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን ተለይቷል።

## ዘመናዊው ሰባልዮሳዊነት - ኢየሱስ ብቻ

በዘመናችን ከ፲፱፻፲፬(1914) ዓ.ም. ጀምሮ ***"ኢየሱስ ብቻ"*** በማለት ከፕሮቴስታንት (ፔንት ኮስታል ቸርች) የተገነጠሉት ቡድኖች ሐሳባቸው ***"ክርስቲያን ሞኖተይዝም"*** በማለት የሰባልዮስን ሐሳብ በአዲስ አቀራረብ ያምናሉ። በሌላ አገላለጽ ዩኒታሪያኒዝም (Unitarianism) ሲባሉ፤ እንቅስቃሴአቸውንም ‹‹ኢየሱስ ብቻ›› (The only Jesus movement) ብለውታል። ሌላኛው ስማቸው ‹‹ዋንነስ ቸርች›› (one ness church) ይባላል። በኢትዮጵያ ያለው ቅርንጫፋቸው ‹‹የኢትዮጵያ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን›› ተብሎ የሚጠራው ነው። ‹‹በካሪዝማቲካዊ›› እንቅስቃሴያቸው ‹‹ፔንቴኮስታል›› ከሚባሉት ሌሎች የፕሮቴስታንት ቡድኖች ጋር አንድ ሲሆኑ የጥንታዊቱን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮም አይቀበሉም። በዓለም ላይ ወደ 26 ሚልዮን ተከታዮች እንዳሏቸው ይናገራሉ።

## እምነታቸው ምንድነው ?

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ዳግመኛ በኢየሱስ ስም መጠመቅ ይኖርባቸዋል፤ ካልተጠመቁም አይድኑም በማለት ፀረ-ሥላሴ አቋማቸውን ይገልጣሉ። በእነኚህ ቡድኖች እምነት መሠረት፡- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የመዓርግ ስሞች እንጂ የአካላት ስሞች አይደሉም፤ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ የመዓርግ ስሞች ናቸው፤ ኢየሱስ የላቀውና ብቸኛው የአምላክ ስም ነው ይላሉ።

ባለ አንድ አምላክ ነን ፤ የሚሉት እነዚህን ክፍሎች የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚያምኑትን አብያተ ክርስቲያናትን ባለ ብዙ አማልክት አድርገው ይፈርጃሉ። በብዙ አስተምህሮዎቻቸው ከሌሎች የፕሮቴስታንት ቡድኖች ጋር ይመሳሰላሉ፤ በሚከተለው አስተምህሯቸውም ይለያሉ፡-

www.zeorthodox.org

መጠሪያ ስማቸው እንደሚያስገነዝበው አብ ወልድ መንፈስ ቀዱስ የሚባለው አንድ ኢየሱስ ነው ባዮች ናቸው። "መለኮት ከዘላለም በአካል በባሕርይ በስም በግብር አንድ እንጂ ሁለት ወይም ሦስት አልነበረም። በሦስት መንገድ ግን ራሱን ለሕዝብ ገልጾአል። በሦስት መንገድ የተገለጸበትም ምስጢር በአብነት በሥጋ ዓይን ሳይታይ፣ በወልድነት በሥጋ እየታየ በመንፈስ ቅዱስነት እስትንፋሱን በሕዝቡ ልብ ውስጥ በማሳደር ተገልጦአል"። ይህ የ"ኢየሱስ ብቻ" አማኞች ትምህርት ከሰባልዮስ ትምህርት ጋር አንድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስገነዝበን ግን አብ ወልድ መንፈስ

ቅዱስ፤ በአካል ፣ በስም በግብር ፍጽም ሦስት መሆናቸውን ነው። ጌታችን ሲጠመቅ አብ በተለየ አካሉ ሆኖ ስለ ወልድ ሲናገር ***"በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው።"*** /ማቴ.፫፥፲፯/ ሲለን እርሱ አባት በዮሐንስ እጅ እየተጠመቀ ያለው ወልድ መሆኑን በግልጥ ያሳያል። ሉቃስ በጻፈልን ወንጌልም መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳም ***በአካል*** ታይቷል። /ሉቃ.፫፥፲፮-፲፯/

አብ በሥጋ ተገለጠ ብለው የሚያምኑት እነዚህ ክፍሎች ቃል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ሰው መሆኑን ፍጹም ይክዳሉ። ከዚህ ይልቅ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሥጋነት ተለወጠ ሲሉ ያምናሉ።

ሆኖም ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ሲያበስራት ***"ከአንቺ የሚወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።"*** /ሉቃ.፩፥፳፮-፴፰/ አላት እንጂ፤ አብ ወልድ ይባላል አላላትም። ***"የአብርሃምን ዘር ይዞአል"*** /ዕብ. ፪፥፲፬/ የሚለውን ቃልም አያስተውሉም። ጌታም ስለራሱ ሲናገር "የሰው ልጅ" እያለ መናገሩ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው በመሆኑ ነው።

## ማጠቃለያ

ሰባልዮስ በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያነሣውን ሐሳብ እንደ አዲስ የሚያምኑት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማኞች የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት ክደዋል። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድም ሦስትም መሆኑን ይነግረናል።

**ተግባር፡-** የእግዚአብሔርን ሦስትነት አስረዱ።

***ጥያቄዎች፡-***

1. የእግዚአብሔርን ሦስትነት ምስጢረ ሥላሴን በማብራራት አስረዱ።
2. በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣው መናፍቅ የስሕተት ትምህርት ምን ነበር?
3. በዘመናችን ‹‹Only Jesus›› በማለት የሚያምኑት ‹‹የሐዋርያት ቤተክርስቲያን›› ነን የሚሉ አማኞች የክህደት እምነት (ትምህርት) ምንድነው?
4. የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት የተገለጠበትን ከመጽሐፍ ቅዱስ አስረጂ ኃይለ ቃል በማቅረብ አብራሩ።

www.zeorthodox.org

# አቡነ ዜና ማርቆስ
# አርባ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የቅዱሱን ታሪክ ያውቃሉ፤ ከቅዱሱ ሕይወት ለወንጌል አገልግሎት መትጋትን መማር፡፡|

**የሚጠና ጥቅስ፡-***"መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤"* ፪ኛጢሞ.፬፥፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-**‹‹ገድለ ዜና ማርቆስ››፣ ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መረጃዎች›› በዲ/ን ዳንኤል ክብረት፣

**መግቢያ፡-** በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ትምህርታችን እንዳየነው ዐሥራ ሦስተኛውና ዐሥራ አራተኛው ዘመን በርካታ ቅዱሳን የተነሡበት ዘመን ነው፡፡ እነኚህ ቅዱሳን በሐዋርያዊ ተልእኮ ወንጌልን በመስበክ ፣ ገዳማትን በመገደም ….. ለክርስትና መስፋፋት ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ከእነዚህ ቅዱሳን አንዱ የሆኑትን የአቡነ ዜና ማርቆስን የስብከት እና የምንኩስና ሕይወት ተጋድሎ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### ትውልድ እና እድገታቸው

አቡነ ዜና ማርቆስ ከካህኑ ዘርዐ ዮሐንስና ከእናታቸው ከማርያም ዘመዳ በሰሜን ሸዋ ኢቲሳ ኅዳር ፳፬ ቀን ፲፪፻፺፪ ዓ.ም ተወለዱ፡፡ ለትምህርት ሲደርሱ በአባታቸው ቤት ንባብና ዳዊት ከተማሩ በኋላ ከአቡነ ቂርሎስ ዲቁና ተቀብለው በኢቲሳ ቅዱስ ሚካኤል አገለገሉ፡፡

www.zeorthodox.org

### አባታችን በእስክንድርያ

***"እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል። የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም።" ፪ኛ ጢሞቴ.፪፥፫-፬***

አቡነ ዜና ማርቆስ ገድላቸው መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል እየመራቸው እስክንደርያ ሄዱ ይለናል፡፡ ይህም በዚያን ዘመን ፣ በፊትና አሁንም ድረስ የኢትዮጵያ አባቶች የሚያደርጉት መንፈሳዊ ጉዞ

ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ወደ ግብጽ ሄደው ከአቡነ ብንያም ጋር ተገናኙ፡፡ በዚያም መንኩሰው የቅስና መዓርግ ተቀበሉ፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ለአገልግሎት ለመመለስ ሲዘጋጁ ከአባቶች ቡራኬና ጸሎት ተቀበሉ፡፡ በዚህ ጊዜም ሊቀ ጳጳሱ፤ ***"የእግዚአሔር እንግዳ ዜና ማርቆስ ሆይ እንደ ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት በስብከትና በትሩፋት ብዙ ሰዎችን አሳምነህና አጥምቀህ ታድናለህ፡፡ የጣዖታትን ቤት ታፈርሳለህ በኢትዮጵያ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ታሳንፃለህ"*** ብለው አሰናበቷቸው፡፡

## ታላቅ አገልግሎት በኢትዮጵያ

ጌታችን ሲያርግ ***"በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።"*** የሐዋ.፩፥፰ ያለው ቃል በሐዋርያት እና በእነርሱ ዘመን ብቻ የሚፈጸም ምስክርነት አልነበረም፡፡ እነርሱን መስለው በሚነሱ ሌሎች ቅዱሳንም የሚደረግ ምስክርነት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም፦ አቡነ ዜና ማርቆስ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አገልግለዋል፡፡

### *በይፋት እና አካባቢው*

በዚያን ዘመን ራሳቸውን ቤተ እስራኤል የሚሉ በልማደ አይሁድ በሥርዓተ ኦሪት የሚኖሩና ክርስትናን ያልተቀበሉ እስራኤላውያን በይፋት በብዛት ይገኙ ነበር፡፡ አባታችን እነዚህን በማስተማር ብዙዎችን አጠመቁ፡፡ በእመቤታችን፣በቅዱስ ሚካኤል፣በአባ ኖብና በሰማዕቱ ጊጋር ስም አራት አብያተ ክርስቲያናትንም ተከሉላቸው፡፡ የማኅሌተ ጽጌ ደራሲ አባ ጽጌ ድንግል ወደ ክርስትና የተማረኩት በዚህ የአባታችን አገልግሎት ነው፡፡ አባታችን ለሐዋርያዊ አገልግሎታቸው ሲተጉ ጽጌ ብርሃን አገኟቸውና ‹‹እንዴት አምላክ ይወርዳል ይወለዳል?›› ብሎ ጠየቃቸው፡፡ እርሳቸውም እርሱ ከሚያምነው መጽሐፍ ከትንቢተ ኢሳይያስ(፲፩፥፩) ጠቅሰው አስተማሩት፡፡ እርሱም ኦሪትን የተማረ የብሉያት ሊቅ ስለነበር አቡነ ዜናማርቆስ ያስተማሩትን ተረድቶ ፣ አምኖ ተጠመቀ፡፡ ከአቡነ ዜና ማርቆስ ጋርም በማስተማር ተጋ፡፡ ከዕረፍታቸው በኋላም የገዳማቸው አበ ምኔት ሆኖአል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበትን ‹‹ሰቆቃወ ድንግል›› አዘጋጀ፡፡

www.zeorthodox.org

አባታችን ሐዋርያዊ ተልዕኮቸው ተጉለት በሚባለው አካባቢ ቀጥሎ ያላመነውን ሕዝብ በማስተማርና በማሳመን ክርስቲያን አደረጉ፡፡ ያመነውንም አጸኑ፡፡ በዚያም በተባሕትዎ ብዙ ተጋደሉ፡፡ ዛሬ በተጉለት የምትገኘውንና ነጭ ገደል በዓታ ማርያም የምትባለውን ገዳምም በዚህ አገልግሎታቸው አቀኑ፡፡ ዛሬ ገርባ ቅዱስ ጊዮርጊስ በሚባለው ደብርም ሰፊ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡

### *በደቡብ ኢትዮጵያ*

አባታችን አዋሽን ተሻግረው ለሐድያ ሕዝቦች ወንጌልን ሰብከዋል፡፡ ከዚያም ወደ ሰባት ቤት ጉራጌ ምሑር ወረዳ ሄደው ወንግል ሰበኩ፡፡ ጣዖታትንም ከሕዝቡ አራቁ፡፡ በአካባቢው እጅግ የሚፈራና የሚመለክ ‹‹ማኮስ›› የሚባል ጣዖት ነበር፡፡ የጣዖትን ከንቱነት ለሕዝቡ በድፍረት አስተምረው በተሰጣቸው ሀብተ ፈውስ ድውያንን ፈወሱ፡፡ ሕዝቡንም ከጣዖት ጨለማ ወደ ክርስቶስ ብርሃን መለሱ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ምሑር ኢየሱስ ገዳምን መሥርተው በርካታ መነኮሳትን አፈሩ፡፡

ይህ አገልግሎታቸው በይፋትና በሸንኩራ እስከ አዋሽ ወንዝ የተዳረሰ ነበር፡፡

### *የተፈጸመላቸው ተአምራት*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***"ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤"*** ማር.16፡17 እንዳለ አቡነ ዜና ማርቆስ ከሐዋርያዊው አገልግሎት ጋር ሀብተ ፈውስና ገቢረ ተአምራት የተሰጣቸው አባት ነበሩ፡፡ ከላይ እንዳየነውም ብዙዎችን እየፈወሱ ወደ ክርስቶስ ትምህርት መልሰዋል፡፡

ብዙ ተአምራት ይደረግላቸውም ነበር፡፡ ከእነዚህ አንዱም በገዳማቸው ለነበሩ መናንያን እንጀራ ባርከው ስምንት ሺሕ ሕዝብ በልቶና ጠግቦ አንድ መቶ ስምንት መሶብ ተነሥቷል፡፡ ቅዳሴ ሲቀድሱ አስተምረው ያሳመኑት ስምንት ሺ ሕዝብ እስኪቆርብ ፀሐይ ገባችባቸው፡፡ ሆኖም ሕዝቡን አቁርበው እስኪያበቁ እንደ ኢያሱ ፀሐይ ቆሞላቸዋል፡፡

### *ዕረፍታቸው*

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈልን ቅዱሳን የሚያርፉበትን ቀን ዐውቀው ሲሰናዱና ሥራ ሲሠሩ እናነባለን፡፡ ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስ ***"ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመለከተኝ ከዚህ ማደሪያዬ መለየቴ ፈጥኖ እንዲሆን አውቃለሁና። ከመውጣቴም በኋላ እነዚህን ነገሮች እንድታስቡ በየጊዜው ትችሉ ዘንድ እተጋለሁ።"*** ፪ኛ ጴጥ.፩፥፲፬-፲፭ ሲል ቅዱስ ጳውሎስም ለልጁ ለጢሞቴዎስ ***"በመሥዋዕት እንደሚደረግ፥ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፥ የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል። መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም። በቶሎ ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ፤"*** ፪ኛ ጢሞ.፬፥፮-፱ ብሎታል፡፡

www.zeorthodox.org

አቡነ ዜና ማርቆስም በሃይማኖትና በግብር የመሰሉዋቸው ሐዋርያትን ፈለግ ተከትለው በተጋድሎ ከደከሙ በኂላ መልአከ እግዚአብሔር ተገለጠ፡- ‹‹*ዛሬ ገዳማቸው በሚገኝበት ቦታ*

***በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን ሠርተህ ገዳም ገድም የብዙ መናንያን የጸሎት ቦታ ይሆናል። ዕረፍትህ በዚሁ ነው፡፡›››*** አላቸው፡፡ እርሳቸውም መልአኩ እንዳመለከታቸው አደረጉ፡፡ ገዳሙንም ደብረ ብሥራት ብለው ሰየሙት፡፡

አባታችን አቡነ ዜና ማርቆስ በዕድሜ ገፍተው፡፡ በገዳሙት ገዳምም መናንያን በዝተዋል፡፡ በዚህ መንፈሳዊ ተጋድሎ እያሉ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳን ጋር ተገልጦ ቃል ኪዳን ተቀበሉ፡፡ ለገዳማቸው ሕግና ሥርዓት ደነገጉ፡፡ ገዳሙንና መነኮሳቱን ባርከው ዕድሜ ጠግበው፤ በ130 ዓመታቸው ታኅሣሥ ሦስት ቀን ዐረፉ፡፡

## ማጠቃለያ

1. ሁሉም ክርስቲያን ልዩ ልዩ ጥሪ አለው፡፡ አቡነ ዜና ማርቆስም ገና በልጅነታቸው ከቤተሰባቸውና በአካባቢው ካዩት፤ በመንፈስ ቅዱስ ከተረዱትም በደረሳቸው ጥሪ ለማገልገል ራሳቸውን ከልጅነት ጊዜያቸው በትምህርትና በሕይወት ዝግጁ አደረጉ፡፡ እስክንድርያ ድረስ ሲሄዱም ለአገልግሎታቸው የሚያደርጉት ዝግጅት አካል ነበር፡፡ ይህም ታላቅ ፍሬ አስገኘላቸው፡፡ እኛም ***"መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፤ እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና።"*** ፪ኛ ጴጥ.፩÷፲ እንደተባለው ቃል ለአገልግሎት መዘጋጀትን እንማራለን፡፡
2. ጻድቁ አቡነ ዜና ማርቆስ በዐሥራ ሦስተኛውና ዐሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደነበሩት አባቶች፤ በሐዋርያዊ ተልዕኮ እና በገዳማዊ ሕይወት ብዙ የደከሙና የተጋድሏቸው ፍሬ በድምቀት በቤተ ክርስቲያን የተቀመጠላቸው አባት ናቸው፡፡***"ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ጸዳል÷ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።"*** ዳን.፲፪÷፫ እንደተባለም ከይሁዲነት፣ ከአረማዊነት (ጣዖት አምልኮ)ብዙዎችን የመለሱ እና ወደ በክርስቶስ ጽድቅ ያቆሙ አባት ናቸው፡፡
3. ከእነዚህ ቅዱሳን ሕይወት ለክርስቶስ ወንጌል መዳረስ፣ለቅድስና ሕይወት መስፋፋት፣ለቤተ ክርስቲያን ጥንካሬ መሥራትን እንማራለን፡፡ ***"ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው÷ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን÷ የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ።"*** ያዕ.፭÷፲፱-፳
4. ክርስቶስ ለአገልግሎታችን ዋጋ የሚሰጠን ቀን አለው፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው ታምነን መሰማራት ነው፡፡ ***"በእግዚአብሔር ታመን፥ መልካምንም አድርግ፥ በምድርም ተቀመጥ፥ ታምነህም ተሰማራ፡፡ በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፥ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል፡፡"*** መዝ.፴፮(፴፯)÷፫-፬ አዎን ለእነ ቅዱስ ጳውሎስ የጽድቅን አክሊል የሰጠ ለአቡነ ዜና ማርቆስም

www.zeorthodox.org

ሰጥቷቸዋል፡፡ እኛም መንገዳቸውን ብንከተል፣ እንዳመኑ ብናምን፣በሥራቸው ብንመስላቸው ይህ ክብር ይጠብቀናል፡፡ ***"የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።"*** ፪ኛ ጢሞ.፬፥፯-፱

## ተግባር፡-

♣ ቅዱሳንን በሕይወትና በአገልግሎት ለመምሰል በልባችሁ ቁረጡ፤በተግባርም ተለማመዱ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. አቡነ ዜና ማርቆስ አባታቸው እና እናታቸው ማን ይባላሉ? መቼ እና የት ተወለዱ?
2. የዲቁና መዓርግ የተቀበሉት ማን ከሚባሉ አባት ነው? አገልግሎት የጀመሩትስ የት ነው?
3. አቡነ ዜና ማርቆስ ከኢትዮጵያ ውጪ ያደረጉት መንፈሳዊ ጉዞ ወዴት ነበር? ማን እየመራቸው ሄዱ? በሄዱበት ሀገር ያገኙት አባት ማን ይባላሉ?
4. አቡነ ዜና ማርቆስ የመነኮሱት የት ነው? ቅስና የተቀበሉትስ?
5. አባታችን በደቡብ ኢትዮጵያ ወንጌልን በመስበክ የጣዖት አምልኮን በማጥፋት ከፍተኛ አገልግሎት ከፈጸሙባቸው ቦታዎች ዋና ዋናዎቹን ግለጹ? በደቡብ የመሠረቱት ገዳም ማን ይባላል?
6. አቡነ ዜና ማርቆስ ከተደረገላቸው ተአምራት ዋናውን ግለጹ?
7. አቡነ ዜና ማርቆስ ያረፉት በስንት ዕድሜያቸው ነው? ያረፉበትን ቀን እና ገዳም ግለጹ?

www.zeorthodox.org

# ቂርቆስና ኢየሉጣ

# አርባ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የቅድስት እየሉጣ እና የልጇን ሕፃኑ ቂርቆስን ታሪክ ያውቃሉ፤ ስለመንፈሳዊ ተጋድሎና ክብሩ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል፡፡"*** የሐዋ.ሥ. ፲፬፥፳፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መጽሐፈ ስንክሳር

**መግቢያ፡-** ዛሬም ስለ ቅዱሳን የጀመርነውን ትምህርት በመቀጠል እናት እና ልጅ የነበሩትን ቅዱሳን ታሪክ እንማራለን፡፡ እናትና ልጁ ብዙ መከራን በጽናት የተቀበሉና የጽድቅ አክሊል የተቀዳጁ ናቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡

ሐምሌ ፲፱ ቀን የቅድስት እየሉጣ እና የቅዱስ ቂርቆስ ሰማዕትነት የሚዘከርበት ዕለት ነው፡፡ ተርሴስ በተባለች ቦታ የነበረ ሀገረ ገዢ እየሉጣ የተባለችውን እናት ጣዖት እንድታመልክ አዘዛት፡፡ ነገር ግን እርስዋም ሆነች ጣዖት ማምለክ እንደማይገባ የተማረው የሦስት ዓመት ሕፃን ልጅዋ ቂርቆስ ጣዖት እንደማያመልኩ ነገረችው፡፡

አገረ ገዢው ሕፃኑንም ለጣዖት ስገድ አለው፡፡ ሕፃኑ ቂርቆስ፤ ***"ያንተ አምላክ ከድንጋይና ከእንጨት የተሠሩ የሰው እጅ ውጤቶች ናቸው፡፡ ከጌታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ የለም"*** አለው፡፡ እናቱንም ***አናንያ፣ አዛርያንና ሚሳኤልን ያዳናቸው አምላክ እኛንም ያድነናልና አትፍሪ›› *** በማለት እናቱን አጽናንቶ፤በጽናት ለንጉሡ መሠከረ፡፡

www.zeorthodox.org

ሀገረ ገዢው የተርሴስ ንጉሥ በእየሉጣና በሕፃኑ ቂርቆስ እምነት ጽናት ተበሳጭቶ ወደ እሳት ተጥለው ተሰቃይተውና ተቃጥለው እንዲሞቱ አዘዘ፡፡ ሦስቱን ወጣቶች ከእሳት ያዳናቸው (ዳን . ፫፥፲፫-፴) መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ወደ እሳት የተጣሉትን እናትና ልጅ አዳናቸው፡፡ ብዙ ሕዝብም ጽናታቸውን አይቶ አመነ፡፡ የሦስት ዓመቱ ቅዱስ ቂርቆስም የሠለስቱ ደቂቅን ታሪክ አስተምሮ፣ የእምነታቸው ጽናት ወራሽ ሆነ፡፡ አገረ ገዢው በተለያዩ የቅጣት መንገዶች እየሉጠንና ሕፃኑ

ቂርቆስን እንዲሰቃዩ ቢያደርጋቸውም እግዚአብሔር ያጸናቸው ነበር።

በመጨረሻም እግዚአብሔር ወደ ዘላለማዊው ዕረፍት ጠራቸው፣የሰማዕትነት አክሊል ሐምሌ ፲፱ ተቀዳጁ።

### ከዚህ ትምህርት የምንወስዳቸው ጠቃሚ መልእክቶች

ሕፃኑ ቂርቆስ እና እናቱ እየሉጣ ዘመነ ሰማዕታት እየተባለ በሚጠራው ዘመን ነበሩ። በወቅቱ ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ ታላቅ ዐዋጅ ወጥቶ ነበር። አንዳንዶች ሞትን ፈርተው ወይም የዚህ ዓለም ባለጠግነት አታሏቸው እምነታቸውን ሲተው እንደ ቂርቆስ እና እየሉጣ ያሉት በጽናት ቆሙ። ራሳቸውን መሥዋዕት አድርገው በማቅረብም ዘላለማዊ የሰማዕትነት ክብር አገኙ ከሐዋርያት የተቀበሉትን እምነትም ለእኛ አስተላልፈውልናል። ከእነሱ የእምነት ጽናት እኛም ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ዘላለማዊ ሕይወትን ለመቀዳጀት ማድረግ ያለብንን መንፈሳዊ ጥንካሬ እንማራለን።

ለዚህም ነው ቅዱሳንን የምናከብረው፤ እንዲያማልዱንም እንጸልያለን። የሰማዕታት ሞት ለክብር ነው። በከንቱ አልሞቱምና።

**በሰማዕትነት፡-**

ለብዙዎች የመዳን ምክንያት ይሆናሉ። ምክንያቱም በሰማዕትነታቸው የጣዖት አምልኮንና ክፉ ልማድ እያጠፉ ብዙዎች ክርስቲያን እንዲሆኑ የመዳንን መንገድ በማሳየት አርአያ ይሆናሉና።

እምነትን በመጠበቅና ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፍ ያደርጋሉ። ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ እምነታችንን ጠብቀን ለሌሎች ስለማስተላለፍ እንዲህ ሲል ያስታውሰናል።***"ወዳጆች ሆይ ስለምንካፈለው ስለመዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፣ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኳችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።"*** ይሁዳ ቁ.፫ ቂርቆስ ታማኝነትና ጽናትን ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሠለስቱ ደቂቅ ተምሮአል። እኛም ከእኛ በፊት ከነበሩት አባቶች ልንማርና ታሪካቸውንም በቅድስና ሕይወትና መልካም ሥራ ልንደግመው ይገባል።

## ማጠቃለያ www.zeorthodox.org

ከዚህ ቀደም በነበሩት የተምህርት ክፍሎች የአራት ቅዱሳንን ታሪክ ተምረናል። ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ቅድስት እየሉጣ እና ቅዱስ ቂርቆስ። ቅዱስ ጴጥሮስ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ሲሆን፣ ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ለማሳደድ እየሄደ ጌታችን በታላቅ ኃይል ተገልጦ ሐዋርያ ያደረገው ነው፤ ቅዱስ ቂርቆስ እና ቅድስት እየሉጣም ከሐዋርያቱ ሰማዕትነት ከብዙ ዓመታት በኋላ የተነሡና ሰማዕትነትን የተቀበሉ ቅዱሳን ናቸው።

ሁሉም የሞቱት ስለ ክርስቶስ ሲመሰክሩ ነው፡፡ ዓለምን በሞታቸው አሸነፈውታልና የክብር አክሊልን ተቀዳጅተዋል፡፡

## ተግባር

- የሚከተለውን መዝሙር አጥኑና ዘምሩ

*መዝሙር፡*

ይቤላ ሕፃን ለእሙ
አትፈርሒ እም ነበልባለ እሳት
ለአናንያ ወኣዛርያ ወሚሳኤል ዘአድኃኖሙ ወእቱ ያድኅነነ

***ጥያቄዎች፡-***

1. የቅድስት እየሉጣ እና ሕፃኑ ቂርቆስ ሰማዕትነት ዕለት በቤተ ክርስቲያን የሚዘከረው መቼ ነው?
2. ቅድስት እየሉጣ እና ልጇ ሕፃኑ ቂርቆስ ሰማዕትነት የተቀበሉት ለምንድነው? አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ዘላለማዊ መንገድን መመርመር

## ዐርባ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ዘላለማዊው ሕይወትና ጉዞውን ያውቃሉ፤ መምህሩ ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***«የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየው ግን የዘላለም ነው፡፡፡»*** ፪ኛ ቆሮ ፬÷፲፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ.፴፩÷፴፫፣ማቴ.፳፭÷፲፬-፴፣ራዕ.፳፩÷፩-፲፤ ‹‹መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው››፣ አቡነ ሺኖዳ በአያሌው ዘኢየሱስ የተተረጎመ፡፡

**መግቢያ፡-** በዛሬው ትምህርታችንም የሕይወት ጉዞአችንን መፈተሽና ስለ ዘላለማዊው ሕይወታችን ስለሚኖረን ዝግጅትም እንማራለን ፤

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. ዘላለማዊነትህ

**ስለ ምድራዊ ሕይወት ብቻ የሚያስቡ አሉ፡፡**

ብዙ ሰዎች የሚያስቡት በዚህ ምድር ስላለው ሕይወታቸው ብቻ ነው፡፡ ምኞቶቻቸው ሁሉ በምድራዊው ሕይወት ላይ የተጠመዱ ናቸው፡፡ ጥረታቸውና ድካማቸው ሁሉ ለዚህኛው ሕይወት ብቻ ነው፡፡ ስለ ዘለዓለማዊነታቸው ምንም ላያስቡ ይችላሉ፡፡

www.zeorthodox.org

በምድር ላይ የምታሳልፈው ሙሉ የሕይወት ዘመንህን መጨረሻ ከሌለው ዘላለማዊነትህ ጋር ስታነጻጽረው የዓይን ጥቅሻ ያህል ነው፡፡ በምድር ላይ ያለ ሕይወትህ እንዲህ ላለው ዘላለማዊነት ይኸውም ሕያው ለሆነ ሕይወት የሚደረግ ዝግጅት ነው፡፡

**ከዓለማዊ ክብር ወደ ቅዱሳን ክብር ተመለሱ፡፡**

ከዓለማዊው ክብር ጋር መጣበቅህ ቅዱሳን ማብቂያ በሌለው ክብር ውስጥ የሚቀበሉትን ክብር ሁሉ እንድታጣ ያደርግሃል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን አንተ ምንም ጉዳይ እንደማይሰጠው ሰው ገና

ራስህን ከዓለማዊው ክብር አልነጠልህም !! ራስህን ጊዜያዊ ወይም ኃላፊ በሆኑ ዓለማዊ ደስታዎች መጥመድህ ዘለዓለማዊ ደስታህን ሊያሳጣህ ይችላል። ስለሆነም በዘለዓለማዊ ጥቅም ማመን አለብህ።

**ዘላለማዊነትን አስብ።**

ዘላለማዊነትን ዘወትር በዐይኖችህ ፊት አስቀምጥ። ማንኛውም ዓለማዊ ነገር ከዘለዓለማዊነት ጋር ሲነጻጸር ዋጋው በጣም ኢምንት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ የላከው መልእክት ምንኛ ድንቅ ነው። ‹‹ ***የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየው ግን የዘላለም ነውና።*** ˝፪ኛ ቆሮ.፬፥፲፰።

## 2. በጭፍንና በጠቢብ ሰው መሐል ጊዜያዊነትና የዘላለማዊነት እይታ ልዩነት አለ።

በዚህ እይታ ውስጥ ጠቢብ በሆነውና በጭፍኑ ሰው መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ መሆኑ እውነት ነው። ጭፍን የሆነው ሰው እይታ ቅርብ ነው፤ እይታው ከሚታዩት ነገሮች አልፎ አይሄድም። ጠቢቡ ሰው ግን አርቆ ይመለከታል፤ ከሞት በኋላ ያለውን ስለሚመለከትም እንዲህ እያለ ያሰላስላል። ከዚህ ሥጋዬ ስላቀቅ ምን ይገጥመኛል? ወዴት እሄዳለሁ? ምንስ እሆናለሁ? **እናንተስ ? ምን በማድረግ ነው ባተሌ የሆናችሁት?** ልብህን ያኖርሃትስ በየት ነው? በወዲህ ወይስ በወዲያ? ሀብትህ ባለበት ልብህ በዚያ ይኖራልና። ጠቢብ ሰዎች በዚህ ምድር ላይ እንግዶች መሆናቸው ስለሚያውቁ ተስፋቸውን በዚህ ምድር ላይ አያደርጉም። የሚጠብቁት ***እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ..*** ˝(ዕብ.፲፩፥፲)ነውና።

ለዘለዓለማዊነቱ ዋጋ የሚሰጥ ሰው ከምድርና ከምድራዊ ነገሮች በላይ ከፍ ከፍ ይላል። በዚህ ዓለም ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ዓይነት ነገር አይማርከውም። ለዚህ ሰው መላው ዓለም ከእርሱ በስተጀርባ ነው እንጂ ከእርሱ ፊት ለፊት አይደለም።

## 3. መንገዳችሁን መርምሩ

www.zeorthodox.org

***በስሕተት ሆነው መንገዳቸውን የማያርሙ አሉ።***

በመንገዱ ላይ የሚጣደፍና ምንም ይምጣ ምን መንገዱን መቀየር የማይችል ሰው አለ።ይህ ሰው መንገዱ የተሳሳተ መሆኑ ከተረጋገጠለትና ውጤቱ ወደማያምር ፍጻሜ የሚያመራ መሆኑ ከተነገረው በኋላም በመንገዱ ላይ ችክ ብሎ ይቆያል። ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን ካስገደለ በኋላ የሠራው ሥራ ትክክል አለመሆኑን እያወቀ ክብሩ እንዲጠበቅለት ያስብ ነበር።

ለእነኚህ ሰዎች መንገድን መቀየር ማለት ከብርታትና ከጥብቅነት ጋር አብሮ ሊጓዝ የማይችል ወላዋይነት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ችኮነት ይህን በሚያደርጉት ሰዎችና በተከታዮቻቸው ላይ

የሚያመጣው ጉዳት ግልጽ ሆኖ እየታያቸው ይህን ጠባያቸውን ሊቀይሩት አይፈልጉም። እንደዚህ ያሉት ሰዎች በዚህ ጠባያቸው ውስጥ ለዘመናት ሊቆዩ ይችላሉ.... ይህ ጠባይም ለዘመናት የሚጓተት ቅራኔ ወይም ሙግት ሊሆን ይችላል።

ጉዳዩ ያበቃለት ቢሆንም ሰውየው ሊያቆመው አይፈልግም፤ ወይም ደግሞ መጨረሻው ባያምርም ሰውየው ጉዳዩን የማይተው ግንኙነት አድርጎ ይይዘዋል።

*በችኮነትና በመወላወል ሕይወታቸውን የሚያባክኑ አሉ።*

ከዚህም አልፈው በዚህ የተሳሳተ መንገድ ላይ ብዙዎችን ከራሳቸው ጋር ያጠፋሉ። እነዚህ ሰዎች የሚኖሩት ያለ አንዳች መርሆ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሰዎች የሚደገፉት በራሳቸው አሳብ ነው፤ከዚህ በበለጠም በስሜቶቻቸው ነው። በመሆኑም ሕይወታቸውን የሚያባክኑት በከንቱና ያለ ምንም ጥበብ ይሆናል።

*እናንተ ግን መንገዳችሁን በየጊዜው መርምሩ*

ሁኔታዎችን፣ አካባቢንና የሚከተሉትን ውጤቶችን መገምገም ምንም ስሕተት የለበትም። ሰው ይህን የሚያደርግ ከሆነ ላለፈው ሳይሆን ለአሁን አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል።

*የራስን መንገድ መመርመር ጠቢብነት ነው*

ወደ ፈለጉት ግብ መድረስ የሚቻልበት መንገድ ቁም ነገሩ አንድ ጉዳይ ላይ መጣበቅ ሳይሆን የተጣበቁበት መንገድ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጡ ላይ ነው። እንዲህ ከሆነ ትኩረት ልትሰጡት የሚገባችሁ ጉዳይ ለግባችሁና ለዓላማችሁ ሊሆን ይገባል። ይህ የሚከናወነው ሊያገኙት የሚሹትን አመቺ ዘዴ በመምረጥ ነው።

## ማጠቃለያ፡-

ሰዎች ዘላለማዊ ሕይወት አለን። ይህን አውቀን ራሳችንን ማዘጋጀት መቻል አለብን። ይህንን ለማድረግም ዘወትር ራሳችሁን መርምሩ።

www.zeorthodox.org

**ተግባር** መንፈሳዊ ሕይወታችሁን ለማሰብ ከጸሎት ጋር ጥቂት ጊዜ ለራሳችሁ ስጡ።

***ጥያቄዎች፡-***

1. ዘላለማዊ ሕይወትን የሚያሳጡ ነገሮች ምንድናቸው?
2. ለዘላለማዊ ሕይወት ራስን ለማዘጋጀት ምን ማድረግ ይገባል?

# ፍልሰታ ለማርያም

# አርባ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ እመቤታችን ዕረፍተ ሥጋና ፍልሰት ያውቃሉ፤መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** **"ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል።"** /ሉቃ.፩÷፵፰/

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መጽሐፈ ስንክሳር።

**መግቢያ፡-** ከነሐሴ 1-15 እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የምናስብበትን ጾም እንጾማለን። ይሄም ሐዋርያት ከእመቤታችን ሞተ ዕርፍት በኋላ የጾሙት ነው። ይህን መሠረት በዛሬው ትምህርታችንም ስለ እመቤታችን ዕረፍት እና ሐዋርያት በዕረፍትዋ ተሰባስበው ስለተፈጸመው ተአምራት እንማራለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደች በስልሣ አራት ዓመቷ በልጅዋ በኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ተከባ ዐርፋለች። ሐዋርያቱም ከእነርሱ በመለየትዋ እጅግ አዝነው ነበር። አይሁድ ይሄን ሲሰሙ ***"እንደ ልጅዋ ተነሥታ ዐረገች እንዳይሉን"*** ብለው ሥጋዋን ወስደው ለማቃጠል ፈለጉ። ከአይሁድ ታውፋንያ የሚሉት ጉልበተኛ መጥቶ እመቤታችን ያረፈችበትን አልጋ ገለበጠው። ነገር ግን የጌታ መልአክ እጁን ቆረጠው።

እጆቹም ከትከሻው ተለይተው በአልጋው ላይ ቀሩ። ታውፍንያም በታላቅ ድጋጤና መደነቅ ወደ ሐዋርያት ዞሮ ይቅርታ ጠየቀ። እነርሱም እመቤታችንን እንዲለምን ነገሩት። እንዳሉትም ወደ እመቤታችን ዞሮ እያለቀሰ ለመናት። እመቤታችንም ቅዱስ ጴጥሮስ እጁን ወደ ክንዱ እንዲመልስለት ነገረችው፤ ወዲያውም ዳነ።ቅዱስ ጴጥሮስም ሄዶ የጌታችን ምሥክር እንዲሆን አስተማረው።

እመቤታችን ካረፈች በኋላ ቅዱስ መልአክ የእመቤታችንን ሥጋ ወስዶ ከሕይወት ዛፍ በታች አስቀመጠው ሐዋርያው ዮሐንስ ብቻ ይሄን አይቶ ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው። በዚህ ምክንያትም ሐዋርያት የእመቤታችንን ሥጋ እንደ ዮሐንስ ለማየት ለዐሥራ አራት ቀናት ጾሙ። ይህ የሐዋርያት ጾምም የእመቤታችን መታሠቢያ ጾም (ጾመ ፍልሰታ) ይባላል። ጌታችንም ጸሎታቸውን

www.zeorthodox.org

ተቀብሎ ሥጋዋን ሰጣቸው፡፡

**ከዚህ ታሪክ የምንማረው**

በክርስቶስ የሚያምኑ ምልክቶች ይከተሉዋቸዋል፡፡ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከፅንሰቷ ጀምሮ ብዙ ተአምራት ፈጽማለች፡፡ እንደ ክርስቶስ እናትነትዋም ከትውልድ ሁሉ ትበልጣለች፡፡ እኛን ለማማለድም ወደ እግዚአብሔር የቀረበች ናት፡፡ ለዚህም ነው በወንጌል ***"እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሠግኑኛል"*** /ሉቃ.፩፥፵፰/ ያለችው፡፡

**ማጠቃለያ**:- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስልሣ አራት ዓመታት በዚህ ምድር ኖራለች፡፡ ጥር ፳፩ ቀን ዐርፋ፡፡ ሐዋርያት ሥጋዋን ነሐሴ ፲፬ ቀበሩት፡፡ ነሐሴ ፲፮ ቀን ከሞት ተነሥታ ዐርጋለች፡፡

**ተግባር:-** የታወቀ ምክንያት ከሌላችሁ በፍልሰታ ቅደሴ አታስታጉሉ፡፡

***ጥያቄዎች:-***

1. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የምናስብበትን ጾም የምንጾምበት ጊዜ መቼ ነው? ምን ተብሎ ይታወቃል?
2. እመቤታችን በዚህ ዓለም ለምን ያህል ጊዜ ኖራለች? ያረፈችው፣ የተቀበረችው እና ተነሥታ ያረገችው መቼ ነው?
3. እመቤታችንን ለማሰብ የምንጾመው ጾም ምክንያቱን እና ታሪኩን ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# መታመንና መታረም

## አርባ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የሕይወታችንን መንገድ በተሰጠን በመታመንና ራሳችንን በማረም ስለ ማሳደግ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየው ግን የዘላለም ነውና፡፡"*** ፪ኛ ቆሮ.፬፥፲፰፡፡

**ምንባብ፡-** ዘፍጥ.፴፩፥፴፫፤ማቴ.፳፭፥፲፬-፴፤ራዕ.፳፩፥፩-፲

**መግቢያ፡-** በዛሬው ትምህርታችን ጥቂት በጥቂት እየታመንን ጌታ ስለሚጨምርልንና ስለሚሰጠን ጸጋ፣ ለዘላለማዊው ሕይወታችን በሚኖረን ዝግጅትም ከስሕተቶቻችን ትምህርት በመውሰድ እንዴት እንደምንታርም እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርቱ

**በጥቂቱ መታመን**

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- ***"በጥቂቱ ታምነሃል፤በብዙ እሾምሃለሁ፤..."*** ማቴ.፳፭፥፳፩፡፡ ይህ ማለት በምድራዊ ነገሮች ላይ ታማኝ ሆነህ ስትገኝ በሰማያዊ ነገሮች ላይ እሾምሃለሁ ማለት ነው፡፡ በዚህኛው ዓለም ውስጥ ታማኝ ሆነህ ከቆየህ በዘላለማዊነት ውስጥ እሾምሃለሁ ማለትም ነው፡፡ ይህ መመሪያ በብዙ መስኮች ላይ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል....

- ዘመዶችህን በመውደድ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ጠላቶችህንም በመውደድ ላይ ይሾምሃል፡፡ ጠላትህን የምትወድበትን ጸጋ ያድልሃል ማለት ነው፡፡
- በትርፍ ጊዜህ እግዚአብሔርን የምታገለግል ከሆንክ በሕይወትህ ጊዜ ሙሉ በእርሱ ላይ ትኩረት የምታደርግበትን ፍቅር ያድልሃል፡፡ የፈቃድ ኃጢአቶችን ከአንተ በማስወገድ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ያለ ፈቃድ ከሚመጡ ኃጢአቶች ነጻ ያወጣሃል፡፡
- ንቁ ኅሊናህን ከክፉ አሳቦች የምትጠብቅ ከሆንህ እግዚአብሔር ንቁ ያልሆነው ኅሊናህን ንጽሕና ያድልሃል፤ከዚህ በተጨማሪ የሕልሞችህን ንጽሕናም ያድልሃል፡፡
- ልጅ እያለህ ታማኝ ከሆነህ እግዚአብሔር ውጊያዎች በሚበዙበት በወጣትነት ዘመንህ ውስጥም ታማኝነትን ያድልሃል፡፡

www.zeorthodox.org

- ሌሎች ሰዎች ላይ በቃላት ብቻ የማትፈርድባቸው ሆነህ ለመገኘት ታማኝ ከሆንህ ይበልጥ አስቸጋሪ በሆነው በአሳብ እንዳትፈርድባቸው ያስችልሃል።
- ልክ እንደዚሁ ራስህን ከውጪያዊ ንዴት በመጠበቅ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ከውስጣዊ ቁጣ፣ ንዴትና ቅናት ነጻ ያወጣሀል።
- በተለመዱ መንፈሳዊነቶች (በመንፈስ ፍሬዎች) ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር የመንፈስ ስጦታዎችን ያድልሃል፣ በመጀመሪያው ላይ ታማኝ ሆነህ ካልተገኘህ ሁለተኛውን ፈጽሞ ልታገኘው አትችልምና።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሚፈትሽህ በጥቂት ነገር ነው። በዚህች በጥቂቷ ነገር ላይ ታማኝ መሆንህን ካረጋገጥህ እርሱ በሚበልጠው ነገር ላይ ይሾምሃል።

ውድቀትህንና አለመታመንህን በጥቂቱ ነገር ላይ ከገለጽህ ግን እግዚአብሔር በሚበልጠው ነገር ላይ አይሾምህም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና፡-***"ከእግረኞች ጋር በሮጥህ ጊዜ እነርሱ ቢያደክሙህ ከፈረሶች ጋር መታገል እንዴት ትችላለህ?"*** ኤር.፲፪፥፭።

ብዙ ሰዎች ዝቅተኛውን ሓላፊነት መወጣት ሳይችሉ ከፍተኛውን ኃላፊነት ለመቀበል ማሰባቸው እጅግ አስደናቂ ነገር ነው። እነዚህ ሰዎች በተሰጣቸው ጸጋ ሳይጠቀሙ ተጨማሪ ጸጋ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ናቸው። ይህን ሲያደርጉም ***"በጥቂቱ ታምነሃል፤ በብዙ እሾምሃለሁ፤..."*** የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል በመዘንጋት ነው። ይህ ቃል ለእነርሱ እንደ ሆኔታው የሚወሰንበት ነው የሚሆነው።

በጥቂቱ ነገር ላይ የምትታመን ከሆነህ እግዚአብሔር በብዙ ነገር ላይ ይሾምሃል። ልታደርገው በምትችለው ነገር ላይ ታማኝ ከሆንህ እግዚአብሔር ልታደርገው በማትችለው ነገር ላይም ይሾምሃል።

በሚታዩ ነገሮች ላይ ታማኝ ከሆንህ እግዚአብሔር በማይታዩ ነገሮች ላይ ይሾምሃል። በዚህም ዐይን ባላየው፣ ጆሮ ባልሰማውና በሰው ልብ ባልታሰበ ዘላለማዊ ከተማ ላይ ይሾምሃል።

እግዚአብሔር ታማኝነትህን በማንኛውም ነገር ላይ ሊፈትን ይችላል። ፈተናው አንድ ቀላል ትእዛዝ መጠበቅ ወይም ከአንዲት ፍሬ መከልከል ሊሆን ይችላል። በእውቀት ዛፍ ላይ ታማኝነትህ ከተረጋገጠ እግዚአብሔር በሕይወት ዛፍና ከሰማይ በወረደው መና ላይ ይሾምሃል።

www.zeorthodox.org

ያሉህን መክሊቶች አሳንሰህ አትመልከት። ይልቁንም ባሉህ መክሊቶችህ ላይ ታማኝ ሆነህ ተገኝ። እግዚአብሔር የሚመለከተው ያሉህን መክሊቶች ማነስ ወይም መብዛት አይደለም፤ ባሉህ መክሊቶች ላይ ታማኝ ሆነህ መገኘትህን እንጂ።

**ከስሕተቶች መጠቀም(መማር)**

*ማንኛውም ሰው ለስሕተት የተጋለጠ ቢሆንም ከስሕተቱ የሚጠቀም (ተምሮ የሚታረም) ሰው ግን ብልኅ ነው። ይህ ሰው ዳግመኛ ኃጢአት እንዳይሠራ መንፈሳዊ ልምድን፤ ዕውቀትንና ጥንቃቄን ገንዘቡ ያደርጋል። ከአባቶች አንዱ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡* ***"ዲያብሎስ ለተመሳሳይ ኃጢአት ሁለቴ የቀሰቀሰኝን ጊዜ አላስታውስም።"***

***መንፈሳዊ ሰው በስሕተቶቹ ውስጥ ትሕትናን የራሱ ያደርጋል።***

*ይህ ሰው ድካሙን ስለሚረዳ የሰዎችንም ድካም ለመረዳት እድል አለው። በራሱ አይመካም፤ ትሑት ነው። ይህ ሰው ስሕተቱን በመለየትና እንደ ሌሎች ሰዎች እንዴት ለስሕተት እንደሚጋለጥ በማወቅ ከስሕተቱ ይማራል። በመሆኑም አይኮራም ወይም እብሪት አይሰማውም ወይም ራሱን ከሌሎች ልዮ አድርጎ አይመለከትም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ* ***"ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።"*** *(፩ኛ ቆሮ.፲፥፲፪) ብሎ የተናገረው ቃል በእርሱ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል።*

*እብሪተኛ ሰው ሲወድቅ ስለሚደክም ለውድቀት የሚያበቁት ጥፋቶቹን በተደጋጋሚ መሥራቱን ይቀጥላል። በመጨረሻም ይሰላቻል፣ ተስፋ ይቆርጣል፣ ላይነሣም ወድቆ ይቀራል።*

*መንፈሳዊው ሰው ለራሱና ለሌሎች በሚያደርገው የጸሎት ልምምድ ውስጥ ከስሕተቱ በመማርና በመታረም ይጠቀማል። እርሱ የሰው ልጆች ድል ነሺነት የሚመሠረተው በእነርሱ ኃይልና ብልሃት ላይ ሳይሆን ምንጊዜም ቢሆን ወደ ድል በሚመራን በእግዚአብሔር ዕርዳታ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል። ይህ በመሆኑም ሰው* ***"እርዳኝ እድናለሁም፤..."*** *(መዝ.፻፲፰፥፻፲፯) እና* ***"አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል፤..."*** *(ነህ.፬፥፳) በማለት በጸሎቱ ከእግዚአብሔር ጋር ይጣበቃል።*

***ብልኅ ሰው ግን በኃጢአቶቹ ውስጥ ያሉትን የዲያብሎስ ማታለያዎችና ውጊያዎች ይገነዘባል።***

*እርሱ ዲያብሎስ ወደ ሰው ልጆች ነፍስ እንዴት እንደሚገባ? እንዴት አድርጎ እርሱን መጠንቀቅ እንዳለበትና እንዴት ትክክለኛ ሰው መሆን እንደሚገባው? ይማራል። ይህ ብቻ አይደለም፣ አመጣጡንና መንገዱን ይበልጥ እየተረዳ ሲመጣም ሌሎችን ለመርዳት የሚያስችለውን ሁኔታ ያዘጋጃል።*

www.zeorthodox.org

**ከስሕተቱ የሚማር ለሌሎች አዛኝ ነው።**

*መንፈሳዊ ሰው ሲወድቅ ለሌሎች ለወደቁ ሰዎች ይበልጥ ኀዘን ስለሚሰማው እነርሱን አይገሥጽም። በእነርሱም ላይ አይፈርድም፤ እርሱ ራሱ የዲያብሎስን ኃይልና የሰው ልጆችን ደካማ ተፈጥሮ ያውቃልና። በመሆኑም የሌሎች ሰዎች ኀዘን ኃዘኑ ነው።* ***"ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰራችሁ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፣ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።"*** *ዕብ.፲፫፥፫።*

መጠቀምን የሚሻ ሰው ከራሱም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ስሕተት ይጠቀማል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌሎች ስሕተት የተጠቀሰው ለዚህ ነው፡፡ በዚህ መሠረት እኛ እንጠቀምባቸው ዘንድ የነቢያትና የጻድቃን ስሕተቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲጻፉ አምላካችን ፈቅዷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ *"...ከብርቱም ውስጥ ጥፍጥ ወጣ...."* (መሳ.፲፬÷፲፬) በማለት ያናገረ አምላካችን እግዚአብሔር ለድኅነታችን ይሆን ዘንድ ከእያንዳንዱ ኃጢአት ጠቃሚ ትምህርት ሊሰጠን ይችላል፡፡

ከዚህም በላይ በሕይወታችን ዘመናት ከምናገኛቸው ሰዎቸ ሁሉ እንጠቀማለን፡፡ ከጻድቅ ሰው ምሳሌ ስንወስድ ከእኛና ከሌሎች ሰዎች ኃጢአት ደግሞ ልምድና ንቃትን ገንዘብ እናደርጋለን፡፡

## ማጠቃለያ

በጥቂቱ መታመን በብዙ ያሾማል፡፡ በተሰጣችሁ ታማኞች ሁኑ፡፡ ትንሹን ማብዛትና በሚበልጠው መሾም የሚችለው እግዚአብሔር በታማኝነታችሁ ብዙ ኃይል ድንቅ ነገር ያደርጋል፡፡ ስሕተቶች አይሠሩም አይባልም፡፡ ነገር ግን ቶሎ ማረም ከውድቀት ምክንያቶች መጠበቅ፤ ከራስና ከሌሎች ስሕተት መማር ብልህነት ነው፡፡

## ተግባር

- ለቤተሰብ ለቃላችሁና ለፈጣሪ ቃል ታማኞች ሁኑ፡፡
- ባለፈው ስሕተታችሁ ምክንያት ላይ ተወያዩ፡፡

| መዝሙር | ትርጉም |
|---|---|
| እግዚአብሔር ኀበነ ልሳነ ጥበብ | እግዚአብሔር ሆይ የቤተ ክርስቲያንን ሕግ |
| ከመ ናዕምር ሕጋ ለቤተ ክርስቲያን | የምናውቅበት ጥበብ ስጠን፡፡ |

www.zeorthodox.org

**ጥያቄዎች፡-**

1. ‹‹በጥቂቱ ታምነሃል፤ በብዙ እሾምሃለሁ፤›› ማቴ.፳፭÷፳፩ የሚለውን ኃይለ ቃል በተማራችሁት መሠረት አብራሩ፡፡
2. ‹‹ከስሕተቱ የሚማር ሰው ለሌሎች ያዝናል›› የሚለውን አባባል ግለጹ፡፡

# አቡነ ተክለ ሃይማኖት

## ሃምሳኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ተማሪዎች ስለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ፣ ተጋድሎና ያውቃሉ፤ በዚህም መሠረት መንፈሳዊ ኑሮን ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፦** ***"እግዚአብሔር በጻድቁ እንደተገለጠ እወቁ"*** መዝ. ፬÷፫

**መግቢያ፦** በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የተፈጸመውን የሐዋርያትን መንፈሳዊ ሥራና በክርስቶስ ስም የፈጸሙትን ተጋድሎ ተምረናል። በዛሬው ትምህርታችንም በኢትዮጵያ ከተነሱት ትላልቅ ቅዱሳን አንዱ ስለሆኑትና ኢአማንያንን አስተምረው ስላጠመቁ ቅዱስ አባት እንማራለን።

### ልደትና እድገት

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አዲስ ሐዋርያ የተባሉት የ፲ሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጻድቅ ናቸው - አቡነ ተክለሃይማኖት። አባታቸው **ጸጋ ዘአብ** እናታቸው **እግዚእ ኀረያ** ይባላሉ። የአቡነ ተክለሃይማኖት ወላጆች ልጅ ስላልነበራቸው ፤ ቅዱስ ሚካኤልን እንዲያማልዳቸው በመለመን ሀብታቸውን ሁሉ ለድኾች ይመጸውቱ ነበር። አንድ ቀን ቅዱስ ሚካኤል በሕልም ተገልፆ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ዓይነት የተባረከ ልጅ እንደሚወልዱ አበሠራቸው። እንደ ሕልማቸውም **ታኅሣሥ ፳፬** ቀን ልጅ ወለዱ። **ፍስሐ ጽዮን** ብለውም ሰየሙት። (የጽዮን ደስታ ማለት ነው።)ቤተ ሰቦቻቸው በነበሩበት አካባቢ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ስለነበር አባታቸው እዚያ ያገለግሉ ነበር።

www.zeorthodox.org

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተአምራትን ማድረግ የጀመሩት ገና በልጅነታቸው ነው። በተወለዱ በሦስተኛ ቀናቸው **‹‹አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ››** ብለው አመስግነዋል። በአካባቢው በተከሠተው ድርቅ የተነሣ የሚበላና የሚጠጣ በመጥፋቱ የቅዱስ ሚካኤልን **ዝክር** ለመዘከር ወላጆቻቸው ተቸገሩ። ፍሥሓ ጽዮን እናታቸውን የዱቄቱን ዕቃ እንድታመጣላቸው ጠይቀው እጃቸውን ሲያሳርፉበት በዱቄት ተሞላ። በዚህ መልኩም ፲ሥራ ሁለት ቅርጫት ሙሉ ዱቄት ተገኘ። የዘይቱንም ዕቃ እንዲሁ ሞሉት። በዚህም የቅዱስ ሚካኤል ዝክር ተዘከረ።

### ትምህርት፣ ጥሪ እና ክህነት

በልጅነታቸው የመጀመሪያውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያገኙት ከአባታቸው ነው፡፡ በአስራ አምስት ዓመታቸው አባታቸው ወደ ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ዘንድ ወስደዋቸው ድቁናን ተቀብለዋል፡፡ በአካባቢያቸው ያለውን ፈረስ መጋለብንና ቀስት መወርወርን የመሳሰለውንም ትምህርት ተምረው ነበር፡፡ አንድ ቀን ከጓደኞቻቸው ጋር ቀስት በመወርወር ላይ እያሉ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጦ፤ ካሁን በኋላ ሕዝብን ለማዳን መመረጣቸውን፣ እግዚአብሔርም ሙት የማስነሣት፣ ድውይ የመፈወስና አጋንንትን የማውጣት ጸጋ እንደ ሰጣቸው ገለጠላቸው፡፡ ስማቸውንም ተክለ ሃይማኖት ብሎ ለወጠው፡፡ "ተክለ ሃይማኖት" ማለትም የሃይማኖት ተክል ማለት ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ወደ አቡነ ቄርሎስ ዘንድ ሄደው ቅስና  በመቀበል አባታቸው በሚያገለግሉበት ደብር በርጋታና በትሕትና  ማገልገል ጀመሩ፡፡

### ሐዋርያዊ አገልግሎት

መጀመሪያ እግዚእ ኀረያ በመቀጠልም ጸጋ ዘአብ ሲያርፉ ሀብታቸውን ለድኾችና ለአብያተ ክርስቲያናት ሰጥተው ለሐዋርያዊ አገልግሎት ወጡ፡፡ ከአቡነ ኢየሱስ ሞዓ ጋር በሐይቅ ከመገናኘታቸው በፊት ቅስናን ተቀብለው በሸዋና በዳሞት በስብከተ ወንጌል አገልግለዋል፡፡

በዚያን ጊዜ ቡልጋ ዙርያውን በጣዖት አምልኮ የተከበበ ነበር፡፡  ከታ በተባለው ቦታ ለሦስት ዓመታት በማስተማር አምልኮ ጣዖትን አጥፍተው ታቦትና ካህን ከዞረሬ አምጥተው አብያተ ክረስቲያናትን ተክለውላቸዋል፡፡

ቀጣዩ የስብከተ ወንጌል ሥራቸው በደቡብ ሸዋ በዳሞት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ መጀመሪያ በይፋት ተራራ ይመለክ የነበረውን ጣዖት በማስቀረት ክርስትናን ለሰባት ወራት አስተምረዋል፡፡ ከዚያም ቢላት ወደሚባል በጠንቋይ ንጉሥ ወደሚመራ ሀገር ገብተው ማስተማር ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጂ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞአቸዋል፡፡ በመጨረሻ ግን አልመለስ ያሉትንና ሕዝቡ እንዳይማር እንቅፋት የሆኑትን ጠንቋዮች እና ጋሻ ጃግሬዎቻቸውን በፈቃደ እግዚአብሔር መሬት ውስጥ አሰጠሚቸው፡፡ ብዙ ሕሙማንን ፈውሰውና ሕዝቡንም አስተምረው አሳምነዋል፡፡

www.zeorthodox.org

ይህ ቦታ በወላይታ ውስጥ ሆኖ በዳሞቱ ንጉሥ ሥር ነበር፡፡ አቡነ ተክለሃይማኖት  ቤተ ጣዖቱን በማፈራረሳቸው የአካባቢው መስፍን ቃፈረ ውድም አስይዞ ከሞተለሚ ዘንድ ሊያቀርባቸው ማሰቡ በገድላቸው ተጽፎ ይገኛል፡፡ በኋላም በመስፍኑ ልጅ ላይ ያደረው ሰይጣን "ፍስሓ ጽዮን ሆይ÷ልታጠፋኝ መጣህን?" እያለ እየጮኸ ሲለቅ በማየቱ መስፍኑ ደንግጦ ከታሠሩበት ፈታቸው፤ ይቅር ይሉት ዘንድም ለመናቸው፤ እርሱም አምኖ ተጠምቆ ስሙ ገብረ ዋሕድ ተባለ፡፡ ቤተሰቡም በሙሉ ተጠመቀ፡፡

የዳሞቱ ንጉሥ ሞተለሚ እግዚእ ኀረያን አገባለሁ ብሎ ባሰበበት በሰርጉ ዕለት ቅዱስ ሚካኤል በመብረቅና በብርሃን ተገልጦ ሲነጥቀው ስላየ አእምሮው ሁሉ ታውኮ ነበር። የቢላቱ መስፍን ንጉሣችን አእምሮው ታውኳልና ይፈውሱት ብሎ ነገራቸው። እርሳቸውም ከመስፍኑ ጋር ወደ ዳሞት አብረው ተጓዙ። ሞተለሚ የሁለቱን መምጣት ሲሰማ ደንግጦ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን በሁለት ቅርጫት ከትተው በጠመ ግራርያ ገደል እንዲጥሏቸው አዘዘ። ነገር ግን ቅዱስ ሚካኤል በክንፉ ስለጠበቃቸው ምንም ሳይሆኑ ቀሩ። ተመልሰውም በፊቱ ቆሙ። ሞተለሚ የላካቸውን ሰዎች ባለማመኑ ሌሎችን በተመሳሳይ ትእዛዝ ገደል እንዲጥሏቸው አዝዞ ከዐሥር ምስክሮች ጋር ላከ። ነገር ግን አሁንም በሰላም ከገደሉ ወጡ። ይህን ሲመለከቱ ምስክሮቹም ሆኑ የዳሞት ሕዝብ በክርስትና አምነው አምልኮ ጣዖትን ተው።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከጠንቋዮች ጋር እንደ ሙሴ ተከራክረው በማሸነፍና ሙት በማስነሣት ሞተለሚን አሳምነው ካጠመቁ በኋላ ንጉሡ ለቤተክርስቲያን ብዙ ርስትና ገንዘብ ሰጠ። እርሳቸውም በዳሞት ለዐሥራ ሁለት ዓመታት አስተምረዋል።

በርካታ አባቶችን በ‹‹ንቡረ ዕድ›› ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን መዓርግ እየሾሙ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በስብከተ ወንጌል እንዲሰማሩና ክርስትናን እንዲያስፋፉ አድርገዋል። **ለምሳሌ** አቡነ ሳሙኤል ዘደብረ ወገግ፤ አቡነ ዜናማርቆስ ይጠቀሳሉ።

## ገዳማዊ ሕይወት

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ሐይቅ የገቡት በሠላሳ ዓመታቸው ነው። በሐይቅ እስጢፋኖስም ሥርዓተ ምንኩስናን እየተማሩ፣ ገዳሙንም እየረዱ በዚያን ጊዜ ታዋቂ ከነበረውና በሊቃውንትና በቅዱሳት መጻሕፍት ከዳበረው የሐይቅ ትምህርት ቤት ብዙ ዕውቀትን ገብይተዋል።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ቅዱሳት መካናትን ከጎበኙና ከአባቶች ጋር ከተገናኙ በኋላ ደብረ ዳሞ ገብተው አገልግለዋል። በዚያም ሥርዓተ አስኬማ ተፈጽሞላቸዋል። የመጀመርያዎቹን ደቀ መዛሙርት ያፈሩት በደብረ ዳሞ ገዳም በነበሩበት ጊዜ እንደነበር የደብረ ዳሞ ገዳም ታሪክ ይገልጣል።

www.zeorthodox.org

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከደብረ ዳሞ ገዳም ሲወርዱ ሰይጣን የመውረጃውን ገመድ ቆረጠባቸው። በዚህ ጊዜ ስድስት አክናፈ ጸጋ ተሰጥቷቸው ከተራራው ስር ሁለት ሺሕ ክንድ ያህል ርቀው በሰላም ደረሱ። ከዘመናት በኋላ ባረፉበት ሥፍራ በስማቸው ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበታል።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዕድሜያቸው ወደ ሰባዎቹ አጋማሽ ሲሆን እርሳቸው ብቻቸውን ከሚያደርጉት የስብከተ ወንጌል ተልእኮ በተጨማሪ ሌሎችንም ለዚህ ተልእኮ ለማሠማራት ይችሉ ዘንድ እንደ ሐይቅ እስጢፋኖስ አመቺ የሆነ ገዳማዊ ቦታ ለመመሥረት ወደ ደብረ አስቦ ገቡ። አቡነ

ተክለ ሃይማኖት በዚህ ገዳም በተጋድሎ መኖራቸው በየአካባቢው እየተሰማ ብዙ መነኮሳት ተሰባሰቡ፡፡ እርሳቸውም እመቤታችንን ይወዱ ስለነበር በዋሻው እኩሌታ በሰሌን ጋርደው ታቦተ ማርያምን አኑረው ነበር፡፡ በእኩሌታው ደግሞ እርሳቸው ከአሥራ አምስት ደቀ መዝሙሮቻቸው ጋር ይኖሩ ነበር፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በደብረ አስቦ ለሃያ ዘጠኝ ዓመታት ኖረዋል፡፡

**ብሔራዊ ሓላፊነቶች በሀገርና በቤተ ክርስቲያን**

በነአኩቶ ለአብና ይኩኖ አምላክ በተፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ የእርስ በርስ ጦርነት ተነሥቶ ሀገሪቱ ስትታመስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገላግለዋል፤ይኩኖ አምላክ ሲነግሥ ጳጳስ ስላልነበር የቀቡት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው፡፡

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በወላይታ ባደረጉት ታላቅ የሐዋርያነት ሥራ ሕዝቡ "ጨጌ"/በወላይትኛ ሽማግሌ፣ ታላቅ፣ አባት ማለት ነው/ ብሎ ጠርቷቸዋል፡፡ ይህ ስምም በኋላ ለደብረ ሊባኖስ አበ ምኔቶች መጠርያ ሆኗል፡፡

የግብጹ ሡልጣን ጳጳስ ተሹሞ እንዲመጣ ባለመፍቀዱ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለአዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትና፣ በሞተለሚ ጊዜ የጠፉትንም ለመተካት ታቦት የሚባርክላቸው ሊያገኙ አልቻሉም ነበር፡፡ ወደ እግዚአብሔር ቢጸልዩ እግዚአብሔር ***"በሊቃነ ጳጳሳት እንደሚሾሙ ሌሎች ጳጳሳት ሳይሆን አንተን ግን እኔው ሾምኩህ"*** በማለት እንደሾማቸው ገድላቸው ይናገራል፡፡ በተሰጣቸው ሥልጣንም ሜሮን አፍልተው፤ ታቦታትን ባርከው አብያተ ክርስቲያናትን ተክለዋል፡፡

**ዕረፍታቸው**

ዕረፍታቸው በደረሰ ጊዜ ደቀ መዝሙሮቻቸውን ***"ልጆቼ ሆይ÷ሁሉም መነኮስ መንግሥተ ሰማያት ይገባል ማለት አይደለም፡፡ ዓለምን በሚገባ የናቀ ብቻ ይገባል እንጂ፡፡ መጀመሪያ የእግዚአብሔር ጽድቁን ብቻ ፈልጉ፤ ጾምና ጸሎትን አዘውትሩ፤ እርስ በርሳችሁም ተዋደዱ፤ ትእዛዛቱንም ጠብቁ"*** እያሉ ይመክሯቸው ነበር፡፡ አንድ ቀንም ጌታችን ተገልጦ እርሳቸውና ሦስት ደቀ መዝሙሮቻቸው በንዳድ በሽታ እንደሚያርፉ ገለጠላቸው፡፡ ወዲያውም ሦስት ደቀ መዝሙሮቻቸው በንዳድ በሽታ ዐረፉ፡፡

www.zeorthodox.org

ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርትን ሰብስበው አባ ኤልሳዕ የገዳሙ አበ ምኔት እንዲሆን ነገሯቸው፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም በነሐሴ ፳፬ ቀን በዘጠና ዘጠኝ ዓመታቸው ዐረፉ፡፡ መነኮሳቱም በኣታቸው በነበረው ዋሻ ውስጥ ቀበሯቸው፡፡

## ማጠቃለያ

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወሳኝ የሆነ ቦታ ያላቸው ቅዱስ ናቸው። ክርስትናን በደቡብ ኢትዮጵያ በመስበክ፣ ምንኩስናን በሸዋና በደቡብ ኢትዮጵያ በማስፋፋት፣ ደቀ መዝሙሮቻቸው በጎንደር፣ በጎጃም፣ በደቡብ፣ በምዕራብና በምሥራቅ ኢትዮጵያ ባከናወኑት ሐዋርያዊ ተልእኮ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ባለ ውለታ ናቸው።

ታኅሣሥ ፳፬ ቀን የተወለዱበት፣ ግንቦት ፲፪ ቀን ዐጽማቸው የፈለሰበትና ነሐሴ ፳፬ ቀን ያረፉበት በቤተ ክርስቲያን ይከበራል።

### ጻድቁ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሙሴ ጸሊም ቀጥለው በግብጽ ቤተ ክርስቲያን በቅድስናቸው የሚታወቁ ኢትዮጵያዊ አባት ናቸው። የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የልደት ቀናቸውን በበዓልነት ከምታከብርላቸው አራት ቅዱሳን/የጌታችንን፣ የእመቤታችንንና የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን ጨምሮ/ አንዱ ናቸው።

በግብጽ የነበሩ /በዋዲ ኤል ናትሮን/ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ተረፈ ዐጽም ወደ ግብጽ አምጥተውታል በማለት ግብጾች ይተርካሉ። በኋላም ተረፈ ዐጽሙ በአሮጌው ካይሮ በሚገኘው የቅድስት ባርባራ ቤተ ክርስቲያን ተዛወረ።

በመጨረሻም በታኅሣሥ ፳፬ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ትእዛዝ በእስክንድርያ ወደ ሚገኘው የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን እንዲዛወር ተደረገ።

### ከታሪኩ የተወሰዱ ትምህርቶች

በእኛም ሕይወት በግል ጉዳዮቻችን ተጠምደን÷ለሌሎቹ ሕመምና ችግር ትኩረት ሳንሰጥ እናሳልፋለን። የጻድቁ ተክለ ሃይማኖት ቤተሰቦች በቅዱስ ሚካኤል ቀን ችግረኞችን ይረዱ ነበር። የቅዱሳን መታሠቢያ ቀናት ሌሎችን መርዳትን ያስታውሰናል። በዚህም በረከትን እንቀበልበታለን። ***"የጻድቅ መታሠቢያ ለበረከት ነውና።"*** ምሳ. ፲÷፯

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ሚካኤል የጻድቁ ተክለ ሃይማኖት ጠባቂ መልአክ ነበር። ጻድቁም እንደቤተሰቦቻቸው ያከብሩት ነበር። እኛም ከቤተሰቦቻችን የተቀበልነውን መልካም ነገር መልቀቅ የለብንም። በመጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ተብሏል ***"ልጄ ሆይ የአባትህን ምክር ስማ÷የእናትህንም ሕግ አትተው፤ለራስህ የሞገስ ዘውድ ለአንገትህም ድሪ ይሆንልሃልና።"*** ምሳ ፩÷፰-፱ ቅዱስ ጳውሎስም ***"እንደ አባቶቼ አድርጌ በንጹሕ ሕሊና የማመልከውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።"*** ፪ኛ ጢሞ. ፩÷፫ ብሏል።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት እግዚአብሔር በጠራቸው አገልግሎት በትጋትና በታማኝነት የተሰለፉና

ለዓለም ብርሃን የሆኑ ናቸው፡፡ እኛም በታማኝነት እና በትጋት መኖርን በሕይወታችን ለመተግበር ከዛሬዋ ዕለት መጀመር አለብን፡፡

**ተግባር፡-** ከቤተ ሰብ ጋር በመመካከር ገዳማትን ጎብኙ፡፡

*ጥያቄዎች፡-*

1. የአቡነ ተክለ ሃይማኖት እናትና አባት ማን ይባላሉ? መቼ ተወለዱ? እናትና አባታቸው በመጀመሪያ ያወጡላቸው ስም ማን ይባላል?
2. አቡነ ተክለ ሃይማኖት መጀመሪያ ያደረጉት ተአምራት ምንድ ነው? በስንት ዓመታቸው?
3. ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት የዲቁና እና ቅስና መዓርግ የሰጧቸው ማን ናቸው? ተክለ ሃይማኖት የሚለውን ስም ያወጣላቸው ማን ነው?
4. በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን በወላይታ የዳሞቱ ንጉሥ ማን ይባል ነበር? በዚያን ዘመንና ቦታ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የፈጸሙትን ሐዋርያዊ አገልግሎት፣ ተጋድሎ እና የተደረገላቸውን ተአምራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት የፈጸሙትን ሐዋርያዊ አገልግሎት፣ ተጋድሎ እና የተደረገላቸውን ተአምራት ግለጹ፡፡
5. አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሥርዓተ አስኬማ የተፈጸመላቸው የት ነው? የክንፍ ጸጋ የተሰጣቸውስ የት ነው? እንዴት ተሰጣቸው?
6. ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት የወላይታ ሕዝብ የሰጣቸው መዓርግ ስያሜ ምን ይባላል? በዚህ መዓርግ የሚጠሩት የየትኛው ገዳም አባቶች ናቸው፡፡
7. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምታከብራቸው የአቡነ ተክለ ሃይማኖት በዓላት መቼ እና ምን ምን ናቸው?
8. የግብጽ ቤተ ክርስቲያን በቅድስናቸው የምታከብራቸው ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አባቶች እነ ማን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም


www.zeorthodox.org

- ኅሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም፡፡
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ የኢትዮ. ኦርቶ.ተዋ. ቤ.ክ ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም፡፡ አዲስ አበባ ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )፡፡ 2000፡፡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ 1996 ዓ.ም.፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡
- ጎርጎርዮስ(ብፁእ አቡነ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡
- መሐሪ ትርፌ (በሊቀ ሊቃውንት) ፡፡ 19 ዓ.ም፡፡ የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
www.zeorthodox.org
- ዳንኤል ተሾመ፡፡ 19 ዓ.ም፡፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ስልቶች፡፡ አ.አ
- Pulpet ; 19 A.D; Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN;
- Tadros Yakob Malaty (Father); 2007-2008 A.D; The Epistle of Saint Paul to the Romans; Alexandria,Egypt.

- መብራቱ ኪሮስ (ዲያቆን)። አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ። የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ መማሪያ።
- ጎርጎርዮስ (በብጹእ አቡነ)። 1981 ዓ.ም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ። አዲስ አበባ።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )። 2001 ። የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ 1ኛ እና 2ኛ። አዲስ አበባ።
- Lule Melaku (Asst. Professor); 2010; History of the Ethi. Orthodox Tewahido Church; A.A ; Elleni p.p.plc.
- ሰሎሞን መላኩ(ዲያቆን)። 2001ዓ.ም። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት። አዲስ አበባ። ባናዊ ማተሚያ።
- Syrian Sunday school curriculum.
- Introduction to Coptic orthodox Church ; Father Tadros Y Malaty
- Ian Gillman,Hans-Joachim Klimkeit ; Christian in asia before 1500 ;
- ዜና ሐዋርያት
- ገድለ ቅድስት አርሴማ
- ሺኖዳ(ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ) ቅንዓት
- የኢትዮፕያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ ፤ ስንክሳር ፤ በትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ
- ያረጋል አበጋዝ (ዲ/ን)። ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ፤ አዲስ አበባ
- በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር)። 1997 ዓ.ም። የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
- ዳንኤል ክብረት(ዲ/ን)። 1998ዓ.ም። የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች። አዲስ አበባ። ሜጋ ማተሚያ ቤት።
- ………። አዋልድ መጻሕፍት። ሐመረ ተዋሕዶ።
- Douglas J.D and Tenney M.c (1987) New International BIBLE DICTIONARY. ZONDERVAN'S.Grand Rapids,MICHIGAN USA
- Holy Trinity College.(2004) Patrology፡ Holy Trinity College module/ unpublished./


www.zeorthodox.org

Malaty T.Y( Father)Patrology ;

- Malaty T.Y( Father).(199). Tradition and Orthodoxy. Alexandria .Egypt.
- ማኅበረ ቅዱሳን፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የማዕረግ ቃል ማተሚያ ቤት፡፡
- ነገረ ማርያም Shenoda - Pope (1999). The Holy virgin Saint Mary. Cairo,Egypt.
- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ (1988) ወንጌል ቅዱስ ትርጎሜ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
- የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት መማሪያ ፤ ካናዳ
- ሺኖዳ ሰው ምንድነው ፤ በብጹዕ ወቅዱስ ፤
- ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ
- ሺኖዳ (ብጹዕ ወቅዱስ ፤ አቡነ)፡፡ መንፈሳዊው ሰው
- John Mark (Father). 19 . Ascending the heights ; A lay man guide to the ladder of divine ascent
- አበራ (በሊቀ ጉባዔ ፤ አባ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፡፡
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 200 ዓ.ም፡፡ መሸኮርመምና ማሸኮርመም፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ ቅድመ ጋብቻ፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ተስፋ ገብረ ሥላሴ፡፡ 1988፡፡ መጽሕፍተ መነኮሳት፡፡ አዲስ አበባ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት፡፡
- ጥዑመ ልሳን፡፡() ያሬድና ዜማው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ሙሳ (ሊቀ ጳጳስ)፡፡ ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ፡፡ በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ፡፡

www.zeorthodox.org